# የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት

## የተማሪ መጽሐፍ
## 6ኛ ክፍል


**ፀሐፊዎች፡-**

1. አቶ ሸዋቀና ቸርነት
2. አቶ ቦጋለ ስብሃቱ
3. አቶ አሰግደው ተስፋዬ
4. አቶ ተስፋዬ ከፋለ
5. አቶ ጌታቸው በለጠ
6. ወ/ሮ ፀሐይ መሳኩ
7. ወ/ሮ ውዳሳት ገዳሙ
8. ወ/ሮ የዝና ወርቁ
9. ወ/ሮ አጋረደች ጀማነህ
10. አቶ ብቃለ ሥዩም
11. አቶ የሻው ተሰማ

**አዘጋጆችና አርታኢአን፡-**

አቶ ግርማ አለማየሁ
አቶ ዳንኤል አበበ
አቶ ቱጂባ በቃና



የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

AL GHURAIR
PRINTING AND PUBLISHING LLC

© ትምህርት ሚኒስቴር
የመጀመሪያ እትም 2003 ዓ.ም

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

ISBN 978-99944-2-052-0

# ማውጫ

ገፅ

**ምዕራፍ አንድ፡-** ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት .............................. 1

**ምዕራፍ ሁለት፡-** የሕግ የበላይነት .............................. 12

**ምዕራፍ ሦስት፡-** እኩልነት .............................. 23

**ምዕራፍ አራት፡-** ፍትሐዊነት .............................. 34

**ምዕራፍ አምስት፡-** የሀገር ፍቅር .............................. 44

**ምዕራፍ ስድስት፡-** የኃላፊነት ስሜት .............................. 58

**ምዕራፍ ሰባት፡-** ጠንካራ የሥራ ባህል .............................. 67

**ምዕራፍ ስምንት፡-** ራስን መቻል .............................. 76

**ምዕራፍ ዘጠኝ፡-** የቁጠባ ባህል .............................. 85

**ምዕራፍ አሥር፡-** ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ .............................. 93

**ምዕራፍ አሥራ አንድ፡-** ዕውቀትን መሻት .............................. 101

# ምሥጋና

ይህ መጽሐፍ ጥራቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲወጣ በርካታ ሰዎች ያልተቆጠበ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፡፡ Ms. Myra Murphy ለመጽሐፉ አዘጋጆች ተማሪ አሳታፊና ምቹ የሆነ የመጽሐፍ አዘገጃጀት ሥልጠና በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ አድረገዋል፡፡ Ms. Myra Murphy በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ወጪያቸውን የሸፈነው የአውሮፓ ዩኒየን በመሆኑ ከፍተኛ ምሥጋና ይገባዋል፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉትን የተለያዩ ምስሎች በመለገስ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ኮሚሽን፣ በወቅቱ የነበረው የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ መምህራን ማህበርና የኢትዮጵያ የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት ላደረጉት ድጋፍ ምሥጋና ሊቸራቸው ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ትምህርት የሥርዓተ ትምህርት መመሪያ ውስጥ የሚገኘው የመማሪያ ማስተማሪያ አዘገጃጀት ዩኒት መጽሐፉን ለማሣተም የሚያስችል የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀትና ለዓለም ባንክ በመስጠት ላደረገው አስተዋጽኦ ሊመሰገን ይገባዋል፡፡

በተለይም የቪኤሶ ኢትዮጵያ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አባል የሆኑት Mrs. Helen Papworth መጽሐፉን ከወትሮ ለየት ባለመልኩ ፎርማት በማድረግ ልዩ አድናቆት የሚሰጠው ተግባር በማከናወናቸው ሊመሰገኑ የሚገባ ሲሆን፤ የቪኤሶ ኢትዮጵያም የበጎ ፈቃደኞች ወደሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን በመምጣት ሙያቸውን እንዲያካፍሉን በማድረጉ ከፍተኛ ምሥጋና ስናቀርብ በከፍተኛ ደስታ ነው፡፡

# የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር

የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ፣
ታዬ ሕዝባዊነት ዳር እስከዳር በርቶ::
ለሰላም፣ ለፍትህ ለሕዝቦች ነፃነት፣
በእኩልነት በፍቅር ቆመናል ባንድነት::
መሠረተ ፅኑ ሰብዕናን ያልሻርን፣
ሕዝቦች ነን ለሥራ በሥራ የኖርን::
ድንቅ የባህል መድረክ የአኩሪ ቅርስ ባለቤት፣
የተፈጥሮ ፀጋ የጀግና ሕዝብ እናት፣
እንጠብቅሻለን አለብን አደራ፣
ኢትዮጵያችን ኑሪ እኛም ባንቺ እንኩራ::

## ይህን መፅሐፍ በጥንቃቄ ያዝ/ያዥ




- ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤትህ/ቤትሽ ንብረት ነው::
- መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይንም እንዳይጠፋ በጥንቃቄ ያዝ/ያዥ::
- ቀጥሎ መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ የሚረዱ 10 ነጥቦች ቀርበውልሃል/ቀርበውልሻል::

1. መጽሐፉን እንደ ኘላስቲክ፣ ጋዜጣ ወይንም መሰል ወረቀቶች በመጠቀም ሸፍን/ሸፍኝ::
2. ምንጊዜም መጽሐፉን በንፁህ እና ደረቅ ቦታ አስቀምጥ/አስቀምጭ::
3. መጽሐፉን በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት እጆችህ/እጆችሽ ንፁህ መሆን አለባቸው::
4. በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ወይንም በውስጥ ገጾች ውስጥ አትፃፍ/አትፃፊ::
5. ለመጽሐፉ የገፅ ማስታወሻ መያዝ ሲያስፈልግ ቁራጭ ወረቀት ተጠቀም/ተጠቀሚ::
6. ከመጽሐፉ ውስጥ ገጾችን ወይንም ስዕሎች በፍፁም ቀደህ/ቀደሽ አታውጣ/አታውጪ::
7. የተቀደዱ ገጾች ሲኖሩ በማጣበቂያ ወይንም በኘላስተር ጠግን/ጠግኝ::
8. መጽሐፉን ከትምህርት ቤት ቦርሳህ/ቦርሳሽ ውስጥ በምታስገባበት/በምታስገቢበት እና በምታስወጣበት/በምታስወጪበት ጊዜ ጥንቃቄ ውሰድ/ውሰጂ::
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በምታቀብልበት/በምታቀብይበት ወቅት ጥንቃቄ አድርግ/አድርጊ::
10. አዲስ መፅሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ በምትጠቀምበት/በምትጠቀሚበት ወቅት በመጀመሪያ መጽሐፉን በጀርባው አስቀምጥ/አስቀምጭ:: ቀጥሎ በአንድ ጊዜ ጥቂት ገፆችን ብቻ ግለጥ/ግለጭ:: መጽሐፉ የሚታጠፍበት ገፅ ላይ በዝግታ ጫን በማድረግ አስተካክል/አስተካክይ:: ይህም ሽፋኑ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዲቆይ ይረዳል::

# ምዕራፍ አንድ
# ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ፡፡
- የዴሞክራሲና የሰብዓዊ መብቶችን አንድነትና ልዩነት ትረዳለህ/ትረጃለሽ፡፡
- የዴሞክራሲ ሥርዓትን ምንነትና አስፈላጊነት ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፡፡
- በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ያሉትን ልዩነቶች ትረዳለህ/ትረጃለሽ፡፡
- የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት መሠረቶችን ታውቃለህ/ታውቂያለሽ፡፡

## 1.1 የዴሞክራሲ ሥርዓት ትርጉም

- ዲሞክራሲ የሚለው ቃል የተወሰደው ከግሪክ ቋንቋ መሆኑን 5ኛ ክፍል ተምራችኋል፡፡ ለመሆኑ ዴሞክራሲ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ታስታውሳላችሁ? የዴሞክራሲ ሥርዓትስ?

### የአቶ እሱባላው ንግግር፤

አቶ እሱባላው የመሸንቲ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕስ መምህር ናቸው፡፡ መሸንቲ ከአዲስ አበባ ተነስተው ባህርዳር ለመድረስ 20 ኪ.ሜ ሲቀር የምትገኝ ከተማ ናት፡፡ የመጀመሪያው ሴሚስተር ትምህርት በተጀመረ በሳምንቱ አቶ እሱባላው የትምህርት ቤቱን ተማሪዎች በሙሉ በትምህርት ቤቱ የኳስ ሜዳ ውስጥ በመሰበሰብ የሚከተለውን ንግግር አደረጉ፡፡

«ውድ ተማሪዎች! እንኳን ለአዲስ ዓመት ሁላችንንም በሠላም አደረሰን፡፡ የአዲሱን ዘመን ትምህርት ለመጀመር በመብቃታችን እንኳን ደስ አለን፡፡ ይህ ዓመት የተለየና አጥጋቢ ውጤት የምናስመዘግብበት እንደሚሆን እምነቴ የፀና ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ዘመን ልናከናውን ካቀድናቸው ነገሮች አንድ ሁለቱን እጠቅስላችኋለሁ፡፡ የስብሰባውም ዓላማ ይሄው ነው፡፡

1. በወር 1 ቀን የትምህርት ቤቱ የፅዳት ቀን እንዲሆን፡፡ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች መፀዳጃ ቤቶቹን፣ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ቢሮዎችንና መማሪያ ክፍሎችን፣ ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ደግሞ ግቢውን በአጠቃላይ እንዲያፀዱ፤ ቀኑም የትምህርት ፕሮግራምን እንዳያዛንፍ ቅዳሜ እንዲሆን፣

2. ተማሪዎችን እንዲመሩና ሥራውን እንዲያስተባብሩ ደግሞ የሚከተሉትን ልጆች መድቤአለሁ፡፡ ለ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ተማሪ ለአበበች፣ ለ5ኛ ክፍል ተማሪ ፎዚያ፣ ከ1ኛ- 4ኛ ላሉ ተማሪዎች ተማሪ አስማማው መድቤአቸዋለሁ፣

ተማሪዎቹ ትኩር ብለው በመገረምና በመደነቅ ሲያዳምጡ ቆይተው ወደ መጨረሻ ላይ ማጉረምረም ጀመሩ፡፡ አቶ እሱባላውን «ምንድነው? ችግር አለ እንዴ?» ብለው ጠየቁ፡፡ ተማሪ እመቤት እጇን ቀድማ በማውጣቷ አንድትናገር ፈቀዱላት፡፡ እመቤት መምህር እኛ ተማሪዎች ሳንወያይበት ለብቻዎ እንዴት ተወካዮችን ሊመድቡልን ቻሉ? አሁን የምንመራውና የምንተዳደረው በአንድ ሰው ፈቃድና ፍላጐት መሆን አይገባውም፡፡ ባለፈው ዓመት በሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት መምህራችን እንዲህ ያለው አካሄድ ዴሞክራሲያዊ አካሄድ እንዳይደለ ተገልፆልናል፡፡

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማንኛውም ነገር ከመወሰኑ በፊት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሰዎች በጋራ ሆነው መወያየት፣ መመካከርና ሃሳብ መለዋወጥ እንደሚገባም ተምረናል፡፡

ስለዚህ እኛም የዚህ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በሚመለከተን ጉዳይ ላይ ልንወያይበትና ልንመካከርበት ሲገባ በእርሶ ብቻ መወሰኑ አግባብ አይደለም፡፡

ቅዳሜ እና እሁድ ተማሪዎች ሌሎች ሥራዎችና ኃላፊነቶች ቢኖሩባቸውስ? በማለት ሃሳብ እያቀረበች ሳለ ተማሪዎች በማያባራ ጭብጨባ አድናቆታቸውን ለእመቤት ገለፁላት፡፡ አቶ እሱባለው የደስታ እና የእርካታ ስሜት ፊታቸው ላይ እየተነበበ ተማሪዎችን አንዴ ፀጥ ብለው እንዲያዳምጧቸው ጠየቋቸው፡፡ ተማሪዎቹም የእመቤት ንግግር አቶ እሱባለውን ሊያበሳጫቸው ይችላል ብለው ሲያስቡ ይልቁኑ በተቃራኒውሲደሰቱ በማየታቸው ግራ ተጋቡ፡፡

አቶ አርካይዶ በአጠቃላይ ተማሪዎቹን፣ በተለይ ደግሞ ለሳሮቴ ያላቸውን አድናቆት ገለፁ:: «በቃ! የሚፈለገው ይሄ ነው! እኔም የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ምን ያህል ተግባራዊ እየሆነ ነው? ተማሪው ምን ያህል ገብቶታል የሚለውን ለማየት ነበርና አስደስታችሁኛል:: በሃሳባችሁም ረክቻለሁ:: ስለ ዴሞክራሲና የዲሞክራሲ ሥርዓት ምንነት በሚገባ እንደተረዳችሁ ተገንዝቤአለሁ:: በዚሁ ቀጥሉ:: በርቱ!» በማለት ስብሰባውን አጠናቀቁ::

### መልመጃ 1

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ ::**

?

1. ከምንባቡ ዴሞክራሲ እና የዴሞክራሲ ሥርዓት ምን እንደሆነ ተረዳችሁ?
2. በውይይቱ አጠቃላይ ሂደት ላይ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዴት እንደተንፀባረቀ ተወያዩበት::
3. የአቶ ኦርካይዶ የመጨረሻ መዝጊያ ንግግር ተገቢና ትክክለኛ ነው? ለምን?
4. የአቶ ኦርካይዶ ሁለት ውሳኔዎች ከዴሞክራሲ ሥርዓት አንፃር ተገቢ ናቸው ወይስ አይደሉም:: ለምን? ተወያዩበት::

***ዴሞክራሲ*** ማለት ሥልጣን ወይም አስተዳደር የሕዝብ የሆነበትና በሕዝብ ፈቃደኝነትና ፍላጐት ላይ የተመሠረተ መንግሥት ያለበት ሥርዓት ማለት ነው:: በዴሞክራሲ ሥርዓት ሕዝቡ የሚያስተዳድሩትን በፍላጐቱ ይመርጣል፣ በመረጠው መሪ ይተዳደራል፣ በዴሞክራሲ የተመረጠውም መሪ አስተዳደር ካልተስማማውም መሪውን መሻር ይችላል::

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሕዝብ ንቁ ተሳትፎ የሚመሠረት ሠላም እና እድገት የሚረጋገጥበትና ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጥ ሥርዓት ነው:: በዴሞክራሲ ሥርዓት ሰዎች ኑሮአቸውን የሚመሩት፣ ችግራቸውን የሚፈቱት፣ ውሳኔዎችን የሚወስኑት በውይይት፣ በምክክርና ሃሳብ ለሃሳብ በመግባባት ነው::

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በመንግሥት ከፍተኛ ሥልጣን እርከን ላይ ሕዝቡ ራሱ ወኪሎቹን መርጦ የሚያስቀምጥበት ሥርዓት ነው:: ባለሥልጣናትም ከሕግ ውጭ የሆኑ ተግባራትን የሚፈፅሙ ከሆነ ከሥልጣናቸው በማውረድ በምትካቸው ሌሎችን መርጦ በኃላፊነት ቦታ ላይ ማስቀመጥ የሚቻልበት ሥርዓት ነው::

### መልመጃ 2

?

***በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ::***

**ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሕዝብ ንቁ ተሳትፎ የሚመሠረትና ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ የሚሠጥ ሥርዓት ነው ሲባል ምን ማለት ነው?**

## 1.1.1 የዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊነት፣

- የዴሞክራሲ ሥርዓት አስፈላጊና ጠቃሚ ነው የሚባለው ለምንድን ነው?

ሀገራችን ከሌሎች ሀገሮች በተለየ ሁኔታ በርካታ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያሏት ሀገር ናት:: ስለዚህ የዴሞክራሲ ሥርዓት በተለይ ለኢትዮጵያ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው:: ምክንያቱም:-

1. የሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነታቸውና ጥቅማቸው እንዲከበር ያደርጋል፣ ከአድልኦ የፀዳ ፍትሐዊ አሠራርን በማስፈንም ሁሉንም አንድ አድርጐ በማየት መብታቸውና ጥቅማቸው እንዲጠበቅ ያደርጋል:: በሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት የዴሞክራሲ ሥርዓት በመገንባት ላይ በመሆኑ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቋንቋቸው፣ ታሪካቸው እና ባህላቸው ተከብሯል:: ሕዝቦች በቋንቋቸው የመጠቀም መብታቸው መከበሩ አንድ መሠረታዊ የእኩልነታቸውና የእኩል ተጠቃሚነታቸው መብት ተግባራዊ መሆኑን ያሳያል::
2. የዴሞክራሲ ሥርዓት በተለይ ለኢትዮጵያ እጅግ አስፈላጊ የሚሆንበት ሌላው ምክንያት እነዚህ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ሃይማኖቶች ልዩነቶቻቸውን አቻችለው በጋራ ዓላማ ዙሪያ በመግባባት መኖር እንዲችሉ ስለሚረዳ ነው::

### መልመጃ 3

***የሚከተለውን ጥያቄ በቡድን ተከፋፍላችሁ ተወያዩበት::***

?

**የዴሞክራሲ ሥርዓት በተለይ ለሀገራችን ኢትዮጵያ እጅግ አስፈላጊ ነው የተባለበት ምክንያት ምንድን ነው?**

### 1.1.2 የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫዎች፣

- በክፍላችሁ ውስጥ የዴሞክራሲ አሠራር አለ? የዴሞክራሲ አሠራር በክፍላችሁ ውስጥ በምን በምን ይገለፃል?
- የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር ማለት ምን ማለት ነው?

የሃሳብ ልዩነት ካላችሁና ከማትግባቡት አንድ የክፍላችሁ ተማሪ ጋር የሚኖራችሁን ግንኙነት በተመለከተ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ብትጠየቁ ምላሻችሁ ምንድን ነው? ሠንጠረዡን በደብተ ራችሁ ላይ ገልብጡና ደስተኛ ከሆናችሁ "ደስተኛ ነኝ" በሚለው ሥር፣ ደስተኛ ካልሆናችሁ "ደስተኛ አይደለሁም" በሚለው ሥር የ«✓» ምልክት አድርጉ::

| ድርጊቶች/ ተግባራት | ደስተኛ ነኝ | ደስተኛ አይደለሁም |
|---|---|---|
| የክፍል አለቃ እንድትሆን/ እንድትሆኝ ቢደረግ፣ | | |
| የክፍል ሥራ በጥንድ ሆናችሁ እንድትሠሩ ቢደረግ፣ | | |
| የክፍል ፅዳት ላይ ከሌላ ሰው ጋር አብረህ/አብረሽ እንድትሠሩ ብትመደብ/ብትመደቢ፣ | | |
| በአንድ ዴስክ ላይ ጎን ለጐን እንድትቀመጥ/እንድትቀመጪ ቢደረግ፣ | | |
| የአንድ ክበብ አባል ብትሆን/ ብትሆኚ እናንተ የክበቡ ሊቀመንበር ብትሆን/ብትሆኚ፣ | | |
| የቡድን ሥራ ቢሰጥህ/ቢሰጥሽና የቡድኑ መሪ እንድትሆኚ/ እንድትሆን ቢደረግ፣ | | |

***ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት*** የሚገለፅባቸው በርካታ ባህርያት አሉ:: ከነዚህ ባህርያት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፣

#### ሀ) የሕዝብ ተሳትፎ መኖር፣

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሕዝቦች በተ ለያዩ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋሉ:: ተሳትፎ ሲባል ሕዝቦች ራሳቸውን እጩ ተመራጭ አድርገው በማቅረብ፡ አሊያም በምርጫ ጊዜ ይሠራልኛል ብለው የሚያምኑበትን ግለሰብ በመምረጥ ሊሆን ይችላል::

በአካባቢ ጉዳዮች ላይ በሚመክሩ ስብሰባዎችና በተለያዩ ሕዝባዊ ማሕበራት ውስጥ በአባልነት መሳተፍ ይችላል:: መንግሥት የሚያወጣቸውን መመሪያዎችን ሥራ ላይ ማዋልና እንደየሁኔ ታው የሚሻሻሉበት መንገዶች እንዲኖሩ ጥረት በማድረግ መሳተፍ ሊሆን ይችላል::

#### ለ) የሕዝቦች እኩልነት መከበር፣

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የሕዝቦች እኩ ልነት ይከበራል:: ማንኛውም ሰው በዘር፣ በሃይ ማኖት፣ በፆታና በመሳሰሉት ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግበት እኩል ዕድልና መብት ይኖረዋል:: በዴሞክራሲ ሥርዓት የሰዎች እኩልነት የሚገ ለፅባቸው ተጨባጭ መንገዶችም በርካታ ናቸው:: ሕዝቦች በሀገራቸው ውስጥ በመምረጥም ሆነ በመመረጥ የመሳተፍ የእኩልነት መብት አላ ቸው:: በሕግ ፊትም በእኩል ዓይን የመታየት መብት አላቸው፡

#### ሐ) የመቻቻል ባህል መኖር፣

**የሃሳብ ልዩነቶችን መቀበል** ማለት ሰዎች በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በመልክ እና በመሳ ሰሉት ልዩነቶች እንዳሏቸው ሁሉ በሀሳብም ልዩነ ቶች ሊኖራቸው እንደሚችል ማመን ነው:: የሃሳብ ልዩነቶችን መቀበል ልዩነቶች መኖራቸውን አምኖ ከመቀበል ባሻገር አንዱ የሌላውን ሃሳብ ማክበር ንም ይጨምራል::

**የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር** አንድ ሃሳብ እኛ የማናምንበትና የማንስማማበት ቢሆን ለሌሎች ደግሞ ሀሳቡ መልካም የመሠላቸውን ሃሳብ መሠንዘር መብታቸው መሆኑን መረዳትና በፅሞና እና በአክብሮት ማዳመጥ መቻል ነው:: ከዚህም ባሻገር ከተቻለ ሃሳብ ከሃሳብ ተፋጭቶ ድል አድርጐ ልዩነቶችን ለማስወገድ በሠላማዊ መንገድ መወያየትና መከራከር፣ ልዩነትን ማስወ ገድ ካልተቻለ ልዩነቶቹ እንዳሉ ተቀብሎ በሠላም አብሮ መኖር መቻል ማለት ነው::

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የሚኖሩ ሕዝ ቦች በውስጣቸው የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የብሔርና የብሔረሰብ እንዲሁም የሌሎች ባህላዊ መገለጫ ዎች ልዩነቶች መኖራቸው መልካም መሆኑን ያምናሉ::

የሃሳብ ልዩነት መኖሩ አይቀሬና ጠቃሚ መሆኑን አምነው ይቀበላሉ:: ስለዚህ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ እርስ በእርሳቸው ተቻችለው መኖርን ባህላቸው ያደርጉታል::

የሃሳብ ልዩነቶችን መቀበልም ሆነ የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር የዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረታዊ መርህ ነው::

**መልመጃ 4**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ::**

1. የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ ናቸው ከሚባሉት ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ::
2. ልዩነቶችን በማቻቻል አብሮ መኖር ምን ጥቅም አለው?
3. የሃሳብ ልዩነቶችን መቀበልም ሆነ እነዚህን ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር የዴሞክራሲ ሥርዓት መርህ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?

## 1.2 ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች፣

### 1.2.1 የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች አንድነትና ልዩነት፣

- ሰብዓዊ መብቶች በመባል ከሚታወቁት ውስጥ ሦሥቱን ጥቀሱ::
- ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመባል ከሚታወቁት ውስጥ ሦሥቱን ጥቀሱ::

**ሰብዓዊ መብቶች** የሰው ልጆች ሁሉ ሰው ሆነው በመፈጠራቸው ብቻ በተፈጥሮ ያገኟቸው መብቶች ናቸው:: ሰብዓዊ መብቶች በመባል ከሚታወቁት ውስጥ በሕይወት የመኖር መብት፣ የአካል ደህንነት መብት እና ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

**ዴሞክራሲያዊ መብቶች** በዴሞክራሲ ሥርዓት የሚተዳደሩ ሕዝቦች የሥርዓቱ አባል በመሆናቸው የሚያገኙዋቸው መብቶች ናቸው:: ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሰዎች በሚኖሩበት ሀገርና ሕብረተሰብ ውስጥ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችሏቸው መብቶች ናቸው::

ዴሞክራሲያዊ መብቶች በመባል የሚታወቁትም ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብት፣ የመደራጀትና ሠላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት እና የመምረጥና የመመረጥ መብት ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተመሳሳይነት እና ልዩነት አላቸው:: ሁለቱም ለሰው ልጆች ሁሉ የሚያስፈልጉና መሠረታዊ መብቶች መሆናቸው ተመሳሳይ ናቸው ያሰኛቸዋል:: ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የተለያዩ የሚያደርጋቸው ደግሞ ምንጫቸው ነው:: ይኸውም ሰብዓዊ መብቶች ሰው ሰው በመሆኑ ምክንያት ተከብሮ እንዲኖር ሊከበሩለት የሚገቡ በተፈጥሮ ያገኛቸው መብቶች ናቸው:: ዴሞክራሲያዊ መብቶች ደግሞ ማንኛውም ሰው የሚያምንበትን አመለካከት በሠላማዊ መንገድ ያራምድ ዘንድ ሊከበሩለትና ሊረጋገጡለት የሚገቡ ከሥርዓቱ ያገኛቸው መብቶች ናቸው::

☞ ማንኛውም ሰው የሙብቱ ተጠቃሚ የሚሆነው የሌላውን ሙብት እስካልተጋፋ ድረስ ነው::

**መልመጃ 5**

ሰንጠረዡን በደብተራችሁ በመገልበጥ የሚከተሉትን የመብት ዓይነቶች «ሰብዓዊ» ከሆኑ ሰብዓዊ «ዲሞክራሲያዊ» ከሆኑ ደግሞ ዴሞክራሲያዊ በሚሉት ሣጥን ውስጥ የ(✓) ምልክት አድርጉ፤

| | ሰብዓዊ መብት | ዴሞክራሲያዊ መብት |
|---|---|---|
| የአካል ደህንነት መብት | | |
| የመደራጀት መብት | | |
| የመሰባሰብ መብት | | |
| የግል ሃይማኖትን በነፃነት የማራመድ መብት | | |
| የመምረጥና የመመረጥ መብት | | |
| በሕይወት የመኖር መብት | | |

**ተማሪ መኳንንት እና መምህር ሐሰን፤**

መኳንንት የሚባለው የ6ኛ ክፍል ተማሪ ጠዋት ተማሪዎች ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት በአደረጉት የሠልፍ ሥርዓት ላይ የትምህርት ቤታቸው አመራር እየተበላሸ እንደሄደ፣ በተለይም የተማሪው ዴሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶች እየተረገጡ እንደሆነ እና ሌሎችም በርካታ ችግሮች እንዳሉ በመናገር ላይ ሳለ የፈረቃ መሪው መምህር ሐሰን ወደ ሠልፉ መጡ::


ምንድን ነው? ብለው መኳንንትን ጠየቁት:: "ንግግር እያደረግኩ ነው":: ብሎ መለሰ:: "የምን ንግግር?" ጠየቁ መምህር ሐሰን:: "የምንስ ቢሆን ምን አገባዎት? የፈለግኩትን መናገር ዴሞክራሲያዊ መብቴ ነው!" አላቸው:: መምህር ሐሰን በመኳንንት መልስ ስለተበሳጩ በጥፊና በእርግጫ እያጣደፉ ወደ ቢሮ ይዘውት ሄዱ:: እቢሮ አስገብተው በሩን በመቆለፍ በአለንጋ ገረፉት::

**መልመጃ ፩**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. መኳንንት ያደረገው ንግግር ተገቢ ነው አይ ደለም? ለምን?
2. አቶ ሐሰን መኳንንትን መደብደባቸው ትክክል ነው አይደለም? ለምን?
3. መኳንንትም አቶ ሐሰንም የመብት ጥሰት ፈፅመዋል። የተጣሱት መብቶች የትኞቹ መብቶች ናቸው?
4. መኳንንት ሆነ አቶ ሐሰን መብት ሳስመ ጣስ ምን ማድረግ ነበረባቸው?

### 1.2.2 የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር አስፈላጊነት፣










**ሥዕል 1.1 የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ጥቅሞች**

- *እያንዳንዱ ሥዕል ምን መልዕክት ያስተላል ፋል?*
- *ሥዕሎቹን መሠረት በማድረግ የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ለሰው ልጆች የሚ ሰጡትን ጥቅሞች ዘርዝሩ።*

***የሰዎች ሁሉ ትልቁ ምኞት*** *ግፍና ጭቆና የሌ ለበት፣ ከችግርና ከፍርሃት ነፃ በሆነ ዓለም ውስጥ መኖር ነው። ከፍተኛው ምኞቱ ሠላም፣ ፍት ህና፣ እኩልነት ሠፍነው ማየት ነው።*

*ስለዚህ ሰዎች ግፍና ጭቆናን ለማስወገድ አመ ፅን፣ ሃይልን፣ ብጥብጥን የመጨረሻ አማራጭ አድርገው እንዳይወስዱ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በአግባቡ እንዲከበሩ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተከ በሩ ማለት የሰው ልጅ የሚመኘውን ሠላም፣ ፍትሕ እና እኩልነት አገኘ ማለት ነው። ፍትሕ የሚያዛባና አድልዎ የሚፈፅም መጥፎ አመራር በሚያጋጥምበት ጊዜ በነፃነትና በግልፅ በመቃ ወም እንዲወገድ ወይም እንዲስተካከል ማድረግ ይቻላል። የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች እጅግ በጣም አስፈላጊ መብቶች ናቸው። ምክን ያቱም፣*


- *በሠላም ለመኖር፣*
- *ማንኛውንም ሥራ በሠላም ለማከናወን፣*
- *ከአድልኦና ከጭቆና ነፃ ሆኖ በእኩልነትና በፍትሐዊ አስተዳደር ሥር እንዲኖር ያግዙ ታል፡፡*

**መልመጃ ፯**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

- የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ለሰው ልጆች እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ መብቶች ናቸው የምንለው ለምንድን ነው? (በክፍል ውስጥ እና በት/ቤት ውስጥ ከጓደኞቻችሁም ሆነ ከመም ህራኖቻችሁ፣ እንዲሁም ከሌሎች የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ጋር የሚኖራችሁን ግንኙነት መሠረት በማድረግ መልሱ።)

## 1.3 በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል የሚታዩ ልዩነቶች፤



ሥዕል 1.2. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና፣ ሕዝቦች

- ከሥዕሉ ምን ተገነዘባችሁ?
- ኢትዮጵያ የብሔሮችና የብሔረሰቦች ሙዚየም ናት ሲባል ምን ማለት ነው?
- የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ያላቸውን ልዩነቶች ዘርዝሩ::
- በክፍላችሁ ውስጥ ከተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የመጡ የተለያዩ ኃይማኖቶች ተከታይ መብቶችን ማክበር ምን ጥቅም ይኖረዋል?

ኢትዮጵያ ከ80 በላይ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚኖሩባት ሀገር ናት:: እነዚህ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የየራሳቸው የሆኑ መገለጫዎች አሏቸው:: እያንዳንዱ ሕዝብ የራሴ ብሎ የሚኮራበት ቋንቋ፣ ሃይማኖት እና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች አሉት::

እነዚህ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተቀላቅለው በአንድነት የሚኖሩባት ሀገር በመሆኗ የብሔሮች የብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሙዚየም የሚል ስያሜ አግኝታለች:: ይህም ለዜጐቿ ኩራት ነው:: ስለዚህ ይህንን ተፈጥሮ የለገሠችንን ልዩ ስጦታ ተንከባክበን ማቆየት ይኖርብናል::

ይህንን ልዩ ፀጋ ተንከባክቦ ለማቆየት ሁላችንም በመካከላችን አንድነትና ፍቅር እንዲነግሥ መጣር አለብን:: ፀብ እና ግጭት እንዳይፈጠር መተሳሰብና መቻቻልን የእለት ተዕለት ልምድና ተግባር ማድረግ ይኖርብናል::

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በልዩነት ውስጥ አንድነት መኖሩን በሚገባ ተገንዝበው በመፈቃቀድና በራሳቸው ፍላጐት ላይ ተመስርተው አንድ ፌዴራላዊ ሥርዓት መሥርተዋል::

ከዚህም ባሻገር ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት የሠፈነባት፣ በኢኮኖሚ የበለፀገችና የዴሞክራሲ ሥርዓት የዳበረባት ኢትዮጵያን ለመገንባት እጅ ለእጅ ተያይዘው በዕድገትና በልማት ወደፊት እየተራመዱ ነው::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን መብት ሙሉ ለሙሉ የሚቀበል ሥርዓት ነው:: በልዩነቶቹ ውስጥ አንድነት ያለ ቢሆንም አለመግባባቶችና ግጭቶች ቢፈጠሩ እንኳ ሥርዓቱ በመቻቻል እና በሠላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል:: በውይይት ሊፈቱ የማይችሉ ሆነው የተገኙትን ደግሞ ለፍትሕ አካላቱ እንዲቀርቡ በማድረግ የብዙሃኑን ውሳኔ በፀጋ ተቀብሎ ተግባራዊ እንዲሆኑ ይረዳል::

**መልመጃ 8**


*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?

1. በኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል የሚታዩ ልዩነቶች ምን ምን ናቸው?
2. የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በውስጣቸው ባሉት ልዩነቶች የተነሳ ግጭት እንዳይፈጠር ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል? ግጭት ቢፈጠርስ ምን ማድረግ ይኖርባቸዋል?

## 1.4 የውጭ ግንኙነት፤

### 1.4.1 ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት ግንኙነት፣




ሥዕል 1.3 ኢትዮጵያ እና ጎረቤት አገሮች

- ካርታውን በደብተራችሁ ላይ በመገልበጥ የኢትዮጵያን ጎረቤት ሀገሮች ሥም ጻፉ::
- ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት ግን ኙነት የተመሠረተው በምን መርህ ላይ ነው?

ከኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መርሆ ዎች ውስጥ አንዱ ከጎረቤት ሀገሮችም ሆነ ከሌ ሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ሕብረትና የሕዝቦችን ወንድማማችነት ማጎልበትን ነው:: ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት ግንኙነት መልካም ጉርብትናን፣ ወንድማማችነትን እና በሠላም አብሮ መኖርን በማጠናከር ላይ የተመሠረተ ነው::

ሀገሪቱ ከጐረቤት ሀገሮች (ከጅቡቲ፣ ሱዳንና ኬንያ) ጋር ያላት ግንኙነት እጅግ አበረታች እና በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ በመሄድ ላይ ነው:: ለምሳሌ የመሰረተ ልማት ግንኙነቱን ብንወስድ ከሱዳን ጋር በምድር ቀጥታ የስልክ ግንኙነት ተዘርግቷል:: ሁለቱን አገሮች የሚያገናኝ መንገድ ተሰርቷል:: ለበርካታ ዘመናት ጎረቤቶች ሆነን የኖርን ቢሆንም ሁለቱንም አገሮች በአስተ ማማኝ ሁኔታ በበጋና በክረምት የሚያገናኝን አንድም መንገድ አልነበረም::

ለመጀመሪያ ጊዜ ከጎንደር መተማ ጋላባትና ገዳሪፍን የሚያገናኘውን መንገድ ለሕብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል:: መንገዱ ከተከፈተ በኋላ በሁ ለቱ ሀገሮች መካከል እየተካሄደ ያለው የንግድ ግንኙነት እየተጠናከረ ሄዷል:: የድንበር ሕዝቦች የንግድ ግንኙነት፣ የጋራ የፀጥታ ትብብር የመሳሰሉት ሁሉ በተሳካ ሁኔታ እየተካሄዱ ናቸው::

ስለዚህ ከሱዳን ጋር ያለው ግንኙነት በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል:: ይህ ደግሞ ለልማታችን፣ ለሠላማችንና ለዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ጥረታችን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው::

በተመሳሳይ ሁኔታም ከጅቡቲም ጋር በተመ ሰረተው ጠንካራ ግንኙት ሁለቱም ሀገሮች ተጠ ቃሚ እየሆኑ ነው:: በአሁኑ ወቅት እንደሚታ ወቀው የጅቡቲ ወደብ ዋናው የሀገራችን የውጭ ንግድ መውጫያና መግቢያ በር ነው:: ከዚህ ጋር በተያየዘ የንግድ፣ የሕዝብ ለሕዝብ፣ የፖለ ቲካና የፀጥታ ግንኙነቶች እንደዚሁ እየሰፉና እየተጠናከሩ በመሄድ ላይ ናቸው::

**መልመጃ ፱**

***በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ::***

? ኢትዮጵያ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላት ግንኙነት የተመሠረተው መልካም ጉርብትናን በማጠናከር መርህ ላይ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? በምሳሌ አስረዱ::

### 1.4.2 የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሠረቶች፣





ሥዕል 1.4 የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት መሠረቶች

- *ሥዕል 1.4 ምንን ያመለክታል?*
- *ከሥዕሎቹ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት መሠረቶች ምን እንደሆኑ ለመረዳት ቻላ ችሁ? ከቻላችሁ የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙ ነት መሠረቶች ምንድን ናቸው?*

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሠረቶች ልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ናቸው። በሀገራችን ሕዝቡ ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት ማምጣትና ከድህነትና ከኋላ ቀርነት ተላቆ የተመቻቸ ኑሮ እንዲኖር ማድረግ ወሳኝ ነው። የሀገራችን ሕዝብ እጅግ መሠረታዊ የሆነው ጥቅም ድህነትን፣ በሽታንና ኋላቀርነትን ማስወገድ ነው።

የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ሀገራዊ ጥቅምን የማስ ጠበቅ ተልዕኮ ያለው ነው፡፡ ስለዚህ የሀገራችን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲም ከዚህ የተለየ ተል ዕኮ የለውም። የሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም ማለት የአጠቃላይ የሕዝቡ ጥቅም ነው። እጅግ መሰረታዊ የሆነውና ወሳኝ የሚባለው የሕዝቡ ጥቅም ደግሞ ፈጣን ልማትን ማምጣትና ከዚሁ ተጠቃሚ መሆን ማለት ነው። የአጠ ቃላይ የሕዝቡ ጥቅም በሀገራችን ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ነው።

ስለሆነም ብሔራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማለት በሀገራችን ፈጣ ንና ሕዝቡን የሚጠቅም ልማትን ለማረጋገጥ፣ ዴሞክራሲ በሀገራችን ስር እንዲሰድ ለማድረግ የሚረዳ ፖሊሲ ማለት ነው። ብሔራዊ ጥቅማችን መነሻና መድረሻ ልማትና ዴሞክራሲ ናቸው፣ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን መነሻና መድረሻም ልማትና ዴሞክራሲ ናቸው።

**መልመጃ 10**

***በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ፡፡***

- የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሠረቶች ልማትና የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ናቸው የተባለበት ምክንያት ምንድነው?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

*ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት* በሕዝብ ምርጫ የተቋቋመ መንግሥት የሚመራበት፣ሕዝቦች እራሳቸው በመ ረጧቸው መሪዎቻቸው የሚተተዳደሩበት ሥርዓት ነው፡፡ የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ሃይማኖቶች ባሉባት ሀገራችን ሁላችንም ተከባብረን፣ተቻችለን እና ተፋቅረን እንድንኖር የሚረዳን የዴሞክራሲ ሥርዓት ነው፡፡

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚገለፅባቸው በርካታ ባህርያት አሉ፡፡ ከነዚህ ባህርያት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሕዝቦች ተሳትፎ መኖር፣ የሕዝቦች እኩልነት መከበር፣ እና የመቻቻል ባህል መኖር ናቸው፡፡

*ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች* ተመሳሳይነት እና ልዩነት አላቸው፡፡ ሁለቱም መሠረታዊ መብቶች በመሆናቸው ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ልዩነታቸው ደግሞ ሰብዓዊ መብቶች ሰው ሰው በመሆኑ በተፈጥሮ ያገኛቸው መብቶች መሆናቸው፣ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ግን በዴሞክራሲ ሥርዓት ዜጎች ከሥርዓቱ ያገኟቸው መብቶች መሆናቸው ነው፡፡

የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ለሰው ልጆች ሁሉ እጅግ በጣም አስፈላጊ መብቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በሠላም ለመኖርና፣ በሠላም ማንኛውንም ሥራ ለማከናወን፣ ከአድልኦና ከጭቆና ነፃ ሆኖ በእኩልነትና በፍትሐዊ አስተዳደር ሥር መኖር እንዲችል የሚረዱት እነዚህ መብቶች ናቸውና፡፡

ኢትዮጵያ ከ80 የሚበልጡ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሚኖሩባት ሀገር ናት፡፡ እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች አለው፡፡ ስለዚህ እነዚህ ብሔ ሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የተለያዩ ባህሎቻቸውን ይዘው በአንድነት የሚኖሩባት ሀገር በመሆኗ የብሔሮች የብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሙዚየም የሚል ስያሜ አግኝታለች፡፡ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በልዩነት ውስጥ አንድነት መኖሩን በሚገባ በመገንዘባቸው በመፈቃቀድና በራሳቸው ፍላጐት ላይ ተመስርተው አንድ ፌዴራላዊ ሀገር መሥርተዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ዘላቂ ሠላምና መረጋጋት የሠፈነባት፣ በኢኮኖሚ የበለፀገችና የዴሞክራሲ ሥርዓት የዳበረባት ኢትዮጵያን ለመገንባት እጅ ለእጅ ተያይዘው እየተጓዙ ነው፡፡

ከኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መርሆዎች ውስጥ አንዱ ከጎረቤት ሀገሮችም ሆነ ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ሕብረትና የሕዝቦችን ወንድማማችነት ማጎልበት ነው፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ ይህንን መርህ በአግባቡ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናት፡፡

የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሠረቶች ልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ናቸው፡፡ በአገራችን ሕዝቡ ተጠቃሚ የሚሆንበት ፈጣን ልማት ማምጣትና ከድህነትና ከኋላቀርነት ተላቆ የተመቻቸ ኑሮ እንዲኖር ማድረግ ወሳኝ ነው፡፡ የሀገራችን ሕዝብ እጅግ መሠረታዊ የሆነው ጥቅም ድህነትን፣ በሽታንና ኋላቀርነትን ማስወገድ ነው፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

*ፌደራላዊ፣* ራሳቸውን በራሳቸው በሚያስተዳድሩ የክልል መንግስታት ትብብር የተዋቀረ መንግሥት።

*ዲሞክራሲያዊ፣* ከፍተኛ የመንግሥት ሥልጣን የሕዝብ የሆነበትና ሥልጣኑም ተግባራዊ የሚሆነው በሕዝቡ ወይም ሕዝቡ በነፃ በመረጣቸው ተወካዮች አማካይነት የሆነበት ሥርዓት።

*ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ፣* ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች የጋራ ታሪክ፣ ሕልውና፣ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

I. *የሚከተሉትን ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ «ሀሰት» ብላችሁ መልሱ::*

1. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲያችን ሀገራዊ ጥቅምን የማስጠበቅ ተልዕኮ አለው::
2. የዴሞክራሲ ሥርዓት በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መካከል ከአድልዎ የፀዳ ፍትሐዊ አሠራር ያሰፍናል::
3. ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አንድነታቸው የሚገለፀው ሁሉም የሰው ልጅ በተፈጥሮ የሚያገኛቸው መሆናቸው ላይ ነው::
4. ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሕዝቦች እራሳቸው በመረጡዋቸው መሪዎቻቸው የሚተዳደሩበት ሥርዓት ነው::
5. የሃሳብ ልዩነቶችን መቀበል ልዩነቶች መኖራቸውን አምኖ መቀበል ብቻ ሳይሆን አንዱ የሌላውን ሃሳብ የማይስማማበት ቢሆንም ማክበርንም ይጨምራል::

II. *በ"ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ::*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ሀሳብን በነፃ መግለጽ፣ ሠላማዊ ሰልፍ ማድረግ፣ | ሀ. ሰብዓዊ መብቶች:: |
| 2. በሕይወት መኖር፣ የአካል ደህንነት፣ | ለ. የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መርሆዎች:: |
| 3. መልካም ጉርብትና፣ ወንድማማችነት፣ | ሐ. ዴሞክራሲያዊ መብቶች:: |
| 4. ልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ፣ | መ. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሠረቶች:: |
| | ሠ. ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች:: |

III. *ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::*

1. የዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረታዊ ባህሪ የሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ) መቻቻል፣
   - ለ) እኩልነት፣
   - ሐ) የሕዝብ ተሳትፎ፣
   - መ) ሁሉም መልስ ናቸው::
2. በዴሞክራሲ ሥርዓት ህዝቦች የሚሳተፉት እንዴት ነው?
   - ሀ) በመምረጥና በመመረጥ፣
   - ለ) በአካባቢ ስብሰባዎች በመገኘት፣
   - ሐ) በተለያዩ ሕዝባዊ ማሕበራት አባላት በመሆን፣
   - መ) ሁሉም መልስ ናቸው::
3. ሀገራዊ ጥቅማችንን የሚያስጠብቅ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማለት ምን ማለት ነው?
   - ሀ) በሀገራችን ፈጣን ልማትን ለማምጣት የሚረዳ ፖሊሲ ማለት ነው፣
   - ለ) ዴሞክራሲ በሀገራችን ስር እንዲሰድ ለማድረግ የሚረዳ ፖሊሲ ማለት ነው፣
   - ሐ) ሕዝባችንን ቀጥታ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚረዳ ፖሊሲ ማለት ነው፣
   - መ) ሁሉም ልክ ነው::

IV. *የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. የቋንቋ፣ የሃይማኖት እና የሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች ልዩነቶች ባሉባት ሀገራችን ሁላችንም ተከባብረን፣ተቻችለን እና ተፋቅረን እንድንኖር የሚረዳን ሥርዓት ------------------ነው::
2. የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሠረቶች-------------------እና ---------------- ናቸው::

V. *የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ::*

1. የሃሳብ ልዩነቶችን መቀበል እና የሃሳብ ልዩነቶችን አቻችሎ አብሮ መኖር ማለት ምን ማለት ነው? ጥቅሙስ ምንድን ነው? በምሳሌ አስረዱ::
2. የዴሞክራሲ ሥርዓት በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገሮች እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው የሚባለው ለምንድነው? በምሳሌ አብራሩ::

# ምዕራፍ ሁለት

# የሕግ የበላይነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** *ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፣*

- የሕገመንግሥትን አስፈላጊነት ታውቃለህ/ታወቂ ያለሽ፣
- ሕግን ማክበርና ማስከበር ለዜጐች የሚና ረውን ጠቀሜታ ትረዳለህ/ትረጂያለሽ፣
- በሕዝብ ተመራጮችና የመንግሥት ባለሥል ጣናት ላይ ገደብ የመጣል አስፈላጊነትን ት ረዳለህ/ትረጂያለሽ::

## 2.1 ሕገመንግሥት ምንድን ነው?

- ስለ ፌዴራል ሕገመንግሥትና ስለ ክልል ሕገመንግሥት ምን ተምራችሁ እንደነበር ታስታውሳላችሁ? ምን ግንኙነት አላቸው?

ሕገመንግሥት የአንድ ሀገር የበላይ ሕግ ሲሆን፣ የአንድ ሕዝብ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ዋና ዋና ዓላማዎች ተደንግገው የሚገለፁበት ሰነድ ነው:: ሕገመንግሥት ዜጐች በመብታቸው እንዲጠቀሙና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ይረዳል::

የፌዴራሉ ሕገመንግሥት በዋነኝነት በሀገር አቀፍ ደረጃ ዋና ዋና የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ጉዳዮችን የሚመለከት ሰነድ ነው:: የክልል ሕገ መንግሥታት ደግሞ ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረጉ፣ የክልሉን የኢኮኖሚያዊ፣ የማሕበራዊና የልማት ፖሊሲ ስትራቴጂዎችን ያካተቱ መሠረታዊ ሰነዶች ናቸው::

**መልመጃ 1**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. ሕገመንግሥት ምንድን ነው?
2. ፌደራል ሕገመንግስት በውስጡ ያካተታቸው ደዘቶች በምን ላይ ያተኮሩ ናቸው?

### 2.1.1 የክልል ሕገመንግሥታት አስፈላጊነት፣

- ክልሎች የራሳቸውን ሕገመንግሥት ማዘጋጀት ለምን ያስፈልጋቸዋል?

የክልል ሕገመንግሥታት እንደ የክልሎቹ ተጨባጭ ሁኔታ ክልሎች ራሳቸውን የሚመሩብትና ሕዝቡን የሚያስተዳድሩበት ሕገመንግሥት ነው:: በመሆኑም የክልል ሕገ መንግሥታት ከሚያስፈልጉበት ምክንያቶች ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

- የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን የሥልጣን ባለቤትነት ያረጋግጣሉ።
- ራስን በራስ የማስተዳደር ሁኔታን ያመቻቻሉ።
- የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበ ሕግ ማውጣት ያስችላሉ።
- የፆታ፣ የቋንቋና የባህል እኩልነቶችን ያረጋግጣሉ።

**መልመጃ 2**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. የክልል ሕገመንግሥት ዓላማ ምንድ ነው?
2. የክልል ሕገመንግሥት አስፈላጊነት የማያ ጉድሉ ምንክያቶች ሦስቱን በመጥቀስ አብራሩ::

**የቡድን ሥራ 1**

*የፌዴራልና የምትኖሩበትን ክልል ሕገ መንግስታት በቡድን አንብቡና የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመሥራት አጭር ሪፖርት አቅርቡ/ እያንዳንዱ ቡድን የፌደራሉንና የራስን ክልል ሕገ መንግስት ያንብብ።*

1. የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት ያተኮረባቸውን ዋና ዋና ጉዳዮች ዘርዝሩ::
2. የየክልሎች ሕገመንግሥታት ያተኮሩባቸው ዋና ዋና ጉዳዮችን ግለፁ::
3. የፌዴራልና የክልል ሕገመንግሥታት አንድነትና ልዩነት ምንድንነው?

### 2.1.2 የአካባቢያዊ ባህላዊ ደንቦች ሥርዓትን በማስከበር ረገድ ያላቸው ድርሻ፣

- የአካባቢያዊ ባህላዊ ደንቦች መኖር ለምን ያስፈልጋል?

ሰዎች የዕለት ተዕለት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ማንኛውንም ዓይነት ተግባራት አሸንፎ ለመውጣት የተለያዩ ማሕበራዊ ተቋማትን በማቋቋም ሲንቀሳቀሱ ኖረዋል፣ አሁንም ይህንን እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቻቸውን ለመወጣት ዕድር፣ ዕቁብ፣ የቁጠባና ብድር ማሕበር፤ መንፈሳዊ ችግሮቻቸውን ለመወጣት ደግሞ መንፈሳዊ ማሕበራትን ያቋቁማል፡፡ ግጭቶች ሲነሱ ደግሞ ግጭቶችን ማብረድ የሚችሉ ገላጋይ አካላትን ያቋቁማሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች የሚመሩባቸው ደንቦችና መመሪያዎች ሲኖራቸው በማዕከላዊና በክልል ደረጃ የሚወጡ ሕጎችን በማጠናከርና ሥርዓትን በማስከበር ረገድ አስተዋጽኦቸው ከፍተኛ ነው፡፡

**መልመጃ 3**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

?
1. የአካባቢያዊ ባህላዊ ደንቦች መኖር ጠቀሜታው ምንድነው?
2. የአካቢባቢያዊ ባህላዊ ደንቦች ሥርዓትን በማስከበር ረገድ ምን ሚና ይጫወታሉ?

### 2.1.3 ሕግን አለማስከበር በዜጎች ላይ የሚያስከትለው ጉዳት፣

- ሕግን ማስከበር አለመቻል ምን ጉዳት ያስከትላል?

**የይስሙላ ሕግ፤**

የታሪክ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከክፍል ተጠሪ መምህራቸው ጋር በመሆን የክፍል ሕግ አውጥተዋል፡፡ ላወጡትም ሕግ ሁሉም ተገዥ እንደሚሆኑ ስምምነት ላይ ደርሰዋል፡፡ ካወጧቸውም የክፍሉ ህጎች መካከል በሰዓት ክፍል ውስጥ መገኘትና የትምህርት ቤቱን ሥርዓት አክብሮ መከታተል የሚሉ ይገኙበታል፡፡ የክፍል ሥርዓቱን እንዲያስከብር የተመረጠው ሚናስ ነው፡፡

ሚናስ የወጡትን ሕጎች ሙሉ በሙሉ የሚያከብር ቢሆንም፤ ሌሎች ተማሪዎች በተመሳሳይ መንገድ እንዲያከብሩ የሚያደርገው ጥረት ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን ሚናስ ሕጉን ቢያከበርም ሌሎች የክፍል ጓደኞቹ በተመሳሳይ ሁኔታ ሕጉን እንዲያከብሩ ባለማድረጉ ሠላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ሊኖር አልቻለም፡፡ የአብዛኛው ተማሪ የመማር ማስተማር ፍላጎትም እየቀነሰ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡

**መልመጃ 4**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?
1. ለሕጉ ተግባራዊ አለመሆን ተጠያቂው ማን ነው?
2. ሕጉ ቀጣይነት እንዲኖረው የክፍሉ ኃላፊ መምህር ምን ማድረግ ነበረባቸው?

ሕግን ማክበር ማለት ዜጎች ሁሉ በሕጎች መገዛትንና መመራትን ያመለክታል፡፡ ሕግን ማስከበር ደግሞ ሕጎች በሌሎች ሲጣሱ ሕጋዊ በሆነ መንገድ መከላከልን የሚገልጽ ሃሳብ ነው፡፡ ሕግ ከሌለ ወይም ካልተከበረ ትምህርትን በአግባቡ መማር አይቻልም፣ ሠላም ስለሚጠፋ እንደ ልብ መውጣት መግባትም አይቻልም፣ ሰላማዊ ዜጎችም በጉልበተኞች ይጠቃሉ፡፡

**መልመጃ 5**

*የሚከተሉትን ሁኔታዎች አንብቡና ምን መደረግ እንደነበረበት ተወያዩ።*

?
1. አርፍዶ የሚመጣ የትምህርት ቤት ሠራተኛ ተማሪዎችን አታርፍዱ ቢል፣
2. ለትምህርት ቤቱ ውበት የማይቆረቆር ሠራተኛ የትምህርት ቤት ንጽህና ይጠበቅ ቢል፣

☞ ሕግን ለማስከበር መጀመሪያ ሕግን ማክበር ያስፈልጋል፡፡

**መልመጃ 6**


*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

?
1. ሕግ የማይከበር ከሆነ ምን ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ?
2. ሕግን ማክበር የማን ኃላፊነት ነው? ማስክበርስ?

## 2.2 ሥነ ምግባር፤
### 2.2.1 የሥነምግባር ምንነት



ሥዕል 2.1 አዛውንቶችን መርዳት አንዱ የሥነምግባር መገለጫ ነው፡፡



ሥዕል 2.2 መልካም ሥነምግባርን የሕይወታችን መመሪያ እናድርግ፡፡

- በሥዕሉ ውስጥ ምን ምን ተግባራትን ተመለከታችሁ?
- እናንተስ በየትኞቹ ተግባራት ብትሳተፉ ደስ ይላችኋል?

**የመልካም ሥነምግባር ዋጋ፤**

ምሥግና የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነው፡፡ በጥሩ ባህሪው በቤተሰቡ፣ በጐረቤቶቹና በትምህርት ቤቱ የተመሰከረለት ነው፡፡ ምሥግና በባህሪው ብቻ ሣይሆን በትምህርቱም በጣም ጉበዝ ከመ ሆኑ የተነሣ በጓደኞቹና በመምህራኑም ዘንድ ተወዳጅ ነው፡፡

የትምህርት ቤቱን ሕግና ሥነሥርዓት በማክበ ርም የታወቀ ነው፡፡ በብዙዎችም ዘንድ "የልጅ አዋቂ" የሚል ሥም አትርፎአል፡፡ ከትምህርት ሰዓት ውጭ በተለያዩ ክበባት ውስጥ ይሳተ ፋል። በተለይም በሥነዜጋና ሥነምግባር ክበብ ውስጥ የሚያደርገው ተሣትፎ ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህም ሁለት ጊዜ ተሸልሟል፡፡

በትምህርቱም ሆነ በመልካም ሥነምግባሩ ከአ ጠቃላይ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ተመርጦ ከርዕሰ መምህሩ ማበረታቻ ሽልማቶችን ተቀ ብሏል፡፡

ምሥግና በቤተሰቡና በጐረቤቶቹ በመልካም ሥነምግባሩና በትምህርቱም ውጤታማ በመ ሆኑ በአካባቢው "ልጅ ከወለዱ አይቀር እንደ ምሥግና ነው" ተብሎ በምሣሌነት የሚጠቀስ ሆኗል፡፡

**መልመጃ 7**

**በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡**

1. ለምሥጋና መልካም ሥነምግባርና በትምህር ቱም ውጤታማ መሆን አስተዋጽኦ ያደረጉት እነማን ይመስሏችኋል?
2. የመልካም ሥነምግባር ባለቤት መሆን ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኛል?

ድርጊቶች ጥሩ ወይም መጥፎ መሆናቸውን የምንመረምርበት መለኪያ ሥነምግባር ነው፡፡ የሥነምግባር ትኩረቱ አንድ ሰው የመልካም ምግባር ባለቤት ሆኖ እንዲገኝ ማድረግ ነው፡፡ መልካም ሥነምግባር የሚባለውም ሕብረተ ሰቡ የሚቀበለውና ጠቃሚነት ያለው ባህርይ ወይም ተግባር ነው፡፡ መጥፎ ሥነምግባር የሚባለው ደግሞ ሕብረተሰቡ የማይቀበለው

ማንኛውም ዓይነት ተግባር ወይም አድራጎት ነው፡፡ በአጠቃላይ ሥነምግባር የጥሩ ወይም የመጥፎ ፀባይ ወይም ተግባር መለኪያ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

**መልመጃ ፰**

? ከዚህ በታች የተመለከተውን ሰንጠረዥ በደብተራችሁ ገልብጡ፡፡ በማስከተልም የተዘረዘሩትን የሥነምግባር መገለጫዎች «መልካም ምግባር» ወይም «መልካም ያልሆነ ምግባር» በሚሉት ሥር ከያንዳንዱ ሐረግ ትይዩ «✓» ምልክት በማድረግ አመልክቱ፡፡

| የሥነምግባር መገለጫዎች | የመልካም ምግባር ምሳሌ | መልካም ያልሆነ ምግባር ምሳሌ |
|---|---|---|
| የትምህርት ቤትንና የክፍል ደንቦችን ማክበር፣ | | |
| አቅመ ደካሞችን መርዳት፣ | | |
| በሕብረተሰቡ ተቀባይነት የሌለው ተግባር መፈፀም፣ | | |
| ከሰዎች ጋር ግጭት መፍጠር፣ | | |
| ወላጆችንና ታላቅን አለማክበር፣ | | |
| አቅመ ደካማዎችን መናቅ፣ | | |
| ምሥጢር መጠበቅ፣ | | |
| ግልፅና ታማኝ አለመሆን፣ | | |
| እውነተኛ መሆን፣ | | |
| መዋሸት፣ | | |
| ማታለል፣ | | |

### 2.2.2 በትምህርት ቤት ደረጃ የሚጠበቅ የተማሪ ሥነምግባር፣

- በትምህርት ቤት ውስጥ ከተማሪዎች የሚጠበቅ ሥነምግባር ምንድን ነው?

የተማሪ ሥነምግባር መገንባት የሚጀመረው በቤተሰብ ውስጥ ነው፡፡ ልጆችን በጥሩ ሥነምግባር አንጾ ለማሳደግ የወላጆች ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ልጆች ከማንኛውም መጥፎ ድርጊት ርቀውና መልካም ሥነምግባር ኖሮአቸው እንዲያድጉ የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነትም አለባቸው፡፡ ትምህርት ቤቶችም ከወላጆች ባልተናነሰ ተማሪዎች በመልካም ሥነምግባር ታንጸው እንዲያድጉ ለሥነምግባር ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ከተማሪዎች የሚጠበቁ የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች በርካታ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የማፍራት ከፍተኛ ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል፡፡ እነሱም ከቀለም ትምህርት ጎን ለጎን መልካም ሥነምግባር ያለው ዜጋ በማፍራት ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ፡፡

**ሀ. የት/ቤትና የክፍል ሕጎችንና ደንቦችን ማክበር፣**

የመማር ማስተማሩን ሒደት ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል አሠራር ማስፈን አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንንም ለማስፈን የት/ቤት ሕጎችና ደንቦች ዓይነተኛ መሣሪያዎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸው የሚያወጣቸውን ሕጎችና ደንቦች ማክበር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከትምህርት ቤት ሕግና ደንብ በተጨማሪ ተማሪዎች ከመምህራኖቻቸው ጋር ተስማምተው የሚያወጧቸው የክፍል ሕጎች ይኖራሉ፡፡ እነዚህንም ሕጎች ማክበር ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ የትምህርት ቤቱንና የክፍሉን ሕጎችና ደንቦች አክብሮ መገኘት ከተማሪዎች የሚጠበቁ የመልካም ሥነምግባር መገለጫዎች ናቸው፡፡

**ለ. የትምህርት ቤትና የመማሪያ ክፍሎችን ንብረቶች ከጉዳት መከላከል፣**

በትምህርት ቤትና በመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙ ንብረቶች ከሕዝብ በተሰበሰበ ገንዘብ የተገዙ ናቸው፡፡ ንብረቶቹ ብዙ ሃብት የፈሰሰባቸው በመሆናቸው በቀላሉ የሚተኩ አይደሉም፡፡ ስለሆነም ረዘም ላለ ጊዜ እንዲያገለግሉ ይጠበቃል፡፡ ረዥም ጊዜ ማገልገል የሚችሉት ደግሞ ተማሪዎች በጥንቃቄ ሲጠቀሙባቸውና ንብረቶቹ እንዳይጎዱ ከጥፋት ሲጠበቁ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተማሪ በኃላፊነት ስሜት ይህንን ማድረግ ከቻለ ንብረቶቹ ተጠብቀው መጪው ትውልድ የሚጠቀምበት ይሆናል፡፡

**ሐ. የትምህርት ቤትንና የመማሪያ ክፍሎችን ጽዳትና ውበት መጠበቅ፣**

ከተማሪዎች ከሚጠበቅ የመልካም ሥነምግባር ባህሪያት መካከል አንዱ የት/ቤታቸውንና የመማሪያ ክፍሎቻቸውን ጽዳትና ውበት መጠበቅ ነው፡፡ ይህ ዓላማ እንዲሳካ ደግሞ ሁሉም ተማሪ ክፍሉን ማጽዳት፣ በት/ቤት ተተክለው ያሉ ዛፎችንና እፅዋትን መንከባከብ፣ ጥፋት እንዳይደርስባቸው መከላከልና ደርሶም ሲገኝ ለት/ቤቱ አስተዳደር ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

የት/ቤቱ ጽዳትና ውበት የተስተካከሉ ከሆኑ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ለመማር ምቹ ሥፍራዎች ይሆኑላቸዋል፡፡ ይህ ሲሆን ት/ቤቶች እንደመማሪያ ሥፍራ ብቻ ሳይሆን እንደመዝናኛ ቦታዎችም ሆነው ያገለግላሉ፡፡

**መ. የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ ማክበር፣**
በት/ቤት ውስጥ የሚካሄደው የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማነት የሁሉም የት/ቤቱ ማሕበረሰብ ጥረት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን አካላት ሁሉ ማክበር ከተማሪዎች የሚጠበቅ የመልካም ሥነምግባር መገለጫ ነው፡፡

**መልመጃ 9**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

?

1. የክፍል ጠረጴዛዎችና መቀመጫዎች በጥንቃቄ ጉድለት ምክንያት ቢሰባበሩ በሚቀጥለው ዓመት ወደዚህ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች እንዴት መማር ይችላሉ? ተወያዩበትና መፍትሄ የምትሏቸውን ሃሳቦች ጠቁሙ፡፡
2. በት/ቤት ውስጥ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ሥነምግባሮች ምንድን ናቸው?
3. ተማሪዎች መልካም ሥነምግባር እንዲኖራቸው ለምን ይፈለጋል?
4. በመልካም ሥነምግባር የተገነባ ትውልድ በማፍራት ረገድ የቤተሰብ ድርሻ ምን ሊሆን ይችላል፡፡

## 2.3 የሥልጣን ገደብ፤

### 2.3.1 የሥልጣን ገደብ ምንድነው?

- በቀበሌያችሁ ወይም በወረዳችሁ ተመራጭ ሆኖ በሕግ ከተፈቀደለት ሥልጣን ውጪ ሰርቷል ተብሎ የተከሰሰ ሰው መኖሩን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
- በእንደዚህ ዓይነት ተግባር የተሳተፈ ሰው ምን እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል ትላላችሁ?

የሥልጣን ገደብ አንድን ሥራ ለማከናወን በሕግ የተሰጠ ሥልጣን ነው፡፡ በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የህዝብ ተመራጭ ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን ለሚሠራው ሥራና ለተሰጠው ኃላፊነት ሁሉ በልዩ ልዩ ሕጎችና ደንቦች የተወሰነ የሥራ መፈፀሚያና ማስፈፀሚያ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይህን ሕጋዊ ሥልጣኑን በተገቢው ጊዜና ቦታ በአግባቡ ተጠቅሞ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ የሥልጣን ገደቡ ነው፡፡ ከተሰጠው የሥልጣን ገደብ ውጭ በማንኛውም መልኩ መሥራትና ማሰራት አይፈቀድለትም፡፡

ሰዎች ከተሰጣቸው ሥልጣን ውጭ የሚሰሩ ከሆነ ትክክለኛ አሠራር የሚባል ነገር ይጠፋል፡፡ ሁሉም የመሰለውን ተግባር በመሰለው መንገድ ያከናውናል፡፡ ለምሳሌ የክፍል አለቃ የክፍል ሥነ-ሥርአትን ከማስከበር ያለፈና ያልተፈቀደ ተግባር ካከናወነ በክፍል ውስጥ ሰላም ይጠፋል፣ ተማሪዎችም ተረጋግተው መማር አይችሉም፡፡

**መልመጃ 10**

?

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. የሥልጣን ገደብ ማድረግ ለምን ያስፈልጋል?
2. የሥልጣን ገደብ ባይኖር ምን ምን ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ?

### 2.3.2 በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሥልጣን ገደብ የመጣል አስፈላጊነት፣

- የሕዝብ ተመራጮች እነማን ናቸው?

**የአቶ ሙሳቱ ትዕቢት፤**

አቶ ሙሳቱ በሕዝብ የተመረጡ የአንድ ቀበሌ ሊቀመንበር ናቸው፡፡ እሳቸውም ሃላፊነት ከተሰጣቸው ጊዜ ጀምሮ ድሮ የነበራቸው ተወዳጅ ፀባያቸው እየተለወጠ መጥቷል፡፡ በሕግ ከተሰጣቸው ስልጣን ውጭም መሥራት ጀምረዋል፡፡ በአድሎ እና በዘመድ እንደሚሰሩ ይታማሉ፡፡ ለምሳሌ የተለያዩ ሰዎችን ቀበሌው ከሚያከራየው ቤት ያለበቂ ምክንያትና በቀበሌው ማሕበራዊ ፍርድ ቤት በሕግ ሳያስወስኑ በማን አለብኝነት አስወጥተው ለቅርብ ዘመዶቻቸው መስጠታቸው ያደባባይ ምሥጢር ነው፡፡

ከዚህም ሌላ ከሥልጣን ገደባቸው በማለፍ ለመኖሪያ ቤት በሊዝ ጨረታ ለመሸጥ የተዘጋጀውን መሬት የተለያዩ ጥቅሞችን በመቀበል ሸጠዋል፡፡ ሕገወጥ ግንባታም እንዲከናወን ፈቅደዋል፡፡ በዚህም የተነሳ የመረጣቸው ሕዝብ ቅሬታ አድሮበታል፡፡ ጉዳዩን ይፋ አውጥተው ሊወቅሷቸውና እርምጃ ሊወስዱባቸው አልቻሉም፡፡

አንድ ቀን ቀበሌው ለሌላ ጉዳይ ባስጠራው የሕዝብ ስብሰባ ላይ የአቶ ሙሳቱን ምስጢር የሚያውቅ ሰው አቶ ሙሳቱ እያደረሱ ያሉትን በደል በዝርዝር ጠቅሶ ግለሰቡ ከሥልጣናቸው

እንዲወርዱና ለአደረሱትም ጥፋት በሕግ እንዲ ከሰሱ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ ነገሩ በሁሉም ልብ ውስጥ የነበረ በመሆኑ የተሰበሰበው ሕዝብ የቀረ በው ጥያቄ ትክክለኛ መሆኑን በማጨብጨብ ገለጸ፡፡ አቶ ሙላቱ ግን የቀረበባቸውን የጥፋተ ኝነት ክስ የማይቀበሉ እና ሥልጣናቸውንም እንደማይለቁ ገለጹ፡፡

**መልመጃ 11**

***ከላይ በቀረበው ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. አቶ ሙላቱ ከሕግ ውጭ የፈፀሙት ተግባር ምንድነው?
2. ሰውየው ጥያቄ ሲያቀርብ ሕዝቡ ለምን ያጨበጨበ ይመስላችኋል?
3. አቶ ሙላቱ ሥልጣኔን አለቅም በማለታቸው በሥልጣን ላይ ሊቆዩ ይችላሉ? ለምን?
4. በአካባቢያችሁ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሁኔታ መከሰቱን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ውጤቱስ ምን ሆነ?

የሕዝብ ተመራጮች የሚባሉት በአንድ አካባቢ የሚኖር ሕብረተሰብ ወይም ሕዝብ ሕጋዊ መብቶቹን እንዲያስከብሩለትና እሱን ወክለው ሕጋዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑለት ከመካከሉ የሚመርጣቸው ተወካዮች ናቸው፡፡ በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሥልጣን ገደብ ማድረግ የሚያስፈልገው፤

**መልመጃ 12**

***በሚከተለው ጥያቄ ላይ ተወያዩ፡፡***

1. በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሥልጣን ገደብ መኖሩ የሚያስፈልግባቸውን ምክንያቶች በመ ዘርዝር ተወያዩባቸው፡፡

## 2.4 ምስጢር

### 2.4.1 የጓደኛ ምሥጢር፣

- የጓደኛ ምሥጢር ማለት ምን ማለት ነው?
- ከጓደኞቻችሁ ጋር ምሥጢር ብላችሁ ተነ ጋግራችሁ ታውቃላችሁ?
- በጓደኞሞች መካከል ምን ምን ጉዳዮችን ነው ምስጢር ብሎ መያዝ የሚቻለው?

**የአደራ ቃል አምካኝ፣**

ምሥጢሬን ጉዳይህ ብዬ ባጫወትኩህ፣
ለምን ያለቦታው እንደ ወፍ ዘራኸው?
በመሃላ ኪዳን ቃሌ ቃልህ ብለህ፣
ምነዋ ከዳኸኝ አደራህን ሰብረህ፡፡
የሰው ዐይን አስፈራኝ ጀርባዬ ጉብጠ፣
ባንተ ኪዳን ማፍረስ ውስጤ ተናወጠ፡፡
እኔስ ላንተ ይብላኝ ጉዳቴ ያገግማል፣
ዓመታት ቢፈጅም ቁስሌ ይፈወሳል፡፡
*(ዳግላስ ጴጥሮስ - 1977 ዓ.ም.)*

**መልመጃ 13**

***ከላይ የቀረበውን ግጥም መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ግጥሙ ስለ ምሥጢር አጠባበቅ ምን ያስተ ምራል?
2. ምስጢሩ የባከነበት ሰው ጉዳት በግጥሙ ውስጥ እንዴት ተገልጧል?
3. ምስጢሩ የማይጠበቅለት ሰው ምን ጉዳት ይገጥመዋል?

የጓደኛ ምሥጢር ማለት በሁለት ወይም ከሁ ለት በላይ በሆኑ ጓደኞሞች መካከል በቃል ኪዳን ተጠብቆ የሚያዝ ጉዳይ ማለት ነው፡፡ ምሥጢሩ ለሌላ ሰው ወይም አካል ቢነገር ተገቢ ምግባር አይደለም፡፡ ምናልባትም ችግር ወይም አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ የጓደኛ ምሥጢር በትዳር ጓደኛሞች፣ በክፍል ወይም በት/ቤት ጓደኛሞች፣ በሥራ ጓደኛሞች፣ በአካ ባቢ ጓደኛሞች ወዘተ መካከል ሊፈፀም ይችላል፡፡ አንዳንድ ሰዎች በባህሪያቸው ምሥጢር ተብሎ የተነገራቸውን የመጠበቅ ችሎታ ሲኖራቸው አንዳንዶች ደግሞ ምሥጢርን አሣልፎ ለሌላ ሰው የመስጠት ባህሪያት አላቸው፡፡ ምሥጢርን መጠበቅ የማይችሉ ሰዎች የጓደኛን፣ የቤተሰብን እንዲሁም የሕብረተሰቡን ፍቅር አያገኙም፤ የተ ናቁና የተጠሉ ይሆናሉ፡፡ ምሥጢርን ለመጠበቅ ቃል በተገባበ ጓደኞሞች መካከል በተለያየ ምክን ያት ግንኙነታቸው ቢቋረጥም እንኳ ምሥጢሩ እንደተጠበቀ ሊቆይ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ምሥ ጢሩ ቢባክን በአንደኛው፣ በሁለቱም ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ ችግር ወይም አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡

**መልመጃ 14**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. የጓደኛ ምሥጢር ምንድን ነው?
2. በጓደኛሞች መካከል ሊኖር የሚችል ምሥጢር ምሳሌ ስጡ::
3. በጓደኛሞች መካከል ሊያዝ የሚገባው ምሥጢር ቢባክን ምን ችግር ሊከሰት ይችላል?

## 2.5 ሙስና፤

### 2.5.1. የሙስና ምንነት፣




ሥዕል 2.3 ሙስና የሕግ የበላይነት እንዳይከበር ያደርጋል::

- በሥዕሉ ውስጥ የምትመለከታቸው ሰዎች ምን እያደረጉ ነው?
- የተወሰኑ ሰዎች ሕብረተሰቡን የሚጐዳ ተግባር ቢፈፅሙ ምን ታደርጋላችሁ?

**ይህች ናት ውጤት፤**

የሰባተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ሉባባ የሀብታም ልጅ ናት:: በትምህርቷ ግን በጣም ደካማ ከሚባሉት ተማሪዎች አንዷ ናት:: መምህር አስጨናቂ የሉባባ የሂሣብ መምህርና የክፍሉም ተጠሪ ናቸው:: መምህር አስጨናቂ የሉባባን የቤተሰብ ሁኔታ ጠንቅቀው ያውቃሉ:: ስለዚህም ቤተሰቦቹን በማስጠራት ልጅቷ በትምህርቷ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋት መሆኑን ይነግሯቸዋል:: ቤተሰቦቿም መምህር አስጨናቂን በትርፍ ጊዜው ሉባባን እንዲያስጠኑላቸው ለድካማቸውም ጥሩ ገንዘብ እንደሚከፍሉ ተነጋግረው የማስጠናቱን ሥራ ይጀምራሉ:: በማስጠናት ሥራ የሚያገኙት ገንዘብ በመደበኛ የማስተማር ሥራ ከሚያገኙት ገንዘብ የሚበልጥ በመሆኑ ኑሮአቸውን ደጉሞላቸዋል:: መምህር አስጨናቂ ሉባባን ለመርዳትና ወደ ውጤት ለማምጣት ብዙ ጥረት ቢያደርጉም የታለመው አበረታች ውጤት ሊመጣ አልቻለም:: በዚህ ሁኔታ የፈተና ጊዜ ይደርሣል:: ሉባባ ጥሩ ውጤት ማምጣት እንደማትችል በማወቅና ይህ ውጤት ካልመጣ ደግሞ ሊገኝ የሚችለው ጥቅም ሊቋረጥ እንደሚችል በመገንዘብ መምህር አስጨናቂ የፈተና ጥያቄዎችን በምሥጢር በማውጣት ልጅቷ በመልመጃ መልክ እንድትሠራ ያደርጋሉ:: ሉባባም ዝግጅቷን አጠናቃ ለፈተና ትቀርባለች:: በመጨረሻም ውጤቷ ከክፍሉ ተማሪዎች ሁሉ ከፍተኛ ሆነ:: ጉዳዩን ተማሪዎችና መምህራን ለትምህርት ቤቱ አስተዳደር ያመለክታሉ:: ጥቆማ የደረሰው አካል ጥቆማውን መሠረት አድርጎ ሲያጣራ መምህር አስጨናቂ በጉዳዩ እንዳሉበት ታወቀ:: አሁን የመምህር አስጨናቂ ጉዳይ ለትምህርት ቤቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እየታየ ይገኛል::

**መልመጃ 15**

***ከላይ በቀረበው ምንባብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. መምህር አስጨናቂ ሙስና ፈጽሟል ወይስ አልፈፀመም?
2. ምን ምን የሙስና ወንጀሎችን ነው መምህር አስጨናቂ የፈፀመው?
3. መምህር አስጨናቂ ለሠራው ጥፋት ምን ውሳኔ ሊሰጠው ይገባል?

ሙስና የአንድን ሀገርና መንግሥት መልካም አስተዳደር የሚያቃውስ፣ ለዴሞክራሲ እና ኢኮኖሚ እድገት የሚደረገውን ጉዞ የሚያደናቅፍ፣ በሰዎች መካከል አብሮ የመኖርንና ለአካባቢና ለሀገር ልማት ተባብሮ የመስራትን ውድ እሴቶች የሚሸረሽር መጥፎ ድርጊት ነው:: ሙስና አለመታመን፣ በተሰጠ አደራ ላይ እምነትን ማጉደል፣ በገንዘብ መገዛትና በሞራል መዝቀጥ፣ በጉቦ በመማለጃና አድሎ፣ ሀቀኝነትንና ታማኝነትን ማጉደል ነው::

**መልመጃ 16**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

1. ሙስና ምንድን ነው? መገለጫዎቹስ ምን ድን ናቸው?
2. ሙስና ምን ጉዳት ያስከትላል?

### 2.5.2 ኃላፊነታቸውን በዘነጉ የሕዝብ ተመራጮችም ሆነ የመንግስት ባለስልጣናት ሲፈፀሙ የሚችሉ የሙስና ተግባራት፣

- *ኃላፊነታቸውን በዘነጉ ባለሥልጣናት ሊፈፀሙ የሚችሉ የሙስና ተግባራት ምንድንናቸው?*
- *በሕዝብ የተሰጠን ሥልጣን በምን ዓይነት መንገድ ነው መጠቀም ያለብን?*

***ሥልጣን*** በሕዝብ ምርጫ፣ በፖለቲካ ሹመት ወይም በትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ሊገኝ ይችላል፡፡ ሕዝቡ መርጦ ሥልጣን ላይ የሚያስ ቀምጣቸው ሰዎች የሕዝብ ተመራጮች ሲባሉ በፖለቲካ ሹመት፣ በትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ምክንያት ሥልጣን የሚያገኙ ደግሞ የመንግሥት ባለሥልጣናት ይባላሉ፡፡

ማንኛውም ባለሥልጣን የሚጠበቅበትን ኃላፊ ነት እና ግዴታ ከመወጣት ባሻገር በህግና በመመሪያው በተደነገገው መሠረት ሥራውን ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ ከቀበሌ እስከ ተወካ ዮች ምክር ቤት ድረስ በሕዝብ ተመርጠው የተወከሉ ግለሰቦች ኃላፊነታቸውን ካልተወጡ፣ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ካልሠሩ አድራጎታቸው እንደ ጥፋት ተደርጐ ይወሰዳል፡፡ በሕዝብ ተመ ራጮች ወይም በመንግሥት ተሿሚዎች ከሚፈ ፀሙ የሙስና ተግባራት መካከል የሚከተሉት በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

- መደለያን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ስጦታን መቀበልና አላስፈላጊ በሆነ መንገድ ሰውን መጥቀም ወይም መጉዳት፣
- የመንግሥትን ወይም የሕዝብን መገል ገያ ለግል ጥቅም ማዋል፣
- የመንግሥት ሥልጣንን መከታ በማድ ረግ በዘመድ አዝማድና በመሣሰሉት ድር ጊቶችን መፈፀም፣
- በማስገደድ መጠቀምና የግልን ጥቅም ማመቻቸት፣
- ምሥጢር ማባከን፣
- ስርቆትን፣ ማጭበርበርና ምዝበራን ማራ መድ፣
- በዝምድናና በጓደኝነት መሥራት፣

**መልመጃ 17**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

?

1. የሕዝብ ተመራጮችና የመንግሥት ባለስ ልጣናት ልዩነት ምንድነው?
2. በሕዝብ ተመራጮችና በመንግሦት ባለስ ልጣናት ሲፈፀሙ ከሚችሉ የሙስና ተግባራት መገለጫዎች አራቱን በመጥቀስ ማብራሪያ ስጡ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

*ሕገ መንግስት* የአንድ ሀገር የበላይ ሕግ ሲሆን፣ በዋነኛነት የሀገሪቱን ዋና ዋና የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ማሕበራዊ ጉዳዮችን የያዘ ሰነድ ነው፡፡ የክልል ሕገመንግስታት ደግሞ ክልሎች እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳደሩ የሚያስችሏቸው የክልሎች የበላይ ሕጎች ናቸው፡፡

ሕግን ማክበር ማለት ዜጎች ሁሉ በሕጎች መገዛትና መመራትን የሚያመለክት ሲሆን፣ ሕግን ማስከበር ደግሞ ሕጎች በሌሎች ሰዎች ሲጣሱ ሕጋዊ በሆነ መንገድ መከላከልን ያሳያል፡፡

ለማንኛውም ነገር ገደብ ካልተደረገለት ልኩ ሳይታወቅ ቀርቶ ሥርዓት ይበላሻል፡፡ እንደዚሁም ለማንኛውም ነገር ገደብ ካልተበጀለት ልኩ ሳይታወቅ ቀርቶ ሥርዓት ይበላሻል፡፡ እንደዚሁም በማንኛውም ደረጃ ለሚገኝ የሕዝብ ተመራጭም ለሚሠራው ሥራ እና ለተሰጠው ኃላፊነት ሁሉ በልዩ ልዩ ሕጐችና ደንቦች የተወሰነ የትክክለኛ የሥራ መፈፀሚያና ማስፈፀሚያ ሥልጣን ወሰን ውስጥ እንዲሠሩ ለማድረግ ነው፡፡

ሥነ ምግባር ድርጊቶችን ጥሩ ወይም መጥፎ መሆናቸውን የምንመረምርበት መስኪያ ነው፡፡ ጥሩውን ከመጥፎ እውነተኛውን ከሀሰተኛው፣ ተገቢ የሆነውን ተገቢ ካልሆነው ለይተን ለመፈፀም የውዴታ ግዴታ የምንገባበት ነው፡፡ በትምህርት ቤት ደረጃም ተማሪዎች ሲጠብቋቸው የሚገቡ በርካታ ሥነምግባሮች አሉ፡፡

የጓደኛ ምሥጢር ማለት በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ጓደኛሞች መካከል በቃል ኪዳን ተጠብቆ የማያዝ ጉዳይ ነው፡፡ ምሥጢሩ ቢባክን በአንደኛው ወይም በሁለቱም ጓደኛሞች ላይ የሚያስከትለው ችግር ወይም አደጋ ሲኖር ስለሚችል ምሥጢሩ ተጠብቆ መቆየት ይኖርበታል፡፡

ሙስና የአንድን ሀገር መንግሥት መልካም አስተዳደር የሚያቃውስ፣ ለዲሞክራሲ ግንባታና ለኢኮኖሚ ዕድገት የሚደረገን ጉዞን የሚያደናቅፍ፣ አብሮ የመኖርንና ተባብሮ የመስራትን ውድ እሴቶች የሚሸረሽር ነው፡፡ ሃላፊነታቸውን የዘነጉ የሕዝብ ተመራጮችም ሆኑ የመንግስት ባለስልጣናት ሲፈጽሟቸው የሚችሉ የሙስና ተግባ ራት አሉ፡፡ እነዚህ አሳፋሪ ተግባራት እንዳይፈፀሙ ማንኛውም ዜጋ የመከታተልና የመከላከል ኃላፊነት አለበት፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

***የሕዝብ ተመራጭ፣*** በአንድ አንባቢ የሚኖር ሕብረተሰብ ወይም ሕዝብ ሕጋዊ መብቶቹን እንዲያስከብርለትና እንድያገለግለው የሚመርጠው ተወካይ፡፡

***የሥልጣን ገደብ፣*** ሕገመንግሥትና ሌሎች ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ የተሰጠ የሥልጣን ወሰን፡፡

***ሙስና፣*** ከመንግስት ወይም ከሕዝብ የተሰጠን ሥልጣን ሃቀኝነትና ታማኝነት በጐደለው መንገድ ከሥነምግባር ውጭ በመሥራት የሕዝብን ሃብት ለራስ ወይም ለሌላው ሰው ጥቅም ሲባል የሚፈፀም ጥፋት፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*I የሚከተሉትን ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡*

1. የክልል ሕገ መንግሥታት ራስን በራስ የማስተዳደርን ሁኔታ ያመቻቻሉ፡፡
2. አንድ ዜጋ ሕግን የማክበር እንጂ ሕግን የማስከበር ግዴታ የለበትም፡፡
3. በህዝብ ተመራጮች ላይ የስልጣን ገደብ መደረግ የለበትም፡፡
4. በሁለት ጓደኛሞች መካከል የተያዘ ምሥጢር ቢባክን ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡

*II ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ፡፡*

1. ከሚከተሉት ወስጥ የመልካም ሥነምግባር ምሳሌ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የትምህርት ቤትና የክፍልን ደንብ ማክበር፣
   ለ. የክፍሎችን ጽዳት መጠበቅ፣
   ሐ. የሌሎች ተማሪዎችን ንብረት አለመውሰድ፣
   መ. መልስ አልተሰጠም፡፡
2. ከሚከተሉት ወስጥ በሕዝብ ተመራጮች ላይ የሚደረግ የሥልጣን ገደብን በተመለከተ እውነት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ከተሰጠው የሥልጣን ገደብ ውጭ መሥራት፣
   ለ. ከተሰጠው ሥልጣን ገደብ በታች አከናውኖ መገኘት፣
   ሐ. ሥልጣኑን በተገቢው መንገድ መጠቀም፣
   መ. ሁሉም መልስ ነው፡፡
3. በሕዝብ ተመራጮች ወይም በመንግስት ባለሥልጣናት ከሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መካከል ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. መደለያና ጉቦ መቀበል፣
   ለ. የመንግሥት ንብረት ለግል አገልግሎት ማዋል፣
   ሐ. ሚስጢርን መጠበቅ፣
   መ.በዝምድና መሥራት፡፡
4. በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ወዳጆች መካከል በቃል ኪዳን ተጠብቆ የሚያዝ ጉዳይ ምን በመባል ይታወቃል?
   ሀ. የቤተሰብ ምሥጢር፣ ሐ. የሀገር ምሲጢር፣
   ለ. የጓደኛ ምሥጢር፣ መ. የግል ምሥጢር፣

*III የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡*

1. ሕብረተሰቡ የሚቀበለው ማንኛውም በጎ ምግባር_______ሥነምግባር ይባላል፡፡
2. መልካም ሥነምግባር የሚጀምረው ከ ____________________________ ነው፡፡
3. ሕግን ለማስከበር መጀመሪያ ______________________ ማክበር ያስፈልጋል፡፡

*IV የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡*

1. የክልል ሕገመንግሥታት ከሚያስፈልጉባቸው ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን ግለጹ፡፡
2. ከተማሪዎች ከሚጠበቁ ሥነምግባሮች መካከል ሦስቱን ዘርዝሩ፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# እኩልነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተ ምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የኢትዮጵያ ብሔሮችን፣ ብሔረሰቦችንና ሕዝቦ ችን እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ፡፡
- ሴቶች በልማትና በሀገር ግንባታ ሲኖሯቸው የሚገቡ ተሳትፎዎችን ታውቃለህ/ ታውቂያለሽ፡፡
- የአካል ጉዳተኞች በትምህርት ቤት ደረጃ ሊኖ ሯቸው የሚገቡ መብቶችን ትረዳለህ/ት ረጂያለሽ፡፡

## 3.1 የእኩልነት መብቶች፤

- በአካባቢያችሁ እየተተገበሩ ያሉ የእኩልነት መብቶችን ምሣሌ በማቅረብ አስረዱ፡፡

የዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረታዊ መርህ ከሆ ኑት ነገሮች መካከል እኩልነት አንዱ ነው፡፡ ትክክለኛና የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚመዘነው መብቶች በእኩል ሲከበሩ ነው፡፡

እኩልነት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲ ሁም ዜጎች አንዳቸው ከአንዳቸው ሳይበላለጡ መብቶቻቸው በእኩልነት የሚከበሩበት ነው፡፡ በ1987 ዓ.ም የፀደቀው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት የእኩ ልነት መብቶችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በአካባቢያችሁ በአሁኑ ወቅት የእኩልነት መብቶች ምን ያህል እየተከበሩ ናቸው?
2. ከምታውቋቸው የእኩልነት መብቶች ውስጥ ሦስቱን ጥቀሱ፡፡
3. የሕገመንግሥቱን አንቀፅ 25፣ 40 እና 41ን በማንበብ በውስጣቸው የተካተቱ የእኩ ልነት መብቶችን በመለየት ተወያዩበት፡፡

### 3.1.1 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶች፣

- በአካባቢያችሁ የዜጐችን የእኩልነት ተጠ ቃሚነትን የሚያሳዩ ተግባራትን ጥቀሱ፡፡

የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነት ሲባል፣ አንዳቸው ከአንዳቸው ሳይበላለጡ መብ ቶቻቸው በእኩል ደረጃ መከበር ማለት ነው፡፡ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩል ተጠ ቃሚነት መብት የሚያመለክተው የሕዝቦች አንዱ የሌላውን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶ ቻቸውን በማክበር፣ በሀገራቸው ሀብት እኩል የመጠቀምና የልማት እድል የማግኘት መብትን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በማንኛውም ፖለቲ ካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳታፊና ተጠቃሚ መሆንን ያመለ ክታል፡፡

አሁን በሀገራችን እየተገነባ ባለው የዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝ ቦች እኩል በመሆናቸው ከሚያገኙት የልማት ውጤቶች ተጠቃሚ የመሆን መብታቸው በሕግ የተረጋገጠ ነው፡፡ ስለዚህ የሀገራቸውን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀምና ለመንከባከብ በጋራ ሊሠሩ ይገባል፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦችን የእኩ ልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብቶችን የሚያ ረጋግጡ ተግባራትን ጥቀሱ፡፡
2. ሠንጠረዡን በደብተራችሁ በመገልበጥ ከሚ ከተሉት የልማት ፕሮግራሞች መካከል በአካባ ቢያችሁ የተዘረጉትን በመለየት የተሠራ ያልተ ሠራ በሚሉት አምዶች ሥር በአካባቢያችሁ የተዘረጉትንና ያልተዘረጉትን በመለየት የተሠራ ያልተሠራ በሚሉት አምዶች ሥር የ«✓» ምልክት በማድረግ አሳዩ፡፡

| የልማት አውታሮች | የተሰራ | ያልተሰራ |
|---|---|---|
| መንገድ | | |
| የጤና ኬላ | | |
| የመብራት አገልግሎት | | |
| የውሃ አገልግሎት | | |
| ትምህርት ቤት | | |

### 3.1.2 በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሕዝቦች የሚጠቀሙባቸው ተቋማት፣








ሥዕል 3.1 ሕዝቦች የሚጠቀሙባቸው የልማት ተቋማት

- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ሕዝቦች የሚጠቀሙባቸውን የልማት ተቋማት ዘርዝሩ ::
- እነዚህ ተቋማት ባይኖሩ ሊከሰቱ ይችላሉ የምትሏቸውን ችግሮች ጥቀሱ::

ቀደም ባሉት ሥርዓቶች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከሀገራቸው ሀብቶችና ተቋማት በእኩልነት የመጠቀም እድል አልነበራቸውም:: ዛሬ ሀገሪቱ በምትገነባው የዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ግን ብዙ ለውጦች ተደርገዋል ::

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል፣**
የቤንሻንጉል ጉምዝ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት መሠረተ በ1987 ዓ.ም ከተቋቋሙት ክልሎች መካከል አንዱ ነው:: በክልሉ ውስጥ በርካታ፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ይገኛሉ:: እነዚህም ጉሙዝ፣ በርታ፣ ሺናሻ፣ ማኦና ኮሞ ሲሆኑ እነሱም በመፈቃቀድ በመሠረቱት አንድነትና መተሳሰብ እየኖሩ ይገኛሉ::



ሥዕል 3.2 ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች መካከል

ቀደም ባሉት ዘመናት ቤንሻንጉል ጉሙዝ በኢትዮጵያ ውስጥ በየት አቅጣጫ እንደሚገኝ እንኳን ብዙዎች አያውቁም ነበር:: የክልሉ ሕዝቦች ታሪካቸው፣ ባህላቸውና ቋንቋቸው ተረስቶ ኖሯል:: በአካባቢያቸው የሚገኙ ልዩ ልዩ ሀብቶችና ገቢዎች ለሕዝቡ ሳይሆን ለጥቂት ገዢ መደቦች ጥቅም ብቻ እንዲውሉ ሲደረግ ኖሯል:: በዚህም ምክንያት የሕዝቦቹ የልማትና የእኩል ተጠቃሚነት መብቶች ተነፍገው ቆይቷል:: ዛሬ ግን የክልሉ ብሔረሰቦችና ሕዝብች ራሳቸውን በራሳቸው በማስተዳደር ላይ ይገኛሉ:: በሀገሪቱ የጋራ ሀብትም ከሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ጋር በእኩልነት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል:: የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠንም አብዛኞቹ የክልሉ ከተሞችና መንደሮች የልማት ተጠቃሚዎች በመሆናቸው ተሰፋ ሰጪ ለውጦች እየታዩ ነው:: ከተዘረጉት የልማት አውታሮች መካከልም

የመብራት፣ የስልክ፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ የመንገድ፣ የጤና ኬላ፣ የፖስታና የትራንስ ፖርት አገልግሎቶች ይጠቀሳሉ:: በእነዚህ ተቋ ማትም ሕዝቦቹ በየአካባቢያቸው በእኩልነት እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ:: አገልግሎቱንም ቀጣይ ለማድረግ ሕዝቡና መስተዳድሩ በጋራ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

የእኩልነት መብት በክልሉ በተግባር በመረጋገጡ ሕዝቦቹ ለልማትና ለእድገት የበለጠ ተነሳስተ ዋል:: በአሁኑ ጊዜም ድህነትን ለማሸነፍ በትጋት በመረባረብ ላይ ይገኛሉ::

**መልመጃ 3**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. የቢንሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች በጋራ የሚ ጠቀሙባቸውን ተቋማት ከምንባቡ ውስጥ ዘርዝሩ ::
2. ማሕበረሰቡ እነዚህን ተቋማት በእኩ ልነት እንዴት ሊጠቀምባቸው ይችላል ?
3. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የልማት ተቋማትን በመዘርዘር የሕብረተሰቡን እኩል ተጠቃ ሚነት እንዴት እንደሚያረጋግጡ አብራሩ::
4. የአካባቢ መስተዳደር ልማትን በማፋጠን ረገድ የሚኖረውን ሚና ግለጹ::

### 3.1.3 የእኩልትና እኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ማክበር የሚያስገኘው ጠቀሜታ፣

- በምትኖሩበት አካባቢ በሕዝብና በመንግ ሥት የልማት ተቋማት በእኩል የመጠቀም መብት ምን ያህል ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል?

የእኩል ተጠቃሚነት መብት ስንል በአንድ ሀገር ውስጥ ከሚከናወኑ ማናቸውም የልማትና የእድ ገት ውጤቶች በእኩልነት መጠቀምን የሚያመ ለክት ነው:: ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሀገር ልማት ውስጥ እኩል ሀላፊነት እንዳ ላቸው ሁሉ ከማንኛውም ጥቅም እኩል ማግኘት አለባቸው:: ነገር ግን የዜጎች እኩል ተጠቃ ሚነት መብት በሌለበት ሥርዓት ውስጥ እኩልነት ሊሰፍን አይችልም::

እኩልነት ካልሰፈነ ደግሞ ሕዝቦች መብቶቻ ቸውን ለማስከበር ሲሉ ወደ ግጭት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ:: ይህም የሕግ አለመከበርና የሠላም መታጣት ያስከትላል:: ይህ ከሆነ ደግሞ እድገትና ልማትን በማፋጠን ከድህነትና ኋላቀርነት ለመላቀቅ አዳጋች ይሆናል:: ስለዚ ህም ሕዝቦችን ሁሉ ከማንኛውም ልማት በእኩ ልነት ተጠቃሚ ማድረግ ለሀገር እድገትና ብል ፅግና ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ይህ እንዲ ሆንም ሕብረተሰቡና መንግስት በጋራ ሊሰሩ ይገባቸዋል::

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. የእኩል ተጠቃሚነት መብት ስንል ምን ማስታችን ነው?
2. የዜጎች እኩል ተጠቃሚነት መብት በሌለበት ሥርዓት ውስጥ ምን ምን ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ?

## 3.2 የእኩልነት መገለጫዎች፤

- በአካባቢያችሁ የእኩልነት መገለጫዎች ከሆ ኑት ጉዳዮች መካከል ሦስቱን ዘርዝሩ::
- የሕዝቦች እኩልነት መከበር የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ::

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብትን በመ ጠቀምና ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ እኩል ናቸው:: በሀገራችን የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔ ረሰቦችና ሕዝቦች በሃይማኖት፣ በቋንቋና በመሳሰ ሉት የተለያዩ መሆናቸው ይታወቃል:: ይሁን እንጂ ይህ ልዩነት በሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ላይ ተፅዕኖ አይኖረውም::

ማንኛውም ዜጋ በሀገሪቱ ውስጥ የትም አካባቢ ቢወለድ በመብት መከበር ረገድ ከማንም አይበ ልጥም ወይም አያንስም :: በዚህም መሠረት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የእኩልነት መገለጫዎች ከሆኑት መካከል ቋንቋዎች፣ ሃይ ማኖቶችና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች በእኩ ልነት መከበራቸው ተጠቃሽ ነው::

### 3.2.1 የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የእኩልነት መገለጫዎች፣

- የሚከተለውን የሕገመንግሥት ድንጋጌ በሚ ገባ በማንበብ የተረዳችሁትን ሐሳብ ግለፁ::

"ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለፅ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ

መብት አለው:: ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀፅ 39/2

**ሀ. የቋንቋ እኩልነት፣**

- የቋንቋ እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?

ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች እኩል ናቸው:: ቋንቋዎቻቸው በእኩልነት እንዲከበሩላቸው ይፈልጋሉ:: ይህም መብት በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 39 ላይ ተካቶ ይገኛል::

ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በራሳቸው ቋንቋ የመጠቀም መብት አላቸው:: ይህም ሲባል ቋንቋቸውን ለትምህርትና ለስነ-ፅሁፍ የመጠቀም፣ በቋንቋቸው የመናገርና የመዳኘት፣ እንዲሁም ቋንቋቸውን የማበልፀግ መብቶችን ያካትታል:: ከዚህም ሌላ ሕዝቦች ከራሳቸው ቋንቋ በተጨማሪ ሌሎች ቋንቋዎችን የመማርና የማወቅ መብታቸው ተከብሮላቸዋል:: ስለዚህ ቋንቋዎችን ሁሉ በእኩልነት ማክበርና ማስከበር ለሠላም፣ ለእድገትና ለጋራ መግባባት እጅግ ጠቃሚ ነው::

**ለ. የፆታ እኩልነት፣**

- የፆታ እኩልነት መከበር እንዳለበት ታምናላችሁ?

ሰዎች በተፈጥሮአቸው ሴት ወይም ወንድ በመሆናቸው የፆታ ልዩነት ቢኖራቸውም መብቶቻቸው ግን በእኩል ደረጃ ሊከበሩላቸው ይገባል:: ሴት በተፈጥሮ ፆታዋ ብቻ የምታጣው መብት ሊኖር አይገባም:: ወንድ እንዲሁ ወንድ ሆኖ በመፈጠሩ ምክንያት ከሴት ያነሰ ወይም የበለጠ መብት ሊኖረው አይገባም::

የፆታ እኩልነት ማለት የወንዶችና የሴቶች እኩልነት ማለት ነው:: በዚህም መሠረት ወንዶችና ሴቶች በፆታቸው ምክንያት ሳይበላለጡ እኩል ናቸው:: ሴቶች የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል በመሆናቸው እነሱን ያላሳተፈ ማንኛውም የልማት ተግባር ውጤታማ ሊሆን አይችልም:: በመሆኑም የሴቶችና የወንዶችን እኩልነት ማክበር ለአንድ ሀገር ለዕድገት መሠረታዊ ጉዳይ ነው::

ከታሪክ የወረስነውን ሴቶችን በበታችነት የማየት አመለካከት ሊቀየር ይገባዋል:: ሴቶች በአስተሳሰባቸው፣ በአዕምሮ ብቃታቸው፣ በፈጠራ ችሎታቸውና በአመራር ሰጭነታቸው ከወንዶች አያንሱም::

**መልመጃ 5**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው::***

1. በቋንቋ የመጠቀም መብት ምን ምን ጉዳዮችን ያጠቃልላል?
2. ያለሴቶች ንቁ ተሳትፎ የተሟላ ልማት ማምጣት የማይቻለው ለምን ይመስላችኋል?

### 3.2.2 የሴቶች እኩል ተሳትፎ ለልማትና ለሀገር እድገት፣

- ሴቶች ከወንዶች እኩል እንዲሳተፉ መደረጉ ለሀገር ልማትና እድገት የሚያስገኘውን ጥቅም ግለፁ::

**"ሴቶችና ቱሪዝም"**

ለረጅም ዘመናት ምግብና መጠጥን ለቤተሰቦቻቸው አጣፍጦ የማዘጋጀቱ ሥራ በሴቶች ትከሻ ላይ የወደቀ ሆኖ ቆይቷል:: በተጨማሪም ለተለያዩ ጉዳዮች ከሩቅም ከቅርብም በእንግድነት ለሚመጡ የማሕበረሰቡ አባላት ተመሳሳይ አገልግሎት የመስጠቱን ልምድ አዳብረዋል:: ቀስ በቀስም የውጭ ሀገራት እንግዶችን በተለያዩ አካባቢዎች ያለምንም ክፍያ አብልቶ፣ አጠጥቶና ማረፊያ ሰጥቶ የመሸኘቱ ተግባር የሴቶች ድርሻ ሆኖ ቆይቷል::

ዘግይቶም ከውጭ የሚመጡትም ሆኑ የአገር ውስጥ ቱሪስቶች ገንዘብ ከፍለው የሚገለገሉባቸው ሆቴሎች መደበኛ ሥራ ሲጀምሩ ኃላፊነቱ ከሴቶች ጫንቃ አልወረደም:: ይህ ሲጠቃለል በሀገራችን ለቱሪዝም መፀነስ፣ መወለድ፣ ማደግና መዳበር የሴቶች ሚና ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል::

በምግብና መጠጥ አዘገጃጀት ተግባር ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ወንዶች መሣተፍ የጀመሩ ቢሆንም ከቆየው ልማዳዊ አሠራር ጀምሮ ሴቶች ቅድሚያውን ይዘው ይገኛሉ:: ከዚህም በተጨማሪ ሴቶች የእጅ ጥበብ ውጤቶች በሆኑት በፈትል፣ በስፌት፣ በሸክላ ሥራ እና በመሳሰሉት ሥራዎቻቸው የስጦታና የመታሰቢያ መደብሮችን እያስፋፉ ይገኛሉ:: ይህም ሀገራችን ከቱሪዝም ሴክተር ከፍተኛ ተጠቃሚ እንድትሆን እያደረጋት ነው:: በመሆኑም ሴቶች ለቱሪዝም እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጋቸው፣ ዘርፉም ለሴቶች ሰፊ የሥራ ዕድል መፍጠሩ፣ በሀገራችን ብቻ ያልተወሰነ ዓለምአቀፋዊ ሐቅ ነው::

እቴጌ ጣይቱ የቱሪዝም የጀርባ አጥንት የሆነውን የሆቴል ሥራ በሀገራችን በመጀመር ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛሉ:: ከዚያ ወዲህም

የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ከሀገራችን የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ ሆኗል:: ለዚህም ሴቶች በቱሪዝም መስክ በመቀጠርም ሆነ በኢንቨስተርነት በመሠማራት ለኢንዲስትሪውና ለሀገራችን እድገት ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ::

*ምንጭ:- ቱሪዝም አዲስ 5ኛ ዓመት ቁጥር 6 በከፊል የተወሰደ::*

**መልመጃ 6**

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. በምንባቡ መሠረት ሴቶች ለሀገራችን የቱሪዝም እድገት ያደረጉትን አስተዋፅኦ ዘርዝሩ::
2. በአካባቢያችሁ ሴቶች የተሰማሩባቸው የልማት መስኮችን ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው::
3. የሴቶችን እኩልነት ማክበር ለሀገር ግንባታ ያለውን ጠቀሜታ በደብተራችሁ ላይ ፃፉ:: ከዚያም አብረዋችሁ ከተቀመጡ ተማሪዎች ጋር ተወያዩበት::

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገራችን እየተመዘገበ ባለው ልማትና ዕድገት ሴቶች ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛሉ:: ነገር ግን በሃገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በቂ ባይባልም ብዙ ለውጦች ተመዝግበዋል:: ለምሳሌ በትምህርት መስክ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ እያደገ መጥቷል:: ከ1998-1999 ዓ.ም ድረስ ጥቅል የተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ የሚከተለውን ይመስላል::

| | የተማሪዎች ብዛትከ1-8ኛ ክፍል | | የሴት ተማሪ ዎች ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ክልል | ወንድ | ሴት | በመቶኛ /%/ |
| ትግራይ | 456,336 | 446,343 | 100.0 |
| አፋር | 49,669 | 27,973 | 23.7 |
| አማራ | 1,863,387 | 1,767,140 | 90.5 |
| ኦሮሚያ | 2,939,750 | 2,336,970 | 84.3 |
| ሶማሌ | 157,429 | 94,962 | 23.8 |
| ቤንሻንጉል ጉሙዝ | 91,477 | 66,508 | 105.5 |
| ደቡብ ብ.ብ.ህ | 1,676,866 | 1,326,424 | 85.0 |
| ጋምቤላ | 37,117 | 21,773 | 100.6 |
| ሐረሪ | 19,502 | 15,329 | 100.3 |
| አዲስ አበባ | 230,764 | 280,751 | 159.8 |
| ድሬዳዋ | 26,112 | 20,060 | 62.8 |
| ድምር | 7,548,409 | 6,404,233 | 84.8 |

*ምንጭ:- ፌዴሬሽን ምክር ቤት ዓመታዊ መፅሔት ትምህርት ሚኒስቴርን ጠቅሶ ካቀረበው*

**መልመጃ 7**

### ከላይ የቀረበውን ሠንጠረዥ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::

1. የሴት ተማሪዎች ቁጥር በፐርሰንት ከፍተኛ የሆነበት የኢትዮጵያ ክልል የቱ ነው? ዝቅተኛውስ? ልዩነቱ ምን ያህል ነው?
2. ይህንን ልዩነት ለማጥበብ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?
3. በምትኖሩበት ክልል የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ምን ይመስላል? የበለጠ ለማሳደግ ከእናንተ ምን ይጠበቃል?

ከላይ በተሰጠው መረጃ መሠረት የሴት ተማሪዎች ቁጥር በአንደኛ ደረጃ እያደገ መምጣቱን ያሳያል:: ነገር ግን ይህ በቂ ነው ማለት አይደለም:: በመሆኑም በቀጣይ የሴቶችን ተሳትፎ በትምህርትም ሆነ በሌሎች ዘርፎች ለማሳደግ ራሳቸው ሴቶች፣ ሕብረተሰቡና መንግሥት ኃላፊነት አለባቸው:: ሴቶች የእኩልነት መብታቸው ከተከበረላቸውና ዕድሉ ከተሰጣቸው ከወንዶች ያላነሰ ብቃት እንዳላቸው በተለያዩ የሙያ መስኮች በመሠማራት አስመስክረዋል:: ለዚህም ጉልህ ማስረጃው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገራት የሴቶች ተሳትፎ በሁሉም መስክ እየጐለበተ መምጣቱ ነው:: ለምሳሌ በሀገራችን ሴቶች በአመራር ደረጃ በሚኒስትርነት፣ በአፈጉባኤነት፣ በአምባሳደርነት፣ እየሰሩ ይገኛሉ:: በሌሎችም ዘርፎች በኢንቨስተርነት፣ በስፖርት፣ በትምህርትና በመሳሰሉት ከፍተኛ ሚና በመጫወት ላይ ይገኛሉ:: ስለዚህ በሀገራችን ለሴቶች መብት መከበርና ለተሳትፎአቸው መጠናከር ሁሉም ዜጋ ኃላፊነት አለበት:: ወንድና ሴት በጋራ በመተሳሰብና በመተጋገዝ አብረው መሥራት ከቻሉ ውጤቱ አስተማማኝ ልማትና እድገት መሆኑ አያጠራጥርም::

## 3.3 የአካል ጉዳተኞች ሊኖሯቸው የሚገቡ መብቶች፤



ሥዕል 3.3 የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ ካገኙ የተለያዩ ሥራዎችን ማከናወን ይችላሉ::

- ከሥዕሎቹ የተገነዘባችሁትን ለጓደኞቻችሁ ግለጹ::

### "ሃሊማና ኤርኮ"

ሃሊማና ኤርኮ በፖሊዮ በሽታ ምክንያት ከልጅነታቸው ጀምሮ የአካል ጉዳተኞች ናቸው:: ከዚህም የተነሳ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱት በተሽከርካሪ ወንበር ነው:: በዚህ ዓመት ሃሊማ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ኤርኮ ደግሞ የ8ኛ ክፍል ተማሪ ነው:: ይሁንና የሚማሩት ትምህርት ቤት ባለ አራት ፎቅ ህንጻ በማሠራት የቀድሞዎቹን መማሪያ ክፍሎች ቀይሯቸዋል::



በአዲሱ ህንጻ ምድር ባሉ ክፍሎች ውስጥ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች ተደልድለዋል:: የ5ኛ እና የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ በቀጣዮቹ የአንደኛና ሁለተኛ ፎቆች ላይ ባሉ የመማሪያ ክፍሎች ተመድበዋል:: የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ በሶስተኛ እና በአራተኛ ፎቆች ላይ ባሉ ክፍሎች ውስጥ እንዲማሩ ተደረገ:: ሃሊማና ኤርኮ ግን በትምህርት ቀናት የፎቆቹን ደረጃዎች በተሽከርካሪ ወንበር መውጣትና መውረድ አልቻሉም:: በየጊዜው የሚረዳቸውን ሰው በማጣትም እጅግ ተቸገሩ:: ስለሆነም አመቺ የመማሪያ ክፍሎች እንዲቀየርላቸው ለትምህርት ቤቱ ጥያቄ አቀረቡ:: ትምህርት ቤቱ ግን ከአቅሜ በላይ ነው በማለት ምንም ማድረግ እንደማይችል ገለጸላቸው:: ጥያቄያቸውም ምላሽ ስላላገኘ እና ሌላ ትምህርት ቤት በአካባቢያቸው ባለመኖሩ ሃሊማና ኤርኮ ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ::

**መልመጃ 8**

***ከዚህ በላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

?

1. ትምህርት ቤቱ ለሃሊማና ኤርኮ የሰጣቸው ምላሽ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ለምን?
2. ትምህርት ቤቱ ምን ማድረግ ነበረበት?
3. በአካባቢያችሁ ተመሳሳይ ችግር የደረሰባቸው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ታውቃላችሁ? ችግራቸው ተቃሎላቸዋል? ለወደፊቱ ከእናንተና ከሕብረተሰቡ ምን ይጠበቃል?

የአካል ጉዳተኝነት ማንኛውም ሰው ሊያጋጥመው የሚችል አደጋ ሲሆን በተፈጥሮአዊ ወይም በሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት ሊከሰት የሚችል ነው:: የአካል ጉዳተኝነት አንድን ተግባር ወይም እንቅስቃሴ እንደ ሙሉ ጤናማ ሰው ሆኖ ማከናወን አለመቻል ነው:: የአካል ጉዳተኝነትን ከሚያስከትሉ ተፈጥሮአዊ ችግሮች መካከል እንደ ፖሊዮ፣ የሥጋ ደዌ በሽታዎችና የምግብ እጥረት ይጠቀሳሉ:: ሰው ሠራሽ ከሚባሉት የአካል ጉዳተኝነት ምክንያቶች መካከል የጤና አገልግሎት አናሳ መሆን፣ የንፅህና ጉድለት፣ አደጋ፣ ግጭቶችና ጦርነቶች ይጠቀሳሉ::

በሀገራችን ውስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የአካል ጉዳተኞች ይገኛሉ:: እነዚህም ወገኖች በተለያዩ የመንግሥትና የግል ተቋማት ውስጥ ሲገለሉና መድሎ ሲደርስባቸው ይታያል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሁኔታዎች እየተሻሻሉ የመጡ ቢሆንም ገና ብዙ መሥራትና የሁሉንም ወገን ጥረት የሚጠይቅ ነው::

የአካል ጉዳተኞች በማንኛውም ሥፍራና ጊዜ ተገቢ የሆኑ እንክብካቤ ማግኘት ይገባቸዋል:: ለምሳሌ በትምህርት ቤት ተስማሚ የመማሪያ ክፍል፣ የመማሪያ ቁሳቁስ፣ ፍቅር፣ እንክብካቤና ትኩረት ማግኘት አለባቸው:: ለዚህም ተማሪዎች፣ መምህራንና የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች በተቻለ መጠን ሊንከባከቧቸው ይገባል::

የአካል ጉዳተኞች መብቶቻቸው በሕገመንግሥቱ እወቅና የተሰጣቸው ሲሆን እነደማንኛውም ሰው መስራት ይችላሉ:: ከዚህም በተጨማሪ ድህነትን ለማሸነፍ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥም ከፍተኛ ተሳታፊ መሆንና በልማት ሥራ ውጤት ማስመዝገብ አያቅታቸውም::

**መልመጃ 9**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

?

1. ከኢፌዲሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 41/5 በማንበብ መንግሥት አካል ጉዳተኞችን ለመርዳት ምን ምን ተግባራት ሊያከናውል እንደሚገባ ተወያዩ::
2. በትምህርት ቤት ደረጃ ለአካል ጉዳተኞች ሊደረጉ የሚገቡ ድጋፎች ምንድንናቸው?

## 3.4 የሃይማኖት እኩልነት መከበር አስፈላጊነት፤

- የሃይማኖት እኩልነት መከበር አስፈላጊነቱን ግለጹ::

በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ሃይማኖቶች በሕገመንግሥቱ መሠረት እኩል ናቸው፡፡ እኩል ነታቸው ከሚገለፁባቸው ጉዳዮች ውስጥ ማንኛ ውም ሰው በተናጠልም ሆነ በጋራ ሃይማኖትን መከተል፣ ማስተማርና ማስፋፋት ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን ግን አንዱ የሌላውን ሃይማኖት ማን ቋሸሽና ማናናቅ አይችልም፡፡ ከዚህ ይልቅ በፍ ቅር፣ በመደጋገፍና በመከባበር ላይ የተመሠረተ እንቅስቃሴ ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል፡፡ በሀገ ራችን የረጅም ዘመን ታሪክ ውስጥ ሃይማኖቶች በአብሮነት ተቻችለው ኖረዋል፤ እየኖሩም ይገ ኛሉ፡፡ በመሆኑም የአብሮነትና የመቻቻል ባህላ ችን ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል፡፡

በሀገራችን በጋራ በመተባበርና በፍላጎት ሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንድነት ፈጥ ረው እየኖሩ ነው፡፡ ይህ አንድነታቸው ቀጣይነት እንዲኖረው የሕዝቦች እሴቶቻቸው በእኩልነት መከበር አለባቸው፡፡ ምንም አድሎ ሳይደረግ ቋንቋቸው፣ ሃይማኖታቸውና ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎቻቸው እኩል ከተከበሩላቸው በሕዝ ቦች መካከል ሠላምና መተሳሰብ ይስፋፋል፡፡

ዜጎች የመሰላቸውን ሃይማኖት የመያዝ ነፃነ ታቸው የተጠበቀ ካልሆነ፣ መብታቸው የተ ሟላ አይሆንም፡፡ ሥርዓቱም አድሎአዊ ነው ማለት ነው፡፡ የዜጎች መብት የተገፈፈ፣ አድሎ የሚፈፀምበት ሁኔታ ካለ፣ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ሕብረተሰቡ መብቱ መረገጡ አይቀ ርም፡፡ የአንዱን ሃይማኖት ከፍ ሌላውን ሃይማ ኖት ዝቅ አድርጎ መመልከት የዴሞክራሲ ሥርዓት መገለጫ አይደለም፡፡

☞ የአካል ጉዳተኞችን መንከባከብ የሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው፡፡

የዴሞክራሲ ሥርዓት የበለጠ ይጠናከር ዘንድ ከዜጎች መብቶች ውስጥ አንዱ የሆነው የሃይማ ኖት እኩልነት መከበርና ሁሉም ዜጋ እምነቱን በነፃ ማራመድ መቻል አለበት፡፡ ስለሆነም የሃይ ማኖቶች የእልነት መብት መከበር የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዳይናድ፣ የሕዝቦች ሠላም እንዳይና ጋና የእድገት ተስፋ እንዳይጨልም ለማድረግ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡

የሃይማኖቶች የእኩልነት መብት በተሟላ መን ገድ ሊረጋገጥ የሚቻለው ሃይማኖትን በተመ ለከተ ዜጎች የጋራ አመለካከት ሲኖራቸው ነው፡፡ የጋራ አመለካከታቸውም እንዲዳብር ለሚከተ ሉት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡

ሀ. ለሌሎች ሃይማኖቶች እውቅና መስጠትና አለመግባባቶች ሲነሱም በውይይትና በሠላ ማዊ መንገድ ብቻ መፍታት፤
ለ. አለመግባባቶችን በውይይትና በሠላማዊ መን ገድ መፍታት ካልተቻለ በሕግ መሠረት ብቻ መፍታት፤
ሐ. ሃይማኖት የግል መሆኑን በመረዳት የራ ስን እምነት በሌላው ላይ ለማስረፅ በማሰብ ለግጭት አለመነሳሳት፤
መ. ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን፤
ሠ. በጋራ አብሮ ለመኖር የሃይማኖት ልዩነት እንቅፋት እንዳይሆን ሁልጊዜም መቻቻል፣ መከባበርና መተባበር፤
ረ. ምንግዜም እራስን ለሕግ የበላይነት ማስገ ዛት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

**መልመጃ 10**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. የሃይማኖት እኩልነት መከበር ለአንድ ሀገር ምን ምን ጥቅሞችን ያስገኛል?
2. የሃይማኖት እኩልነት እንዲከበር ከያንዳንዱ ዜጋ ምን ይጠበቃል?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የብሔሮች የብሔረሰቦችና የሕዝቦች የእኩልነት መብት መከበሩ ለሀገራችን ልማትና እድገት ወሳኝ ነው፡፡ አሁን በሀገራችን ውስጥ እየተገነባ ባለው የዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ሕዝቦች እኩል በመሆናቸው ከሀገራቸው ልማት እየተጠቀሙ ይገኛሉ፡፡

በሀገራችን የእኩልነት መገለጫ ከሆኑት መካከል ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በቋንቋቸው መገልገላቸው፣ ሌሎች ባህላዊ መገለጫዎቻቸውን ማበልፀግ መቻላቸውና ሃይማኖታቸው በእኩልነት መከበሩ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በጋራ ሆነው የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠን እንዲረባረቡ አስችሏቸዋል፡፡

በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ሰዎች ሴት ወይም ወንድ በመሆናቸው የፆታ ልዩነት ቢኖራቸውም መብቶቻቸው ግን በእኩል ደረጃ ይከበሩላቸዋል፡፡ ሴት በተፈጥሮ ፆታዋ ብቻ የምታጣው መብት አይኖርም፡፡ ወንድ እንዲሁ ወንድ ሆኖ በመፈጠሩ ምክንያት ከሴት ያነሰ ወይም የበለጠ መብት ሊያገኝ አይገባውም፡፡

የአካል ጉዳተኝነት በተፈጥሯአዊ ወይም ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት የሚከሰት ነው፡፡ በሀገራችን ለአካል ጉደተኞች የሚደረገው ድጋፍ እጅግ አናሳ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በቀጣይነት ግን በትምህርት ቤቶችም ሆነ በሌሎች ሥፍራዎች የአካል ጉዳተኞችን መደገፍ ለሀገር ልማት እጅግ ጠቃሚ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል ይገባዋል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

*እኩልነት፣* በምንም ምክንያት መድሎ ሳይኖር ዕድሎችንና ጥቅሞችን በእኩል ማግኘትና ኃላፊነትን በእኩል መወጣት።

*ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ፣* "ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ-ልቦና አንድነት ያላቸውና በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ሕዝቦች::" (ኢፌዲሪ ህገ መንግሥት አንቀፅ 39/5።)

*ቱሪዝም፣* በተለያዩ አካባቢዎች ለጎብኚዎችና ለመዝናናት ለሚመጡ ወገኖች የተለያዩ አገልግሎቶችና መስተንግዶዎች የሚደረጉበት የኢኮኖሚ ዘርፍ::

*ቱሪስት፣* ለመዝናናት ወይም ለሌላ ሥራ የሚጓዝ ጎብኚ።

*ኢንቨስተር፣* ያለውን ሀብት ወይም ገንዘብ በአንድ የልማት ሥራ ላይ ያዋለ ግለሰብ ወይም ድርጅት።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

*I የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡*

1. በ1987 የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት ለብሔሮች፣ ለብሔረሰቦችና ለሕዝቦች የእኩልነት መብቶች ተገቢው ቦታ አልተሰጠውም፡፡
2. በአካባቢያችን እየተከናወኑ የሚገኙትን የልማት ፕሮግራሞች ማስፈፀምና መጠበቅ ያለበት መንግሥት ብቻ ነው፡፡
3. የሕዝቦች እኩልነት በሕገመንግሥቱ መከበሩ በሀገራችን ልማትንና እድገት ለማምጣት ጠቃሚ ነው፡፡
4. ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች ትኩረትና እንክብካቤ መስጠት የሀገር እድገትን ያጓትታል፡፡

*II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የእኩል ተጠቃሚነት አለመኖር፣ | ሀ. የወንድና የሴት እኩልነት። |
| 2. የፆታ እኩልነት፣ | ለ. አንድ ሰው ሊደርስበት የሚያስበው ግብ፡፡ |
| 3. የአካል ጉዳተኝነት፣ | ሐ. በተፈጥሮአዊ ወይም በሰው ሰራሽ ችግር የሚከሰት፡፡ |
| 4. ራዕይ፣ | መ. እድገት እንዳይመጣ የሚያደርግ፡፡ |

*III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡*

1. ሀገራችን ውስጥ እየተተገበሩ ካሉ የእኩልነት መብቶች መካከል አንዱ፣
   ሀ. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነት፣
   ለ. የፆታ እኩልነት፣
   ሐ. የቋንቋ፣ የባህል፣ የሀይማኖትና የሌሎች ባህላዊ መገለጫዎች እኩልነት፣
   መ. ሁሉም መልስ ነው፡፡
2. ከሚከተሉት መካከል ስለ ሴቶች ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሴቶች ከወንዶች እኩል እንዲሳተፉ ማድረግ ምንም ጥቅም የለውም፣
   ለ. ያለ ሴቶች ተሳትፎ ልማትና ዕድገት ሊመጣ አይችልም፣
   ሐ. በማደግ ላይ ባሉ ክልሎች የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች ይበልጣል፣
   መ. ባለፉት ሥርዓቶች ለሴቶች የሚሰጠው ግምት ከፍተኛ ነበር፡፡
3. የአካል ጉዳተኝነትን ሊያስከትል የሚችለው?
   ሀ. በሽታ፣
   ለ. የምግብ ዕጥረት፣
   ሐ. ግጭቶችና ጦርነቶች፣
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
4. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል ስለ ቋንቋ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. አንዱ ቋንቋ ከሌላው ይበልጣል፣
   ለ. ሁሉም ቋንቋዎች በመግባቢያነታቸው እኩል ናቸው፣
   ሐ. ሌሎች ቋንቋዎችን መማርና ማወቅ ምንም ጥቅም አይሰጥም፣
   መ የቋንቋዎች እኩልነት ባይከበር የሚፈጠር ችግር የለም፡፡

5. በሀገራችን የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እኩልነት መከበሩ ምን ጥቅም ያስገኛል?
   ሀ. ቋንቋቸው፣ ባህላቸውና ሃይማኖታቸውን መጠቀምና ማበልፀግ ያስችላቸዋል፣
   ለ. ከድህነትና ከኋላቀርነት ለመላቀቅና በጋራ ለመሥራት ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣
   ሐ. ፍትሐዊ የሀገር ሀብት ክፍፍል እንዲኖር በማድረግ ሰላምን ያጠናክራል፣
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

### IV *የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡*

1. ቋንቋ፣ ባህልና ሃይማኖት የሌለው ------------------የለም፡፡
2. በኢትዮጵያ በኋላቀር ልማዶች በአብዛኛው የሚጠቁት------------------ናቸው፡፡
3. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍና ቋንቋውን የማሳደግ ------------------አለው፡፡

### V *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡*

1. የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችንና የሕዝቦችን እኩልነትና የእኩል ተጠቃሚነት መብቶችን ማክበር የሚያስገኘውን ጥቅም ግለፁ፡፡
2. በትምህርት ቤት ውስጥ ለሴቶችና ለአካል ጉዳተኞች ሊደረግላቸው የሚገቡ እንክብካቤዎችን ግለፁ።

# ምዕራፍ አራት

# ፍትሃዊነት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ *ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- በተለያዩ ቦታዎች የሚፈፀሙ አድሏዊ አሠራሮችን ትረዲያለሽ/ትረዳለህ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ማሕበራዊ ተቋማትን አስፈላጊነት ትገነዘቢያለሽ/ትገነዘባለህ፡፡
- የማሕበራዊ ተቋማት አሠራሮች ከአድሎ የፀዱና ፍትሐዊ ሲሆኑ እንደሚገቡ ትረዲያለሽ /ትረዳለህ፡፡

## 4.1 አድሏዊ አሠራሮች፤

### 4.1.1 በአካባቢያችሁ የሚታዩ የልዩ ልዩ አድሎአዊ አሠራሮች ተግባራት፣

- አድሎአዊ አሠራር ማለት ምን ማለት ነው?

ከታች የተዘረዘሩት ተግባራት አድሎአዊ መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ለይታችሁ ምክንያታችሁን ግለጹ፡፡

1. መምህሩ ጎበዝ ለሚሏቸው ተማሪዎች የፈተና ውጤት ማስተካከያ አደረጉ፡፡
2. ሀኪሙ በሚሠሩበት ሆስፒታል ልጃቸው ቅድሚያ ህክምና እንዲያገኝ አደረጉ፡፡
3. የቀበሌ መታወቂያ ሊወስዱ ተራ ከሚጠብቁት ለአዛውንቶች ቅድሚያ ተሰጠ፡፡
4. በተመሳሳይ ጥፋት በሕግ ቁጥጥር ሥር ከዋሉት መካከል ዳኛው ጎረቤታቸውን በነፃ አሰናበቱ፡፡
5. አብዱ ከጓደኞቹ ጋር እንዲጫወት ሲፈቀድለት መሪማ ቤት እንድታፀዳ ታዘዘች፡፡

**"ኔልሰን ማንዴላ" /ክፍል አንድ/**

በዓለማችን ከፍተኛ ክብር እና ዝና ካገኙ ጥቂት ሰዎች መካከል ኔልሰን ማንዴላ በቀዳሚነት ይጠራሉ፡፡ ማንዴላ በአንድ ጠባብ ክፍል ውስጥ 27 ዓመታትን በእስር አሳልፈዋል፡፡ ማንዴላ ለረጅም ዓመታት ለእስር የተዳረጉት ወንጀል ፈጽመው አይደለም፡፡ ይልቁንም በሀገራቸው የነበረውን አድሏዊ አሰራር በግልፅ በመቃወማቸው ነበር፡፡ በዘመኑ ደቡብ አፍሪካዊ ጥቁር ሕዝቦች በጥቂት ነጮች አገዛዝ ከፍተኛ በደል ይደርስባቸው ነበር፡፡ ከተፈፀሙ መድሎዎች መካከል የሚከተሉት በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡



**ሥዕል 4.1 ኒልሰን ማንዴላ**

ተወላጅ የአፍሪካ ሕዝቦች ለም መሬታቸውን ተቀምተዋል፡፡ የእርሻ፣ የመኖሪያ እና የንግድ ቦታዎች እንዲኖራቸው ፈፅሞ አይፈቀድም ነበር፡፡ በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ መሳተፍ ለጥቁሮች በሕግ የተከለከለ ነበር፡፡ ጥቁር ሕዝቦች ነጮችን ለማገልገል የተፈጠሩ ናቸው ተብሎም ይታመን ነበር፡፡ ስለዚህ ተወላጅ የአፍሪካ ሕዝቦች የሚፈለጉት ለቤት አገልጋይነትና ለጉልበት ሠራተኝነት ብቻ ነበር፡፡ ነጮች በተዋቡ ከተሞች ሲኖሩ ጥቁር አፍሪካዊያን ግን በትንንሽ ስፍራዎች እንዲኖሩ ይደረግ ነበር፡፡

እነዚህንና ሌሎች አስከፊ በደሎችን የተቃወሙ ለከፍተኛ እስር እና እንግልት ተዳርገዋል፡፡ አድሎአዊ ሥርዓቱን በአደባባይ የተቃወሙ ህጻናት ሳይቀሩ የተጨፈጨፉበት ወቅትም ነበር፡፡ በሌላ በኩል ግን ይህን አድሏዊ አሠራር የሚቃወሙትን የሚያንገላቱ፣ የሚያስሩ፣ የሚደበድቡ፣ የሚገሉ ወዘተ... ይሸለሙ እና ይሾሙ ነበር፡፡

ማንዴላ ለረጅም አመታት ለእስር የተዳረጉት ይህን ዓይነቱን ሥርዓት ለዓለም ሕብረተሰብ በማጋለጣቸውና የሕዝብ ተቃውሞን በማስተባበራቸው ነው፡፡ ከ27 ዓመታት በኋላ ማንዴላ ከእሥር ተፈተው የመጀመሪያው ጥቁር የደቡብ አፍሪካ መሪ ሆነው ተመረጡ፡፡ በሥልጣናቸው ዘመን ምን ዓይነት እርምጃዎችን ይወስዱ ይሆን?

**መልመጃ 1**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ከጽሁፉ ውስጥ በደቡብ አፍሪካ የተፈፀሙ አድሏዊ አሰራሮችን ዘርዝሩ፡፡
2. የኔልሰን ማንዴላ ተግባር ትክክል ነበር ወይ? እንዴት?
3. ከማንዴላ ተግባር ምን ትማራላችሁ?
4. ማንዴላ የሀገር መሪ ሲሆኑ አድሏዊ አሠራሮችን ለማስወገድ ምን ዓይነት እርምጃ መውሰድ ይገባቸዋል ትላላችሁ?

አድሏዊ አሠራር የፍትሕ ተቃራኒ ከሆኑት አሠራሮች አንዱ ነው፡፡ አድሏዊ አሠራሮች በማንኛውም የሕይወት እንቅስቃሴ ውስጥ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ አድሏዊ አሰራሮች በተለያዩ አካባቢዎች ማለትም በትምህርት ቤት፣ በጫወታ ቦታዎች፣ በቀበሌ፣ በፍትሕና ማሕበራዊ ተቋማት ወዘተ... ይፈፀማል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚፈፀሙ አድሏዊ አሠራሮች ምክንያታቸው እንደዚሁ የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡

አድሏዊ አሠራሮች ሰዎችን እኩል ባለማየት እና በሰዎች መካከል ልዩነት የሚፈጥሩ ተግባራትን በመፈጸም ይገለፃል፡፡ ይህም የሚሆነው ሰዎች ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ዝምድናን፣ ጋብቻን፣ ጓደኝነትን ወዘተ መሠረት አድርጎ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችን ሲያከናውኑ ነው፡፡ ሰዎች አንዳንዴም በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፆታ እና በፖለቲካ አመለካከት ላይ ተመስርተው አድሎ ይፈፅማሉ፡፡ ሥልጣንን መከታ በማድረግ የሚፈፀሙ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶች ሁሉ አድሏዊ ተግባራት ናቸው፡፡

አድሏዊ አሰራሮች ልማዳዊ በሆነ ኋላቀር አመለካከትም የተነሳ ሲፈፀሙ ይስተዋላል፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በሴት ሕጻናት ላይ የሚፈፀሙ ድርጊቶች ናቸው፡፡ በሀገራችን ሕብረተሰቡ ሴት ሕጻናት ከወንዶች እኩል የትምህርት እድል አይሰጣቸውም፡፡ በቤት ውስጥ የሥራ ጫናም ከወንዶች ይልቅ በሴት ልጆች ትከሻ ላይ ይወድቃል፡፡ ስለዚህ ሴት ልጆች ከወንዶች እኩል የተፈጥሮ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበትና ራሳቸውን የሚያሻሽሉበት መንገድ የተነፈጉ ናቸው፡፡

**መልመጃ 2**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. አድሏዊ አሠራሮችን ለመከላከል ምን ዓይነት እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው ብላችሁ ታስባላችሁ?
2. በአካባቢያችሁ አድሎአዊ ናቸው የምትሏቸውን ድርጊቶች ዘርዝሩ፡፡
3. አድሎአዊ አሠራሮች በማን ይፈፀማሉ? ለእያንዳንዱ ሶስት፣ ሶስት ምሳሌዎችን ዘርዝሩ፡፡
   ሀ. በግለሰብ፣
   ለ. በመንግሰት ተቋማት፡
   ሐ. በሌሎች አካላት፣

## 4.2 ማሕበራዊ ተቋማት፤

### 4.2.1 በአካባቢያችሁ የሚገኙ ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚያሳዩት አሠራር ብቃትና ፍትሐዊነት፣

- በአካባቢያችሁ በጣም ጥሩ ትምህርት ቤት ነው የሚባለው የትኛው ነው? ጥሩ ያሰኙትን ምክንያቶች ዘርዝሩ፡፡
- በአካባቢያችሁ ከሚገኙ ሌሎች ማሕበራዊ ተቋማት መካከል መልካም አገልግሎት ይሰጣል የሚባለውን በመለየት መልካም ያሰኙትን ሥራዎች ዘርዝሩ፡፡

ማሕበራዊ ተቋማት ያለምንም ልዩነት ለሁሉም ዜጎች እኩል አገልግሎት የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ተቋማቱ ተገቢ አገልግሎት ለመስጠት ሁለት ጉዳዮችን ሊያሟሉ ይገባል፡፡ አንደኛው ፍትሐዊነት ሲሆን ሁለተኛው ጉዳይ ብቃትን የተላበሰ አሠራር መኖር ነው፡፡ የማህበራዊ ተቋማት አገልግሎት ፍትሐዊነት የተላበሰ መሆን አለበት ሲባል ከቦታ ቦታ ልዩነት ሳይደረግ የተመጣጠነ ስርጭት መኖር ነው፡፡ በሌላ በኩል ማሕበራዊ ተቋማት ፍትሐዊነት የሚገለጸው ዜጎች ያለምንም ልዩነት ማግኘት የሚገባቸውን አገልግሎቶች ከተቋማቱ ማግኘት ሲችሉ ነው፡፡ የማሕበራዊ ተቋማትን ብቃት የሚገለፀው ተቋማቱ አስፈላጊ በሆኑ የሰው ኃይልና መሳሪያዎች የተደራጁ ሲሆኑ፣ የተቋማቱ ሠራተኞች የሙያ ብቃት ሲላበሱ፣ የሥራ ሰዓትን እና የተቋማቱን ኃብትና ንብረት በአግባቡ ለሥራው ማዋልዋና የብቃት መመዘኛ ነጥቦች ናቸው፡፡

### የቡድን ሥራ 1

*ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን በአካባቢያችሁ የሚገኙትን ማሕበራዊ ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ በሚከተለው መስፈርት በመዳሰስ ከታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች ሥሩ።*

1. የትኛው ተቋም የተሻለ ነው?
   ሀ. የሥራ ሰዓት አከባበር ____________
   ለ. በቂ ባለሙያዎች መኖር ____________
   ሐ. የሥራ ሰዓትን ለሥራ ማዋል ________
   መ. የበቂ መሣሪያዎች መኖር ___________
2. በአጠቃላይ ውጤት የትኛው ተቋም በፍትሐዊነትም ሆነ በብቃት ከሌሎች የተሻለ ነው?
3. የምትኖሩበት አካባቢ ከሌሎች አጎራባች አካባቢዎች አኳያ ሲነፃፀር የማሕበራዊ ተቋማት ፍትሐዊነትና ብቃት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ግለፁ።

### የቡድን ሥራ 2

ሀገራችን ድሀ ከሚያሰኟት ጉዳዮች መካከል አንዱ የማሕበራዊ ተቋማት በበቂ መጠን በሁሉም ቦታዎች አለመሟላታቸው ነው። ስለዚህ የማሕበራዊ ተቋማትን ሥርጭት በማስተካከሉ ሂደት ምን ዓይነት አስተዋፅኦ ለማበርከት ታስባላችሁ?

## 4.3 የመብት መጣስና የፍትሕ መጓደል መንስኤዎች፤

ሰዎች ለምን የሌሎች መብት የመጣስ ድርጊቶችን ይፈፅማሉ? መብት የመጣስ አሠራር ለመፈፀሙ ምክንያት ናቸው የምትሏቸውን ነጥቦች ዘርዝሩ።

| የተቋማቱ ዝርዝር | የስራ ሰዓት መከበር | | በቂ ባለሙያ መኖር | | ልዩነት /አድሎ/ አለማሳየት | | የአስፈላጊ መሣሪያዎች መኖር | | የሥራ ሰዓትን በአግባቡ መጠቀም | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ጥሩ | ደካማ | ጥሩ | ደካማ | ደካማ | ጥሩ | ደካማ | ጥሩ | ደካማ | ጥሩ |
| 1. ቀበሌ | | | | | | | | | | |
| 2. ትምህርት ቤት | | | | | | | | | | |
| 3. ጤና ጣቢያ | | | | | | | | | | |
| 4. ግብርና ጣቢያ | | | | | | | | | | |

**"አቶ ንጉሱ የከተማ ሹሙ"**

አቶ ንጉሱ የአንዲት ትንሽ ከተማ የማዘጋጃ ቤት ሹም ናቸው። በከተማዋ የልማት ሥራዎች ላይ ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ማዘጋጃ ቤቱ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል። ለምሳሌ ያህልም ማዘጋጃ ቤቱ እንዳላቸው የገንዘብ መጠን ለባለ ሀብቶች በቂ የግንባታ ቦታዎችን ያመቻቻል። በባለሀብቶቹ የሚፈለጉ ቦታዎች የሚሰጡት በአቶ ንጉሱ በሚመራ ኮሚቴ ነው። ኮሚቴው በቂ ጥናት ካደረገ በኋላ ሕግን መሠረት በማድረግ ማንንም በማይጎዳ መልኩ በቀረቡ የቦታ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔዎችን ያሳልፋል።

ነገር ግን በአንድ ወቅት አቶ ንጉሱ በኮሚቴ ሳይወሰን ሦስት ተከታታይ የቀበሌ ቤቶችን ኢንቨስተር ነኝ ለሚሉት ለባለቤታቸው ወንድም እንዲሰጥ ወሰኑ። በቤቶቹ ውስጥ ለረጅም ጊዜያት ነዋሪ የነበሩት ግለሰቦች ቤቶቻቸው ለሌላ መሰጠቱን ያወቁት በአካባቢያቸው የግንባታ እቃ ሲራገፍ ነው።

ጉዳዩን ለኮሚቴውም ሆነ ለከተማ ሹሙ ለማቅረብ ያደረጉት ሙከራ አልተሳካም። ኃላፊዎቹ ሥራ ላይ ናቸው በሚል የሚያስተናግዳቸው አላገኙም። ነገር ግን በመጡባቸው ቀናት ሁሉ ኃላፊዎቹ ወደ ቢሮዎች ሲገቡና ሲወጡ ያስተውሉ ነበር።

ከብዙ ጊዜ መመላለስ በኋላ ለአቶ ንጉሱም ሆነ ለኮሚቴው ጉዳዩን ቢያስረዱም ምንም መልስ አላገኙም። ይባስ ብሎ አቶ ንጉሱ አካባቢያቸው ለግንባታ ስለሚፈለግ በአስር ቀናት ውስጥ ቤታቸውን እንዲለቁ በተላላኪያቸው በኩል መልእክት አስተላለፉ። ባለጉዳዮቹም ምንም የምናደርገው ነገር የለም በሚል የሚመጣውን መጠበቅ ጀመሩ።

**መልመጃ 3**

***በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ፍትሕ ተጓድሏል ብላችሁ ታስባላችሁ? የተጓደሉትን የፍትሕ ድርጊቶች ጥቀሱ።
2. ለባለሀብቱ የተሰጡት ቤቶች የእናንተ ቢሆኑ እናንተም ሆነ ቤተሰቦቻችሁ ምን ማድረግ አለባችሁ?
3. የኮሚቴው ዝምታ ተገቢ ነበር ትላላችሁ?
4. በዚህ ጥፋት ውስጥ ሥልጣኑን ያለአግባብ የተጠቀመው ማነው? ያልተጠቀመውስ ማነው?

*ለፍትህ መጓደልና ለመብት መጣስ የሚከተሉት ነጥቦች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡*

ሀ. **የዜጎችን መብቶች አለማክበር፣** ዜጎች የተለያዩ መብቶች አሏቸው:: ለምሳሌ በነጻነት የመኖር፣ የመማር፣ አቅማቸው በሚፈቀደው የሥራ መስኮች የመሰማራት፣ በመረጡት የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን፣ ወዘተ... ጉዳዮች የሚጠቀሱ ናቸው:: የዜጎች መብቶች እንዲጣሱ ከሚያደርጉት ጉዳዮች መካከል የፍትሕ አለመከበር አንዱ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የሕብረተሰቡን ሕግ ወይም ሥርዓት አለማክበር ማለት ነው፡፡

ፍትሕ የዜጎችን መብቶች ማስከበሪያ ዋና መሳሪያ ነው፡፡ በሀገር ላይ ፍትሐዊ አሰራር ችግር ካጋጠመው የዜጎች መብቶች ይጣሳሉ:: የዚህ ዓይነት ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ የአንድ ሀገር የፍትሕ ሥርዓት በግለሰቦች ሆነ በመንግሥት አካላት ሊከበር ይገባል::

ለ. **የተሰጠ የሕዝብና የመንግሥት**
ይህንን ኃላፊነት ለሥራ አገልግሎት ማዋል ተገቢ ሲሆን ሥልጣንን ከገደብ በላይ መጠቀም ግን አግባብ አይደለም፡፡ ስለዚህ የመንግሥትንና የሕዝብን ሥልጣን አላግባብ መገልገል የፍትሕ መጓደል እና የመብት ጥሰትን ያስከትላል፡፡

ሐ. **ዜጎችን በእኩልነት መንፈስ አለማስተናገድ፣** በሰዎች መካከል የጎላ ምክንያታዊ ልዩነት ከሌለ በስተቀር እኩል አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸው ሰዎች በእኩል የመስተናገድ መብት አላቸው፡፡ ለምሳሌ አንድ ዓይነት ጥፋት ያጠፉ ሰዎችን ተመሳሳይ ቅጣት መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በሰዎች መካከል በሚደረገው የአገልግሎት አሰጣጥ ተገቢ ያልሆኑ ልዩነቶችን በመፍጠር የሚሠሩ ድርጊቶች ለመብት መጣስና ለፍትሕ መጓደል መንስኤ ይሆናሉ፡፡

**መልመጃ 4**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

?

1. የመብት መጣስና የፍትሕ መጓደል ድርጊቶች በማን ይፈፀማሉ?
2. እስካሁን ካጋጠማችሁ ወይም ካያችሁት /ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ፣ ወይም ከአካባቢ ወዘተ.../ መብትን የሚጥሱ ተግባራት ናቸው የምትሏቸውን ድርጊቶች አብራሩ::
3. 'መብትሕ እንዲከበር የሌሎችን መብት አክብር' በሚለው አባባል ትስማማላችሁ? ለምን?
4. የዜጎችን መብት ማክበርና ማስከበር አለባቸው የምትሏቸውን አካላት ዘርዝሩ::

## 4.4 ፍትሕ እንዲኖር የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች፤

- በትምህርት ቤት እና በመማሪያ ክፍላችሁ ፍትሕ እንዲሰፍን የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?
- ፍትሕ የተጓደለበት እና መብቱ የተጣሰ ሰው ምን ማድረግ አለበት?

**ኔልሰን ማንዴላ፣ /ክፍል ሁለት/**

ማንዴላ ከእሥር ከተፈቱ በኋላ በደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው ጥቁር መሪ ሆነው ተመረጡ:: ወደ ሥልጣን እንደመጡም በእሳቸው የሚመራው መንግሥት ፍትሕን የሚያሰፍኑ ተከታታይ እርምጃዎችን ወሰደ:: ከእርምጃዎች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፤

- አድሏዊ የሆኑ ማናቸውም ሕጎች እንዲሰረዙ ተደረገ::
- ሁሉም ደቡብ አፍሪካዊ እኩል የዜግነት መብት እንዳለው ተደነገገ::
- ነጮችና ጥቁሮች በአንድ ትምህርት ቤት መማር፣ በተመሳሳይ ጤና ማእከሎች መገልገል ጀመሩ::
- ስፖርታዊ እና መዝናኛ ቦታዎች፣ ወዘተ... በእኩል ሁሉንም ማገልገል ጀመሩ::
- ፍትሕ ለረጅም ጊዜ ተነፍገው የነበሩት ጥቁር ሕዝቦች በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ተቀጥረው እና ተመድበው መሥራት ጀመሩ::
- በሀገራቸው ጉዳዮች ላይ በነጻነት የመሳተፍ መብታቸው ተረጋገጠ::
- በገጠርና በከተማ የሚገኙ የአስተዳደር፣ የፀጥታ እና የፍትሕ ተቋማት ሁሉንም ሕብረተሰብ ያለአድሎ በእኩል የሚያስተናግዱ ሆነው ተዋቀሩ::

በአጠቃላይ በነጭና ጥቁር ሕዝቦች መካከል ለዘመናት የነበረው የጥላቻና የበቀል ስሜቶች መቀነስ ጀመሩ:: በሀገሪቱም ሠላምና ፀጥታ መስፈን ጀመረ፡፡ ሠላምና ፀጥታም ለእድገትና ለብልፅግና መሠረት መሆኑ ታወቀ፡፡ ማንዴላ ለረጅም ጊዜ የቆየውን የመድሎ ሥርዓት በፅናት በመታገላቸው እና በመሪነት ዘመናቸው በወሰዱቸው ፍትሐዊ እርምጃዎች የዓለማችን ታዋቂ ሰው ለመሆን በቁ፡፡

መልመጃ 5

1. የምንባቡ መሠረት ፍትሕን ለማስፈን የተ ወሰዱትን እርምጃዎች ዘርዝሩ፡፡
2. በአንድን ሀገር ፍትሕ ለማስፈን ምን ዓይ ነት እርምጃዎች ሊወሰዱ ይገባል?
3. በፁሁፉ ላይ ተመሥርታችሁ የፍትሕን ጠቀ ሜታ ዘርዝሩ፡፡
4. የሚከተሉት ነጥቦች ለፍትሕ መስፈን ያላቸ ውን ጠቀሜታ ግለፁ፡፡
   - ሥነምግባር፣
   - የሕግ የበላይነት፣
   - ዴሞክራሲ፣
   - እኩልነት፡፡

ፍትሐዊነት እንዲሰፍን ከሚያስፈልጉ ተግባራት መካከል የሚከተሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ሀ. ፍትሐዊ አሠራሮችን ተግባራዊ ማድረግ፣ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጣቸው ፍትሐ ዊነትን የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ ወዘተ... የሚገኙ የመንግ ሥት ተቋማት ሁሉንም ዜጋ በእኩል የሚያስተናግዱ መሆን አለባቸው፡፡

ለ. የአካባቢ የፍትሕ አካላት በተሰጠ ሥልጣንና ሕግ ብቻ መሥራት፣ በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የፍትሕ አካላት የሚዋቀሩት የሕብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት ለማስ ጠበቅ ነው፡፡ ስለዚህ እነዚህ አካላት ኃላፊ ነታቸውን ሲወጡ ሕግን መሠረት አድር ገው መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚወጡ ሕጎችና ደንቦች የሕዝቡን ጥቅምና ፍላጎት እንዲያ ስከብሩ ሆነው የተዘጋጁ መሆን አለባ ቸው፡፡

ሐ. ዜጎች ፍትሕ የማግኘት መብታቸውን መጠ ቀም፣ ዜጎች በግል የሚደርስባቸውን በደል ለሚመለከታቸው የፍትሕ አካላት በማቅረብ ተገቢ መፍትሄ እንዲሰጣቸው መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ በዴሞክራ ሲያዊ ሥርዓት ውስጥ አንድ ዜጋ በራሱ ላይ ስለሚደርሰው በደል ብቻ ሳይሆን በሌ ሎችም ላይ የደረሱ አድሏዊ ድርጊቶችን መቃወም ይኖርበታል፡፡

መ. መብትን ለማስከበርና ፍትሕን ለማግኘት የተነሳሽነት ስሜት መኖር፣ የመብት መጣስንና የፍትሕ መጓደልን ከሚያስ ከትሉት ጉዳዮች መካከል ዜጎች መብታ ችውን ለማስከበር እና ፍትሕን ለማግኘት ያላቸው ተነሳሽነት አናሳ መሆን ነው፡፡ ዜጎች የደረሰባቸውን የመብት መጣስም ሆነ የፍትሕ መጓደል ድርጊቶችን ለማስ ወገድ የራሳቸውን ጥረት ሊያደርጉ ይገ ባል፡፡ በዚህም አድሎአዊ አሠራሮችን እንዳ ይከሰቱ ከመታገል ባሻገር ጉዳዩን ለሚመለ ከተው የፍትሕ ተቋም የማቅረብ ወይም የማ ሳወቅ ልምድንም ሊያጎለብቱ ይገባል፡፡

መልመጃ 6

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. እናንተም ሆናችሁ ጓደኞቻችሁ የደረሰን አድ ሏዊ ድርጊቶች በማሳወቅ ተገቢ ፍትሕ ለማግኘት ያደረጋችሁት ጥረትን በምሳሌነት አቅርቡ፡፡
2. ቤተሰቦቻችሁ መብትን ለማስከበር ያደረጓቸው ጥረቶች በመጠየቅ ዘርዝሩ፡፡
3. በትምህርት ቤታችሁ ፍትሕን በማስከበሩ ሂደት ያላችሁን ኃላፊነቶች ዘርዝሩ፡፡




ሥዕል 4.2 ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታ ነው፡፡

## 4.5 ግብር

### 4.5.1 ግብር መቼና እንዴት ተጀመረ

- መንግሥት ለዜጎች የጋራ ጥቅም የሚ ውሉ ጉዳዮችን ማሟላት የሚቻለው ከየት ከሚገኝ ገንዘብ ነው?

### «የ'ከድጃ ዘገባ»

ከድጃና ጓደኞቿ ሰሞኑን በግብር "ታሪካዊ አመጣጥ እና የግብር ዓይነቶች" ላይ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የቡድን ስራ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ቤተሰቦቻቸውንና ባለሙያዎችን በመጠየቅ ያዘጋጁት ዘገባ በሚከተለው ሁኔታ ተቀናብሯል፡፡

#### "የግብር ታሪካዊ አመጣጥ፣" /ክፍል አንድ/

"የግብር ታሪካዊ አመጣጥ ከመንግሥት መፈጠር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተመሠረቱ ጥንታዊ መንግሥታት ከሕብረተሰብ የሚሰበስቡት ግብር ዋና የገቢ ምንጫቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ ያህል ከዛሬ ሶስት ሺህ ዓመታት በፊት የነበሩት የግሪክ እና የግብፅ ጥንታዊ መንግሥታት ከሚያስተዳድሩት ሕዝብ ግብር ይሰበስቡ ነበር፡፡

በእኛም ሀገር በጥንት ዘመን የነበሩት መንግሥታት ዋና የገቢ ምንጭ ከሕዝቡ በንብረትና በገንዘብ የሚሰበስቡት ግብር ነበር፡፡ ነገር ግን በሀገራችን በሕግ ተደንግጎ ግብር መክፈል የተጀመረው ከ15ኛው ምዕተ ዓመት ከአፄ ወይም ንጉሥ ዘርዐያዕቆብ ዘመን ጀምሮ ነው፡፡"

**መልመጃ 7**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

?

1. የግብር አመጣጥ ለምን ከመንግሥት መመሥረት ጋር ተያያዘ?
2. በሀገራችን ግብርን መሰብሰብ መቼ ተጀመረ?
3. ሰዎች ግብርን መክፈል መቼ ጀመሩ?

#### "የ'ከድጃ ዘገባ" /ክፍል ሁለት/

ግብርን መክፈል ለምን ተጀመረ?

"ሰዎች በአንድ አካባቢ ለመኖር የአካባቢያቸው ሠላምና ፀጥታ ሊከበርላቸው ይገባል፡፡ ከውጪ የሚመጣ ጥቃትን ለመከላከል በጋራ የተደራጀ ኃይል አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም የሕብረተሰቡ የእርስ በእርስ ትስስር ጠንካራ መሆን አለበት፡፡ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ጥቃቶችን ለመከላከል እና ሕብረተሰቡን ለማስተዳደር መንግሥት የሚባል አካል ተፈጠረ፡፡ እነዚህን ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት እና ሌሎች የዜጎችን የጋራ ጉዳዮች ለማሟላት መንግሥት ከዜጎቹ የገንዘብ፣ የጉልበትና የንብረት ድጋፍ ማግኘት አስፈላጊ ሆነ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ዜጎች ለመንግሥታቸው የሚከፍሉት ክፍያ ግብር በመባል ይጠራ ጀመር፡፡"

ከላይ ከነከድጃ ሪፖርት እንደተረዳችሁት ግብር ሰዎች በአንድ ላይ ተደራጅተው በአንድ መንግሥት ሥር መተዳደር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ የተጀመረ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መንግሥት ከሚያስተዳድረው ሕብረተሰብ ግብርን ይሰበስብ እንደነበር ተብራርቷል፡፡ ስለዚህ ከዚያ ጀምሮ ግብር የመንግሥታት ዋና የገቢ ምንጭ ሆኖ ማገልገል ጀመረ፡፡

ከግብር የሚገኘው ገቢ የሕብረተሰቡን የጋራ ጥቅሞች ማስጠበቂያ መሣሪያ ሆኖ ማገልገል ጀመር፡፡ ለምሳሌ ጥቃትን መከላከል እና ውስጣዊ ሠላምና ፀጥታን ማስከበር የተቻለው ከግብር በሚሰበሰብ ገንዘብ እና ሀብት ነበር፡፡

**መልመጃ 8**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. በዓለማችን የሚገኙ ጥንታዊ መንግሥታት ከግብር የሚሰበስቡትን ንብረትና ገንዘብ ለምን ተግባራት ያውሉታል?
2. ሰዎች ግብርን መክፈል የጀመሩት በምትኩ ምን ለማግኘት አስበው ነው?

### 4.5.2 ግብር የሚሰበሰብባቸው የገቢ ዓይነቶች፣

- በጥንት ዘመን ሰዎች ለመንግሥታቸው የሚከፍሉት ግብር ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

#### "የነከድጃ ዘገባ" /ክፍል ሦስት/

የነከድጃ ክፍል ሦስት ሪፖርት በግብር ዓይነቶች ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ከዚህ በታች በሁለት ክፍሎች ተከፍሎ ቀርቧል፡፡

#### "የግብር ዓይነቶች ጥንትና በአሁኑ ዘመን"

ሀ. በጥንት ዘመን፣ "በጥንት ዘመን የነበሩ መንግሥታት ግብርን ከተለያዩ የገቢ ዓይነቶች ይሰበስቡ ነበር። አብዛኛው ጊዜ ግብር በገንዘብ እና ከምርት ውጤቶች የሚገኝ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የጉልበት አገልግሎት በመስጠት የግብር ግዴታቸውን ይወጣሉ፡፡ ከጊዜ በኋላም ግብርን በኃይልና በተፅእኖ የማስከፈል አሠራርም እየተስፋፋ መጣ፡፡

በዚህ መሠረት የግብር አከፋፈሉ ፍትሐ ዊነት የጎደለው መሆን ጀመረ:: ለምሳሌ ግብርን ከአቅማቸው በላይ የሚከፍሉ እንዳሉ ሁሉ ከግብር ነፃ የሚሆኑ ነበሩ:: በይበልጥ ሀብትና ሥልጣን ያላቸው የግብር ክፍያ አይመለከታቸውም ነበር:: ከግብር የሚገኘው ገቢ ለሕዝቦች የጋራ ጥቅም መዋሉ ቀርቶ ሥልጣን ላይ ላሉ ለጥቂ ቶች መንደላቀቂያ መዋል ጀመረ::"

ለ. **በአሁኑ ጊዜ ግብር የሚሰበሰብባቸው የገቢ ዓይነቶች፣** "የግብር አሰባሰብ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለዋወጠ የሚሄድ ነው:: የሚ ሰበሰበው የግብር ምንጮች ከዘመን ዘመን እና ከመንግሥት መንግሥት እንደዚሁም ከሀገር ሀገር ይለያያሉ:: በዴሞክራሲዊ ሥርዓት የግብር አሰባሰብ የተሻሻለ ደረጃ ላይ ይገኛል:: ግብር ለማን፣ ለምን ተግ ባር እና ከምን ከምን ገቢዎች እንደሚሰ በሰቡ በሕግና በደንብ ተለይተው ይዘረዘራሉ::"

ከሪፖርቱ እንደምትረዱት ግብር የሚሰበሰቡ ባቸው የገቢ ዓይነቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተ ለዋወጡ የሚሄዱ ናቸው:: ለምሳሌ በጥንት ዘመን ግብር በገንዘብ ብቻ የሚከፈል አልነ በረም:: ከተለያዩ የምርት ውጤቶች እና የጉ ልበት አገልግሎት በመስጠት ዜጎች የሚጠ በቅባቸውን የግብር ግዴታዎች ይወጡ ነበር:: በአሁኑ ወቅት ግብር የሚሰበሰበው በገንዘብ ሲሆን የአሰባሰብ ሥርዓትና ሂደት የተሻሻ ለበት ደረጃ ላይ ይገኛል::

ግብርም ከተለያዩ የገቢ ዓይነቶች ይሰበሰ ባል:: ግብር በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ከቀ ድሞ ጊዜያት በተሻለ ከተለያዩ ምንጮች ወይም አካባቢዎች ይሰበሰባል::

ዋና ዋና የግብር መሠረቶች ወይም ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው:: ከግብርና፣ ከተለያዩ የን ግድ ሥራዎች፣ ከደመወዝ፣ ከፋብሪካዎች እና ከማእድን ሀብቶች፣ ከአርብቶ አደሩ፣ ከሌሎችም የአገልግሎት ዘርፎች ለምሳሌ ቱሪዝምና ሆቴ ሎች ወዘተ... ዋና ዋናዎቹ የግብር መሠረ ቶች ናቸው::

**መልመጃ 9**

? ***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. በየሀገሮች ያሰው የግብር ክፍያዎች ተመ ሳሳይ ናቸው ብላችሁ ትገምታላችሁ? ለምን?
2. ከሚከተሉት ውስጥ ቤተሰቦቻችሁ ግብር የሚ ከፍሉባቸውን የአገልግሎት ዓይነቶች ዘርዝሩ::

- ከእርሻ መሬት፣
- ከንግድ፣
- ከደመወዝ፣
- ከመኖሪያ ቤት፣
- ከቦታ ይዞታ፣
- ከገበያ ቦታ፣
- ከቴሌቪዥን፣
- ከስልክ ቀፎ፣
- ከመብራት ቆጣሪ፣
- ከእንስሳት ልማት።

### 4.5.3 ግብርን በሀቀኝነት መክፈል የዜግነት ግዴታ ነው፣

- ግብርን መክፈል ለምን የዜጎች ግዴታ ሆነ?
- ዜጎች ግብርን ለመክፈል ምን ዓይነት ሥነምግባር ሊኖራቸው ይገባል::

ግብር በፍቃደኝነት እና በፍላጎት መከፈል ያለበት የዜግነት ግዴታ ነው:: በዴሞክራሲ ሥርዓት ግብር መክፈል እንደ እዳ ተደርጎ አይወሰድም:: ግብር ለጋራ ልማት የሚውል ከዜጎች የሚሰበሰብ ገቢ ነው። የተለያዩ አገልግ ሎት ሰጪ ተቋማትንና መንገድን ለመገንባት፣ ለብሄራዊ ደህንነት የሚውል ገንዘብ ለማግኘት የሚያስችል ሥርዓት እንደሆነ ሕብረተሰቡ ይገነዘባል::

በዚህም መሠረት ግብር መክፈል የዜግነት ግዴታ መሆኑን በመረዳት ዜጐች የሚጠበቅ ባቸውን ግብር በወቅቱ መክፈል ይገባቸዋል:: በልማት በገፉ ሀገሮች ግብርን በወቅቱ አለመ ክፈል በሕግ የሚያስቀጣ ድርጊት ነው:: ከዚህ በተጨማሪም ይህ ዓይነቱ ተግባር በሕብረተ ሰቡ ዘንድ አስነዋሪ ተደርጎ ስለሚታይ መል ካም ስምን ያጎድፋል:: ስለዚህ የግብር መጠን ለመወሰን ይረዳ ዘንድ ዜጎች ስለገቢያቸው ሁኔታ እውነተኛ መረጃ በመስጠት አስፈላ ጊውን ግብር መክፈል ይጠበቅባቸዋል::

**መልመጃ 10**

? ***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. ዜጎች ግብርን በአግባቡ ባይከፈሉ ምን ዓይ ነት ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ?
2. በጥንት ጊዜ የነበረው የግብር ዓላማ በአሁኑ ወቀት ካለው በምን ይለያል?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

አድሏዊ አሠራሮች በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ይፈፀማሉ፡፡ ከትንሽ እስከ ትልቅ ባሉ አገልግሎት መስጫ ቦታዎችም በየጊዜው ሲከሰቱ ይስተዋላሉ፡፡ የሚፈጠሩ አድሏዊ አሠራሮች ምክንያቶቻቸው የተለያዩ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁሉ አድሏዊ አሰራሮች የሚፈፀሙት በሰዎች አማካኝነት ሲሆን ይህን ለማስወገድ ዜጎች ማንኛውንም አድሏዊ አሠራሮች ከመፈፀም መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡ ተፈፅመው ሲያገኙም ሲቃወሟቸው ይገባል፡፡

አድሏዊ አሠራሮችን ለመከላከል ሌላው መሠራት ያለበት ተግባር የማሕበራዊ ተቋማትን በሰው ኃይልና በቁሳቁስ ማደረጀት እና ያላቸውን ሥርጭት እንዲስተካከል ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ተገቢውን ድጋፍና ትብብር ለመንግሥት አካላት ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡

ለዜጎች መብት መጣስና ለፍትሕ መጓደል ምክንያት ከሚሆኑት ጉዳዮች መካከል የዜጎችን መብት አለማክበር፣ የተሰጠ የሕዝብ ሥልጣንን ያላግባብ መገልገል እና ዜጎችን በእኩልነት አለማስተናገድ ናቸው፡፡ ስለዚህ ፍትሕን በዘላቂነት በህብረተሰብ ውስጥ ለማስፈን ፍትሐዊ አሠራሮችን ተግባራዊ ማድረግ፣ የፍትሕ አካላት በተሰጣቸው ሥልጣን መሠረት አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻልና፣ ዜጎችም ፍትህ የማግኘት መብታቸውን የመጠቀም ተነሳሽነት ስሜታቸው እንዲጐለብት ማድረግ ይገባል።

በሌላ በኩል ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ግብር በወቅቱ መክፈል የዜግነት ግዴታ መሆኑን ማወቅ ይገባቸዋል። ለዚህም በግብር አሰባሰቡ ሂደት ዜጎች ገቢያቸውን አስመልክቶ ለመንግሥት የሚሰጡት መረጃ በሀቅ እና በእውነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

***በደል፣*** ተገቢ ያልሆነ ጎጂ ድርጊት።

***ሕግ፣*** ሕዝቦች ተስማምተው የተቀበሉት የመተዳደሪያ ሥርዓት።

**ደንብ፣** ማን ምን እንደሚሠራ፣ እንዴት እንደሚሠራ የሚያመላክት መመሪያ።

***ብሄራዊ ደህንነት፣*** ሀገራዊ የሠላም ሁኔታ።

***የተደራጀ ኃይል፣*** ማንኛውንም ዓላማ ለማሳካት ሕብረት ፈጥሮ የሚገኝ ኃይል፡፡

***ነገሥታት፣*** በሕዝቦች ሳይመረጡ በቤተሰብ ውርስ እየተፈራረቁ ሕዝብን የሚገዙ ግለሰቦች፣ ዘውዳዊ ሥርዓት፡፡

***ባለሀብት፣*** በተለያዩ ዘርፎች ሀብታቸውን ለልማት የሚያውሉ ሰዎች፣ ቡድኖች ወዘተ...፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

*I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ «ሀሰት» ብላችሁ መልሱ፡፡*

1. ማሕበራዊ ተቋማት በተሟሉበት አካባቢ ፍትሐዊ አሠራሮች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡
2. የአንድ ተቋም ብቃት የሚረጋገጠው በቂ መሣሪዎች ከተሟሉለት ብቻ ነው፡፡
3. አልፎ አልፎ አድሏዊ አሠራሮች መፈፀም ተገቢ ነው፡፡
4. በዴሞክራሲ ሥርዓት ውስጥ ግብርን መክፈል የዜጐች ግዴታ ነው፡፡
5. በተለያዩ ቦታዎች የሚፈፀሙ አድሏዊ አሠራሮች መንስኤዎቻቸው ተመሳሳይ ናቸው፡፡

*II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በትውውቅና በዝምድና መሥራት | ሀ. የብቃት ችግር |
| 2. የዜግነት ግዴታ | ለ. ፍትሕን ማስፈኛ መንገድ |
| 3. አስፈላጊ መሳሪያዎች አለመኖር | ሐ. መድሎ |
| 4. በሀሰተኛ መረጃ ላይ ተመስርቶ ፍርድ መስጠት | መ. የፍትሕ መጓደል |
| 5. ሕግን ማክበር | ሠ. ግብር መክፈል |
| | ረ. ማሕበራዊ ተቋማት |

*III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡*

1. የግብር ፍትሐዊነት የሚገለፀው ከሚከተሉት ድርጊቶች በአንዱ ነው፤
   ሀ. ዜጐች እንደገቢያቸው መጠን ሲከፍሉ፣
   ለ. ሁሉም ዜጐች እኩል መጠን ያለው ክፍያ ሲከፍሉ፣
   ሐ. የሀገር መሪዎች ከግብር ክፍያ ነፃ ሲሆኑ፣
   መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው።
2. ከሚከተሉት መካከል የግብር ምንጭ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. እርሻ፣ ሐ. ንግድ፣
   ለ. ደመወዝ፣ መ. ሁሉም መልስ ናቸው።
3. አድሏዊ አሠራሮች ሲፈፀሙ የሚችሉ አካባቢዎች የትኞቹ ናቸው?
   ሀ. ቀበሌ፣ ሐ. ት/ቤቶች፣
   ለ. የፍትሕ ተቋማት፣ መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡
4. ለፍትሕ መጣስ መንስኤ የማይሆነው የቱ ነው?
   ሀ. በገንዘብና በጥቅማጥቅም መሥራት፣ ሐ. ፍትሕን ማጓደል፣
   ለ. ሥልጣንን ያላግባብ መጠቀም፣ መ. የሰዎችን መብት ማክበር፡፡
5. የሰዎች መብቶች እንዲከበሩ ምን መደረግ አለበት?
   ሀ. በሕግ መጠቀም፣ ሐ. ፍትሕን ማስፈን፣
   ለ. በጉልበት መብትን ማስከበር፣ መ. "ሀ" እና "ሐ" መልስ ናቸው፡፡

*IV የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡*

1. ዜጐች ከገቢያቸው አንፃር ለመንግሥታቸው የሚከፍሉት ክፍያ ______________ በመባል ይታወቃል፡፡
2. አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለሕብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ____________ ሲሆን ይገባል፡፡

*V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡*

1. ትምህርት ቤት ውስጥ ፍትሐዊ አሠራሮች እንዲሰፍኑ ከእያንዳንዳችሁ የሚጠበቁ ኃላፊነቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. አድሏዊ አሠራሮችን ለመከላከል መሠራት ያለባቸውን ተግባራት ዘርዝሩ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# የሀገር ፍቅር

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተ ምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የሀገር ፍቅር መገለጫዎችን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ::
- የሀገርን ታሪክ ማወቅ ለሀገር ፍቅር መጉልበት ያለውን ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ::
- የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ዓላማን ትረዳለህ/ትረጻለሽ::
- ዜግነት የሚገኝባቸውን መንገዶች ታውቃለህ/ታውቂያለሽ::

## 5.1 የሀገር ፍቅር፤

### 5.1.1 ለሀገር ፍቅር መጐልበት የማያስፈልጉ ሁኔታዎች፣

ባለ ብዙ ቋንቋ - ባለ ብዙ ዜማ፣
አኩሪ ታሪካችን - በዓለም የሚሰማ፤
የዕድገት ጐዳናችን - መንገዱ የሰፋ፣
የሠላም ሕዝቦች ነን - ባለ ብሩህ ተስፋ።
ባንድ እንደሚበሩ - የሠላም ርግቦች፣
ባለ ብዙ ቀለም-ህብርነን-ውብ ሕዝቦች፤
ኢትዮጵያ ልጆችሽ - ቃል እንገባለን፣
ለዕድገትሽ ልንሰራ - ላብና ደም ክፍለን።
*(ከህብረ ብሔር መጽሔት፤ህዳር 2000.ዓ.ም)*

- ከዚህ በላይ የቀረበው ግጥም ምን ምን ይዘቶች እንዳሉት ግለፁ፡፡
- በግጥሙ ውስጥ ህብረ ብሔራዊነት የተገለፀው እንዴት ነው?

**የተማሪዎች ክርክር፤**

የአድዋ ድል ትምህርት ቤት ተማሪዎች በየሦስት ወሩ የክርክር ፕሮግራም አላቸው። የዚህ ወር ተከራካሪዎች የስድስተኛ “ሀ”፣ “ለ” እና “ሐ” ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ለመከራከሪያነት የተሰጠው ርዕስም፤ “ለሀገር ፍቅር መጎልበት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች” የሚል ነው። የስድስተኛ “ሀ” ክፍልን ወክለው የሚከራከሩት ኤልሳቤጥና ዳንኤል ናቸው። እነ ዚህ ሁለት ተማሪዎች ለመከራከሪያነት የመረ ጡት ርዕስ፤ “የሀገር ፍቅርን ለማጐልበት የግ ልና የቡድን መብቶች መከበር አለባቸው” የሚል ነው። በዚህ ርዕስ ዙሪያ ምን ምን ነጥቦ ችን ቢጠቃቅሱ በክርክሩ ሊያሸንፉ እንደሚ ችሉ ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር እየተመካከሩ ነው።

የስድስተኛ “ለ” ክፍልን ወክለው የሚከራከሩት ሐሊማና ዘሪሁን ናቸው። እነዚህ ሁለት ተማ ሪዎች የሚከራከሩበት ርዕስ “የሀገር ፍቅርን ለማጐልበት አድሎአዊ አሠራር ሊወገድ ይገ ባል” የሚል ነው። የክፍል ጓደኞቻቸውም የሚ ከተሉትን ነጥቦች ለመከራከሪያነት እንዲያ ቀርቡ ምክር ሰጥተዋቸዋል።

ሀ. በሀገሪቱ የፍትሕ አሠጣጥ ዙሪያ አድሎ አዊ አሠራር ጐልቶ ከታየ ዜጐች ለሀገራ ቸው የሚኖራቸው ፍቅር እናሳ ይሆናል።

ለ. በሴቶችና በወንዶች መካከል የትምህር ትና የሥራ ዕድል ለማግኘት አድልዎ ከተደረገ ለሀገራችን የሚኖረን ፍቅር ይቀ ንሳል።

ሐ. ሰው ሁሉ በተፈጥሮው እኩል ስለሆነ ለህ ፃናት፣ ለአረጋዊያን ወይንም ለሴቶች የተለየ ጥበቃና እንክብካቤ ሊደረግ አይ ገባም።

የስድስተኛ “ሐ” ክፍልን ወክለው የሚከራከ ሩት አበባየሆሽና አህመድ ናቸው። አበባየሆ ሽና አህመድ የሚከራከሩበት ርዕስ፤ “የአካባ ቢንና የሀገርን ታሪክ ማወቅ ለሀገር ፍቅር ስሜት መጐልበት ያግዛል” የሚል ነው። አበ ባየሆሽና አህመድ የመከራከሪያቸውን ነጥብ የከፈሉት በሚከተሉት ሦስት ንዑሳን ርዕሶች ዙሪያ ነው።

1. የሀገር ፍቅር ስሜት ማደግ የሚጀምረው የቤተሰብን ታሪክ በማጥናትና በሚገባ በማ ወቅ ነው።
2. በአካባቢያችን ላሉ ልዩ ልዩ የታሪካዊ መገለጫዎችና ለብሔሮችና ብሔረሰቦች ባህሎች ልዩ ትኩረት ስንሰጥ የሀገር ፍቅር ስሜታችን ያብባል።
3. ለሀገራችን አኩሪ የሕዝቦች ታሪክ በቂ ዕውቀት ሲኖረን የሀገር ፍቅር ስሜታችን ፅኑ መሠረት ይኖረዋል።

**መልመጃ 1**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ኤልሳቤጥና ዳንኤል ክርክሩን ማሸነፍ እንዲችሉ በርዕሱ ዙሪያ ምን ነጥቦችን እንዲያነሱ ትመክሯቸዋላችሁ?
2. ሐሊማና ዘሪሁን ጓደኞቻቸው ለመከራከሪያ በሰጧቸው ከሀ-ሐ በተጠቀሱት ነጥቦች ላይ ትስማማላችሁ? ተወያዩበት፡፡
3. አበባየሆሽና አህመድ ማንሳት የሚገባቸውን ዝርዝር ነጥቦች በተመለከተ ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በቡድን ተወያይታችሁ አጭር የጽሁፍ ሪፖርት ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

የሀገር ፍቅር ስሜት የሚገለብተው የእያንዳንዱ ዜጋ የግልና የቡድን መብቱ ከአድሏዊነት በጸዳ መልኩ ሲከበርለት ነው። የብሔሮችና የብሔረሰቦች መብት ሳይሸራረፍ ሲከበር፣ የሕግ የበላይነት ሲሰፍን፣ ጠንክሮ መማርና መሥራት የዜጎች ባህል ሲሆን የሀገር ፍቅር ስሜት ከፍ ይላል፡፡

ነገር ግን የዜጎች መብት ሳይከበር የሀገሪቱን መልክዓ ምድር ማፍቀርና መውደድ ብቻ በራሱ ትርጉም አይኖረውም። አድሏዊ አሠራር በሰፈነበት ማሕብረሰብ ውስጥ የሀገር ፍቅር ስሜት ከመጎልበት ይልቅ የደበዘዘ ይሆናል። ሀገርን ከማንኛውም አደጋ መከላከልና ራስንም ሆነ ሀገርን ከሚጎዱ ጉዳዮች መጠበቅ ሀገሩን የሚወድ ዜጋ መገለጫ ነው፡፡

**መልመጃ 2**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. መልክዓ ምድርን ማድነቅ ብቻ በዋነኛነት የሀገር ፍቅር መገለጫ ሲሆን አይችልም የሚባለው ለምንድን ነው?
2. አድሏዊነት የሚደታይበት የሕዝቦች መፈቃቀርና መከባበር ውጤቱ ምን ሲሆን ይችላል?
3. እናንተስ ሀገራችሁን መውደዳችሁን የምትገልፁት ምን በማድረግ ነው?

## 5.2 ጉጂና አፍራሽ ተግባራት፤

### 5.2.1 ለጋራ ንብረቶች እንክብካቤ አለማድረግ፣

- የጋራ መገልገያ ንብረቶች የሚባሉት ምንድን ናቸው?

**አርአያነት ያለው ተግባር፤**

የዕውቀት ፋና ትምህርት ቤት፤ "የሀገር ፍቅር" በሚል ስያሜ የሚታወቅ ክበብ አለው። የትምህርት ቤቱ "የሀገር ፍቅር ክበብ" አባላት መምህራንና ተማሪዎች ናቸው። የክበቡ አባላት በየጊዜው በሚያደርጉት አርአያነት ያለው እንቅስቃሴ ዩኒሴፍ (የተባበሩት መንግሥታት የህፃናት መርጃ ድርጅት) ከሚባል ዓለም አቀፍ ድርጅት ልዩ ሽልማት ሊያገኙ ችለዋል። በቅርቡ በትምህርት ቤታቸው ግቢ ውስጥ ያዘጋጁት ልዩ ዐውደ ርዕይ ብዙ ተመልካቾችን አስደንቋል። ዝግጅቱ የቀረበው በዓመታዊ የትምህርት ቤቱ በዓል ላይ ስለነበር በርካታ ወላጆች ተገኝተው ነበር። ዝግጅቱ የቀረበው በሦስት ክፍሎች ተከፋፍሎ ሲሆን የዝግጅቱ ይዘትም የሚከተለውን ይመስላል። የመጀመሪያው ክፍል ትርዒት የቀረበው በትምህርት ቤቱ ቤተ መጻሕፍት ውስጥ ነው። የቤተ መጻሕፍቱን ዋና በር ሲገቡ የተቀዳደዱና ስዕሎቻቸው ከውስጥ ተቦጭቆ የተወሰዱ በርካታ መጻሕፍት ይታያሉ። በግርግዳውም ላይ "ትውልድ ይፍረደን" የሚል ጽሑፍ ተጽፏል።



ሥዕል 5.1 የተገነጣጠሉና የተቀዳደዱ መፃሕፍት

በሁለተኛው ክፍል ውስጥ በግዴለሽነት የተሰባበሩ ወንበሮች፣ ጥቁር ሰሌዳዎች፣ ዴስኮችና የቤተ ሙከራ ዕቃዎች ተሰብስበዋል፤ በግድግዳውም ላይ "በግዴለሽነት የተጐዱና የተሰባበሩ የጋራ መገልገያዎቻችን" የሚል ጽሑፍ ይነበባል።



ሥዕል 5.2 በግዴለሽነት የተጐዱና የተሰባበሩ የጋራ መገልገያዎቻችን

በሦስተኛው የትርዒት ማሳያ ክፍል ተማሪዎች ቦጫጭቀው የጣሏቸው ደብተሮች፣ የገነፈሉ እስክሪቢቶዎችና ቁርጥራጭ እርሳሶች ተሰብስበው ይታያሉ። በግርግዳውም ላይ "ከዚህ ውስጥ ያንተ/ቺ የትኛው ነው?" የሚል ጽሁፍ ተጽፏል።




ሥዕል 5.3 የገነፈሉና የተሰባበሩ እስክሪፕቶዎችና እርሳሶች

ዝግጅቶቹ ተጠናቀው ጎብኚ እንግዶቹ ከየክፍሎቹ ሲወጡ በራፍ ላይ በቆሙ አስተናጋጅ ተማሪዎች አማካይነት አነስተኛ ካርድ ታደላቸው:: በካርዶቹ ላይ የተጻፈው ጽሑፍ እንዲህ የሚል ነው። "እኛስ አንዴ በግዴለሽነት ተፈርዶብናል፤ ለቀሪዎቹ መጻሕፍትና የመማሪያ መሣሪያዎች እንክብካቤ እንዲደረግላቸው አደራችንን አስተላልፉልን።"

**መልመጃ ፫**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ከላይ የቀረበው «የሀገር ፍቅር ክበብ» አባላት ምሳሌያዊ ትርዒት ምን ስሜት አሳደረባችሁ?
2. እናንተስ የትምህርት ቤታችሁን የጋራ መገልገያዎች እንዴት ነው የምትይዙት?

በትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ የጋራ መገልገያ መሣሪያዎች ለመማር ማስተማሩ ሂደት በጣም ወሳኝ ናቸው። ሀገራችን ካላት ውስን ሃብት ተቆንጥሮ ለትምህርት ቤቶች የጋራ መገልገያ እንዲሆኑ የሚሟሉት መሣሪያዎች በጥንቃቄ መያዝ ይገባቸዋል። የመማሪያ ወንበሮች ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ ቢሠበሩ ጉዳቱ የተማሪው ነው። የክፍል ወለሉ ቢቆፋፍር የጤና ጉዳት የሚያስከትለው በራሱ በተማሪውና በመምህሩ ላይ ነው። የጋራና የግል መገልገያ

መሣሪያዎች ጥንቃቄ በጎደለበት ሁኔታ መያዝ ጉዳቱ ከራስ አልፎ የሚጎዳው ቤተሰብንና ሀገርን ስለሆነ እያንዳንዱ ዜጋ ሃላፊነት አለበት።

## ✎ የቡድን ሥራ 3

*ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ የትምህርት ቤታችሁን የጋራ መገልገያ ንብረቶችን በመዘርዘር እንዴት ሊጠበቁ እንደሚገባቸው በቡድን ተወያይታችሁ ለመምህራችሁ የጽሁፍ ሪፖርት አቅርቡ።*

### 5.2.2 ቆሻሻን በየቦታው መጣል፣ በመፀዳጃ ቤት በአግባቡ ያለመጠቀምና ግዴለሽነት፣

- ቆሻሻን በየበታው መጣልና በመፀደጃ ቤት ባግባቡ ያለመጠቀም ምን ጉዳይ ሊያስከትል ይችላል?

**የንፁህ መንደር ክንውኖች፤**

የንፁህ መንደር ወጣቶች በፈቃደኝነት ተሰብስበው የስካውት ቡድን አቋቁመዋል። የስካውት ቡድኑ አሥራ ሁለት አባላት ያሉት ሲሆን ዋነኛ ሥራቸውም የአካባቢያቸውን ጽዳት ማስጠበቅ ነው። ለወጣቶቹ ሙሉ የደንብ ልብስ አዘጋጅቶ የሰጣቸው የቀበሌአቸው ጽ/ቤት ነው። ወጣቶቹ ራሳቸውን በተራ ደልድለው በመኖሪያ ሰፈራቸው አካባቢ እየተዟዟሩ አካባቢያቸውን ያፀዳሉ፣ የጽዳቱንም ሁኔታ ይከታተላሉ፡፡ የውሃ መውረጃ ቦይ እንዳይደፈን፣ የሰፈሩ ወጣቶች የመጫወቻ ሜዳ እንዳይቆሸሽ በጥብቅ ይቆጣጠራሉ።

ነዋሪው ኅብረተሰብ ቆሻሻ በየቦታው እንዳይጥል ትምህርት ይሰጣሉ፣ ልዩ ልዩ ጽሑፎችንና ፖስተሮችንም በመለጠፍ ይቀሰቅሳሉ። እነርሱም ምሳሌ በመሆን ሠርተው ያሠራሉ፡፡ በአካባቢያቸው ከለጠፏቸው ጽሑፎች መካከልም፤

"ቆሻሻ የሚያቆሽሸው ራስን ነው!"
"እኔና ቆሻሻ አንገናኝም!"
"ሰፈሬ በፅዱነቱ ይታወቅ!"
"መፀዳጃ ቤቴ ንፁህ ነው"
"ግዴለሽነት በሰፈሬ አይታወቅም!" የሚሉት ይገኙበታል።

ስካውቶቹ ባሉበት ሰፈር ቆሻሻ የሚደፉ ወይንም በየመንገዱ የሚያዝረከርኩ ሰዎች አይታዩም፡፡ የጋራ መፀዳጃ ቤቶቹን ንፅህና የማይጠብቅና በግዴለሽነት ለአካባቢው ነዋሪዎች ጤንነት ጎጂ የሆነ ተግባር ሲፈፅም የተገኘ ሰው አካባቢው በመረጣቸው ዳኞች ቅጣት ይወሰንበታል።

የስካውት አባላቱን ሥራ የሚተችና ሥራው እንዳይሠራ እንቅፋት የሚሆን ማንኛውም ሰው በተመረጡት ዳኞች ቅጣትና ግሣፄ ይደርስበታል፡፡ በዚህም ምክንያት የቆሻሻ መጣያ የነበሩ ሥፍራዎች የጓሮ አትክልት ማልሚያ ሆነዋል። የቆሻሻ መጣያ ገንዳዎችና የመፀዳጃ ቤቶቹም በንፅህና ሊጠበቁ ችለዋል። ይህን በመሰለው አርአያነት ያለው የወጣቶቹ ተግባርም መንደሩ "ንፁህ" የሚል ስያሜ አግኝቷል።

**መልመጃ 4**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. የንፁህ መንደር ስካውቶች ተግባር ምን ትምህርት እንደሰጣችሁ ለጓደኞቻችሁ አካፍሏቸው::
2. የአካባቢያችሁ የፅዳት ሁኔታ ምን ይመስላል?
3. እንደ ንፁህ መንደር ስካውቶች በእናንተስ አካባቢ ምሳሌ የሆኑ ወጣቶች አሉ?



ሥዕል 5.4 ቆሻሻ ባግባቡ ካልተወገደ ለጤና ጠንቅ ይፈጥራል፡፡



ሥዕል 5.5 የጋራ መጸዳጃ ቤቶች ንጽሕናቸው የተጠበቀ መሆን አለበት

- ከሥዕሎቹ ምን ትማራላችሁ?
- በእናንተ አካባቢስ እንዲህ ዓይነት ችግር አለ?

ቆሻሻን በየቦታው መጣልና ማዝረክረክ በጤና ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከትላል፡፡ የቆሻሻ መጣያ አካባቢዎች በጽዳት ካልተያዙ ከቆሻሻው ላይ የሚነሱት ዝንቦች በአካባቢው ነዋሪ ላይ የጤና ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ያልተከተቡ ውሾች፣ ጅብና የመሳሰሉት አውሬዎችም በዚያ አካባቢ ስለሚርመሰመሱ ከፍ ያለ ጉዳት ሊከተል ይችላል። የመጸዳጃ ቤትን በጥንቃቄ ካለመያዝ የተነሳም በተላላፊ በሽታዎች ምክንያት የአካባቢው ነዋሪ ሊጎዳ ይችላል። እነዚህን መሰል ግዴለሽ ተግባራት እንዲታረሙም የአካባቢው ወጣቶች ከፍተኛ ተግባራትን ሊያከናውኑ ይችላሉ።

**መልመጃ 5**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።*

1. በአካባቢ መቆሸሸና የመፀዳጃ ቤትን በንፅህና ካለመያዝ የተነሳ ሊከሰቱ ስለሚችሉ ችግሮች በቡድን ተወያዩባቸው፡፡
2. በአካባቢያችሁ ግዴለሽነት የሚስተዋልባቸውን ጉዳዮች እያነሳችሁ በቡድን ተወያዩባቸው፡፡
3. «አካባቢዬን በንፅህና ስመጠበቅ የእኔ ድርሻ» በሚል ርዕስ አጭር ጽሑፍ በቡድን ፅፋችሁ አቅርቡ፡፡

## 5.3 በጐ ባህርያት፤

### 5.3.1 ማንኛውም አፍራሽ ተግባር መቃወም፣

"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም፣
ከክፉት ደግነት ሳይሻል አይቀርም።"
*(ሕዝባዊ ግጥም)*

- ይህ ሕዝባዊ ግጥም በጐ ባህርያትን እንድናዳብር ምን ትምህርት ይሰጣል?

**ታማኙ ውሻ፤**

አንድ አርሶ አደር በጣም የሚወደው ታማኝና በባህርይው የተመሰገነ ውሻ ነበረው። ይህ ውሻ የጌታውን ቤት ተግቶ ይጠብቅ ነበር። ሌሎች አራዊቶችም ግቢውንና ከብቶቹን እንዳይደፍሩ በንቃት ይከላከል ነበር። በዚሁ ውሻ ምክንያት የዚህን አርሶ አደር ቤት ሌቦች ሊደፍሩ አልቻሉም። ይህ ገበሬ በአንድ ወቅት ገንዘብ ቢቸግረው ለአንድ ባለጠጋ ሰው ውሻውን አሲዞ ገንዘብ ተበደረ። ብድሩን ከፍሎ እስኪያጠናቅቅም ውሻውን ለአበዳሪው አሳልፎ ሰጠው።

ያ ውሻ የጌታውን ችግር ተረድቶ የአበዳሪውን ቤትና ንብረት ልክ እንደ ቀድሞ አሳዳሪው ቤት በትጋት እየጠበቀና ከሌቦች እየተከላከለለት በታማኝነት ያገለግለው ጀመር። አንድ ቀን የአበዳሪው ልጅ በአልጋው ላይ ተኝቶ ሳለ አንድ ትልቅ እባብ በጣራው ላይ እየተምዘገዘገ መጣ። ውሻው የዚያን እባብ እንቅስቃሴ ይከታተል ኖሮ በፍጥነት ዘሎ እባቡን ቦጫጭቆ በመግደል ልጁን አዳነ።

የዚህን ውሻ መልካም ተግባር የተገነዘበው ሁለተኛው አሳዳሪ በውሻው ድርጊት ተደስቶ ወደ ቀድሞው ጌታው አመስግኖ ሊመልሰው ወሰነ። በአንገቱ ላይ የምሥጋና ቃል ጽፎ በማሰርም ውሻውን መርቆ ሰደደው። ነገር ግን ውሻው በሌብነቱ ያጋለጠውና የውሻውን ባለቤት የማይወድ አንድ ሰው ውሻውንና ጌታውን ለማጣላት ተንኮል በመጠንሰስ በውሻው ላይ ጉዳት እንዲደርስ አንድ ዘዴ ፈጠረ።

ወደ ጌታው ቤት ቀድሞ በመሄድም ውሻው ለሁለተኛው ጌታው እንደማይታዘዝና ጌታ ውም በጣም ስለተቸገረ ወደ እርሱ ሊመልሰው እንደሚያስብ ተንኮሉን አቀነባብሮ ነገረው። የውሻው ጌታም በውሻው ድርጊት በጣም አዝኖ የተበደረውን ገንዘብ ለመመለስ ወደ አበዳሪው ቤት እየገሠገሠ ሳለ ውሻው ወደ እርሱ እየሮጠ ሲመጣ መንገድ ላይ ተገናኙ። ውሻው ጌታውን እንዳየ በደስታ እየሮጠ በመ ቅረብ ፍቅሩን እንደወትሮው ይገልፅለት ጀመር። ነገር ግን ጌታው በሰማው የተንኮል ወሬ ተበሳጭቶ ውሻው ከአበዳሪው ቤት አም ልጦ የመጣ ስለመሰለው በያዘው ዱላ አንዴ ቢያሳርፍበት ውሻው ወዲያው ሞተ።

ገበሬው የውሻውን ሬሣ ቆሞ በሀዘን ሲያስ ተውል በአንገቱ ላይ የታሰረ ወረቀት አገኘ። ወረቀቱን ገልጦ ሲያነብም የውሻውን በጐ ተግ ባር የሚዘረዝር የምሥጋና ቃላት የተጻፈበት ደብዳቤ መሆኑን ተረዳ። ስለ ውሻው መልካም ባህሪም ባለፀጋው ሰው የገበሬውን ዕዳ እንደ ማረው ይገልጻል። የውሻው ጌታ ምሥጢሩን ሲረዳ ስቅሰቅ እያለ በማልቀስ በሥራው ተጸጸተ።

*(ከበደ ሚካኤል፣ ተረትና ምሣሌ፣ 2ኛ መጽሐፍ፣ 6ኛ ዕትም 1994ዓ.ም ሊዚህ ክፍል እንዲመጥን ተደርጐ የተወሰደ)*

**መልመጃ ፩**

*ከላይ የቀረበውን ታሪክ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

? 
1. የውሻው መልካም ተግባር የተገለጠው እንዴት ነው?
2. ያስ አድልዎ የጌታውንና የአሳዳሪውን ቤት በእኩልነት ስላገለገለው ውሻ መልካም ተግባር ምን ትምህርት አገኛችሁ?
3. ውሻው ሊሞት የቻለው ለምን ነበር?
4. ውሻ እዲህ ሴባን በማጋለጥና መልካም ተግ ባር የሚያሳይ ከሆነ ከእናንተስ ምን ምን ዓይነት መልካም ተግባርና ባህርያት ይጠበ ቃሉ?

በጐ ባህርያት የመልካም ሰብዕና ማጣፈጫ ቅመሞች ናቸው። በጐ ባህርያት በቅድሚያ የሚጠቅሙት ራስን ነው። በበጐ ባህርይው የሚመሰገን ሰው ሁልጊዜም የህሊና እርካታ ይጐናፀፋል።

የታመመ ሰውን መጠየቅ፣ የተቸገረን መር ዳት፣ ተስፋ የቆረጠን ሰው ማፅናናት፣ ለታላ ላቆችም ሆነ ለታናናሾች ተገቢውን አክብሮት መስጠት በውዴታ ብቻ የምናደርገው ሳይሆን ሰብአዊ ግዴታችንም ጭምር ነው። ለራሳችን የህሊና እርካታ ብለን የምናሳያቸው በጐ ባህርያት ለሌሎችም ሊጠቅሙ ይችላሉ፡፡

በጐ ባህርያት ለቤተሰባችን አባላት፣ ለጐረቤቶ ቻችን፣ ለአካባቢያችን፣ ለትምህርት ቤት ጓደኞ ቻችንና ለጠቅላላው ማኅበረሰብ ማሳየት የአስ ተዋይ ሰው መለያ ባህርያት ናቸው። በጎ ባህ ሪያት የሌላቸው ሰዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸው ተቀባይነት እጅግ አናሳ ይሆ ናል።

ሌሎችን ሊጐዱ የሚችሉ አፍራሽ ተግባራ ትንና አድሎአዊ አሠራርን በፅናት መቃወ ምም የበጐ ባህርይ ሌላው ገጽታ ነው።

ለምሳሌ በሌብነት ላይ የተሰማራ ሰው በአካ ባቢያችን መኖሩን እያወቅን በቸልታና በይሉ ኝታ ብናልፍ እኛም የጥፋቱ ተባባሪዎች መሆ ናችንን መረዳት ይገባናል።

አንድ ሰው በሌባ ሲጠቃ እያየን እንዳላየ ሆነን ብናልፍ እኛንም ነገ ተመሳሳይ ችግር ቢገጥ መን የሌላውን ሰው ትብብር ለመጠየቅ እን ዴት እንችላለን?

**መልመጃ ፯**


*የሚከተለውን ሠንጠረዥ በደብተራችሁ ላይ በመገልበጥ ልታዳብሯቸው የሚገቡ በጐ ባህሪያት ንና ልታስወግዳቸው የሚገቡ አፍራሽ ተግባራትን እየለያችሁ አመልክቱ፡፡*

| ልናዳብራቸው የሚገቡ በጐ ባህርያት (ተግባራት) | ልናስወግዳቸው የሚገቡ አፍራሽ ተግባራት (ባህሪያት) |
|---|---|
| በቤት ውስጥ፣<br>ምሳሌ፣<br>1.ለታላላቆች መታዘዝ።<br>2.<br>3.<br>በትምህርት ቤት ውስጥ፣<br>ምሳሌ፣<br>1. ሰዓትን አክብሮ በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት።<br>2.<br>3.<br>በአካባቢዬ፣<br>ምሳሌ፣<br>1. አርዓያነት ያለው ተግባር መፈጸም<br>2.<br>3. | በትምህርት ቤት ውስጥ<br>ምሳሌ፣<br>1. የጋራ መገልገያ የሆኑ ንብረቶችን የሚያበላሹትን ተማሪዎች ፊት ለፊት አለማጋለጥ።<br>2.<br>3.<br>በአካባቢዬ፣<br>ምሳሌ፣<br>1. ለአካባቢ ንጽህና ችግር የሚፈጥሩትን በግልጽ አለመቃወም።<br>2.<br>3.<br>በቤት ውስጥ<br>ምሳሌ፣<br>1. በውሸት የቤተሰብ አባላትን ማጋጨት<br>2.<br>3. |

## 5.4 ድህነትን ማስወገድ፣

### 5.4.1 ድህነትን ለማስወገድ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አስፈላጊነት፣





ሥዕል 5.6 ተግቶ በመሥራት ድህነትን ማስወገድ ይቻላል፡፡

- *አንዱን ሥዕል ከሌላው ጋር በማነፃፀር ምን መልዕክት እንደሚያስተላልፉ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩበት?*

### የእፎይታ ሰፈር ልጆች፤

ዳምጤ፣ ቦንገር፣ ረዳኢና ሳጉሬን ያስተዋወቃቸው መጥፎ አመላቸው ነበር። ሁሉም ወጣቶች፣ ይሠርቃሉ፣ ይሰክራሉ፣ ለተለያዩ ሱስ አስያዥ ዕፆችም ተገዢዎች ነበሩ።በዚህም ያልተገባ ባህርያቸው ምክንያት ቤተሰቦቻቸውና የአካባቢያቸው ሰዎች እጅግ ተማረው ነበር። በየጊዜው በፖሊስ እየተያዙ ስለሚታሠሩም ከሰፈር በጠፉ ጊዜ ሁሉ እንዳምጤ የት ሄዱ ሲባል፤ "ካምቦሎጆ ገብተዋል" ይባል ነበር።

ካንቦሎጆ የሚሉት እስር ቤትን ነው። በዚህ ዓይነት ሕይወት የእድሜያቸውን ግማሽ ከኖሩ በኋላ በአንድ ወቅት ቢ.ርቢ.ርሶ በሚባል በአካባቢው አርአያነት በነበረው ወጣት አማካይነት ሕይወታቸው ተለወጠ። ቢ.ርቢ.ርሶ ባደረገው ያላሰለሰ ምክርም አራቱም ወጣቶች ከተለያዩ ሱሶቻቸው ሙሉ ለሙሉ ተላቀቁ። መንግሥት በተለይ ለወጣቶች በነደፈው የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑም በቀበሌአቸው ጽ/ቤት አማካይነት የመኪና እጥበት ሥራ እንዲጀምሩ ሁኔታዎች ተመቻቹላቸው።

ዳምጤ፣ ቦንገር፣ ረዳኢና ሳጉሬ የመኪና እጥበት ሥራቸውን በከፍተኛ ታማኝነትና ትጋት ስለሚያከናውኑ በደንበኞቻቸው ዘንድ መወደድና ዝና የተጐናፀፉት በአጭር ጊዜ ነው። በሥራቸውም ስኬታማ ስለሆኑ በርካታ ሃብት ለማከማቸት ችለዋል። አካባቢውን ያስቸገሩ ሌሎች ጓደኞቻቸውንም ሥራ እየሰጧቸው ሕይወታቸውን መለወጥ ችለዋል።

አልፎ ተርፎም አስር ልጆችን ከጐዳና ሕይወት በማውጣት ለልብሳቸው፣ ለምግባቸውና ለትምህርታቸው ተገቢውን በጀት በመመደብ እያስተማሯቸው ይገኛሉ። እነዚህ አራት ጓደኞሞች በአቋቋሙት ድርጅት ስም መነሻነትም ቀደም ሲል አካባቢው የሚታወቅበት ስም ተለውጦ "እፎይታ" የሚል ስያሜ ተሰጠው።

*(በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በ1999 ዓ.ም ተደጋግሞ ከቀረበ የወጣቶች ታሪክ ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ 8**

***ከላይ የቀረበውን ታሪክ መነሻ በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

?
1. ከዳምጤና ጓደኞቹ የሕይወት ለውጥ በኋላ የሕይወት ለውጥ ምን በጐ ውጤቶች ተገኙ?
2. ቀደም ሲል ወጣቶቹ በነበራቸው ዓይነት የተበላሸ ሕይወት ለመለወጥ ምን መደረግ አለበት?
3. ድህነትን ከሀገራችን ለማጥፋት የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ያላቸው ጠቀሜታ ምን ሊሆን እንደሚችል በበድን ተወያዩበት፡፡

ሀገራችን የበርካታ የተፈጥሮ ሀብትና የታሪካዊ ቅርሶች ባለቤት ነች። እነዚህን መሰል ታሪካዊና ተፈጥሯዊ መኩሪያዎች ቢኖሩንም በአንጻሩ ግን ብዙ ችግሮች አሉብን።

የተፈጥሮ ሀብት ቢኖረንም ለሥራ የተነቃቃና ለአዳዲስ ፈጠራ የተነሣሣ በቂ የሥራ ኃይል መፍጠር ስላልተቻለ ሀገራችን በዓለም ፊት በድህነት ለመታወቅ በቅታለች። አስከፊው የድህነታችን ገጽታም በልዩ ልዩ አቅጣጫ ሀገሪቱንና ዜጐቿን ሲያሽማቅቅ ኖሯል። ይህንን ለዘመናት ተከትሎን የመጣውን ድህነት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ታግሎ ለማሸነፍ መንግሥት በርካታ ውጤታማ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ዘርግቷል።

ለልማት ፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎቹ ተፈፃሚነትና ውጤታማነት እያንዳንዱ ዜጋ ተግቶ በመማርና በመሥራት ሀገሩን የማበልፀግ ኃላፊነት አለበት፡፡ መደበኛ ኃላፊነትን መወጣት ብቻ ሳይሆን ለበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት ራስን ማሳተፍም ድህነትን ለመቅረፍ አንዱ ዘዴ ነው።

"የመንግሥት ጉዳይ ነው" ከማለት ይልቅ ጉዳዩ ይመለከተኛል ብሎ የድርሻን መወጣት የመንግሥትን የልማት ፖሊሲዎቹንና ስታራቴጂዎቹን ውጤታማነት ይበልጥ ያጐለብታል፡፡

**መልመጃ 9**

***ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡***

?
1. በቤተሰብ፣ በአካባቢና በሀገር ደረጃ የድህነት መገለጫ ሊሆኑ በሚችሉ ነገሮች ላይ በቡድን ተወያዩ፡፡




ሥዕል 5.7 የበጐ ተግባር የዜጎች የውዴታ ግዴታ ነው

- ሥዕሎቹ ምን መልዕክት ያስተላልፋሉ?

በቤት፣ በአካባቢና በትምህርት ቤት ውስጥ የእኛን በጐ ፈቃደኝነት የሚጠይቁ በርካታ ተግባራት አሉ። በሚከተለው ሠንጠረዥ ውስጥ ጥቂቱን ለማመልከት ተሞክሯል።

| በቤት ውስጥ | በአካባቢ | በትምህርት ቤት ውስጥ |
|---|---|---|
| 1. የወላጆችን ትዕዛዝ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን አስቀድሞ ዕቅድ በመንደፍ የግልና የጋራ ኃላፊነትን መወጣት፡፡<br>2. የመኖሪያ ቤትንና ግቢን በንፅህና መጠበቅና በራስ ፈቃድ ውበትን መፍጠር፡፡ | 1. ረዳት የሌላቸውን፣ አቅመ ደካሞችንና አረጋዊያንን መንከባከብ፡፡<br>2. ከሠፈር ጓደኞች ጋር በመሆን የአካባቢን ፅዳት መጠበቅ፡፡<br>3. ለጐረቤትና ለዘመድ አቅም የፈቀደውን ግልጋሎት መስጠት፡፡ | 1. የትምህርት ቤታችን የስነዜጋ እና ስነምግባር ክበብ አባል በመሆን ማገልገል፡፡<br>2. የትምህርት ቤታችን ግቢ ጽዳትና ውበት እንዲጠበቅ መንከባከብ፡፡<br>3. ወደ አልተገባ ባህርይ እየሄዱ ያሉትን ተማሪዎች በመምከር የባህርይ ለውጥ እንዲያመጡ መርዳት፡፡ |

**መልመጃ 10**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. በበጐ ፈቃደኝነት አገልግሎት በአካባቢያችሁና በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ ብትሳተፉ ያስደስቱናል የምትሏቸውን ተግባራት ዘርዝሩ፡፡
2. ስለሰው ልጆች የበጐ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት በታሪክ ውስጥ ተጠቃሽ ከሆኑ ሰዎች መካከል ስለ አንዱ ከሰዎች ጠይቃችሁ ወይንም ከመጻሕፍት አንብባችሁ ለጓደኞቻችሁ ታሪኩን አካፍሏቸው፡፡

## 5.5 ዜግነት፤

### 5.5.1 ዜግነት የሚገኝባቸው መንገዶች፣

- ዜግነት ማለት ምን ማለት ነው? ቀደም ሲል የተማራችሁትን ትምህርት በማስታወስ ስለ ዜግነት የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

ዜግነት በመወለድ ወይንም በሕግ የሚገኝ መብት ተብሎ በሁለት ይከፈላል። አንድ ሰው ከወላጆቹ አንዱ ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ከሆኑ ከኢትዮጵያዊ ዜጋ በመወለዱ ብቻ የዜግነት መብት ጥቅም ያገኛል። ኢትዮጵያዊ ወላጁ/ወላጇ በውጭ ሀገር ቢኖር/ብትኖር እንኳ የዜግነት መብቶቹን ከማግኘት የሚከለክለው ነገር የለም።

ዜግነት የሚገኝበት ሁለተኛው መንገድ በሕግ የሚገኝ ዜግነት በመባል ይታወቃል። አንድ የውጭ ሀገር ዜግነት ያለው ሰው በራሱ ፈቃድ የኢትዮጵያዊነት ዜግነት እንዲሰጠው ለመንግሥት ጥያቄ ሲያቀርብና የሀገሪቱ ሕግ የሚጠይቀውን ሁኔታ መሟላቱ ሲረጋገጥ የኢትዮጵያዊ ዜግነት መብት ሊያገኝ ይችላል።

**መልመጃ 11**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ።***

1. በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ስንት ዓይነት የዜግነት ማግኛ መንገዶች አሉ?
2. በመወለድ የሚገኘው የዜግነት መብት በሕግ ከሚገኘው የዜግነት መብት በምን ይለያል?
3. ከኢትዮጵያዊያን ወላጆች የተገኘ አንድ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ እየኖረ ኢትዮጵያዊ ዜግነት አልፈልግም ማለት ይችላል?

## 5.6 ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ፤

### 5.6.1 የሰንደቅ ዓላማና የብሔራዊ ዓርማ ትርጉም፣



ሥዕል 5.8 የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

- በሰንደቅ ዓላማችን ላይ ያለው ብሔራዊ ዓርማ ምን መልዕክት ያስተላልፋል?

**ይህች ሰንደቅ ዓላማ፤**

የአብሮ መኖር ሲሳይ የድል ብሥራት ዜና፣
የሀገራችን ኩራት የሕዝቦች ልዕልና፣
ሰንደቅ ዓላማችን ሕያው ባለ ዝና፣
ዘለዓለም አዲስ ናት አታውቅም እርጅና::
ተስፋ ለምለሚቱ አበባና ፍሬ፣
ፍቅር መሥዋዕትነት የውበት ዝማሬ::
ማነው የማያለቅስ ከደስታ ብዛት፣
ማነው የማይኩራ በሀገሩ ነፃነት?
ሰንደቅ ዓላማችን ስታገኝ ከፍታ፣
ማን ይቆጣጠራል የልቡን ትርታ?
*(ታድለ ገድሌ ፀጋዬ፣ ትንቅንቅ፣ 1993 ዓ.ም)*

**መልመጃ 12**

***ግጥሙን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ምንድን ነው?
2. በግጥሙ ውስጥ የሰንደቅ ዓላማችን ቀለም ትርጉም የተገለፀው እንዴት ነው?
3. ሰንደቅ ዓላማችን በድል የሚውለበለብበት ወቅት የተመልካቹ ስሜት ምን እንደሚመስል የተገለፀው እንዴት ነው?

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ ከመሐል ብጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በመሐሉ ብሔራዊ ዓርማ እንደሚኖረው በሕገመንግሥታችን አንቀፅ3 ላይ በዝርዝር ተቀምጧል:: ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው በአግድም ይቀመጣሉ:: የሰንደቅ ዓላማችን ሦስቱ ቀለማት የራሳቸው ትርጉም አላቸው:: አረንጓዴው የሚወክለው ልምላሜንና ብልፅግናን ሲሆን፣ ብጫው ተስፋንና ብሩህ ዘመንን ያመለክታል:: ቀዩ ደግሞ ጀግንነትንና መስዋዕትነትን ይወክላል::

ከሰንደቅ ዓላማው መሃል ለመሃል በሰማያዊ መደብ ላይ የተቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ እኩል መጠን ባላቸው መስመሮች የተሳለ የኩከብ ቅርፅ ነው:: ከኩከቡ የሚፈነጥቁ ነፀብራቆችም በጉልህ ይታያሉ:: ኩከቡ የተሳለው በወርቃማ ቀለም ሲሆን የሚወክለው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ሃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ፅኑ ተስፋ ነው::

**መልመጃ 13**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. የኢትዮጵያን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ሙሉ ቀለማት ዘርዝሩ::
2. የብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማችን ቀለማትን ትርጉም አንድ በአንድ አብራሩ::
3. ብሔራዊ ዓርማችን የያዘውን ትርጉም በአጭሩ ግለፁ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የግልና የቡድን መብቶች መከበር፣ አድሎአዊ አሠራር እንዳይኖር የግልን አስተዋጽኦ ማበርከት፤ የአካባቢንና የሀገርን ታሪክ ጠንቅቆ ማወቅ ለሀገር ፍቅር መጐልበት በእጅጉ ይረዳል፡፡ ጉጂና አፍራሽ ተግባራትን በመዋጋትም የሀገር ፍቅርን ማዳበር ይቻላል። በተለይም ለጋራ መገልገያ ንብረቶች ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ከእያንዳንዱ ዜጋ ይጠበቃል። ከሰብዓዊ መገለጫችን አንዱ በጐ ባህርያትን በማሳየት ምሣሌነት ያለው ተግባር ማከናወን ነው። ነገሮችን በምንችገረኝነትና አያገባኝም በማለት ብናልፋቸው ዞሮ ዞሮ ጉዳቱ በእኛም ላይ ሊንፀባረቅ ይችላል።

ሀገራችን ከምትገኝበት የድህነት አዘቅት ውስጥ ለመውጣት እያንዳንዱ ዜጋ ማበርከት የሚገባው አስተዋጽኦ አለ። መንግሥት ለነደፋቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተፈጻሚነት ዜጐች ሁሉ የአቅማቸውን ማበርከት ይጠበቅባቸዋል። ከቤት፣ ከአካባቢና ከትምህርት ቤት ጀምረን ኅብረተሰቡን በበጐ ፈቃደኝነት ማገልገል የሰብዓዊነታችንና የዜግነታችን ግዴታ ነው።

በመወለድም ሆነ በሕግ የሚገኝ ዜግነት የሚጠይቃቸውን ግዴታዎች በአግባቡ በመፈፀም ተገቢውንም የግልና የቡድን ግዴታ መወጣት የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታም ኃላፊነትም ነው። ከዜግነት ኃላፊነቶች አንዱ ለብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማና ለብሔራዊ መዝሙር ተገቢውን ክብር መስጠት ስለሆነ ሁሉም ዜጋ ይህንኑ መፈጸም ይጠበቅበታል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

*መልክዓምድር፣* የመሬት ተፈጥሮአዊ ገጽታዎች።
*አድልዎ፣* ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ሌላውን ሰው ለመጥቀም የሚፈፀም ተግባር።
*የታሪክ መገለጫዎች፣* የአንድን ሀገር ሕዝብ ታሪክና ባህል የሚገልፁ ቋሚ መረጃዎች።
*ሙስና፣* ሌላውን ሰው ወይንም ራስን ለመጥቀም የሚፈፀም ሕገ ወጥ ተግባር።
*ሕዝባዊ ግጥም፣* ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ የመጡ ደራሲያቸው የማይታወቁ ግጥሞች።
*ፖሊሲና ስትራቴጂ፣* ለአንድ ተግባር አፈፃፀም መንግሥት የሚያወጣው ሕግ፣ ደንብና መመሪያ
*ዕሴት፣* አንድ ማሕበረሰብ በጠቃሚነቱ የያዘው በጐ ልማድ ወይንም ባህል።
*ስካውት፣* በበጐ ፈቃድ አካባቢውንና ነዋሪውን በነፃ የሚያገለግሉ ወጣቶች ቡድን።
*ዐውደ ርዕይ (ኤግዚቢሽን)፣* በይፋ ለሕዝብ ዕይታ የሚቀርቡ ማናቸውም ታሪካዊ ቅርሶች፣ የንግድ ሸቀጦች ወይም የምርምርና የፈጠራ አዳዲስ ግኝቶች።
*ስኬታማ፣* በተግባሩ ወይም በሥራው ውጤታማ የሆነ።
*ስብዕና፣* የሰውን ልጅ ከሌላው ፍጡር የሚለየው ተፈጥሮአዊ ባህርይ።

## የምዕራፍ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ።***

***I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆነ «ሀሰት» በማለት መልሱ።***

1. ጉታችና ጊዜ ያስፈባቸው ልምዶች ለዕድገት ፀር ናቸው።
2. ለበጐ አገልግሎት ተግባራት መመሪያ መስጠት የሚገባው መንግሥት ብቻ ነው።
3. መንግሥት የሚያወጣቸው የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በመንግሥት መ/ቤቶች ብቻ ነው።

***II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡***

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ | ሀ. ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ። |
| 2. የሀገር ፍቅር መገለጫ፣ | ለ. መልክዓ ምድር። |
| 3. ሙስና፣ | ሐ. ለራስ ወይንም ለሌላው ጥቅም ኢ-ፍትሐዊ ተግባር መፈጸም። |
| 4. ዜግነት፣ | መ. ጐጂ ልማዳዊ ድርጊት። |
| 5. በምክንያት ያልተደገፈ ጭፍን አስተያየት፣ | ሠ. ልዩነት መፍጠር። |
| | ረ. ሕዝብን ማክበር። |
| | ሰ. የአንድ ሀገር ሕጋዊ አባል መሆን። |
| 6. አድልዎ፣ | ሸ. አፍራሽ ተግባር። |

***III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡***

1. ሀገሬን እወዳለሁ ከሚል ዜጋ ከሚጠበቁ ተግባራት መካከል ይጠቀሳል፤
   - ሀ. የሕዝቡን ባህልና ቋንቋ ማክበር፣
   - ለ. የሥራ ተነሳሽነት መኖር፣
   - ሐ. አድሎአዊ ያለመሆን፣
   - መ. ሁሉም መልስ ሊሆኑ ይችላሉ።
2. ለሀገራችን ድህነት እንደምክንያት ሊጠቀስ ከሚገባው መካከል አንዱ ነው፤
   - ሀ. የተፈጥሮ ሃብት እጦት፣
   - ለ. የውሃ እጥረት፣
   - ሐ. የሥራ ባህል ያለመዳበር፣
   - መ. የርዳታ መቀነስ።
3. የጋራ መገልገያ ንብረቶችን መንከባከብ የሚገባን ለምንድን ነው?
   - ሀ. ሕጉ ስለሚያስገድደን፣
   - ለ. ጉዳቱ ለእኛም ስለሚተርፍ፣
   - ሐ. የሀገር ሀብት እንዳይባክን፣
   - መ. ሁሉም መልስ ሊሆን ይችላል።
4. የግዴለሽነት መገለጫ ሊሆን የማይችለው የትኛው ነው?
   - ሀ. ቆሻሻን በየቦታው ማዝረክረክ፣
   - ለ. መፀዳጃ ቤትን ያለአግባብ መጠቀም፣
   - ሐ. የትምህርትን ቤት የጋራ መገልገያዎች በአግባቡ መጠቀም፣
   - መ. መልሱ አልተሰጠም።

5. ከሚከተሉት አንዱ በበጐ ፈቃድ የምንሰጠው አገልግሎት ነው።
   ሀ. ለወላጆችና ለመምህራን በመታዘዝ ግዴታችንን መወጣት፣
   ለ. የትምህርት ሰዓትን በአግባቡ መጠቀም፣
   ሐ. አረጋዊያንና አቅመ ደካሞችን መንከባከብ፣
   መ. ለሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ተገዢ መሆን።
6. ሌባንና አድሎአዊ አሠራርን ማጋለጥ፤
   ሀ. ለፖሊስ ብቻ የተተወ ድርሻ ነው፣
   ለ. የፍትሕ አካላትን ብቻ የሚመለከት ነው፣
   ሐ. የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ሊሆኑ ይችላሉ።

## IV የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::

1. በመወለድ ወይንም በሕግ የሚገኝ መብት______________ ይባላል።
2. ሀገርና ሕዝብን የሚወክል መገለጫ ምልክት____________ ተብሎ ይታወቃሉ።

## V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ከዜጎች ሁሉ ከሚጠበቁ መብትና ግዴታዎች መካከል ሁለቱን ጥቀሱ::
2. ጉጂና አፍራሽ ተግባራት በኢኮኖሚ ዕድገት ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖ በአጭሩ አብራሩ::

# ምዕራፍ ስድስት

# የኃላፊነት ስሜት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- ዜጐች የኃላፊነት ድርሻን በወቅቱ በታማኝነትና በብቃት መወጣት ግዴታ እንዳለባቸው ትረዳለህ/ ትረዳለሽ::
- የተፈጥሮ ሀብቶችንና ታሪካዊ ቅርሶችን ከውድመት መጠበቅ የእያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት መሆኑን ትገነዘባለህ/ ትገነዘቢያለሽ::

## 6.1 ቃል ኪዳን፤



ሥዕል 6.1 በሕክምና ሙያ ተመራቂ ወጣት ሀኪሞች ቃለ መሀላ ሲፈጽሙ

- በሥዕሉ ላይ የሚታዩት ወጣት ሀኪሞች ምን እያደረጉ ነው?
- ቃለ መሀላ መፈፀም ማለት ምን ማለት ነው?

### ዘመናዊ አርበኛ፤

አበራ ደጉ በምህንድስና ሙያ ተመርቆ ሥራ ከመጀመሩ በፊት አባቱ አርበኛው ደጉ እንደሳቸው አርበኛ እንዲሆን መክረውታል:: አበራም የአባቱን እምነትና አመለካከት ሁል ጊዜ ያደንቃል:: "ሀገር እናት ነች:: እናቱን በሀቅ የማያገለግል ዜጋ ከሰው አይቆጠርም::" የሚሉትን አባባላቸውን ያምንበታል::

አባቱ ሀገራቸውን ከጠላት ለመከላከል ከጣሊያን ጋር የተፋለሙ ጀግና ናቸው:: አበራም የሚወዳቸውን አባቱን ምኞት ለመፈፀም በሙያው ራሱን አዘጋጀ:: በማዕረግ ከተመረቀ በኋላ የመንገድ ሥራዎች ተቆጣጣሪ ሆኖ ተቀጠረ::

በአንድ ወቅት የመንገድ ጥራት ቁጥጥር ሲያደርግ የተሠራው ሥራ ከደረጃው የወረደና ማጭበርበር የተሞላበት ሆኖ አገኘው:: መንገዱን ሊሠራ ለተዋዋለው ድርጅት መንገዱን አፍርሶ እንደገና እንዲሠራ ውሳኔውን አስታወቀ:: ሆኖም የድርጅቱ ኃላፊ መንገዱ ጥራቱን ባልጠበቀ ሁኔታ መሥራቱ ሳያሳፍረው አበራን በመደለል ዘመናዊና እጅግ ውድ የሆነ አዲስ መኪና ሊያበረክትለትና ውሳኔውን ሊያስለውጠው ተዘጋጀ::

በዚሁ መሠረት የመኪናዋን ሞዴልና ቀለም የሚገልጽ ወረቀትና የመኪናዋን ቁልፍ በፖስታ አድርጐ በቀጠሮ ሲገናኙ ከብዙ የማግባቢያ ቃላት በኋላ ሰጠው:: አበራም ከፍቶ ካየ በኋላ የድርጅቱን ሥራ መሪ በትዝብት በመመልከት "ለመሆኑ ኢትዮጵያዊ ነህ?" ብሎ በመጠየቅ ፖስታውን ወርውሮለት ሔደ:: ስግብግቡም ሥራ መሪ እቅዱ መክሸፉን እንደተመለከተ ለበቀል ተነሳሳና አበራን በአሳቻ ሥፍራና ሰዓት በመኪና አስገጨው:: ሆኖም የወንጀሉ ፈጻሚ በፖሊስ ክትትል በሚያስተማምን ማስረጃ ታወቀ::

አበራ በሕክምና ላይ ሆኖ ሁኔታዎችን ሲያስታውስ ለአባቱ የገባውን ቃል ማክበሩ ከምንም ነገር በላይ የህሊና እርካታ ሰጠው:: አባቱም እናት ሀገሩን በታማኝነት ለማገልገል ቁርጠኛ አቋም በመያዙ አመሰገኑት:: አበራም ሌብነትን የሚዋጋ አርበኛ መሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሰፊው ተወራ::

የሙያ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በተወጡ ሐኪሞች እርዳታ በአጭር ጊዜ ውስጥ ድኖ ሥራውንም ቀጠለ:: ከዚህ ተግባሩ በመነሳት "ዘመናዊ አርበኛ" በሚል ስያሜ እየተጠራ ክብርና መወደድን አተረፈ::

መልመጃ 1

*ከላይ የቀረበውን ታሪክ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. አበራ በስጦታ ስመደለል የሞከረው ሰው ተገ ባር በዕድገት ሳይ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድነው?
2. አርበኝነት ምንድነው? በምን በምን ሁኔታ ይገለጻል?
3. አበራ «ዘመናዊ አርበኛ» የተባለው በምን ምክንያት ነው?

***ቃል ኪዳን*** አንድን ነገር በታማኝነትና በሀቀኝነት ለመሥራት ለራሳችን ወይም ለሌሎች የምንሰ ጠው መተማመኛ ነው። ቃል መግባት ከፍተኛ የኃላፊነት ስሜትንና የሞራል ግዴታን ይጠይ ቃል። ስለዚህ ቃል ከመግባታችን በፊት ቃላችንን ለመጠበቅ አቅምና ችሎታችንን መፈተሽ ተገቢ ነው። ያልታሰበበት ቃል ኪዳን ተፈጻሚነት ስለማይኖረው አለመታመንን ያስከትላል። ክብር ንም ያሳጣል። በተጨማሪም ተገቢ ያልሆኑ ምክ ንያቶችን በማቅረብ ይቅርታ ወደ መጠየቅ ያራ ምዳል።

ስለዚህ በተማሪነት ጊዜያችሁ ለራሳችሁ፣ ለቤተ ሰባችሁ፣ ለሌሎች ወገኖችም ቢሆን፣ ቃል ኪዳን ስትገቡ ከአቅምና ከችሎታ በላይ እንዳይሆን መጠ ንቀቅ ያስፈልጋል። ቃልን አለማክበር ቃልአባ ይነት ነውና። ማድረግ የምትችሉትን ደግሞ በቁርጠኝነትና በታማኝነት ማከናወን ተገቢ ነው። ይህም ኃላፊነትን የመወጣት ትክክለኛ ሂደት ነው።

ቃልኪዳን መግባትና ቃልን ማክበር በቤተሰብ ሕይወት ውስጥ ይጀምራል። ትምህርትን በሥ ርዓት መማርና በጥሩ ውጤት መራመድ ቃልኪ ዳንን መወጣትና የቤተሰብን ምክርና መመሪያ አክብሮ መቀበል ነው። አቅምና ችሎታ በፈቀደው መጠን የቤት ውስጥን ሥራ ማገዝም ለቤተሰብ ፍቅርና አክብሮት ከመግለጽ ባሻገር ኃላፊነትን የመወጣት ተግባር ነው።

መልመጃ 2

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ቃል ኪዳን ምንድነው?
2. ተፈጻሚነት የሌለው ቃል ኪዳን ማለት ምን ማለት ነው?
3. ቃልኪዳኑን በተግባር የፈጸመ ግለሰብ በኅብረተ ሰቡ ውስጥ የሚኖረው ሥፍራ ምንድነው?

## 6.2 ቅንነት፣ ታማኝነትና ሀቀኝነት፤

- ቅንነት ምንድንነው?
- ታማኝነትና ሀቀኝነት የሚገለጠው እንዴት ነው?

### ታማኙ ገንበኛ፤

የጉልበት ሥራ በመሥራት የሚኖር አንድ ላብ አደር ግንብ ሲገነባ ብዙ ሰነዶችና ብሮች ያሉ በት ቦርሳ ወድቆ በማግኘቱ ደነገጠ። ቦርሣውን አገላብጦ ሲመለከት ንብረትነቱ የቀጠረው ግለሰብ መሆኑን አወቀ። ላብአደሩም በዚያ ሰዓት አሠሪ ው የደረሰበት ብስጭትና ጭንቀት ታሰበውና አዘነለት። መመለስ እንዳለበትም ወሰነ።

በመቀጠልም ብዙ ብር ያለበት ቦርሣ ማግኘቱን ለጓደኛው ነግሮ ምን ማድረግ እንዳለበት ጠየ ቀው። ጓደኛውም ሊያገኝ የሚችለውን ልዩ ልዩ ጥቅሞች ዘረዘረለት። ግንበኛው ግን በቀረበለት ሀሳብ አልተስማማም። አስቀድሞ ባቀደው መሠ ረት ንብረቱን ለባለቤቱ ሰጠው። ባለንብረቱም የግንበኛውን የታማኝነቱን ጽናት በማየት ሰነዶ ቹን ብቻ ወስዶ ገንዘቡን ሸለመው። በማግስቱም የግንባታ ንብረቶች ኃላፊና ተቆጣጣሪ አድርጐ ሾመው።

መልመጃ 3

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ግንበኛው ንብረቱን ለባለቤቱ በመመለሱ ያገኛቸውን ጥቅሞች ግለፁ።
2. የግንበኛው ድርጊት ምንን ያስተምራል?
3. ታማኝነት የሚያኮራ የባህርይ ሀብት ነው፤ አይደለም? ማብራሪያ ስጡበት።

***ቅንነት፣ታማኝነትና ሀቀኝነት፣*** የሚገለፀው በሥራ ነው። ሥራም፣ ማኅበራዊ ባህርይ አለው። አንድ ሥራ ከውጤት እስኪደርስ የብዙ ሰዎች እውቀ ትና ጉልበት እንዲሁም ጊዜ ይከፈልበታል። እያ ንዳንዱ ሰው የድርሻውን ተግባር በታማኝነት፣ በቅንነትና በሀቀኝነት ካከናወነ ውጤቱ ብዙ ጥቅም ያስገኛል። ለምሳሌ፣ አንድ የመኪና ሾፌር የመ ኪናውን ደህንነት ፈትሾ፣ ፍጥነቱን ተቆጣጥሮ፣ መንዳቱ ሕይወትንና ንብረትን የማዳን ታላቅ ኃላፊነትን መወጣቱ ነው። ገበሬውም በወቅቱ አርሶና አምርቶ ለተጠቃሚው የማቅረብ የኃላ ፊነት ድርሻ አለበት። ማንኛውም ባለሙያም

የሙያው ተጠቃሚዎችን በቅንነት ማገልገል የሚጠበቅበት ተግባር ነው:: በዚህ ሁኔታ ሰው ሁሉ በያዘው ማንኛውም ዓይነት ሥራ በቅን ነት፣ በሀቀኝነትና በታማኝነት ከሠራ የዜግነት ግዴታውን ተወጣ ማለት ነው::

ኃላፊነትን በቅንነትና በታማኝነት፣ እንዲሁም በሀ ቀኝነት የመወጣት አስፈላጊነት በሁሉም ዜጋ ግንዛቤ ውስጥ መኖር አለበት:: አስፈላጊነቱን እያንዳንዱ ሰው ሲያምንበትና በሥራ ሲተረጉ መው፣ ለዕድገትና ለለውጥ መሠረት የሆኑ፣ በቅ ንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት የተሠሩ ውጤ ቶች ይገኛሉ:: ስለዚህ እናንተም በትምህርት ቤት ውስጥ በምትሳተፉባቸው የቡድንና የተና ጠል ሥራዎች በቅንነትና በታማኝነት በመሥ ራት ውጤት በማሳየት ኃላፊነትን መወጣት አለባችሁ::

**መልመጃ 4**

***ከላይ በተሰጠው ጽንሰ ሐሳብ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ሥራ ማኅበራዊ ባህርይ አለው የሚባለው ለምንድነው?
2. ኃላፊነትን በቅንነት፣ በታማኝነትና በሀቀኝነት መወጣት ለምን አስፈለገ?

## 6.3 የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና ቅርስ፤



*ሥዕል 6.2 የሐረር ግንብ ጥገና ሲደረግለት*




*ሥዕል 6.3 የአፈር መታጠብን ለመከላከል የእርከን ሥራ በኮንሶ*

- ከሁለቱ ስዕሎች ምን ተማራችሁ?

**የሚያዜሙ ወንዞች፤**

የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በአፍሪካ ውስጥ ከሚጠቀሱ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብቶች መገኛ ከሆኑት ፓርኮች መካከል አንዱ ነው:: ሁለት ሺህ ሁለት መቶ እስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት አለው:: በውስጡም በከፍታው በሀገራችን በሁ ለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ቱሉ ዲምቱ ተራ ራን ያጠቃልላል::

ከሃያ በላይ የአጥቢ አራዊትና ከአንድ መቶ አርባ በላይ የአእዋፋት ዝርያዎችን በውስጡ አቅፎ የያዘው ይኸው ፓርክ በልዩ ልዩ ሀገር በቀል እጽዋት ደኖች የተሸፈነ ነው:: በዓለም ውስጥ በየትኛውም ሀገር የማይገኙ ሃያ አራት የአእዋ ፋት ዝርያዎች በሀገራችን ብቻ ይገኛሉ:: ከነዚ ህም መካከል አስራ አራቱ ብርቅዬ የወፎች ዝርያ የሚገኘው በባሌ ተራሮች ፓርክ ውስጥ ነው::





*ሥዕል 6.4 የባሌ ተራሮችና በውስጣቸው የያዟቸው የዱር እንስሳት*

በተጨማሪም የዓለም ብርቅ የኢትዮጵያ ድንቅ ሀብት የሆኑት ኒያላ ወይም የደጋ አጋዘን፣ የሰሜን ቀበሮ ወይም ቀይ ቀበሮ በዚሁ ውብ የተፈጥሮ ክልል ውስጥ ይኖራሉ:: የገናሌና የዋቢ ሸበሌ ወንዞችም በባሌ ሸለቆዎችና ተዳፋቶች እያዜሙ፣ ሕይወት እያለመለሙ ወደ ደቡብ ምሥራቅ በዝግታ ይፈሳሉ::

*(ምንጭ፣ ግራር፣ የወንዶ ገነት ኢንስቲትዩት መጽሔት የ1978 ዓም እትም)*

**መልመጃ 5**

***ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ፓርክ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ቱሉ ዲምቱ የኢትዮጲያ 2ኛው ከፍተኛ ተራራ ከሆነ አንደኛው ማነው?
3. ኒያላ የሚገኘው የት ነው?
4. በአሁኑ ወቅት የባሌ ተራሮች ፓርክ የባሌ ፓርክ ከበፊቱ በተሻለ ይዞታ ላይ የሚገኝ ይመስላችሏል?

***የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና ቅርስን ከጥፋት የመጠበቅ ኃላፊነት፣*** ማለት እያንዳንዱ ሰው የራሱን፣ የማኅበረሰቡን፣ ብሎም የሀገርን ሀብትና ቅርሶች "የኔ" በሚል ወገናዊ ስሜት የመጠበቅ የዜግነት ግዴታ ማለት ነው:: ይህ የኃላፊነት ስሜት በሁሉም ሰው አስተሳሰብ ውስጥ ሲቀረጽና ተቀባይነት ሲያገኝ፣ የተፈጥሮ ሀብቶች ከውድመት፣ ታሪካዊ ሀብቶችና ቅርሶች ከጥፋትና ከብክነት ተጠብቀው ሕልውናቸው አስተማማኝ ይሆናል::

ማንኛውም ሰው በመኖሪያውና በሥራ ቦታው እንዲሁም የጋራ በሆኑ የመገልገያ ሥፍራዎች የሚገኙትን ንብረቶች በመንከባከብ ለአገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ አለበት:: ለምሳሌ ተማሪዎች በዚህ የኃላፊነት ስሜት መስራት የምትጀምሩት ከቤት ነው:: ጊዜ፣ እውቀትና ጉልበት በፈሰሰበት ገንዘብ የተገዛውን ማንኛውንም የቤት ውስጥ ንብረት ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት እንዲሰጥ ልታደርጉ ይገባል:: በትምህርት ቤትም ለመማር ማስተማር ሂደት አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩትን ንብረቶች እንደ ራሳችሁ ሀብት በመጠበቅ ጥቅም ላይ እንዲውሉና ለተተኪ ዜጎችም እንዲተላለፉ ማድረግ አለባችሁ:: በመኖሪያ አካባቢም ያሉትን የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብቶችና ቅርሶችን ለማልማትና ለመጠበቅ ዘብ መቆም ይጠበቅባችኋል:: የተፈጥሮና ታሪካዊ ሀብትና ቅርስን መጠበቅና መንከባከብ፣ ለሁሉም ዜጎች የተመቻቸና የተሟላ ሕይወት እንዲኖራቸው ያስችላል:: ውሀ፣ አፈር፣ ደን፣ ማዕድናት፣ አራዊትና እንስሳት ከውድመትና ከጉዳት ሲጠበቁ በአግባቡ ለልማት ሲውሉ የሀገር ዕድገትና ብልጽግና ይረጋገጣል:: ሥራ አጥነት፣ ረሀብና ድኀነትም ይጠፋል::

በዚሁ አኳያም ብርቅዬ አራዊትና አዕዋፋት ደረጃውን በጠበቀ ፓርክ እንዲኖሩ ሲደረግ የጎብኝዎችን ቁጥር በማብዛት የቱሪዝምን ሥራ ማጠናከር ይቻላል:: ይህም የሀገራችንን ኤኮኖሚ ያጎለብታል:: የቀደምት አባቶቻችንን የዕውቀትና ሥልጣኔ ደረጃ የሚያስረዱ ታሪካዊ ቅርሶችን መጠበቅ፣ የሀገሪቱን ታሪክ መንከባከብና የማንነትንም ማስረጃ ከማጠናከር ባሻገር ለቱሪዝም የሥራ ዘርፍ ሰፊ ሁኔታን መፍጠር ነው::

በመሆኑም ለሀገር ሕልውናና ዕድገት መሠረት የሆኑትን የተፈጥሮ ሀብቶችና ታሪካዊ ቅርሶችን "የኔ ነው" በሚል የኃላፊነት ስሜት ለመንከባከብ መወሰንና ሌሎች ራስ ወዳዶች የሚያደርሱትን ጥፋት ለመከላከል ዝግጁ መሆን አለባችሁ:: ይህም የብቁ ዜጋ መለኪያ ነው::

**መልመጃ 6**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

1. ታሪካዊ ቅርሶችንና የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅ ለማን ይጠቅማል?
2. ሥራ አጥነትን፣ ረሀብን፣ ድኀነትን ስማ ጥፋት የተፈጥሮ ሀብቶች እንዴት ያገለግላሉ?
3. ቱሪዝም ምንድነው? ጥቅሙን ግለፁ::

## 6.4 ኤች. አይ. ቪ/ ኤድስ፤

- የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን ናቸው?
- የኤድስን ስርጭት ለመቀነስ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ምንድነው?

**የአዲስ ተስፋ መንደር፤**

መምህርት በለጡ የስድስተኛ ክፍል የሂሣብ መምህርት ናት:: የክፍል ኃላፊ በሆነችበት "ስድስተኛ መ" ውስጥ ያሉትን ሠላሳ ተማሪዎች በስም በችሎታና በባህሪያቸው ታውቃቸዋለች፣ ትወዳቸዋለችም:: ትምህርት ዋናው ሥራቸው መሆኑን በማስገንዘብ ሥራቸውን በአግባቡ የማከናወን ኃላፊነት እንዳለባቸው ሁልጊዜም ታስገነዝባቸዋለች:: እነሱም ያከብሯታል:: ምክሯንም ይቀበላሉ:: የቤት ሥራ ሳይሠራ የሚመጣ ተማሪ አልነበረም::

ሆኖም በአንድ ወቅት ኪሮስ በተደጋጋሚ የቤት ሥራ ሳትሠራ እየመጣች ክፍል ውስጥ ስትጠየቅ መመለስ አዳገታት:: መምህርቷም ኪሮስ ችግሯን ለማወቅ በዕረፍት ሰዓት ለብቻዋ አነጋገረቻት:: የኪሮስ አባት በኤድስ እንደሞቱና እናቷም ታመው በአልጋ ላይ እንደሚገኙ ተረዳች:: በአባቷ ሞትና በእናቷ መታመም ምክንያት በተፈጠረው ችግር ኪሮስና ሁለት ታናናሽ እህቶቿ ትምህርታቸውን ወደማይቀጥሉበት ደረጃ እንደደረሱም አወቀች::

መምህርቷም ኪሮስና እህቶችዋ ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ለማድረግና በሕመም ላይ ላሉትም እናታቸው እርዳታ ለመፈለግ አቀደች:: ወደ "አዲስ ተስፋ መንደር" ድርጅት በመሔድ ስለድርጅቱ አሠራር ጠየቀች:: የሄደችበትንም ምክንያት አስታወቀች:: ድርጅቱም በበጐ አድራጊ ዜጐች እርዳታና ድጋፍ የኤድስ ሕሙማንና ወላጅ አልባ ልጆችን እንደሚረዳ ገለፁላት ::

መምህርት በለጡም የድርጅቱ አባል በመሆን ቋሚ የድጋፍ መዋጮ ለማድረግ ወሰነች::

የ"ስድስተኛ መ" ክፍል ተማሪዎችም በየወሩ በነፍስ ወከፍ ሃያ አምስት ሣንቲም በማዋጣት የድርጅቱ አባልና አጋር እንዲሆኑ አደረገች:: ከዚያ በኋላ ኪሮስና እህቶቿ ከድርጅቱ ወርሀዊ ድጋፍ እያገኙ ትምህርታቸውን መቀጠል ቻሉ:: የታመሙት እናታቸውም የሕክምና እርዳታ አገኙ:: ኪሮስም እንደተለመደው በትምህርቷ ጥሩ ውጤት እያመጣች መማሯን ቀጠለች::

**መልመጃ 7**

**ከላይ የቀረበውን አጭር ታሪክ መሠረት በማድረግ የሚከተሉተን ጥያቄዎች መልሱ::**

1. የነኪሮስ አባት ሲሞቱና እናታቸው በሕመም ሲጠቁ የተከሰተው ሁኔታ ምን ነበር?
2. የመምህርት በለጡ ተግባር ምንን ያመለክታል?

***ኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ*** በፍጥነት እየተዛመተ ሕዝብ በመጨረስ ላይ ያለ የሰው ልጆች ቀንደኛ ጠላት ነው:: እስካሁን ድረስ ለኤድስ መድኃኒት አልተገኘለትም:: በሽታው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1981 አካባቢ የተከሰተ ሲሆን፣ በዓለም ላይ በፍጥነት በመስፋፋት ላይ ይገኛል::

የበሽታው መተላለፊያ መንገዶች ከሆኑት ውስጥም፤ በቫይረሱ የተበከለ ደም ወደ ጤነኛ ሰው ደም ሲገባ፣

- ሕመምተኛው በተጠቀመባቸው የጥርስ ብሩሽና ስለታም መሣሪያዎች ማለትም እንደ ጥፍር መቁረጫ፣ ምላጭ፣ ወዘተ... ጤነኛው ሰው ሲጠቀም፣
- ሕመምተኛው በተወጋበት መርፌ ጤነኛው ሰው ሲወጋ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በሽታው የማይተላለፍባቸው መንገዶች፤

- በመጨባበጥ፣
- አብሮ በመብላት፣
- የጋራ ሽንት ቤት በመጠቀም፣
- በክፍል ውስጥ አብሮ በመማር ወዘተ... ናቸው።

በኤች.አይ.ቪ/ ኤድስ የተያዘ ሰው በሽታ መከላከል የሚያስችለው ሁኔታ ስለሚዳከም በልዩ ልዩ ሕመሞች በቀላሉ ይጠቃል:: አቅምና ጤናው ስለሚቀንስ ለመሥራት ወይም ለመማር አይችልም:: በዚህ ወቅት የሚረዳውና የሚደግፈው ከሌለ አሳዛኝና ከባድ ሥቃይ ውስጥ ይወድቃል:: መሥራት ባለመቻሉም ቤተሰቡ ይቸገራል። ኤች.አይ.ቪ./ ኤድስ በግለሰብ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ያህል በሀገርም ዕድገት ላይ ተጽእኖ አለው::

ሕዝብን በመጨረስ ላይ ያለው ይህ አስከፊ በሽታ በማስከተል ላይ ያለው ጉዳት ዘርፈ ብዙ ነው:: በበሽታው ምክንያት ወላጆች ሲሞቱ የቤተሰብ ኑሮ ከመናጋቱም በላይ ልጆች ተቸግረው ከትምህርት ገበታ ይለያሉ ሰብሳቢ ስለሚያጡም ይበተናሉ:: ሀገር ተረካቢ የሚሆኑ ወጣቶች የሀገር ሸክሞች ይሆናሉ:: ይህም ሁኔታ ለማኅበራዊ ኑሮ ችግር ከማስከተሉም በላይ ድህነት፣ ኋላቀርነትና ወንጀል እንዲስፋፋ ያደርጋል::

ስለዚህ እናንተም በኤድስ ሕመም አስከፊነት ላይ ተገቢውን ግንዛቤ በመጨበጥ ላለመጋለጥ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባችሂል:: በተጨማሪም ሌሎችን ለማስተማርና በበሽታው ለተያዙትም ድጋፍና እንክብካቤ ማድረግ ግዴታ አለባችሁ:: ራስን ከበሽታው የመጠበቅ ኃላፊነትን የመወጣት ተግባር በመሆኑ ማንኛውም ዜጋ ሊተገብረው ይገባል::

**መልመጃ 8**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።**

1. የኤድስ መተላለፊያ መንገዶችን ግለፁ::
2. በኤድስ ምክንያት የተጐዳ ቤተሰብ ሁኔታ ምን ይመስላል? የዚህ ቤተሰብ ልጆችስ ምን ችግር ይደርስባቸዋል?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ኃላፊነት የሚሰማቸውን ዜጐች ለማፍራት መሠረቱ ቤተሰብ ነው፡፡ ከመልካም ቤተሰብ በመልካም ሥነ ምግባር ታንፀው የሚወጡ ወጣቶች ኃላፊነትን ለመወጣት ብቁ ይሆናሉ፡፡

ኃላፊነት የሚጀምረው በቤተሰብ ኑሮና ሕይወት ውስጥ ነው፡፡ እሱም የወላጆችን ምክርና መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ የሚሰጠውን ኃላፊነት በመወጣትና ቃል ኪዳንን በማክበር ይረጋገጣል፡፡ በትምህርት ቤት ሕይወትም ከመምህራንና ከትምህርት ቤቱ የሚሰጠውን ትእዛዝ በቅንነትና በሀቀኝነት መፈፀም ሌላው ኃላፊነትን የመወጣት ሂደት ጅማሮ ነው፡፡

የቤተሰብን፣ የኅብረተሰብን፣ የሀገርን የተፈጥሮ ሀብትና ንብረትን እንዲሁም ታሪካዊ ቅርሶችን መጠበቅና መንከባከብ የራስን ሕልውናና ታሪክ መጠበቅ የሚያስችል ተገቢ ድርጊት ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ራስን ከኤች.አይ. ቪ/ኤድስ መጠበቅና ስርጭቱን ለመግታት በሚደረግ እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ ታላቅ ኃላፊነትን መወጣት ነው፡፡

ኃላፊነት ልዩ ልዩ ዓይነቶችና ደረጃዎች አሉት፡፡ ሠራተኞች ሁሉ እንደ ትምህርት ደረጃቸውና የሙያ ችሎታቸው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሠማርተው ይሠራሉ፡፡ ሆኖም የደረጃና የኃላፊነት መጠን ልዩነት መኖሩ ግልጽ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በያዘው ሥራ ላይ በሀቀኝነትና በታማኝነት ከሠራ አጠቃላይ ውጤቱ ልማትና ዕድገት ይሆናል፡፡

## ቁልፍ ቃላት

***መመረቅ፣*** የአንድ ትምህርት ደረጃን በማጠናቀቅ ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) ማግኘት።
***አርበኛ፣*** በተሰለፈበት ማንኛውም የሙያ መስክ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ ዜጋ።
***ጥራት፣*** ደረጃውን የጠበቀ ሁኔታ/ ውጤት።
***ቃል ኪዳን፣*** ቅድሚያ የሚሰጥ የቃል መተማመኛ።
***ሥነ ምግባር፣*** የሰውን ባህሪና ተግባር ትክክል መሆን አለመሆኑን የሚገልጽ ሀሳብ።
***ምሪል፣*** ግብረገብ፣ የጥሩና የመጥፎ ድርጊቶች መመዘኛ ሁኔታ።
***ቅርስ፣*** ዜና ታሪክን የሚጠቁሙ፣ የቀደምት ሰዎችን ሥልጣኔና ጥበብ የሚያሳዩ የተግባር ውጤቶች።
***ፓርክ፣*** የተፈጥሮ ሀብቶች/ አራዊት፣ አእዋፋት፣ እጽዋት/ የሚጠበቁበት ቦታ።
***ላብ አደር፣*** የጉልበት ሥራ የሚሠራ።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

*I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ «ሀሰት» ብላችሁ መልሱ::*

1. በተግባር ሲተረጉም የታቀደ ለራስ ወይም ለሌሎች የሚሰጥ የቃል መተማመኛ ወይም ተስፋ ቃልኪዳን ይባላል::
2. አንድ ሰው ሰዓት አክብሮ መገኘቱ ብቻ ኃላፊነቱን እንደተወጣ ይቆጠርለታል::
3. ሠራተኞች በሙሉ ያለባቸው የሥራ ኃላፊነትና የሥራቸው ደረጃ ተመሳሳይነት አለው::
4. አራዊት፣ አእዋፋት፣ ልዩ ልዩ አጸዋት የሚጠበቁበት ሥፍራ ፓርክ ይባላል::
5. የኤድስ መስፋፋት ለድህነትና ለኋላቀርነት አስተዋጽኦ ይኖረዋል::

*II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ::*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ኃላፊነት፣ | ሀ. ዘመንና ታሪክን የሚገልጽ ሀብት:: |
| 2. ቤተሰብ፣ | ለ. በፈቃደኝነት ወይም በትእዛዝ ሥራን መስራት:: |
| 3. ቀደ ቀበሮ፣ | ሐ. ታሪካዊ ቅርሶችንና የተፈጥሮ ሀብቶችን በማስጐብኘት ገቢ የሚያስገኝ የሥራ ዘርፍ:: |
| 4. የተፈጥሮ ሀብት፣ | መ. የሀገር እድገት እንቅፋትና ፀረ ሰው። |
| 5. ቱሪዝም፣ | ሠ. በሰዎች ዕውቀትና ሥራ ሊሰማ የሚችል እንክብካቤ የሚሻ ንብረት:: |
| 6. ኤች.አይ.ቪ፣ | ረ. በወላጆችና በልጆች የተደራጀ የኀብረተሰብ ክፍል:: |
| 7. ታሪካዊ ቅርስ፣ | ሰ. ብቸኛ የሀገር ሀብት። |

*III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::*

1. በታማኝነትና በቅንነት ኃላፊነትን መወጣት ማለት፧
   ሀ/ ትዕግስተኛ መሆን፣
   ለ/ በትእዛዝም በፍላጐትም ለሥራ አለመነሳሳት፣
   ሐ/ ለውጤት መታገልና የዜግነትን ግዴታን መወጣት፣
   መ/ ተግባቢነትን ማሳየት::
2. የቤተሰብን ምክርና መመሪያ መተግበር፧
   ሀ/ በቤት ውስጥ ሥራ መወጠር፣
   ለ/ ሥነ ምግባርን መተላለፍ፣
   ሐ/ ለጥናት በቂ ጊዜ ማጣትና በተጽዕኖ ሥር መውደቅ፣
   መ/ ቃል ኪዳንን ማክበር::
3. እያንዳንዱ ሰው ኃላፊነቱን ባይወጣ፧
   ሀ/ ማኀበራዊ ኑሮ ላይ ችግር አይከሰትም፣
   ለ/ ቃልኪዳን ይጠበቃል፣
   ሐ/ በአካባቢና በአገር እድገት ላይ ተጽእኖ ያመጣል፣
   መ/ ሰላማዊ ሕይወት ይቀጥላል::
4. የሕዝቦችን ሥልጣኔና ባህል እንዲሁም የዕድገት ደረጃን የማይገልፀው፧
   ሀ/ የተፈጥሮ ሀብቶች፣
   ለ/ የታሪክ መጻሕፍት፣
   ሐ/ ታሪካዊ ቅርሶች፣
   መ/ የአረጋውያን ምስክርነት::

5. የኤች.አይ.ቪ/ኤድስን ስርጭት መከላከል የሚቻለው፤
   ሀ/ መተሳሰፊያውን መንገድ በማጋለጥ፣
   ለ/ ከሕመምተኞች በመራቅ፣
   ሐ/ መተሳሰፊያውን በማወቅና በመጠንቀቅ፣
   መ/ ማሕበራዊ ግንኙነትን በመቀነስ።

## IV. *የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. ማንኛውንም ዓይነት የሥራ ድርሻ በብቃትና በውጤት ማከናወን____________________ ተብሎ ይገለጻል::
2. ወርቅ፣ ነሀስ፣ ብረት፣ ፖታስየም__________________ሲሆኑ፣ የብራና መጻሕፍት፣ አብያተ መንግሥታትና ገዳማት፣ የዋሻ *ሥዕሎችና መስጊዶች*____________________ናቸው።
3. የአገርን ዕድገት ከሚያዳክሙት ችግሮች መካከል አደገኛው__________________ነው::

## V. *የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::*

1. ቃልኪዳንን በተግባር ማረጋገጥ ኃላፊነትን መወጣት የሚሆነው እንዴት ነው?
2. ፓርኮችንና ውስጣቸው የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች የመንከባከብ ኃላፊነት የማነው?
3. ኤች.አይ.ቪ. ወላጆችን ሲያጠቃ በልጆች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት አስረዱ::

# ምዕራፍ ሰባት

# ጠንካራ የስራ ባሕል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣ *ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የሥራን ክቡርነት ትረዳለህ/ትረጂለሽ።
- ጠንክሮ የመሥራትንና ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ የማዋልን ጥቅም ትገነዘባለህ/ለሽ።
- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት ውስጥ የተደነገጉ የኢኮኖሚና የልማት ነክ ዓላማዎችን ትዘረዝ ራለህ/ትዘረዝሪያለሽ።

## 7.1 ጠንካራ የሥራ ባህል ምንነት፤

### 7.1.1 ጠንክሮ መሥራት፣

- *ጠንክሮ መሥራት ሲባል ምን ማለት ነው?*
- *ጠንክሮ በመሥራት ምን ጥቅም ይገኛል?*

***ታጠቁ ስሥራ፤***

*ያረሰ ገበሬ እርፍ የነቀነቀ፣*
*ወፍጮው እንዳገሳ መስከረም ዘለቀ።*
*ያላረሰ ሰነፍ እርፍ ያልነቀነቀ፣*
*ለሐምሌ መባቻ ተጣጥፎ ወደቀ።*
*መሬቱን ያረሰ በደንብ አለስልሶ፣*
*ጉልጉሎና አርሞ ደጋግሞ መላልሶ፡*
*አዝመራው ሲፋፋ ሰብሉ መኸር ደርሶ*
*እህሉን ያስገባል ከአውድማው አፋፍሶ።*
*ጎበዞች ሲተጉ ዕረፍት የፈለገ፣*
*ለሥራው ዕውቀቱን ጉልበት የነፈገ፣*
*ልጆች ዳቦ ቢሉት ጓሮ ተሸሸገ።*
*በእርሻ በኢንዱስትሪው በገጠር ከተማ፣*
*ጠንክሮ መሥራት ነው ሀገር እንድትለማ።*
*ሰው በሠራው ሥራ ውጤት እንዲከበር፣*
*ሥራን ባህል አርጎ ማምረት ነው ለሀገር።*

*(ከህዝባዊ ግጥሞች ጋር በማከል ለማስተማሪያ እንዲመች ሆኖ የተዘጋጀ ጥር/2000 ዓ/ም)*

**መልመጃ 1**

*በግጥሙ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. ከግጥሙ ያገኛችሁትን ፍሬ ሃሳብ ፃፉና በየተራ ስመምህራችሁ አንብቡላቸው።

«ያላረሰ ሰነፍ እርፍ ያልነቀነቀ፣
ለሐምሌ መባቻ ተጣጥፎ ወደቀ።»

2. የዚህ ግጥም ተቃራኒ የሆኑ ሌሎች ሁለት ስንኞች የትኞቹ ናቸው?
3. እስኪ እናንተ ደግሞ ስለጎበዝ ተማሪ አጭር ግጥም ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

ጠንካራ የሥራ ባህል ማለት አንድ ሕዝብ ሠርቶ ለመኖር ያለው ጠንካራ ፍላጐትና ልምድ ሲሆን ሠራተኞች ያላቸው የመሥራት ፍላጎትና በሙያው የተሻለ ውጤት ለማስመ ዝገብ ያላቸው ቁርጠኝነት ማለት ነው። ሥራ የሰው ልጆች ሁሉ የመኖር ዋስትና ስለሆነ ጠንክሮ ከሠሩ ከራስ አልፎ የቤተሰብንና የአካባ ቢን ኑሮን ለመለወጥ ወደሚያበቃ ታላቅ ደረጃ ያሸጋግራል።

ሥራ ከአካባቢ በሚገኙ ነገሮች ላይ ተመሥ ርቶ ከቀላል ነገር በመጀመር ጠንክሮ ከተሠራ ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ ለማደግ ያስችላል። ጠን ክሮ መሥራት ሲባል በተሰማሩበት የሥራ መስክ የተሻለ የምርት ውጤትን ማስገኘት ብቻ ሳይሆን የሥራ ሰዓትን በማክበር፣ ሙያዊ ሥነ ምግባርን በመላበስና የምርት ጥራትን በማሳደግ ጭምር ይገለፃል።

**መልመጃ 2**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. በእናንተ አካባቢ ሲሠሩ የሚችሉ የሥራ ዓይነቶችን ጥቀሱ።
2. ጠንክሮ መሥራት ለአካባቢና ለሀገር ስላለው ጠቀሜታ በቡድን ተወያዩ።







ሥዕል 7.1 ማንኛውም ሥራ ክቡር ነው

- ከሥዕሎቹ ምን ተገነዘባችሁ?
- በእናንተ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ምን ምን ሥራዎችን ይሠራሉ?
- ሥራን አለመናቅ ሲባል ምን ማለት ነው?

**ጎበዙ ልጅ፤**

በድሩ ጣሂር የተወለደው በሶማሌ ክልል በጅጅጋ አካባቢ ቢሆንም የወጣትነት ዕድሜውን ያሳለፈው በድሬዳዋ ከተማ ነበር::

በልጅነቱ በድሬዳዋ ከተማ ብዙ የሥራ ዕድሎች እንዳሉ ታላላቆቹ ሲያወሩ ሰምቷል:: ስለዚህም ከአጎቱ ጋር ወደ ድሬዳዋ ከተማ በመሄድ አጎቱ በገዙለት የሥራ መሣሪያ ፈጣንና ጎበዝ ጫማ አሳማሪ ለመሆን ቻለ:: ጎበዙ ልጅ በመባል የሚታወቀው በድሩ በጠዋት ተነስቶ ጥቂት ጫማዎችን ካሰማመረ በኋላ ወደ ትምህርት ቤቱ ይሄዳል:: የቤት ሥራውን በሚገባ ሠርቶና ትምህርቱን አጥንቶ ወደ ክፍል ስለሚገባ በድሩ በመምህሮቹና በተማሪዎች ዘንድ የሚወደድ ተማሪ ነበር::

ሥራ ወዳዱ ልጅ ጫማ እያሳመረ ጥቂት ገንዘብ እንዳጠራቀመ ሌላ ዓይነት ተጨማሪ ሥራ መሥራት እንዳለበት አሰበ:: በመጨረሻም ለአካባቢው ኗሪ ጥሩ አገልግሎት ለመስጠት የሚችልበትን የጫማ ማደሻ ሱቅ ከፈተ:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ በድሩ የጫማ ማደሻ ሱቅ የሚመጣው ደንበኛ ቁጥር እየጨመረ ሄደ::

በአሁኑ ጊዜ ባለትዳርና የሦስት ልጆች አባት የሆነው አቶ በድሩ ደቻቱ በሚባል አካባቢ በአቋቋመው የጫማ ፋብሪካ ውስጥ በየትኛውም የዕድሜ ደረጃ ለሚገኝ ሰው ምቹና ጠንካራ ጫማዎች ይመረታሉ:: ከቀላል የሥራ ዓይነት የተነሳው በድሩ ዛሬ በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ ከታወቁት ባለሃብቶች አንዱ ለመሆን በቅቷል::

**መልመጃ 3**

***ከላይ በቀረበው ታሪክ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. በድሩ በደንበኞቹ ዘንድ ምን የሚል መጠሪያ ነበረው?
2. በአካባቢያችሁ ከአነስተኛ መነሻ ገንዘብ ተነስተው በከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች ካሉ ወሳጆቻችሁን ጠይቁና እነዚህ ሰዎች ያለፉበትን የሥራ ሂደት ዘርዝራችሁ በመፃፍ በክፍል ውስጥ አንብቡ::
3. የአቶ በድሩ የሥራ ጥንካሬ ከምን የመነጨ ይመስላችኋል?

ሥራን አለመናቅ ሲባል የትኛውንም የሥራ ዓይነት በእኩል ደረጃ መመልከትና ያገኙትን ሥራ ሳይንቁ መሥራት ማለት ነው:: እያንዳንዱ የሥራ ዓይነት ትንሽ ወይም ትልቅ ሳይባል ትኩረት አግኝቶ ከተሠራ ጥሩ የገቢ ምንጭ ሊሆን ይችላል:: ዛሬ ትንሽ ነው የሚባል አንድ ሥራ ተገቢውን ትኩረት ካገኘ ነገ የሚሠራውን ሰው ከፍ ወዳለና ወደተሻለ ደረጃ ሊያደርሰው ይችላል::

**መልመጃ 4**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ሥራን አስመናቅ የሚኖረውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ፡፡
2. የሥራ ክቡርነት በምን በምን ሁኔታ ሲገለፅ ይችላል?

### 7.1.3 ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል፣

- የእናንተን የጊዜ አጠቃቀም ሁኔታ ለጓደ ኞቻችሁ ንገሩ፡፡
- ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል ማለት ምን ማለት ነው?

**ከብት አርቢዋ ዓለሚቱ፤**

ወ/ሮ ዓለሚቱ በባህርዳር ከተማ በቀበሌ 03 የሚኖሩ የ35 ዓመት ወይዘሮ ናቸው፡፡ እኚህ ሴት በአካባቢያቸው ከሚታወቁባቸው ባህሪያት አንዱ ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋላቸው ነው፡፡ በሚኖሩበት አካባቢ ስለጊዜ ያላቸው አመለካከት እንደምሳሌ የሚታይ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ጊዜአቸውን በመከፋፈልና ጠንክሮ በመሥራት ሕይወታቸውን ወደተሻለ ደረጃ የሚቀይር ሥራ ለመሥራት አቀዱ፡፡

ይህን ለማስፈጸም ወደ የአማራ የገንዘብ ቁጠ ባና ብድር የሕብረት ሥራ ተቋም በመግባት በተወሰነ ጊዜ የሚከፍሉት ብድር ወስደው አን ዲት ክበድ ላም ገዙ፡፡ ላማቸው ብዙም ሳትቆይ ሴት ጥጃ ወለደችላቸው፡፡ ላሚ በቀን ከሦስት ሊትር በላይ ወተት ትታለብ ስለነበር ለሠፈሩ ኗሪዎች ወተት በማከራየት በጊዜ ብድራቸውን ከፈሉ፡፡ በዓመቱ ሌላ የምትታለብ ላም ገዝተው ጨመሩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ጊዜአቸውን በአግባቡ በመጠቀም በከብት ርቢ ተግባር ላይ ጠንክረው ሠሩ፡፡ ዛሬ ወ/ሮ ዓለሚቱ በባህርዳር ከተማ የታወቁ የከብት ርባታ ድርጅት ባለቤት ናቸው፡፡

**መልመጃ 5**

*በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥይቄዎች መልሱ፡፡*

1. ከወ/ሮ ዓለሚቱ የጊዜ አጠቃቀም ምን ትማራላችሁ?
2. ስባስ ታሪኳ የሥራ መነሣሣት ምክንያቶች ናቸው ከምትሏቸው ሁለቱን ጥቀሱ፡፡
3. ጊዜን በአግባቡ በሥራ ላይ በማዋል የሚገ ኘው ጠቀሜታ ምንድነው?

### 7.1.4 ሥራን አስመናቅና ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል ስራስና ስሀገር ያስው ጠቀሜታ፣

- “ጊዜን በአግባቡ“ መጠቀም ማለት ምን ማለት ነው?
- ጊዜ ወርቅ ነው የሚለው ምሣሌአዊ አነጋገር ምንን ያሳያል?

**ዓሣ አጥማጆቹ፤**

ማንኛውም ወደ ባህርዳር ከተማ ለጉብኝት የሚ ሄድ ሰው በጣና ሐይቅ ላይ የሚንሳፈፉ ትንንሽ ታንኳዎችን ማየቱ የማይቀር ነው፡፡ እነዚህን ታንኳዎች እየቀዘፉ የሚነዱት በአብዛኛው በባህር ዳር ከተማና በዙሪያዋ የሚኖሩ አሣ አጥማጆች ናቸው፡፡

ዓሣ አጥማጆቹ በሕብረት የተደራጁና ጠንክረው በመሥራት ለከተማው ሕዝብ ትኩስ የዓሣ ምርት የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ አባላቱ እንደሥራ ችሎታቸው በቡድን የተከፈሉና እያንዳንዱ ቡድን የራሱ ተጠሪና በጊዜ የተወሰነ የሥራ ዕቅድ ያለው ነው፡፡

የቡድኑ አባላት ከሐይቁ ብዙ የዓሳ ምርት ለመ ሰብሰብ የሚያስችለውን ምቹ ጊዜ ያውቁታል፡፡ እያንዳንዱ አባል ይህን ምቹ ጊዜ በመጠቀም ሰዓቱን ሳያዛባ ጠንክሮ ይሠራል፡፡ ዛሬ አባላቱ ጊዜን በዕቅድ ከፋፍለው በመሥራታቸው ለዓሣ ምርትና ማከማቻ የሚያስፈልጓቸውን ዘመናዊ መሣሪያዎች ለማደራጀት ችለዋል፡፡ ትንንሽ ታን ኳዎቻቸው በዘመናዊ የሞተር ጀልባዎች ተቀይ ረዋል፡፡

ዘመናዊ የዓሣ ማጥመጃ መረቦችን፣ ጀልባዎችንና የምርት ማቆያ ማቀዝቀዣዎችን አሟልተዋል፡፡ በባህርዳር ከተማ የዓሣ ማከፋፈያ ሱቅ ስላላቸው የአካባቢው ሕዝብ ዓሣን በምግብነት የመጠቀም ባህሉ ዳብሯል፡፡ ብዙ ሥራአጥ የነበሩ ወጣቶች በዓሣ ምርትና ሽያጭ ላይ ተሠማርተዋል፡፡

ከጊዜ ወደ ጊዜ የዓሣ ምርታቸውንና የሥራ ጥራታቸውን እያሳደጉ በመምጣታቸው ምርታ ቸውን ወደሌሎች ከተሞች ያቀርባሉ፡፡ እንዲሁም ቅርብ ወደሆኑ ጎረቤት ሀገሮች የዓሣ ምርት በመላክ የሀገራቸውን የውጭ ምንዛሬ በማሳደግ ላይ ይገኛሉ፡፡

**መልመጃ ፩**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄ ዎች መልሱ፡፡***

1. የማሕበሩ አባላት የጊዜ አጠቃቀም ምን ይመስላል? ከምንባቡ ማስረጃ እየጠቀሳችሁ አብራሩ፡፡
2. ለዓሣ አጥማጆች ማሕበር የጥንካሬ መሠረት የሆኑትን ሦስት ዋና ዋና ነጥቦችን ጥቀሱ፡፡
3. የእናንተን የአንድ ቀን ውሎ ከፋፍላችሁ በመ ፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩአቸው፡፡

*ሥራን ሳይንቁና ትንሽ ነው በማለት ሳያማርጡ በመሥራት ለውጤት የበቁ ዜጎች ብዙ ናቸው፡፡ ሥራን መናቅ አይገባም፡፡ ሁሉም ሥራ በጥሩ ሁኔታ ሊከናወን የሚችለው ጊዜን በማቀድና ለወጣው የሥራ ዕቅድ ራስን በማስገዛት ከሰሩ ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ይቻላል፡፡*

የጊዜን አጠቃቀም በማወቅ ጠንክሮ የሚሠራ ዜጋ በቤተሰቡም ሆነ በሕብረተሰቡ ኑሮ ላይ ለውጥ ለማምጣት ይችላል፡፡

**መልመጃ ፯**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ጊዜን በአግባቡ ሥራ ላይ በማዋል የሚገኘ ውን ጠቀሜታ ዘርዝሩ፡፡
2. ሥራን መናቅ የማይኖርብን ለምን ይመስ ላችኋል?

## 7.2 ሳይሠሩ መብላት፣

### 7.2.1 ሳይሠሩ መብላት በቤተሰብ ደረጃ የሚያደርሰው ጉዳት፣



ሥዕል 7.2 ልመና ስብዕናን የሚፈታተን ማህበራዊ ችግር ነው

- ልመና ከግለሰብ አልፎ ማሕበራዊ ችግር የሚሆነው በምን ምክንያት ነው?
- ሰዎች ወደ ልመና እንዳይወጡ ምን መደረግ አለበት ትላላችሁ?

**ልመና ቻው! ቻው!**

*አያንቱ በጥቁር አንበሳ ግንብ ሥር በተቀለሰች የላስቲክ ቤት ውስጥ ከ8 ዓመት ልጇ ጋር ትኖ ራለች፡፡ ዘወትር በየመኪናው መስኮትና በየሱ ቆች በር እጇን ዘርግታ በምትመጸወተው ገንዘብ የእሷንና የልጇን ሆድ ለመሙላት ትጥራለች፡፡*

በዓላትን እየጠበቀች በከተማው በሚገኙት አድ ባራት ዞራ ምጽዋት ከመጠየቋም በላይ ከጥቁር አንበሳ ህመምተኞች የምግብ ትርፍራፊ ለማግኘ ት ከሌሎች ጋር ትሻማለች፡፡ ይሁን እንጂ ሙሉ ጤንነትና ጤናማ አዕምሮ ያለው እንደሷ ያለ ሰው ለምን ልመና እንደሚወጣ ለራሷም ግልጽ አልነበረም፡፡ የቤተሰቧን ያለየሌለ ጥሪት በመሸጥ ወደ አረብ አገር ከመንደሯ የተሸኘችው አያንቱ ስንቋን ጨርሳ በአዲስ አበባ ከተማ በጎዳና ሕይወት ከከተመች ድፍን 14 ዓመት ሞላት፡፡ አያንቱ ዕድሜዋ እየጨመረ፣ ልጅነቷ እየደበ ዘዘና ተስፋዋም እንደበጋ ደመና እየበነነ በመም ጣቱ ከዚህ አፀያፊ ተግባር እንዴት መውጣት እንደምትችል ዘወትር ታሰላስል ነበር፡፡

በመጨረሻም ከራሷ ጋር መክራ ከዚያ የከፋ ሕይወት ልጇን አንጠልጥላ በቶሎ ማምለጥ እንደሚሻል ቆረጠች፡፡ ልጇንና ጥቂት የፌስታል ቋጠሮዎቿን ይዛ ወደ ትውልድ መንደሯ በሚያ ደርሳት አውቶቡስ ተሳፈረች፡፡ ከሁለት ቀን ጉዞ በኋላ ወደ መንደሯ ስትደርስ ያየችውን ለውጥ ለማመን አልቻለችም፡፡

አዳዲስ መንገዶች ተዘርግተዋል፣ መብራትና ስልክ ገብተዋል፣ የውሃ ቧንቧ በየሰፈሩ ተዳር ሷል፡፡ ገጠር የነበረው የእነ አያንቱ መንደር ወደከተማነት ተቀይሯል፡፡ አያንቱም ይህን አጋ ጣሚ ተጠቅማ እንደ መንደሯ የራሷንም ሕይ ወት ለመቀየር ታጥቃ ተነሳች፡፡ ለዚህም ቤተ ሰቧና አካባቢዋ እንደሚተባበሯት በማመን በመን ደሩ ከተቋቋመው የብድር የህብረት ሥራ ማህበር ጥቂት ገንዘብ ተበድራ ሽቀጣሽቀጥ መሸጥ ጀመ ረች፡፡ ትናንት ያለቁምነገር ያሳለፈችውን ጊዜ በቁጭት እያስታወሰች ሌት ከቀን ጠንክራ ሠራች፡፡ በአሁኑ ሰዓት አያንቱ አንድ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ከፍታ ራሷን ችላ በመሥራት ላይ ናት፡፡

መልመጃ 8

?

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ፡፡*

1. ስመና አስፀያፊ ተግባር ነው የተባለው በምን ምክንያት ነው?
2. ስመናን ስማስቀረት ምን መደረግ ይኖር በታል ትላላችሁ? በቡድን በቡድን ሁኑና መፍትሄዎችን ዘርዝራችሁ ተወያዩ፡፡
3. ከምንባቡ በተረዳችሁት መሠረት አሁን አያንቱ ምን ደረጃ ላይ ያሰች ይመስ ላችኋል?

በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ የቤተሰብ አባላት እንደየአቅማቸው በሥራ ካልተሳተፉ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ በሥራ ብዛት ሊጎዱ ይችላሉ፡፡ አዋቂዎችም ሆኑ ልጆች ወይም ሴቶችም ሆኑ ወንዶች እንደየዕድሜአቸውና የሥራ ችሎታቸው በሥራ መተጋገዝን የቤተሰቡ የሥራ መርህ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

እንዲሁም ሥራ ሳይሰሩና ሳይደክሙ ሌሎች የለፉበትን የሚበሉ ካሉ ይህ አስነዋሪ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ ራሳቸውን ለሥራ ማነሳሳት አለባቸው፡፡

መልመጃ ፱

?

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ልጆች በቤት ሥራ ውስጥ እንዴት መሳተፍ ይችላሉ?
2. ሳይሰሩ መብላትን ስማስቀረት የሚረዱ ሁለት የመፍትሄ ሃሳቦችን ጥቀሱ፡፡
3. አንድ ቤተሰብ በሥራ የመተጋገዝን ባህል እንዴት ሊያዳብር ይችላል?

## 7.3 የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነ ምግባር፤

### 7.3.1 የሙያ ችሎታና የሙያ ሥነ ምግባር ምንነት፣

- አንድ ሠራተኛ የሙያ ችሎታ አለው ሲባል ምን ማለት ነው?
- ከእናንተ የሚጠበቁ የተማሪ ሥነ ምግባሮች ምን ምን ናቸው?

ሙያ የራሱ የሆነ ልዩ ዕውቀትንና ችሎታን የሚጠይቅ የሥራ ዓይነት ነው፡፡ ለምሳሌም ያህል ግብርና፣ ጋዜጠኝነት፣ መምህርነት፣ ዳኝነት ወዘተ...። የሙያ ችሎታ ማለት በአንድ ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚያስችልና ስለዚያ ሙያ ሊኖረን የሚገባው ዕውቀትና ችሎታን የሚያካትት ነው፡፡ የሙያ ሥነምግባር ማለት ደግሞ አንድ ሙያ በተግባር ላይ ሲውል ባለሙያው ሊያከብረው የሚገባው የሙያው ደንብና የአሠራር ሥነ ሥርዓት ነው፡፡

በዚህ መሠረት የሙያ ችሎታና ሥነ ምግባር ማለት አንድ ሰው አንድን ሥራ ለመሥራት ያለው ብቃትና ሙያው የሚፈልገው የተግባር መግለጫ ባሕሪ ማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሠራተኛ የሙያው ችሎታ ኖሮት የሙያው ሥነ ምግባር ከሌለው የሚፈለግበትን አገልግሎት ስለማይሰጥ ተገልጋዩ ሕዝብ ሊጎዳ ይችላል፡፡

አንድ ሐኪም ታመው ወደ እርሱ ለሚመጡት በሽተኞች ተገቢውን ምክርና የሕክምና ዕርዳታ መስጠት የሙያ ግዴታው ሲሆን ሕብረተሰቡ አስቀድሞ እራሱን ከበሽታ እንዲከላከል ማስተማር የሙያው ሥነምግባር አንዱ ዘርፍ ነው፡፡ በሌላም በኩል ስለመድሃኒት አወሳሰድ፣ በበሽታው ምክንያት ጥንቃቄ ስለሚደረግባቸው ጉዳዮች ሁሉ ማስተማር ይጠበቅበታል፡፡ እነዚህ ተግባራት የሕክምና ሙያ ሥነ ምግባሮች ናቸው፡፡

መልመጃ 10

?

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ሙያና የሙያ ሥነ ምግባር አይነጣጠሉም ሲባል ምን ማለት ነው?
2. እያንዳንዱ ሙያ ስሀገር ልማት አስተዋፅኦ ያደርጋል የሚባለው ስምንድን ነው?

### 7.3.2 የሙያ ሥነምግባር መጓደል በዜጎች ላይ የሚያደርሰው ችግር፣

- የአንድ ባለሙያ የሙያ ሥነ ምግባር መጓደል የሚጎዳው ማንን ነው?
- የሙያ ችሎታ ብቻውን ጠቀሜታው አነስተኛ ነው የሚባለው ለምንድነው?

ማንኛውም ሙያ የግለሰብን፣ የአካባቢንና የሀገርን ልማት መሠረት ካላደረገ ጉዳቱ በባለሙያው ላይ ብቻ አይቆምም፡፡ ሠራተኛውም የሙያውን ሥነ ምግባር ካላከበረ ውጤት አያገኝም፤ የራሱንና የቤተሰቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻልም አይችልም፡፡ በሙያው ውጤት ባጣ ቁጥር ሙያውን የበለጠ ለማዳበር ፍላጎቱ ይቀንሳል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ የተገልጋዮችን ፍላጎት ለማሟላት

የሚኖረው አቅርቦት የተጓደለ ይሆናል::

ይህ ሲሆን ሙያው ሊስፋፋ አይችልም፣ የዜጎች የሥራ ዕድል ይጠባል፤ ይህም በሀገር ልማትና በዜጎች ኑሮ መሻሻል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያመጣል::

**መልመጃ 11**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. በሙያ ሥነ ምግባር መጓደል የተነሳ የሀገር ልማት የሚጎዳው እንዴት ነው?
2. ሙያና የሙያ ሥነ ምግባር እንዲከበር ምን መደረግ አለበት?
3. የሙያ ሥነ ምግባር መጓደል በተገልጋዮች ላይ የሚያደርሰውን ችግር አብራርታችሁ ፃፉ::

## 7.4 ጠንካራ የሥራ ባህልና ልማት፤

### 7.4.1 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት የልማት ዓላማዎች፣

- *የኢኮኖሚ የልማት ዓላማዎች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?*
- *የኢኮኖሚ የልማት ዓላማዎች ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ ምን መደረግ አለበት?*

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት በሀገሪቱ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ ፖሊሲና ስትራቴጂ ቀርፆ ሕዝቡን ለሥራ በማንቀሳቀስ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ ናቸው::

ሀገሪቱ የምታራምደው የልማትና የኢኮኖሚ ነክ ዓላማ ሕዝቦች በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን፣ ከተመፅዋችነት የሚላቀቁበትንና ሁሉም ዜጐች በዕኩልነት በሀገር ልማት ላይ የሚሳተፉበትን የኢኮኖሚ ሥርዓት ማስፈን ነው:: ይህም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች በአንቀጽ 89 በግልጽ ተመልክተዋል:: በሕገመንግሥቱ ከተጠቀሱት የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች የሚከተሉት በአብነት ሊቀርቡ ይችላሉ::

89 (1) *መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ ዕውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት፣*

89 (2) *መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል ዕኩል እድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፣*

89 (5) *መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታው ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና ዕድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣*

89 (7) *መንግሥት በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በዕኩልነት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት::*

እነዚህን የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች በተግባር ለማረጋገጥ ግብርናን ማዕከል ያደረገ የገጠር ልማት ግንባታ ማካሄድና በሌሎችም የልማት መስኮች በጋራ ርብርብ ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው:: ይኸም የሚገለጸው የሀገር ልማት ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ጊዜ መንግሥት ሕዝቡን በየደረጃው በንቃት በማሳተፍና ለተግባራዊነቱም እንዲረባረብ ተገቢ ድጋፍ በመስጠት ነው::

**መልመጃ 12**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው::***

1. የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ምንድነው? ባለሙያ ጠይቃችሁ በክፍል ውስጥ ተወያዩ::
2. ሀገርን በልማት ለማሳደግ የእናንተ ድርሻ ምንድነው? በክፍል ውስጥ ተወያዩበት::
3. የኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎችን ወደ ተግባር በመለወጥ የሚገኘው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ጠንካራ የሥራ ባህልን ያዳበረ ሕዝብ ዕድገቱ ፈጣን ኢኮኖሚውም ከፍተኛ አቅም ያለው ነው፡፡ ሥራ ለሰው ልጅ የሕልውና መሠረትና የዕድገት አብይ ቁልፍ በመሆኑ ጠንካራ የሥራ ባህል ባደገባቸው ሀገሮች የዜጎች ሕይወት በየትኛውም አቅጣጫ የተመቻቸ ነው፡፡ ሥራን ሳይንቁ በሥራነቱ አክብረው የሠሩ ሕዝቦች ከአንደኛው የዕድገት ዕርከን ወደ ተሻለው ዕርከን በመሸጋገር የሀገራቸው ኢኮኖሚ በጠንካራ መሠረት ላይ እንዲቆም ያደርጋሉ፡፡

ሥራ በአብዛኛው ማሕበራዊና የብዙ ዜጎችን ተሳትፎ የሚጠይቅ ስለሆነ ለሀገር ልማት ሁሉም የአቅሙንና የችሎታውን መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ አንዱ እየሠራ ሌላው ሳይሠራ የሚጠቀምበት ሁኔታ ከግለሰብና ከቤተሰብ አልፎ በሀገር ደረጃም ጉዳት የሚያመጣ ነው፡፡ ሥራ በአገልጋይና በተገልጋይ መካከል ያለ ድልድይ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህም እያንዳንዱ ባለሙያ የሙያ ችሎታውንና የሙያ ሥነ ምግባሩን በማጣመር ለጠንካራ የሥራ ባህል ራሱን ማስገዛት ይኖርበታል፡፡

የኢፌዲሪ ሕገመንግሥት የኢኮኖሚ ነክ ዓላማ ሁሉም ዜጎች በሚችሉት ሙያ በዕኩልነት ተሠማርተው ሀገራቸውን እንዲያለሙ ሰፊ ዕድል ሰጥቷል፡፡ ይህንን የዜግነት መብት በመጠቀም እያንዳንዱ ባለሙያ የሙያ ሥነ ምግባርን በመላበስና ሙያውን ከጊዜ ወደ ጊዜ በማሻሻል የሀገሩን ኢኮኖሚ ለማገዝ ይችል ዘንድ ጠንካራ የሥራ ባህልን ማዳበር ይኖርበታል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

*ከእጅ ወደ አፍ፣* ተቀማጭ የሌለው፣ ትርፍ የማይገኝበት ገቢ፡፡
*ፅኑ፣* ጠንካራ፣ የማይበገር፣ የማይሸነፍ፡፡
*ከበድ ሳም፣* ልትወልድ የደረሰች ሳም፡፡
*መኖ፣* ለከብቶች የሚዘጋጅ ምግብ፡፡
*ምፅዋት፣* ለልመና የሚሰጥ፣ የሚለገስ፣ ለጽድቅ ተብሎ በዓይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ፡፡
*የጋን መብራት፣* የማይታይ፣ ዕውቀቱ ለሌሎች የማይተርፍ፡፡
*ተጋሳጭ፣* ተጎጂ፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

*I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ «ሀሰት» ብላችሁ መልሱ::*

1. ሀገር የምትለማው ሕዝቦቿ ጠንካራ የሥራ ባህልን በማዳበር ጠንክረው ሲሠሩ ነው::
2. ጠንክሮ መሥራት ያለበት በገጠር አካባቢ የሚኖረው አርሶ አደር ብቻ ነው::
3. አንድ ባለሙያ ከሙያው በተጨማሪ የሙያ ሥነ ምግባርን ማክበር አለበት::
4. አንድ ሠራተኛ በሠለጠነበት ሙያ ሥራ ካላገኘ ከሙያው ውጭ ቀላል ሥራዎችን መሥራት የለበትም::
5. ሳይሠሩ መብላት ጥገኝነት ከሚገለጽባቸው ሁኔታዎች አንዱ ነው::

*II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የኢኮኖሚ ነክ ዓላማ፣ | ሀ. ጊዜን በአግባቡ መጠቀምና ደንበኛን ማክበር ነው:: |
| 2. የሙያ ሥነ ምግባር አንዱ መገለጫ፣ | ለ. ለሕዝቦች ዕድገትና ልማት መሠረት ነው:: |
| 3. ጠንካራ የሥራ ባህል መዳበር፣ | ሐ. ዕውቀቱ ለሌሎች የማይተርፍ ሰው:: |
| 4. ጥገኝነትን መፀየፍ፣ | መ. የሠራተኛውን ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ማሟላት። |
| 5. የጋን መብራት፣ | ሠ. የዓሣ ማጥመጃ መረብ:: |
| | ረ. ሌሎች በደከሙበት ውጤት ለመኖር አለመፈለግ። |

*III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ::*

1. አንድ ባለሙያ የሚጠበቅበት ግዴታ፤
   - ሀ. የሙያ ችሎታ፣
   - ለ. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣
   - ሐ. የሙያ ሥነ ምግባር፣
   - መ. ሁሉም::
2. አንድ ሀገር ልትለማ የምትችለው፤
   - ሀ.ጠንካራ የሥራ ባህል ሲዳብር፣
   - ለ. ሳይሠሩ መብላት ሲጠናከር፣
   - ሐ. የተወሰኑ ሥራዎች ዕኩል ከበሬታ ሲያገኙ፣
   - መ. ሁሉም መልስ ሲሆኑ ይችላሉ::
3. ለስ ሥራ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ጥገኝነትን መዋጋት፣
   - ለ. በሙያ ሕዝብን ማገልገል፣
   - ሐ. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፣
   - መ. ሳይሠሩ መብላት::
4. የአንድ ሕዝብ ማህበራዊ ችግር የሆነው የትኛው ነው?
   - ሀ. ጠንካራ የሥራ ባህል፣
   - ለ. ልመና፣
   - ሐ. ዕኩልነት፣
   - መ. ሁሉም::
5. ከሚከተሉት መካከል አንዱ የግብርና ሥራ አይደለም::
   - ሀ. ከብት ማድለብ፣
   - ለ. ደን ማልማት፣
   - ሐ. ዘመናዊ እርሻ፣
   - መ. የማዕድን ቁፋሮ

*IV የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ትክክለኛውን ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. የሀገራችን ዕድገት በተግባር ሲታይ የሚችለው የሕዝቡ ——— ባህል ሲዳብር ነው::
2. ከሀገራችን ማሕበራዊ ችግሮች መካከል ——— እና———- ይጠቀሳሉ::
3. አንድ ባለሙያ ከሙያ ችሎታው በተጨማሪ ሲያከብረው የሚገባው ምግባር ______ ይባላል::

*V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::*

1. የሥራ ትንሽ/ትልቅ የለውም ሲባል ምን ማለት ነው?
2. ጥገኝነት በምን በምን ይገለፃል?

# ምዕራፍ ስምንት

# ራስን መቻል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** *ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤*

- የማሕበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ ጥገኝነትን ምንነት ትገነዘቢያለሽ/ትገነዘባለህ፡፡
- የራስን ጽኑ እምነት ከሌሎች ሰዎች ሀሳብ ጋር የማጣጣምን አስፈላጊነት ትገነዘቢያለሽ/ትገነዘባለህ፡፡

## 8.1 ራስን የመቻል ጠቀሜታ፤

- በተለያዩ አጋጣሚዎች የተገነዘባችሁትን መሠረት በማድረግ ራስን የመቻል ጠቀሜታ ግለጹ፡፡
- በምትኖሩበት አካባቢ በራሳቸው የሚተማመኑ ናቸው የምትሏቸውን ሰዎች ስም ጥቀሱ፡፡ በራሳቸው ይተማመናሉ ያላችሁበትን ምክንያትም ግለጹ፡፡

**ራሴን ችያለሁ፤**

ችሎታዬን አቅሜን መዝኜ አውቄያለሁ፣
የቻልኩትን በአቅሜ ተግቼ እሠራለሁ፡፡
እውቀት እያጋራሁ እኔም እየተማርኩ፣
ከሰው ጥገኝነት ከመመጽወትም ዳንኩ፣
ከሰው እንደማላንስ በራሴም ተማመንኩ፡፡
ከእንግዲህ አልኖርም ከሰው ተጠግቼ፣
ለልመና ምጽዋት እጆቼን ዘርግቼ፡፡
ራሴን በራሴ አስተዳድራለሁ፣
አልሆንም ተመጽዋች ራሴን ችያለሁ፣
ራሴን ስለቻልኩ ብርታት አግኝቻለሁ፡፡

**መልመጃ 1**

*ከላይ የቀረበውን ግጥም መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ራስን ስመቻል ምን ማድረግ ያስፈልጋል?
2. ከግጥሙ ውስጥ ራስን በመቻል የሚገኙ ጥቅሞችን የሚገልጹትን ሐረጎች እና ስንኞች በማውጣት ተወያዩባቸው፡፡

ራስን መቻል ማለት በየደረጃው ያለን የራስን ዕውቀት የኢኮኖሚ አቅም እና ጉልበት በመጠቀም ኃላፊነትን ወስዶ ለራስ፣ ለቤተሰብ እና ለሀገር የሚጠቅሙ ተግባራትን በማከናወን ከጥገኝነት መላቀቅ ማለት ነው፡፡ ይህም በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት፣ በማሕበራዊ ግንኙነት፣ በኢኮኖሚም ሆነ በአስተሳሰብ የሌሎች ጥገኛ ሳይሆኑ የራስን ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐትን ለማርካት ያስችላል፡፡ ለምሳሌ ተማሪዎች ኃላፊነትን በመውሰድ ራሳቸውን ችለው ሊያከናውኑት የሚገባ ተግባር የትምህርት ቤታቸውን ሥነሥርዓት በማክበር ትምህርታቸውን በትጋት መማር ነው፡፡

ይህንን ካደረጉ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው እና ለሀገራቸው የሚጠቅሙ ዜጐች ይሆናሉ፡፡ የትምህርታቸውን እና የጥናት ጊዜያቸውን በማይጐዳ ሁኔታ ወላጆቻቸውን በሥራ በመርዳትና ራሳቸውን በማገዝ ለወደፊቱ ሕይወታቸው ጠንካራ መሠረት መጣል ያስፈልጋል፡፡

ባጠቃላይ ራስን መቻል ለማሕበራዊ እና ለኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት ሳይጋለጡ በራስ በመተማመን፣ የራስን አመለካከት መከተል፣ የራስን አቋም መውሰድ እና መወሰን ያስችላል፡፡ ራሳቸውን የቻሉ ሰዎችም የእኩልነት ስሜት ስለሚሰማቸው ከሌሎች ለሚገኝ ጥቅም አያጐበድዱም። ተመፅዋቾችም አይሆኑም፡፡ ስለዚህም ነጻነታቸውን ጠብቀው በራሳቸው ተነሳሽነት እና ሀላፊነት የሚሰሩ ጠንካራ የልማት ሀይል ይሆናሉ፡፡

**መልመጃ 2**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ከመካከላችሁ አንድ አወያይና አንድ ፀሀፊ ምረጡ፡፡ ከዚያም አጻችሁን እያወጣችሁ ራስን በመቻል የሚገኙ ጥቅሞችን ዘርዝሩ፡፡ ፀሀፊው ጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፍ፡፡ በመቀጠል ከቀረቡት ዝርዝሮች ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን እና ያልሆነውን በምክንያት እየለያችሁ ተወያዩ፡፡ በመጨረሻም የጋራ አቋም ላይ ድረሱ፡፡

## 8.2 ጥገኝነት፤

### 8.2.1 ጥገኝነት ምንድን ነው?



ሥዕል 8.1 በፈተና ክፍል ውስጥ የሚኮርጅ ተማሪ

- በሥዕሉ ላይ ሲኮርጅ የሚታየው ተማሪ ጥገኛ የሆነበት ምክንያት ምን ይመስላችኋል?
- ይህ ተማሪ ከጥገኝነት ተላቆ ራሱን ለመቻል ምን ማድረግ አለበት?

**ጥገኛው ልጅ፤**

አቶ እስማኤል፤ ፈትያ እና አህመድ የተባሉ ሁለት ልጆች አሏቸው፡፡ በተጨማሪም ዘይኑን በጉዲፈቻ ያሳድጋሉ፡፡ ዘይኑ ወላጆቹ ስለሞቱበት ነው አቶ እስማኤል የሚያሳድጉት፡፡

አህመድ ክብደት የማንሳት ስፖርት ያዘወትራል፡፡ ምግብም በደንብ ይመገባል፡፡ ስለዚህ አካሉ በጣም ጠንካራ እና የተገነባ ነው፡፡ ፈትያ ልብሱን ታጥብለታለች፡፡ ዘይኑ መኝታ ክፍሉን ያፀዳለታል፡፡ አህመድ ተሠርቶ የቀረበለትን ምግብ ለመብላት እንኳ ለእጆቹ መታጠቢያ ውሀ ቶሎ ካልቀረበለት ይቆጣል፡፡ ትምህርት ቤትም የክፍል ጓደኞቹ በጉልበቱ ስለሚፈሩት በፈተና ጊዜ ያስኮርጁታል፡፡

ዘይኑ ግን ጥገኛ መሆን ስለማይፈልግ በቤት ውስጥ በአቅሙ የቻለውን ሥራ ያግዛል፡፡ ዕውቀት ለማግኘት ስለሚፈልግም ጥናቱን አጥንቶ፤ የተሰጠውን የቤት ሥራም ቶሎ ሠርቶ ወደ አቶ እስማኤል ጋራዥ ይሄዳል፡፡ እዚያም ለመካኒኮቹ እቃ እያቀበለ የሚሠሩትን ያስተውላል፡፡

አቶ እስማኤል በዘይኑ ሁኔታ ቢደሰቱም በአህመድ ግን በጣም ያዝናሉ፡፡ የወደፊት ሕይወቱም በጣም ያሳስባቸው ነበር፡፡

ታዲያ አንድ ቀን አህመድ ያለበትን አደገኛ ሁኔታ የሚያስገነዝቡበት ዘዴ ያገኙ ስለመሰላቸው፣ ሁለቱንም ጠሩዋቸውና "እኔ እያረጀሁ ነው፡፡ ስለዚህ ጋራዡን ከሁለት አንዳችሁ በሀላፊነት ታስተዳድራላችሁ፡፡ በመጀመሪያ ግን አንደኛችሁን ለመምረጥ እንድችል ስለጋራዥ ያላችሁን ዕውቀት የሚያሳውቀኝ ፈተና እሰጣችኋለሁ" አሉ፡፡

ዘይኑ ቶሎ ብሎ "እሺ" አለ፡፡ አህመድ ግን ምንም ሠርቶ ወይም ሌሎች ሲሠሩ አስተውሎ ስለማያውቅ በራሱ መተማመን አልቻለም፡፡ ወዲያውም ተበሳጭቶ "አባዬ እኔ የአንተ ልጅ ነኝ፡፡ ስለዚህ ከጥገኛ ጋር አልወዳደርም" አላቸው፡፡ አቶ እስማኤልም ጥገኛ ባህሪይ ያለው አህመድ መሆኑ የበለጠ ጎልቶ ስለታያቸው በጣም አዝነው "ጥገኛ አንተ እንጂ ዘይኑ አይደለም" አሉት፡፡

**መልመጃ 3**

***በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. አቶ እስማኤል ዘይኑ ጥገኛ አይደለም ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
2. አህመድ በራሱ ተማምኖ እንዳይወዳደር እንቅፋት የሆነበት ነገር ምንድን ነው?
3. በእናንተ አስተሳሰብ ከዘይኑ እና ከአህመድ የጥገኝነት አስተሳሰብ ያለበት ማን ነው?
4. አህመድ ለወደፊት ሕይወቱ በራሱ የሚተማመን ራሱን የሚመራ እና የሚያስተዳድር ዜጋ እንዲሆን ምን ማድረግ አለበት?

ጥገኝነት ማለት የራስ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐት በሌሎች እውቀት ፣ገንዘብ፣ እና ጉልበት እንዲሟላ መጠበቅ ማለት ነው፡፡ ይህ ፍላጐት ባለን አቅም እንዳንጠቀም፣ ለራሳችንም ክብር እንዳይኖረንና ነጻነታችንን ለሌሎች አሳልፈን እንድንሰጥ ያደርገናል፡፡ በራሳችንም እምነት ስለማይኖረን ሥራዎችን ለመሥራት እንፈራለን፡፡

ሥራን ካልሠራን ደግሞ እውቀታችን ሊዳብር አይችልም፡፡

በእውቀት ራሳችንን በማሳደግ ውጤታማ ሥራዎችን የምንሰራበትን የወጣትነት ዘመን በዋዛ እና በፈዛዛ እንድናሳልፍ ያደርገናል፡፡ ይህም የሀገር ሸክም የመሆንን እጣ ፋንታ ይዞ ይጠብቀናል፡፡ ስለዚህ መልካም ዜጐች ሆነን ለሀገርና ለወገን ዕድገትና ብልጽግና መሥራት እንድንችል የጥገኝነት አስተሳሰብን ከልጅነት ጀምረን ልናስወግደው ይገባል፡፡

መልመጃ 4

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

?

1. ጥገኝነት ራሳችንን በእውቀት እንዳናሳድግ እንቅፋት የሚሆንብን እንዴት ነው?
2. ጥገኝነት በራስ መተማመንን እንዴት ያሳጣል?
3. ጥገኝነት እንዴት ነው ነጻነታችንን ሊያሳጣን የሚችለው?

### 8.2.2 ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት፣

- ኮንትሮባንድ ንግድ የሚያደርሰውን ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ግለጹ፡፡

**እንቆቅልሽ/እንቆቅልህ፣**

| እንቆቅልሽ / እንቆቅልህ ቁጥር 1 | እንቆቅልሽ / እንቆቅልህ ቁጥር 2 |
|---|---|
| *1. እንቆቅልሽ (ህ)*<br>*ምናውቅልህ (ሽ)*<br>**ጥያቄ፣** ኮንትሮባንድ ንግድ ምንድነው ጉዳቱ?<br>**መልስ፣** ጥራት የሌላቸውና ያልተመረመሩ እቃዎች፣ መድሃኒት ምግቦችን ወደ አገር ማስገባቱ?<br>**ጥያቄ፣** ሌላስ ምን ይጐዳል?<br>**መልስ፣** ወንጀል መፈጸሚያ የጦር መሳሪያዎች፣ አእምሮ እሚጐዱ አደንዛዥ እፆች፣ ድንበር እየጣሱ በድብቅ ያልፋሉ፣ የሕዝቦችን ሠላምና፣ ጤና ይነሳሉ። | *2. እንቆቅልህ*<br>*ምናውቅልህ (ሽ)*<br>**ጥያቄ፣** ኮንትሮባንድ ንግድ አገር ያደኸያል፣ እርዳታ ጠባቂ ጥገኛ፣ ያደርጋል እንዴት እንደሆነ ይኼን ማን ያብራራል?<br>**መልስ፣** እኔ አብራራዋለሁ፣ ቀረጥ ታክስ ሳይከፍሉ እንደሚያልፉ አውቃለሁ፡፡ ኮንትሮባንዲስቶች ግብር አጭበርብረው፣ የህዝብን ገንዘብ ሰርቀው ያስቀራሉ፡፡<br>**ጥያቄ፣** ምን ይሻላል ታዲያ?<br>**መልስ፣** ኢትዮጵያ እንድትቆም ከሀብታሞች ተርታ፣ ጥገኛ ሳትሆን በብድር በርዳታ፣ የህዝቦቿን ሰላም ጤና የሚነሳውን፣ የግብር የቀረጥ የታክስ ገቢዋን፣ ሰርቆ የሚያስቀረውን እንዋጋዋለን ኮንትሮባንድ ንግድን። |

**መልመጃ 5**

*በእንቆቅልሹ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ከላይ የቀረበውን እንቆቅልሽ በደንብ አጥኑትና በቃላችሁ ይዛችሁ ሁለት ሁለት እየሆናችሁ በእንቆቅልሽ ጨዋታ ደንብ ተጫወቱ።
2. አንድ አወያይና አንድ ፀሀፊ ምረጡ። በመቀጠልም ከእንቆቅልሹ ውስጥ የተገለጹትን ኮንትሮባንድ ንግድ በሀገር ላይ የሚያደርሰውን ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጉዳቶች በዝርዝር እየጠቀሳችሁ ተወያዩ።
3. ዕቃዎች በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ወይም ከሀገር ሲወጡ ስለመያዛቸው በየጊዜው በመገናኛ ብዙሀን ሲዘገብ እንሰማለን። የእቃዎች መያዝ ብቻ አይደለም፤ የዕቃዎቹ ባለቤቶችም በፍርድ ቤት ቀርበው ከፍተኛ የሆነ የገንዘብና የእስር ቅጣት ይበየንባቸዋል። ታዲያ ለኮንትሮባንድ ንግድ ይህ ሁሉ ትኩረት ለምን የተሰጠ ይመስላችኋል?

**የኮንትሮባንድ ንግድ፤**

*የሀገሪቱን ሕግ በመጣስ በሕገወጥ መንገድ ዕቃዎችን ድንበር ጥሶ ከሀገር የማስወጣት እና ወደ ሀገር የማስገባት ተግባር ነው። በመሆኑም መንግሥት ለተለያዩ ማሕበራዊ አገልግሎቶች መገንቢያ ሊገለገልበት የሚችለውን ከቀረጥና ከውጭ ምንዛሪ የሚገኝ ገቢ በማሳጣት ሀገራችንን ለኢኮኖሚ ጥገኝነት ይዳርጋታል።*

*በሌላም በኩል ከባህላችን ጋር ተጻራሪ የሆኑ እና በማሕበራዊ ሕይወት ውስጥ ችግር የሚያስከትሉ ፖስተሮች፣ ፊልሞች፣ ሥዕሎች ወዘተ... ይገባሉ። የጦር መሣሪያዎችም በድብቅ ድንበር ጥሰው እንዲገቡ ያስችላል። እነዚህ በሕገ ወጥ መንገድ የገቡ መሣሪያዎች ባልተፈቀደላቸው ሰዎች እጅ በመዘዋወር ለሽብርና ለዝርፊያ ተግባር ይውላሉ።*

*የምርት ጥራታቸው፣ አገልግሎት ላይ የሚውሉበት ዕድሜ፣ በመንፈስም ሆነ በአካል ላይ ጉዳት ስላለማድረሳቸው በባለሙያ ያልተረጋገጠላቸው ምግቦችና መድሀኒቶች ወደ ሀገር እንዲገቡ ያደርጋል።*

*በዓለም ደረጃ ወደ ተደራጀ የወንጀል እንቅስቃሴ እያደገ የሄደው አዕምሮን የሚጎዱ እጾችም የሚዘዋወሩት በዚሁ በኮንትሮባንድ ንግድ አማካይነት ነው። ስለዚህ በሀገር ላይ ከፍተኛ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ የሚያስከትል በመሆኑ ሁሉም ሰው ኮንትሮባንድ ንግድ የዕድገትና የሠላም ጠንቅ መሆኑን ሊገነዘብና ሊዋጋው ይገባል።*

**መልመጃ 6**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ኮንትሮባንድ ንግድ በኢኮኖሚና በማሕበራዊ ሕይወት ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ዘርዝሩ።
2. በኮንትሮባንድ ንግድ ሥራ ላይ የሚሳተፉ ምን ዓይነት ባህሪ ያላቸው ሰዎች ናቸው?

## 8.3 በራስ መተማመን፤

### 8.3.1 በራስ የመተማመን ባህሪ የሚገለጥባቸው መንገዶች፣

- *በራስ መተማመን የሚገለጹባቸው ተግባራት ናቸው የምትሏቸውን ዘርዝሩ።*
- *በራሳቸው የሚተማመኑ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የሚታወቁባቸውን ባህሪያት ግለፁ።*

**የተማሪው ውጤት፤**

*መምህሩ የፈተና ውጤት ለተማሪዎች በቃል በመንገር ላይ ነበሩ። በመካከሉ አንድ ተማሪ አጠገቡ ለተቀመጠው ተማሪ በሹክሹክታ፣*

*"መምህራችን ውጤቴን አሳስተውብኛል" አለ። ጓደኛውም፣*
*"እረ ዝም በል። እንዴት ተሳሳትክ ትለኛለህ ብለው ይቆጣሉ" አለው።*
*"እኔ እርግጠኛ ነኝ። ማስረዳት እችላለሁ" አለ። ከዚያም ከተቀመጠበት ተነሳና፣*
*"ጋሼ? የኔን ውጤት አሳስተውብኛል" አላቸው።*
*መምህሩም ኮስተር ብለው፣*
*"የፈተና ወረቀታችሁን በትክክል ካረምኩ በኋላ ነው መዝግቤ ያመጣሁት" አሉ።*

ተከታትያለሁ፡፡ የተሰጡ የቤት ሥራዎችንም ሁሉ ሠርቼአለሁ፡፡ ለፈተናም ተዘጋጅቼ ነው የገባሁት። በደንብ ስለተ ዘጋጀሁ ፈተናውም አልከበደኝም፡፡ ስለዚህ የነገሩኝ ዝቅተኛ ውጤት የኔ ሊሆን አይችልም" አላቸው፡፡

መምህሩም ተማሪው ያቀረባቸው ምክንያቶች አሳማኝ ስለሆኑባቸው ወደ ቢሮ ተመልሰው ሄዱ፡፡ ከዚያም የተማሪውን የፈተና ወረቀት ሲያዩ በጣም ተገረሙ፡፡ ምክንያቱም ተማሪው ያመጣው ውጤት በጣም ከፍተኛ ነበር፡፡ ወደ ክፍል ተመለሱና ይቅርታ ጠየቁት፡፡

## መልመጃ 7

### በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ተማሪዎች አንድ አወያይ እና አንድ ፀሀፊ ምረጡ፡፡ ከዚያም ከላይ ከቀረበው ምንባብ ተነስታችሁ ተማሪው በራሱ እንዲተማመን ያስቻሉትን ምክንያቶች በዝርዝር ግለፁ፡፡ ደብተራችሁ ላይም ማስታወሻ መፃፍ አትዘ ንጉ፡፡
2. እናንተ እንደ ጉበዙ ተማሪ ዓይነት ችግር ቢያጋጥማችሁ ምን ታደርጋላችሁ?
3. ጉበዙ ተማሪ ሀሳቡ በመምህሩ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያስቻሉትን ምንክያቶች ግለፁ፡፡

በራስ መተማመን ራስን ከመቻል ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ በጥገኝነት የሚኖር ሰው በምንም ሁኔታ ቢሆን በራሱ የሚተማመን ዜጋ መሆን አይችልም፡፡ ራስን ለመቻል ደግሞ ጠንካራ የሥራ ባህል መኖር መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በጠንካራ የስራ ባህል ታንጾ ራሱን የቻለ ዜጋ በራሱ መተማመኑ አይቀ ርም፡፡ እንዲህ ዓይነት በራሱ የሚተማመን ሰው ስለራሱ ትክክለኛ ግንዛቤ ያለው ነው፡፡

ስለዚህም ተወያይቶ ለመረዳዳትና የራሱን አስተሳሰብ ከሌሎች ጋር ለማስማማት እንዲ ሁም ስህተቶችን አምኖ ለመቀበልና ለማረም አይቸገርም፡፡ ከዚህም ባሻገር በራሳቸው የሚተ ማመኑ ዜጐች የሌሎችን አስተሳሰብ በነጻነት ስለሚያስተናግዱ ለሀገራችን ዴሞክራሲ፣ ሠላ ምና ልማት ግንባታ ወሳኝ ድርሻ አላቸው፡፡

## መልመጃ 8

### የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. በራስ ስመተማመን ራስን መቻል ስምን ያስፈልጋል?
2. በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎችን መለያ ባህር ያት ግለጹ።

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ራስን መቻል የሥራ ባህልን ከማዳበር እና ሀላፊነትን ለመቀበል ዝግጁ ከመሆን ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ራስን መቻል በራስ የመተማመን ስሜትን ይፈጥራል፡፡ ተመጽዋችነትን አስወግዶ በእኩልነት መኖር ያስችላል፡፡ በአንጻሩ ግን ጥገኝነት አቅምን እያዳከመ የሞራል ውድቀትን የሚያስከትል የሕይወት ጠንቅ ነው፡፡

የሀገርን ጤና፣ ኢኮኖሚ፣ ሠላም እና ማሕበራዊ ሕይወት በከፍተኛ ደረጃ የሚያናጋው የኮንትሮባንድ ንግድም እንኳ የጥገኝነት አስተሳሰብ ውጤት ነው፡፡ ስለዚህ ስለራሳችን አቅም ትክክለኛ ግንዛቤ በመያዝ፣ የራሳችንን አስተሳሰብ ከሌሎች አስተሳሰብ ጋር ማስማማት ይገባናል፡፡

ለራሳችን፣ ለቤተሰባችንና ለሀገራችን ይጠቅማሉ ብለን ያመንባቸውን ጉዳዮች በጽናት ማራመድ እና ስህተቶቻችንን አምነን በመቀበል ማረም ጠቃሚ ነው፡፡ ለአንድ ሀገር ዕድገት እና ብልጽግና ዜጐች ራሳቸውን ለመቻል የሚያደርጉት መፍጨርጨር እና በራስ መተማመን ወሳኝ ድርሻ አላቸው፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

***ምፅዋት፣*** ምንም ሳይሰሩ በልመና የሚገኝ ማናቸውም ነገር።

***ተመጽዋቾች፣*** ምንም ሳይሰሩ ቁሳዊና መንፈሳዊ እርካታቸውን ከሌሎች የሚያገኙ፣ ለማኞች፡፡

***ጉቦ፣*** ሕጋዊም ሆነ ሕጋዊ ያልሆነን ጉዳይ ለማስፈፀም ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚሰጡት ወይም የሚቀበሉት ገንዘብ ወይም ሌላ የዓይነት ስጦታ፣ መማለጃ፡፡

***ዕውቀትን ማጋራት፣*** የሚያውቁትን ለሌሎች ማሳወቅ።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

### I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡

1. ራስን መቻል የተመጽዋችነት ስሜትን ለማስወገድ ይረዳል፡፡
2. የጥገኝነት ስሜት አቅማችንን ሙሉ በሙሉ እንዳንጠቀምበት ያደርገናል፡፡
3. ያቅምን ያህል ሌሳውን ሰው መርዳት ራሳችንን እንዳንችል እንቅፋት ይሆንብናል፡፡
4. በራሳችን መተማመን የምንችለው ስለ ራሳችን ትክክለኛ ግንዛቤ ሲኖረን ነው፡፡
5. የራሳችንን አስተሳሰብ ከሌሎች ጋር ማስማማት እንድንችል የሌሎችን ሀሳብ ሁሉ ተቀብለን መፈፀም አለብን ፡፡

### II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ራስን መቻል፣ | ሀ. የአገርን ኢኮኖሚና የሕዝብን ሠላም ይጐዳል፡፡ |
| 2. ራሱን ያልቻለ ተማሪ፣ | ለ. በራሱ የሚተማመን፡፡ |
| 3. ስለራሱ ትክክለኛ ግንዛቤ ያለው፣ | ሐ. ጥገኛ፡፡ |
| 4. ጉቦ በመስጠት ጉዳይ ማስፈፀም፣ | መ. ተከራክሮ ማሳመን ወይንም የሌሳውን ሰው ሀሳብ አምኖ መቀበል፡፡ |
| 5. ኮንትሮባንድ ንግድ፣ | ሠ. ፈተና ኮርጆ የሚሠራ፡፡ |

### III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. በራስ መተማመን፤
   ሀ. ማንም ሰው ጥረት ካደረገ በሩጫ አንደኛ መውጣት ይችላል ማለት ነው፣
   ለ. ችሎታን እና አቅምን አመዛዝኖ በመረዳት በራስ ጥረት ራስን የመቻል መሠረት ነው፣
   ሐ. ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጐትን ለማሟላት የሌሎች ጥገኛ አለመሆን ነው፣
   መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው፡፡
2. ራስን ለመቻል፤
   ሀ. ታዋቂ ሰው መሆን ያስፈልጋል፣
   ለ. ተገዶ መሥራት ያስፈልጋል፣
   ሐ. በዕውቀት ራስን ማበልፀግና ማጠናከር ያስፈልጋል፣
   መ. ለ እና ሐ መልስ ናቸው፡፡
3. በራሳቸው የሚተማመኑ ሰዎች፤
   ሀ. የሌሎችን ሰዎች ሀሳብ አይቀበሉም፣
   ለ. አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር ይደፍራሉ፣
   ሐ. የሰዎችን ሀሳብ በፅሞና በዳመጥ የራሳቸውን እምነትም ለሌሎች ያስረዳሉ፣
   መ. ከሀ በስተቀር ሁሉም ትክክለኛ መልሶች ናቸው፡፡
4. ጥገኝነት፤
   ሀ. ያለድካም መኖር ስለሚያስችል ጠቃሚ ነው፣
   ለ. ሞራልን እያሳሸቀ የበታችነት ስሜትን ይፈጥራል፣
   ሐ. የዕድገት መሠረት ነው፣
   መ. ሁሉም መልሶች ናቸው፡፡
5. ስህተትን አምኖ መቀበል ጠቃሚ የሚሆነው፤
   ሀ. ከሀይለኛ ሰዎች ቁጣና ቅጣት ለመዳን ሲባል ከተደረገ ነው።
   ለ. ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የተደረገ ነው።
   ሐ. የነገሮችን ትክክለኛ ገፅታ ለማግኘት ሲባል የተደረገ ሲሆን ነው።
   መ. ለሌሎች ዘንድ ሙገሳና ጥቅም ለማግኘት ሲባል የተደረገ ሲሆን ነው።

## IV የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ፡፡

1. ድንበርን እየጣሱ ሸቀጦችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ________ ይባላል፡፡
2. እንደ ቦይ ውሃ ሁልጊዜ በሌላ ሰው ሀሳብ መመራት የ ____________ ባህሪ መግለጫ ነው፡፡
3. ሥልጣን ባላቸው ሰዎች አማካኝነት የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የሚሰጥ መደለያ ________ ይባላል፡፡

## V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ጥገኝነት የሚያደርሰውን ጉዳት ግለጹ፡፡
2. ራስን ከመቻል የሚገኙ ጥቅሞች ዘርዝሩ፡፡
3. የራሳችንን ጽኑ እምነት እና አስተሳሰብ ከሌሎች ሰዎች ጋር ማጣጣም ለምን ያስፈልጋል?

# ምዕራፍ ዘጠኝ
# የቁጠባ ባህል

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- የቁጠባ ጠቀሜታን ታውቂያለሽ/ታውቃለህ::
- አላስፈላጊ ወጪዎችን መቀነስ የቁጠባ አንዱ መገለጫ መሆኑን ትረዳለሽ/ትረዳለህ::
- ራስን በአቅም ልክና በእቅድ በመምራት እንዴት የቁጠባ ባህልን ማዳበር እንደሚቻል ትገነዘቢያለሽ/ትገነዘባለህ::

## 9.1 ቁጠባ፤

### 9.1.1 የቁጠባ ጠቀሜታ፣

- በአካባቢያችሁ በቁጠባ አማካኝነት እራሳቸውን የቻሉ ሰዎችን ታውቃላችሁ? የቀድሞውንና የአሁኑን አኗኗራቸውን በማነፃፀር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ::

**ትርሲትና ወንድሞቿ፤**

ትርሲትና ሁለት ወንድሞቿ እናትና አባታቸው በመኪና አደጋ ከሞቱ አንድ ዓመት አልፏቸዋል:: ነገር ግን ወላጆቻቸው በሕይወት ሳሉ በቁጠባ ያጠራቀሙት ገንዘብ በመኖሩ ልጆቻቸው ያለችግር መኖራቸውን ቀጥለዋል:: ትርሲት አስተዋይ ልጅ ስለሆነች ታናናሾች ወንድሞቿን በመምራት ያላቸውን ገንዘብ በአግባቡ እየተጠቀሙ ትምህርታቸውን መከታተል እንዳለባቸው አስረዳቻቸው:: እናም ገንዘቡን እየመጠኑ በመውሰድ ተሳስበው ይኖራሉ::

"ወላጆቻችን ባለውለታዎቻችን ናቸው:: ይህን ጊዜ እነርሱ ያስቀመጡት ገንዘብ ባይኖር ልን ኖሮ ዛሬ መድረሻችን ምን ይሆን ነበር?" እያሉ ያመሰግኗቸዋል::

**መልመጃ 1**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. እነትርሲት ትምህርታቸውን ያለማቋረጥ ሲማሩ የቻሉት ወላጆቻቸው ባስቀመጡላቸው ገንዘብ መሆኑን ከታሪኩ መረዳት ይቻላል:: ወላጆቻቸው ገንዘብ የቆጠቡት በድንገት እንደሚሞቱ አውቀው ነው ወይስ አይደለም? መልሳችሁ አዎን ከሆነ እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? መልሳችሁ አውቀው አይደለም ከሆነ ገንዘብ ለምን እንዳስቀመጡ አስረዱ::
2. በታሪኩ መሠረት እነትርሲት ራሳቸውን እስከሚችሉ ድረስ ያለችግር ለመማር ከወላጆቻቸው የወረሱትን ገንዘብ እንዴት መጠቀም ይኖርባቸዋል?

ቁጠባ ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት:: በተወሰነ ጊዜ የሚገኝ ገቢን በማብቃቃት ለወደፊት ለማስቀመጥና ያልታሰቡ ችግሮች በሚያጋጥሙ ጊዜ እነዚያን ችግሮች ለመቋቋም ይጠቅማል::

ቁጠባ መሰረታዊ ፍላጎቶችን አሟልቶ ለመኖር እጅግ ጠቃሚ ነው:: የሰዎች መሠረታዊ ፍላጎቶች የሚባሉት ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ናቸው:: ቁጠባ ግለሰቦችም ሆኑ ቤተሰቦች ራሳቸውን እንዲችሉና በራስ የመተማመን ችሎታ እንዲኖራቸው ያደርጋል:: ራሳቸውን የቻሉ ሰዎች የጥገኝነት ወይም የበታችነት ስሜት አያድርባቸውም::

ቁጠባ በትምህርት ራስን ለማሳደግ ያስችላል:: ስለትምህርት ሲነሳ ብዙ ጊዜ በአእምሯችን የሚመጣው የልጆች ትምህርት ብቻ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ትምህርት እድሜ አይገድበውም:: ወላጆች ራሳቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ካልሆኑ ኑሯቸውን ለማሻሻል ሲሉ እየሰሩ ሊማሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ በየትምህርት ቤቶቹና በየኮሌጆቹ የማታ ተከታታይ ትምህርት ክፍሎች የሚማሩ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ መደበኛ ሥራ ያላቸውና የቤተሰብ ኃላፊዎች ናቸው:: ይህን ለማድረግ የሚችሉት ግን ከሚያገኙት ገቢ ላይ በመቆጠብ ለትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ክፍያ እየሸፈኑ ነው::

ቁጠባ በህመም፣ በእርጅናና በሌሎችም ምክንያቶች የመሥራት አቅም በማይኖርበት ጊዜ የሰውን እጅ ከማየት ያድናል::

የተመቻቸ ኑሮ ለመኖር ይጠቅማል:: የተመቻቸ ኑሮ ማለት ራስን ችሎ መኖር ማለት ነው::

መልመጃ 2

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

?

1. ከቤተሰባችሁ ወይም ከምታውቁት የአካባቢ ሁኔታ በመነሳት፣ ከላይ በምንባቡ ከተጠቀሱት የቁጠባ ጠቀሜታዎች መካከል ሶስቱን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ገለጹላቸው::
2. በእናንተ ደረጃ ልትቆጥቡት የምትችሉት ነገር ካለ አስረዱ::

### 9.1.2 ልዩ ልዩ የመቆጠቢያ ዘዴዎች፣

- የመቆጠቢያ ዘዴ ሲባል ምን ማለት ነው? ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለፁ።

**አሥር ጊዜ ለካ አንድ ጊዜ ቁረጥ፤**

በአንድ መንደር የዝናብ እጥረት ሊከሰት እንደሚችል የተገነዘቡ የግብርና ባለሙያዎች ለሕብረተሰቡ ትምህርት ለመስጠት ወደዚያ መንደር ተጓዙ:: በዚህም መሠረት በዚያ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች በሚመጣው ዓመት ለረሀብ እንዳይጋለጡ ከወዲሁ ያላቸውን በቁጠባ መጠቀም እንደሚኖርባቸው ባለሙያዎቹ ሰፊ ትምህርት ሰጧቸው::

ከዚያም በኋላ አቶ ተሰማና ባለቤታቸው ወ/ሮ አቻምየለሽ በዚህ ዓመትና በሚመጣው ዓመት ሊያከናውኗቸው ባሰባቸው ተግባሮች ላይ ተቀምጠው መነጋገር እንዳለባቸው ተስማሙ::

በዚህ ዓመት ትልቋ ልጃቸው በግል ኮሌጅ ገብታ መማር እንዳለባት አሳምናቸው ሀሳቧን ተቀብለዋታል:: ወንድ ልጃቸው ደግሞ ባለቤቱ ነፍሰ ጡር ስለሆነች እነርሱ ዘንድ መጥታ ብትወልድ እንደሚሻል ወስነው እስከምትመጣ ድረስ ተዘጋጅተው እየተጠባበቁ ነው::

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ቤታቸውን ከሳር ክዳን ወደ ቆርቆሮ ክዳን መቀየር እንዳለባቸው ቀደም ብለው ወስነው ስለነበር ያንኑ ለማድረግ እየተዘጋጁ ናቸው:: ለእነዚህ ሁሉ የሚያስፈልጋቸውን ወጪ ለመሸፈን ያሰቡት ደግሞ ከሶስቱ በሬዎቻቸው አንዱን፣ በጎተራቸው ከተቀመጠው ያለፈው ዓመት ምርት ደግሞ ሁለት ኩንታል ጥራጥሬ፣ እንዲሁም አንዲት እንቁላል የምትጥል ዶሮና አንዲት ፍየል በመሸጥ ነው::

ከግብርና ባለሙያዎቹ የወሰዱት ትምህርት ግን ሊሰሩ ያቀዱትን ቆም ብለው እንዲያስቡ አድርጓቸዋል:: ከዚሁ ጋር ደግሞ በስራቸው የሚተዳደሩ ዘጠኝ የቤተሰብ አባላትን ልብስና ቀለብ የማሟላት ኃላፊነት አለባቸው::

ስለሆነም "አሥር ጊዜ ለካ አንድ ጊዜ ቁረጥ" እንደሚለው ተረትና ምሳሌ ሊመጣ የሚችለውን ችግር በመገንዘብ ምኞታቸውን ከመፈጸማቸው በፊት ደጋግመው ማጥናት ይኖርባቸዋል::

መልመጃ 3

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

?

1. አቶ ተሰማና ወ/ሮ አቻምየለሽ በዚህ ዓመት ያሏቸው እቅዶች ስንት ናቸው? ምንና ምን?
2. ለወጪ ያሰቡት የገቢ ምንጭ ከችግሮቻቸው ጋር ይመጣጠናል ወይስ አይመጣጠንም? እንዴት?
3. ከእቅዶቻቸው ውስጥ ሊሰረዝ የሚችል አለ ወይስ የለም? መልሳችሁ «አለ» የሚል ከሆነ የትኛው? «የለም» የምትሉ ከሆነ ለምን?
4. የባለሙያ ምክር መስማትና መከተል ለምን ይጠቅማል? ታሪኩን መሠረት በማድረግና ከአካባቢያችሁ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት መልሶቻችሁን ስጡ::

በአንድ ጊዜ ከተገኘ ብዙ ገንዘብም ሆነ በየጊዜው ከሚገኝ ገቢ እንደ ገቢው መጠን መቆጠብ እጅግ አስፈላጊ ነው:: ለመሆኑ የመቆጠቢያ ዘዴዎች የሚባሉት ምንድ ናቸው? ቀጥሎ የቀረቡትን የተለያዩ የመቆጠቢያ ዘዴዎችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል::

**ሀ. አላስፈላጊ ወጪዎችን ማስወገድ ወይም መቀነስ፣**

አላስፈላጊ ወጪዎችን ማስወገድ ወይም መቀነስ አንዱ የቁጠባ መንገድ ነው:: ለምሳሌ ሁለት ልጆቻቸው ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱ ወላጆች ለማሕበር ድግስ ደጋግመው ከሚያወጡት ወጪ ይልቅ የልጆቻቸውን የመማሪያ መሣሪያዎች ማሟላትን ቅድሚያ ሊሰጡት የሚገባ ጉዳይ ነው:: እነዚህ ሰዎች በቂ ገንዘብ ከሌላቸው የቅንጦት እቃዎችን መግዛት፣ በየጊዜው ሽርሽር መጓዝ፣ እንግዶችን እየጋበዙ ማብላትና ማጠጣት አይኖርባቸውም::

**ለ. ራስንና ቤተሰብን በእቅድና በአቅም ማስተዳደር፣**

ራስንና ቤተሰብን በእቅድና በአቅም ማስተዳደር ሌላው የቁጠባ ዘዴ ነው:: በብዙ ኢትዮጵያውን የአኗኗር ዘዴ በርካታ ቤተሰብን አቅፎ መኖርና መደጋገፍ የተለመደ ነው:: ይህ ሁኔታ ከፍተኛ የሆነ የእቅድና በአቅም የመኖር ጥበብን ይጠይቃል:: የብዙ የቤተሰብ አባላትን የምግብ፣ የልብስ፣ የጤናና የትምህርት ወጪን ለመሸፈን የሚያስችል በቂና አስተማማኝ ገቢ የማይኖርበት አጋጣሚ ብዙ ነው::

ስለሆነም ከድህነት የተነሳ ቤተሰብ ለመበተን፣ ልጆችም ወደ ጎዳና መውጣት ወይም ለጉልበት ብዝበዛ የመጋለጥ እድላቸው የሰፋ ይሆናል:: በአንድ ጊዜ ለሁሉም የቤተሰብ አባላት አዲስ ልብስ መግዛት ከባድ ሊሆን ይችላል:: ወይም ደግሞ ለሁሉም የቤተሰብ አባላት በተመሳሳይ ጊዜ ትልቅ ወጪን የሚጠይቅ ጥቅም ለመፍ ጠር አስቸጋሪ ይሆናል:: በቤተሰብ መካከል አድልዎ ሳይፈጽሙ በመግባባት ማስተዳደር ይገባል:: በዚህ ጊዜ ትልቅ ነጥብ ሆኖ የሚመ ጣው ጥሩ የቁጠባ ባህል ማዳበርና ያንኑ ባህል በቤተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ ነው::

የተቆጠበው ገንዘብ በአንድ ጊዜ የሚፈለገውን ሁሉ ማሟላት ካላስቻለ የእያንዳንዱን የቤተ ሰብ አባል ፍላጐቶችን በማጤን ለሚብሰው ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ነው:: ቤተሰብን ከመ መሥረት አንስቶ ገቢን አብቃቅቶ እጅግ ወሳኝና መሠረታዊ ለሆኑ ወጪዎች ብቻ ለማዋል መወሰን ተገቢ ነው:: ቤተሰብን መመጠን፣ ገቢንና ወጪን ማመጣጠን በዕቅድ የመኖር አጋዥ ሁኔታዎች ናቸው::

**ሐ. ተቀማጭ ገንዘብ እንዲኖር ማድረግ፣**

የባንክ ሂሳብ መክፈት፣ እቁብ መጣል፣ በቁጠባና ብድር ሕብረት ስራ ማሕበር መደራጀት ጥሩ የቁጠባ ዘዴዎች ናቸው:: ለመቆጠብ ከፍተኛ የገንዘብ መጠን መመደብ አያስፈልግም:: ቁጠባን ትንሽ ትንሽ ሳንቲም በማጠራቀም መጀመር ይቻላል:: "ሣንቲሞችን ጠብቋቸው፣ ብሮች እራሳቸውን ይጠብቃሉ" የሚል ዘመናዊ አባባል ይህን ጉዳይ አጉልቶ ያሳያል::

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. በእቅድ መመራት ማለት ምን ማለት ነው?
2. በቤተሰባችሁ ወይም በሌሎች አካባቢዎች የተ ለመዱ ናቸው የምትሏቸውን የቁጠባ ዘዴዎች በጽሑፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው::
3. በቤተሰቦቻችሁ መካከል የባንክ ሂሳብ የከፈቱ ወይም እቁብ የሚጥሉ፣ አለበለዚያም በቁ ጠባና ብድር ህብረት ስራ ማሕበር የተደራጁ አባላት ካሉ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይ ቃችሁ መልሱን በጽሁፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ::

*ሀ. ገንዘብ ወደ ባንክ እየወሰዱ የሚከቱት በምን ያህል ጊዜ ነው? የሚያወጡትስ?*

*ለ. ገንዘቡንስ ለማውጣት ወደባንክ የሚሄዱት ምን ዓይነት ጉዳይ ሲያጋጥማቸው ነው?*

## 9.2 በአካባቢ የቁጠባ ባህልን የሚጻረሩ ተግባራት፤



ሥዕል 9.1 ቁጠባን የሚፃረሩ ሁኔታዎች

- በሥዕሉ ላይ ያሉት መልእክቶች እንዴት ቁጠባን የሚጻረሩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ግለጹ::

**ሀ. ከአቅም በላይ ድግስ፣**

- በአካባቢያችሁ ከአቅማቸው በላይ የሚደ ግሱ ሰዎች ካሉ የደረሰባቸውን ችግር ግለጹ::

**የተደራረበ ችግር፤**

ሂሩትና ጸዳሉ የትምህርት ቤት ልብሶቻቸው የተገዙት ከሶስት ዓመት በፊት ነበር:: ልብሶቹ መቀየሪያ ስለሌላቸው ከመጠን በላይ አርጅተው ተቀዳድዋል:: መቀዳደድ ብቻ ሳይሆን ቀለማቸውም ፈዟል:: ወላጆቻቸውን ሲጠይቁም ለእነርሱ ልብስ መግዣ የሚሆን ገንዘብ እንደሌላቸው ይነግሯቸዋል:: ለዚህም ምክንያቱ ወላጆቻቸው የአበልጃቸውን ልጅ መልስ ስለሚጠሩ፣ የተከማቸ ግብር እንዲከፍሉ በመገደዳቸው፣ መጪውን አዲስ ዓመት በዓል ከሌሎች ሰዎች ባላነሰ ሁኔታ ማክበር ስለሚኖርባቸውና ቀጥሎ ለሚከበረው የመስቀል በዓል በሬ ገዝተው ፍሪዳ መጣል ስላለባቸው መሆኑን ይዘረዝሩላቸዋል::

**መልመጃ 5**

***በምንባቡ መሠረት በሚከተሉት ጥያቄ ዎች ላይ ተወያዩ::***

1. የእነዚህ ቤተሰቦች ዋነኛ ችግር ምንድነው?
2. ይህን ችግር እንዴት ማስወገድ ይችላሉ?

**ለ. ኋላቀር አመለካከት፤**

- ስለኋላቀር አመለካከት የምታውቁትን ሀሳብ ግለጹ::

**የአቶ ማህደርና የባለቤታቸው እሮሮ፤**

አቶ ማህደርና ወ/ሮ ትርንጎ ልጃቸው ትዝታ በጠና ታመመችባቸው:: በዚህ ጊዜ የህመሟን ምንጭ ለማወቅና መፍትሔ ለመሻት ከአካባቢያቸው ራቅ ብሎ ወደሚገኝ ጠንቋይ ዘንድ ሄዱ:: ጠንቋዩ ወደእርሱ የሄዱበትን ጉዳይ ከተረዳ በኋላ ልጃቸውን ለህመም የዳረጋት "በቡዳ መበላቷ" ስለሆነ አንድ ነጭ ሙክት ገዝተው እንዲያመጡለትና ከዚያም መፍትሔውን እንደሚነግራቸው አስረዳቸው::

ሰዎቹ እንደተባሉት ሙክቱን በግ ገዝተው ገቢ አደረጉ:: ነገር ግን በጉን ከተቀበለ በኋላ እንደገና ሌላ ወርቅ እንዲገብሩለት ጠየቃቸው:: በዚህ ጊዜ ሁለቱ ሰዎች ያላቸውን ገንዘብ አሟጠው ነበር:: ይሁን እንጂ "የለንም ብንል መፍትሔውን አይሰጠንም" ብለው ስለሰጉ ከጎረቤታቸው ለመበደርና የታዘዙትን ለመፈጸም ተመልሰው ሄዱ:: ይህ ደግሞ ወደ ባሰ ችግር ውስጥ ከተታቸው:: የልጃቸው ህመም እየተባባሰ በመሄዱ በእጃቸው የነበረውን ንብረታቸውን ማጣታቸው፣ በብድር እዳ መዘፈቃቸው ለጊዜው አልታያቸውም:: ሌላው ቀርቶ ልጆቻቸውን እንኳን በመጪው የትምህርት ዘመን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ እንደማይችሉ አልተገነዘቡትም::

**መልመጃ 6**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ኋላቀር አመለካከት ማለት ምን ማለት ነው?
2. ከላይ እንደቀረበው ሰዎችን ለጭንቀት እና ለችግር የሚዳርጉ ኋላቀር አሠራሮችን ከቤተሰብ በመጠየቅና በመወያየት ለመምህራችሁ በጽሑፍ አቅርቡ::

ኋላቀር አመለካከቶች ሰዎች በኑሯቸው እንዳይሻሻሉ የማድረግ ኃይል አላቸው:: ለምሳሌ በይሉኝታ ንብረትን አፍስሶ ለእይታ የሚውሉ የቅንጦት እቃዎችን መግዛት፣ ለጠንቋይ መገበር የመሳሰሉት ለዚህ ማስረጃዎች ናቸው::

ሴቶችን ከወንዶች ያነሱ አድርጎ መመልከትም ሌላው ኋላቀር አመለካከት ነው:: በዚህም የተነሳ ሴት ልጅ ሰርታ የራሷ ንብረት እንድታፈራ አትበረታታም:: እነዚህ የተጠቀሱት ልማዶች ቁጠባን የማያበረታቱ ናቸው::

**መልመጃ 7**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

1. ኋላቀር አመለካከቶች እንዴት የሰዎች ኑሮ እንዳይሻሻል ሲያደርጉ ይችላሉ::
2. በአካባቢያችሁ የሚነገሩ ኋላቀር አመለካከቶች ናቸው የምትሏቸውን ጥቀሱ::

## 9.3 ድህነት፤

### 9.3.1 የድህነት አስከፊነት፤



ሥዕል 9.2 ከድህነት ገፅታዎች አንዱ

- ከላይ ያለውን ሥዕል በመመልከት የድህነትንና የረሃብን አስከፊነት ግለጹ::

ድህነት ስብዕናን ይነካል፡፡ ድህነት የሚወዱትን ያሳጣል፡፡ ድህነት ክብርን ያሳጣል፡፡ ድህነት ሁለት መልኮች አሉት፡፡ የገንዘብ ድህነት አንዱ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ የአስተሳሰብ ድህነት ነው፡፡

ሁለቱም ለሰዎች በዝቅተኛ ኑሮ መኖርና እርስ በርስ መቃቃር መሰረቶች ናቸው፡፡ ሁለቱም ጥገኝነትን ይፈጥራሉ፡፡ ጥገኝነት ደግሞ ከራስ አልፎ ጥገኛ የሆኑበትን ሰው ይጎዳል።

የአስተሳሰብ ድህነት ያለበት ሰው ሥራ መሥራት አይችልም፡፡ ጠንክሮ መሥራት አይቻለውም፡፡ በሰዎች ትከሻ ላይ ለመኖር ይመኛል፡፡ የአስተሳሰብ ድህነት ከገንዘብ ድህነት እጅግ የከፋ ነው፡፡

የገንዘብ ድህነት ጠንክሮ በመሥራትና በእቅድ በመመራት ሊሸነፍ ይችላል፡፡ የአስተሳሰብ ድህነት ግን ሊቀየር የሚችለው መሠረታዊ የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥ ለማምጣት በሚያስችለው ትምህርት ብቻ ነው።

ከዚህም ጋር አዲስ አስተሳሰብና አሠራርን ለመቀበል ፈቃደኝነትን ይጠይቃል፡፡ ለመማርና ለማወቅ ጉጉ መሆንን ይሻል፡፡

**መልመጃ 8**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ድህነት ከሚያስከትላቸው ቀውሶች መካከል ሦስቱን ጥቀሱ፡፡
2. ድህነትና የሥራ ባህል አለመኖር እንዴት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሲሆኑ እንደሚችሉ በጽሁፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

### 9.3.2 የአባካኝነትና የድህነት ዝምድና፣

- አባካኝ ሰው ማለት ምን ማለት ነው? ከድህነት ጋር በምን ይያያዛል?

ድህነት የሚመጣው በተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች መካከል ብኩንነት ዋነኛው ነው፡፡ ብኩንነት ያለንን ማናቸውንም ገንዘብ ወይም የንብረት ዓይነት ያለእቅድ ማውጣትና መጠቀም ነው፡፡ ለምሳሌ እቁብ የደረሳቸው ሰዎች ያለቁም ነገር ሌሎችን በመጋበዝ የሚበትኑት ከሆነ፣ የመሥሪያና የመገልገያ መሣሪያዎችን ያለጥንቃቄ የሚያንገላቱ ከሆነ እንደ ብኩንነት ይቆጠርባቸዋል፡፡ ይህንን ነጥብ በምሳሌ እንመልከተው፡፡

አንድ ጋሪ ነጂ ጋሪውን በየጊዜው አስፈላጊውን ጥገና እያስደረገ ከተንከባከበው፣ ጋሪው ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግለው ማድረጉ ነው፡፡ ፈረሱንም የሚገባውን ምግብ እየመገበ አስፈላጊውን እረፍት እንዲያገኝ በማድረግ ከተንከባከበው ለረጅም ጊዜ የሚገለገልበትን የገቢ ምንጩን እየጠበቀ ወይም እየቆጠበ ነው፡፡

ነገር ግን ጋሪው ሲጎዳ እያየ ማስጠገኛ ገንዘብ ለማውጣት ከሰሰተ፣ ለፈረሱም ቀለብ መግዣ ሳይመድብ ከቀረ አቅም እያሳጣው ነው፡፡ መጨረሻውም የከፋ ይሆናል፡፡

**መልመጃ 9**

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

1. ቁጠባ የሚጠናከርባቸው ዘዴዎች ምን ምን ናቸው?
2. ብኩንነት ለድህነት መንስዔው ነው፡፡ ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል በክፍል ውስጥ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበት፡፡

### 9.3.3 ድህነትን ለማጥፋት ወጪን መቀነስና ቁጠባን መልመድ፣

- ወጪን ለመቀነስ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው?

ወጪን ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑና አስፈላጊ ያልሆኑ ወጪዎችን ለይቶ ማወቅ ወሳኝ ነው፡፡ ለምሳሌ የኤሌክትሪክ መብራት በሌለበት መንደር የሚኖር አንድ ገበሬ የኩራዝ ላምባ ለመግዛት ገንዘብ ማውጣት ለእርሱ አስፈላጊ ነው፡፡ ነገር ግን ዓመት በዓል በመጣ ቁጥር ለልጆች አዳዲስ ልብስ ማልበስና ከማን አንሼ ፍሪዳ መጣል የተጋነኑ ወጪዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

የቤተሰብ በዓልና ድግስ ሲኖርም በጣም ቅርበት ያላቸውን ጥቂት ሰዎች ብቻ በመጋበዝ አብሮ ማክበርና ማሳለፍ ሲቻል ከማን አንሼ ፉክክር ቁጥሩ የበዛ ተጋባዥ መጥራትና ማብላት ሊወጡት ከማይችሉት ችግር ውስጥ ይከታል፡፡

**መልመጃ 1**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. አስፈላጊ የሆኑ ወጪንና አስፈላጊ ያልሆነን ወጪ ከአካባቢያችሁ ከምታስተውሉት ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በምሳሌ ግለጹ፡፡
2. አስፈላጊ ያልሆነን ወጪ በመቀነስ ድህነትን እንፀዳት ማስወገድ እንደሚቻል በቡድን ውይይት አድርጉበት፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሰዎች የተረጋጋና ከድህነት የተላቀቀ ኑሮ ለመኖር የቁጠባ ባህል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ የቁጠባ ባህል መኖር ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ በመቆጠባቸው ረሃብንና ችግርን ድል መትተው የተደላደለ ኑሮ የሚመሩ በርካታ ሰዎች በየአካባቢው አሉ፡፡ ቁጠባ ኑሮን ለማሻሻል፣ ራስን በትምህርትና በእውቀት ለማጎልበት ይጠቅማል፡፡

የተለያዩ የቁጠባ ዘዴዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋነኛው በአቅም ልክ መኖርን መልመድ ነው፡፡ ተቀማጭ ገንዘብ እንዲኖር ማድረግና በአቅም ልክ መኖር አስፈላጊ ሳልሆነ ወጪ ከመዳረግ ያድናሉ፡፡

የቁጠባ ባህልን ለማዳበር ቁጠባን የሚጻረሩ አካባቢያዊ ልማዶችን አውቆ መጠንቀቅ ይጠቅማል፡፡ እነዚህ አካባቢያዊ ልማዶች ለብኩንነትና ለድህነት ያጋልጣሉ፡፡ ከአቅም በላይ መደገስ፣ ኋላቀር አመለካከቶችና የመሳሰሉት ሌሎቹ ለብኩንነት የሚዳርጉ ልማዶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የቁጠባ ባህል አለመኖር ለድህነት ያጋልጣል፡፡ የቁጠባ ባህል አለመኖር  አባካኝነት መኖሩን ያሳያል፡፡ ብኩንነት ተገቢ ያልሆነ የገንዘብ አጠቃቀም ነው፡፡ ይህንን ችግር ለማስወገድ ወጪን መቀነስና ቁጠባን መልመድ ያሻል፡፡ ምክንያቱም ድህነት  ሰብአዊ ክብርን ያሳጣል፡፡ ስለሆነም በራስ በመተማመን ለመኖር፣ እንዲሁም የሌሎች ሰዎች ጥገኛ ሆኖ ችግር ላለመፍጠር ጥሩ የቁጠባ ባህልን ማዳበር ይገባል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

*ድህነት፣* እጦት፣ ችግር፣ ደሃ መሆን።

*ብኩንነት፣* ገንዘብን ያለአግባብ፣ ያለእቅድና ያለዓላማ ማጥፋት።

*ንብረት፣* ገንዘብ፣ ሀብት፣ ጥሪት።

*የተመቻቸ ኑሮ፣* በራስ መተማመን ያለበት፣ የተደላደለና ችግር የሌለበት ኑሮ።

*ብድር፣* ወደፊት ለመክፈል ቃል በመግባት በጊዜው ሳጋጠመ ችግር መወጫ ከሌላ ሰው ወይም አበዳሪ ክፍል የሚወሰድ ገንዘብ ወይም ንብረት።

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

*I የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ «ሀሰት» ብላችሁ መልሱ::*

1. ደሃ የነበረ ሰው ሀብታም ሲሆን እንደሚችል ሁሉ ሀብታምም ሰው ሊደኸይ ይችላል::
2. የአስተሳሰብ ድህነትና የገንዘብ ድህነት ፍፁም ተመሳሳይ ችግሮች ናቸው::
3. የኑሮ እቅድና ቁጠባ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው::
4. አንድ ሰው ብድር ሳይበደር ሕይወቱን መምራት አይችልም::
5. በየትኛውም ዓይነት የሥራ መስክ ቢሰማሩ ቁጠባ አስፈላጊ ነው::

*II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ::*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ድህነት፣ | ሀ. ጥገኝነት:: |
| 2. የቁጠባ ባህላዊ ተቋም፣ | ለ. ምክንያታዊ ያልሆነ ወጪ:: |
| 3. ብኩንነት፣ | ሐ. ራስን መቻል:: |
| 4. ዘመናዊ የቁጠባ ተቋም፣ | መ. ባንክ:: |
| | ሠ. ዕቁብ:: |

*III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::*

1. ቁጠባ፤
   ሀ. ለትውልድ የሚተላለፍ ሀብት ማቆየት ማለት ነው፣
   ለ. የአደጋና የችግር ጊዜ ዋስትና ይሰጣል፣
   ሐ. ለወገን መድረሻ ነው፣
   መ. ሁሉም መልስ ነው::
2. አስፈላጊ ወጪን ማስወገድ ማለት፤
   ሀ. በእቅድ መኖር ማለት ነው፣
   ለ. ቤተሰብን መጨቆን ማለት ነው፣
   ሐ. ራስን ጎድቶ ለወደፊት ማሰብ ማለት ነው፣
   መ. ሁሉም መልሶች ይሆናሉ::
3. ብኩንነት ማለት፤
   ሀ. ስለቁጠባ አለማሰብ ማለት ነው፣
   ለ. የሃላፊነት ስሜት አለመኖር ማለት ነው፣
   ሐ. ስስታምነት ማለት ነው፣
   መ. «ሀ» እና «ለ» መልሶች ናቸው::
4. የቁጠባ ባህል ማዳበር ለሰዎች ደህንነት ዋስትና ይሰጣል ሲባል፤
   ሀ. የራስን ላብ መጠቀም እርካታን ይሰጣል፣
   ለ. ቤተሰብ እንዳይፈርስ ይረዳል፣
   ሐ. ሀ እና ለ መልሶች ናቸው፣
   መ. መልሱ አልተሰጠም::
5. የአስተሳሰብ ድህነት ማለት፤
   ሀ. ሥራን አለመውደድ ማለት ነው፣
   ለ. ለጋራ ጥቅም አለማሰብ ማለት ነው፣
   ሐ. ለኋላ ቀር ልማድ መገዛት ማለት ነው፣
   መ. ሁሉም መልሶች ይሆናሉ::

*IV የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ትክክለኛውን ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::*

1. ቁጠባን ከሚጻረሩ አካባቢያዊ ልምዶች መካከል ________________እና ___________ሊጠቀሱ ይችላሉ::
2. ከቁጠባ ዘዴዎች መካከል ____________________ እና ________________ ይጠቀሳሉ::

*V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ::*

1. የቁጠባ ባህልን ማዳበር ድህነትን ለመዋጋት እንዴት እንደሚረዳ በምሳሌ አስረዱ::
2. የቁጠባ ባህልን ከሚጻረሩ አካባቢዎች ልምዶች መካከል ቢያንስ ሁለት ምሳሌዎችን በመጥቀስ እንዚህን በምን ዘዴ መቋቋም እንደሚቻል ግለጹ::

# ምዕራፍ አስር

# ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፤***

- ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ::
- ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚጠይቁ አካባቢያዊ ጉዳዮችን ታውቃለህ/ታውቂያለሽ::
- በአካባቢህ/በአካባቢሽ የሚገኙ የሲቪክ ማህበራትን ተግባራት ትረዳለህ/ ትረጃለሽ::

## 10.1 የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነት፤



ሥዕል 10.1 የሥራ ዘመቻ በትምህርት ቤት



ሥዕል 10.2 የህብረተሰብ ተሣትፎ በአካባቢ ልማት ሥራ ላይ

- በሁለቱ ሥዕሎች መካከል ያሉትን ልዩነቶች በዝርዝር ግለጹ::
- በሁለቱ መካከል ላሉት ልዩነቶች ምክንያቶቹ ምን ይመስላችኋል? ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚታየው በየትኛው ውስጥ ይመስላል?

### የርዕሰ መምህራችን ንግግር፤

የጉንጀላ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር እንደተለመደው የመንፈቀ ዓመት መልእክታቸውን ለትምህርትቤቱ ተማሪዎች በንግግር አሰምተዋል:: በሳቸው አገላለጽ የትምህርት ቤቱ ራዕይ ብቁ ዜጎችን ለማፍራት መሠረት መጣል ነው:: ለዚህም ትምህርት ቤቱ የሚሰጣቸው ትምህርቶች ጥራታቸውን የጠበቁ መሆን ይገባቸዋል::

በጉንጀላ ትምህርት ቤት የትምህርት ጥራት እንዲረጋገጥ የሚከተሉት ችግሮች ሊወገዱ እንደሚገባም አመልክተዋል:: በቂ የውሀ አቅርቦት አለመኖር፣ የመጸዳጃ ቤት ማነስ፣ የቤተ መጻሕፍት አለመኖር፣ የቤተ ሙከራ አለመሠራት፣ የትምህርቱን ሂደት የሚፈታተኑና ትምህርት በጥራት እንዳይካሄድ መሰናክል እንደነበሩ አስረድተዋል:: ትምህርት ቤቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሚያስፈትን ተማሪዎቹ በበቂ ሁኔታ መዘጋጀታቸውን አለማረጋገጥ ሌላው ችግር ነበር::

ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ወቅት ከክፍል ውጭ ዕውቀታቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉበት ምንም ዕድል አልተፈጠረላቸውም ነበር:: አሁን ግን የተማሪዎች ወላጆች በትምህርት አመራር ተደራጅተው ከትምህርት ቤቱ ጋር መንቀሳቀስ በመጀመራቸው ብዙዎቹ ችግሮች ተቀርፈዋል:: ተጨማሪም የውሀ መስመር ገብቷል::

ጥሩ ቤተመጻሕፍት ተሰርቶ መጻሕፍትም ስለተሰባሰቡ ዛሬ ተማሪዎች የማጣቀሻ ጽሑፎችን በመጠቀም ላይ ናቸው:: አዲስ የቤተ ሙከራ ሕንጻ በመገንባቱ ትምህርቱ በሙከራ እየታገዘ በመሰጠት ላይ ይገኛል:: የክፍል ትምህርት በተጓዳኝ ትምህርት እንቅስቃሴ እንዲታገዝ ከመደረጉ ሌላ እንደ ሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ክበብ ባሉት ስለምርጫ ፍትሐዊነትና ሚዛናዊነት ተግባራዊ ልምምዶች መደረጋቸው ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው አስገንዝበዋል:: በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ ትምህርት ቤቱ ለብሔራዊ ፈተና የሚያሳትፋቸው የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች

በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ በልዩ ልዩ የትም ህርት ዓይነቶች በመምህራን የሚታገዝ ልዩ የጥናት መርሐግብር ተነድፎ በተግባር እየተተ ረጎመ መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

ተማሪዎች በትምህርቱ አስተዳደር እንዲሳተፉ ለማድረግም ተነድፎ የነበረው የተማሪዎች መተ ዳደሪያ ደንብ በተማሪዎች የመማክርት ኮሚቴ ከታየ በኋላ ከጥቂት ማሻሻያዎች ጋር ጸድቋል፡፡ ይህ ሁሉ ርምጃ የተወሰደው ወላጆችና ሕብረተ ሰቡ በትምህርት አመራሩ ላይ በተደራጀ መልክ መሳተፍ በመጀመራቸው እንደሆነ ርእሰ መምህሩ አስገንዝበዋል፡፡ በመሆኑም በዓመቱ ከፍተኛ እንቅስቃሴዎች ስለተደረጉ ትምህርት በትምህ ርት ቤቱ ከተሻለ ጥራት ላይ ሊደርስ እንደሚ ችል ያላቸውን እምነት ገልጸዋል፡፡

*("ልሳነ ናዖድ" አንደኛ ዓመት ቁጥር 1 ጥር - መጋቢት፣ 2000 ከተባለው የአጼ ናኦድ ትምህርት ቤት መንፈቃዊ ጋዜጣ፣ መነሻነት እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ፡፡)*

**መልመጃ 1**

## ? ከላይ በቀረበው ንባብ መሠረት የሚከተ ሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. የጉንጅሳ ትምህርት ቤት ችግሮች ምን ምን ነበሩ? ምን ዓይነት መፍትሔዎችስ ተሰጧ ቸው?
2. የጉንጅሳን ትምህርት ቤት ችግሮች በመለየ ትና በመፍታት ረገድ የትምህርት ቤቱ ተማሪ ዎች ምን አስተዋጽኦ አድርገዋል?
3. በጉንጅሳ ትምህርት ቤት ችግሮች የመለየትና የመፍታት ሂደት ተማሪዎቹ የተሻለ ተሳትፎ ሊያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታ ይኖር ነበር? በምሳሌ አስረዱ፡፡
4. የራሳችሁን ትምህርት ቤት ተጨባጭ ሁኔታ መነሻ በማድረግ ዐበይት የሆኑትን አምስት ችግሮች በመለየት ስያንዳንዳቸው መፍትሔ ዎችን አስቀምጡ፡፡
5. በዚህ ችግርን የመለየትና መፍትሔ የመስ ጠት ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳትፏቸውን ያረጋ ገጡ ዘንድ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ሚና ምን ሲሆን ይገባል?

አንዳንድ ተግባራት በግል ሊከናወኑ የሚችሉ ቢሆንም ሌሎች ደግሞ በጋራ ካልሆነ በቀር በተ ናጠል የማይከናወኑ ወይም ቢከናወኑም እዚህ ግባ የሚባል ውጤት የማያመጡ አሉ፡፡ ለምሳሌ የአካባቢያችንን ጸጥታ የማስከበር ተግባር እናከ ናውን ብንል በግል የምናደርገው ጥረት ብዙ ፋይዳ አይኖረውም፡፡ መንደራችንን ከሌላ አካባቢ እናገናኝ ብለን ብንነሳ ከአካባቢው ሕብረተሰብ ጋር በጋራ ካላከናወንነው ብቻችንን የምንፈ ጽመው ነገር አይሆንም፡፡

ይህ የሚያሳየን በማሕበራዊ ሕይወት ውስጥ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የቱን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡ ታዲያ እንዲህ ካለው ንቁ ተሳትፎ ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው በግል ልንጠቀም እንች ላለን፡፡ ይህም ሲባል ከውጤቱ እያንዳንዳችን ድርሻችንን የምናገኝበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ከሂደቱ እያንዳንዱ ተሳታፊ ተሞክሮና ትምህርት ሊቀስም ይችላል፡፡ እያንዳንዱ ተሳታፊም በየ ግሉ ሊደርስ ይችል ከነበረ ችግር ሊድን ይችላል፡፡

በጋራ በሚከናወን ተግባር ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ግን ከዚህ የላቀ አስፈላጊነት ያለው ነው፡፡ ጥቅሙም ከግል አልፎ ማሕበራዊ የሚሆንበት ሁኔታ ይበዛል፡፡ በውጤቱ ተጠቃሚው የአካባ ቢው ሕብረተሰብ በሙሉ ይሆናል፡፡ ከውስን አካባቢም ተሻግሮ ለወረዳው፣ ለዞኑ፣ ለክፍለ ከተ ማው፣ ለክልሉ ብሎም ለሀገሩ ሊጠቅም ይችላል፡፡ በመሆኑም የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊነት ጎላ ያለ ትርጉም ያለው ነው፡፡

**መልመጃ 2**

## ? የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡

1. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስፈላጊ አይደለም የሚል ሰው ቢገጥማችሁ ምን ማስረጃ በማ ቅረብ ትከራከራላችሁ?
2. ከንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማሕበራዊ ጠቀሜታ እንዴት ሊገኝ እንደሚችል በአጭሩ አስረዱ፡፡

### የመቅረፋ ትምህርት ቤት፤

የመቅረፋ ትምህርት ቤት ከአዲስ አበባ ውጪ በአንድ መለስተኛ ከተማ ውስጥ የሚገኝ የመ ጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ወደ አንድ ሺህ ስምንት መቶ የሚሆኑ ተማሪዎች ያሉት ይህ የመንግሥት ትምህርት ቤት በርካታ ችግሮች አሉበት፡፡ ከችግሮቹም ላቅ ያለ ውና የትምህርቱን ጤናማ ሂደት ክፉኛ ያወ ከው የተወሰኑ ተማሪዎች በፈጠሩት አደገኛ ቡድን የሚፈጽም ተግባር ነበር፡፡ የቡድኑ አባ ላት በትምህርት ሰዓት ጭምር እየጠጡ በመም ጣት በመምህራን፣ በተማሪዎችና በቀሩትም የትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ አባላት ላይ ብዙ ችግር ያደርሱ ነበር፡፡

በየመንገዱና በየመንደሩ ከሚፈጽሙት ሌላ እነዚህ ሥርዓት አልበኛ ተማሪዎች በሴት ተማሪዎች ላይ በትምህርት ቤቱ ግቢ ውስጥ የተለያዩ ጥቃቶች ያደርሱባቸዋል፡፡ የትምህርቱን ሰዓት አክብረው ወደክፍላቸው ስለማይ ገቡ ከመምህራኑ ጋር መጋጨትና መወዛገብ ያበዛሉ፡፡

የሚቆጣጠራቸው ከማጣታቸው የተነሳ ብዙ አስነዋሪ ድርጊቶችን ስለሚፈጽሙ ለቀሩት ተማሪዎች መጥፎ ምሳሌዎች እየሆኑ ነው፡፡ ለመምህራኑ ተገቢውን አክብሮት ስለማይሰጡ ደፍሮ ተግሣጽና ምክር የሚሰጣቸው መምህር አልተገኘም፡፡ በአጠቃላይ ትምህርት ቤቱ በእነሱ ምክንያት የትምህርት ቤት ባህሪ ሊኖረው አልቻለም፡፡

በነበራቸው ልምድ ችግሩን ይፈታሉ ተብለው ወደዚህ ትምህርት ቤት ተመድበው የመጡት አዲስ ርዕስ መምህር መፍትሔ መሻት ጀመሩ፡፡ ችግሩ ጊዜ የሚወስድ መሆኑን ባይክዱም ሁኔታውን ወደጤናማ የትምህርት አካባቢ ለመለወጥ እንደሚቻል አልተጠራጠሩም፡፡ ይህ ውጤት ሊመጣ የሚችለው ግን አንድ ነገር ከተሟላ እንደሆነ አመኑ፡፡ ይኸውም ውጤቱ ሊገኝ የሚችለው በእሳቸው ጥረት ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የትምህርት ቤቱ ማሕበረሰብ አባላትና የአካባቢው ሕብረተሰብ ከልብ በመነሳሳት ጥሩ ተሳትፎ ካደረጉ ብቻ ነው፡፡

በዚህ መሠረት ሁሉንም ወገኖች አብረው ከጐናቸው እንዲቆሙ አነሳሱ፡፡ ይህም ተሳካላቸው፡፡ መምህራንና ወላጆች በኅብረታቸውና በማሕበራቸው ተማሪዎች በመማክርታቸው እንዲሁም የአካባቢው ሕብረተሰብ በቀበሌ ማሕበራቸው አማካኝነት ከጐናቸው ቆሙ፡፡ ችግሩም በጋራ ክንድ ተፈታ፡፡ ውሎ ሲያድርም ይህ ሁሉ ንቁ ተሳትፎ የትምህርት ቤቱን ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት ያለማቋረጥ ተንቀሳቀሰ፡፡ ዛሬ የመቅረፋ ትምህርት ቤት ከዞኑ በትምህርት እንቅስቃሴና በሥነምግባር ምርጥ ሆኖ በምስጉንነት ተሸላሚ ሆኗል፡፡

### የቡድን ሥራ

1. ራሳችሁን የዚሁ ትምህርት ቤት የተማሪዎች መማክርት ምክር ቤት አባል እንደነበራችሁ በመቁጠርና በቀረበው ታሪክ ላይ በመመሥረት፣ በየቡድናችሁ በጊዜው የነበረውን ችግር በዝርዝር በመለየት የራሳችሁን የመፍትሔ ሃሳቦች በጽሑፍ አዘጋጅታችሁ አቅርቡ፡፡
2. በትምህርት ቤታችሁ በአሁኑ ወቅት ያሉትን ዐበይት ችግሮች በየቡድናችሁ በመለየት በእናንተ ንቁ ተሳትፎ ይፈቱ ዘንድ መከናወን ያለባቸውን የመፍትሔ ሃሳብ በመቀመር በጽሑፍ አዘጋጁና ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

እንደማንኛውም ድርጅት ትምህርት ቤትም የራሱ ሕብረተሰብ አለው፡፡ ማንኛውም የትምህርት ቤቱ ጉዳይ ሕብረተሰቡን ያገባዋል፡፡ ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ ውስጥ እያንዳንዱ አባል በግለሰብም ሆነ በቡድን በትምህርት ቤቱ ጉዳይ ሁሉ በንቃት መሳተፉ ተገቢ ነው፡፡

ስለዚህ በሚተላለፉ ውሳኔዎች ሁሉ እያንዳንዱ አባል ተሳትፎው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ አባሉም በበኩሉ ያለማንም ተጽእኖ በነጻ በራስ ተነሳሽነትና በገዛ ፈቃዱ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ለተቋሙ እድገትና መሻሻል የድርሻውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ይህም እያንዳንዱ ተማሪ የትምህርት ቤቱ ጉዳይ የሚመለከተው ስለሆነ ምንጊዜም ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅበታል ማለት ነው፡፡

**መልመጃ 3**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ዴሞክራሲያዊ በሆነ ሥርዓት በአንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ በኃላፊነት ቦታ ላይ ሳይሆን በተራ ሠራተኛነት የሚያገለግል ሰው በመሥሪያ ቤቱ ጉዳይ የሚፈጸምን ተገባር ማወቅና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደትም መሳተፍ ይኖርበታልን? ለምን? እንዴት?
2. እናንተስ በትምህርት ቤታችሁ ጉዳይ በውሳኔ አሰጣጥ ልትሳተፉ ይገባልን? ለምን?

## 10.2 በሲቪክ ማሕበራት ተደራጅቶ የመሳተፍ ጠቀሜታ፤



ሥዕል 10.3 የአካባቢ ብክላ



ሥዕል 10.4 የአካባቢ ብክለትን የመቃወም እንቅስቃሴ

- ከዚህ በላይ ካሉት ሥዕሎች ምን ትረዳላች?
- ሥዕል 10.4 ላይ ያለው ማሕበር ለሕብረተሰቡ ምን ጥቅም ሊያስገኝ ይችላል?

### ከሲጋራ ጢስ ነፃ የሆነ የልጅነት ሕይወት እሻለሁ!

"በዓለማችን ላይ ልጆችን ሊጎዱ የሚችሉ በርካታ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ ሕፃናት ከነዚህ የመጠበቅ መብት እንዳላቸው በዓለም አቀፍ ሕጎች ተደንግጓል፡፡ እናንተም ራሳችሁን ለጉዳት ከሚዳርጉ ነገሮች መጠበቅ ይኖርባችኋል" ይላል ማቲያስ የተባለው ይህንን መልዕክት የላከልን የኢትዮጵያ የፀረ ካንሰር ማህበር አባል የሆነው የ12 ዓመት ታዳጊ፡፡

የዓለም አቀፍ የካንሰር ቀን በመላው ዓለም በየዓመቱ ይከበራል፡፡ ለዚህ ዓመት የተመረጠው መሪ ቃል "ከሲጋራ ጢስ ነፃ የሆነ የልጅነት ሕይወት እሻለሁ!" የሚለው ነው፡፡ ይህም የዓለም ሕፃናት ሁሉ ምኞት እንደሆነ ይታመናል፡፡

"ሲጋራ ከሚያጤሰው ሰው አልፎ በአካባቢው ያሉትን ሌሎች ሰዎችን ጤና ይጎዳል፡፡ በመሆኑም በቤታችን፣ በትምህርት ቤታችንም ሆነ በአካባቢያችን የሚያጤሱ ሰዎች ከድርጊታቸው ሊገቱ ይገባል፡፡ ሁላችንም ሲጃራ የሚያጨሱ ሰዎች በአካባቢያችን ካሉ ከድርጊቱ እንዲቆጠቡ ማሳሰብ ይጠበቅብናል፡፡" ይላል ማቲያስ፡፡

የዓለም አቀፍ የካንሰር ድርጅት የዓለምን ሕጻናት ከሲጋራ ጢስ እንክላከል የሚለውን መሪ ሐሳብ ተግባራዊ ለማድረግ የሁላችንን ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡ ሲጋራ የሚያጤሱትን ሰዎች ጎጂነቱን በማስተማር ከድርጊቱ እንዲቆጠቡ ማድረግ የሁላችን ኃላፊነት እንደሆነም ያሳስባል፡፡

በቤት፣ በመኪና ውስጥ፣ በሕጻናት ማዕከላትና በሕዝብ መሰብሰቢያና መገልገያ ቦታዎች ሲጋራ እንዳይጨስ መከላከል የሁላችንም ተግባር መሆኑን ይገልፃል፡፡ ለዚህ ጥረት መሳካትም የሕጻናት፣ የወላጆች፣ የሕጻናት ወዳጆች፣ ወዘተ... ኃላፊነት ከፍተኛ እንደሆነ ያመለክታል፡፡

በመሆኑም ሕፃናት ባልተበከለ አካባቢ የመኖር መብታቸው ሊጠበቅ እንደሚገባ ያስተምራል፡፡

*(ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥር 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ገጽ 2 እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ፡፡)*



ሥዕል 10.5 በጸዳ አካባቢ የመኖር መብታችን ይከበር

**መልመጃ 4**

***ከላይ በቀረበው ምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. በፅሑፉ የተጠቀሱትን የሁለት የሲቪክ ማሕበራትን ስሞች ጥቀሱ:: ምን ሲያከናወኑ እንደሚችሉም ግለጹ::
2. ስለማቲያስ ምን እንደተገነዘባችሁ አስረዱ::

***የቡድን ሥራ ፅሑፉ የተገነዘባችሁትን መነሻ በማድረግ በቡድን ሆናችሁ የሚከተሉትን አከናውኑ::***

*ሀ. በትምህርት ቤታችሁ ለተመሳሳይ ተግባር ልታቋቋሙ ስለምትችሉት አንድ ክበብ አስረዱ::*

*ለ. ከምታቋቁሙት ከዚህ ክበብ ሊገኙ የሚችሉትን ጠቀሜታዎች ዘርዝራችሁ አቅርቡ::*

*ሐ. ይህንን መሠረት በማድረግ የትምህርት ቤታችሁ ተማሪዎች በክበቡ ውስጥ እንዲሳተፉ የሚረዳ የቅስቀሳ ስልት በማዘጋጀት አቅርቡ::*

የሲቪክ ማሕበራት የየራሳቸውን የተለያዩ ማሕበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎች ይዘው በራስ ተነሳሽነት በግለሰቦች ወይም በቡድኖች የሚመሠረቱ ማሕበራት ናቸው:: እነዚህ ማሕበራት በራስ ፈቃድ የሚመሠረቱ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት የሌለባቸው ነፃና ሕጋዊ የሆኑ ማሕበራት ናቸው:: ስለዚህም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ለሕዝብ ልዩ ልዩ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አገልግሎቶች ለመስጠት ሰፊ ዕድል ይኖራቸዋል::

የሲቪክ ማሕበራት በርካታ ጠቀሜታዎች አሏቸው:: መንግሥት ባለው ውስን አቅም ምክንያት ሊያከናውን በማይችልባቸው መስኮች ብዙ አገልግሎቶች ሊሰጡ ይችላሉ:: ሕዝቡ በመንግሥት ፖሊሲዎች ላይ ተወያይቶ ለማዳበርና የፖለቲካ ሂደቱን ለመቆጣጠር እንዲችል የዴሞክራሲ ልምምድም እንዲያደርግ አመቺ መድረኮችን ይፈጥራሉ::

በተጨማሪም በሲቪክ ማሕበራት ውስጥ ግለሰቦች በአባልነት ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ልምድና እውቀት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል:: አባላቱ የመተሳሰብና የመተባበር ባህል እንዲያሳድጉ እንዲሁም የሥራ ፍቅርን እንዲያጎለብቱ ለማድረግም ይጠቅማሉ::

**መልመጃ 5**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ::***

?

1. በሥራ ፍቅራቸው ስለምታውቋቸው አንድ አዛውንት ወንድ ወይም ሴት መረጃ አሰባስባችሁ አጭር ጽሑፍ አቅርቡ::
2. የሲቪክ ማሕበራትን ጠቀሚታ ዘርዝሩ::

**ቱቱዬና አያቷ አብዬ፤**

**ቱቱዬ፣** አብዬ እማዬ ያከበረችልህ ስንተኛ ዓመት ልደትህን ነው?

**አብዬ፣** *ሰማንያ ስምንተኛ ዓመቴን ነው፣ ልጄ:: እግዚአብሔር ይባርካት!*

**ቱቱዬ፣** *ታዲያ ይህን ካደረገችልህ በኋላ ለምን ትጨቃጨቅሃለች?*

**አብዬ፣** *ባለማወቋ ነው ልጄ፣ ባለማወቋ:: "ዛሬ ልደትህ ስለሆነ ለብሰህና አምረህ መቀመጥ አለብህ! ከቤትም መውጣት የለብህም!" ትለኛለች?*

**ቱቱዬ፣** *አለማወቋ ምኑ ላይ ነው፣ አብዬ? እኔም ብሆን በልደቴ ቀን አዲሱን ልብሴን ለብሼ አሸብርቄ፣ በጓደኞቼ፣ በእህቴና በወንድሜ መሃል በመቀመጥ እቤት ውስጥ እንድንዝናና አይደል የምደረገው? አንተስ በልደትህ ለብሰህና ደምቀህ በቤተሰብ መሃል አትቀመጥም?*

**አብዬ፣** *አይ ቱቱዬ አንቺም ያልገባሽ ነገር አለ:: አየሽ የዕድሜ ባለጸጋ ልሆን የቻልሁት ይህን ያህል ዘመን የአካባቢያችንን የልማት ማሕበር ከማቋቋም ጀምሮ ዛሬ እስከደረሰበት ደረጃ ሳገለግል በመኖሬና መቀመጥን ትቼ ጎንበስ ቀና እያልሁ በመሥራቴ ነበር:: የዚህ እድሜዬ ምክንያት የሥራ ፍቅር ነው:: ስለዚህ ልደቴን ሳከብር ለዚህ ያበቃኝንና የማፈቅረውን ሥራን ልለየው አይገባም:: ለብሼና አምሬ በቤተሰብ መሃልማ ለበቂ ጊዜ ተቀምጬ ነበር:: ከዚያ በኋላም ልብሴን ለውጬ መሥራት ነበረብኝ:: በልማት ማሕበሬ ደግሞ ለብርቱ ሥራ ቀጠሮ አለብኝ:: ልደቴን ካከበርሁ በኋላ እነዚህን ሁለት ወዳጆቼን እንዴት ልርሳቸው? እንግዲህ ከእናትሽ ያልተግባባነው በዚህ ምክንያት ነው::*

**ቱቱዬ፣** *እህ አሁን ገባኝ አብዬ:: እኔም ያንተን አርአያ ነው የምከተለው::*

**አብዬ፣** *እሰይ ልጄ! እደጊልኝ! አንቺም የኔን እድሜ ይሰጥሽ! የሥራ ፍቅር ይኑርሽ!*

**መልመጃ 1**

***የቀረበውን ውይይት መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::***

?

1. በእናንተ ግንዛቤ በቱቱዬ እናትና በቱቱዬ አያት መካከል የተፈጠረው ልዩነት ምንድነው?
2. ከአብዬ ሕይወት ያገኛችሁትን ሁለት ዐበይት ትምህርቶች ግለጹ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ንቁ ሕዘባዊ ተሳትፎ ለማሕበራዊ ልማትና ለሕዝቦች ዴሞክራሲዊ ሥርዓት ግንባታ አስፈላጊ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲጎለብት፣ ፈጣን ማህበራዊ እድገት ሲመጣ፣ ማሕበራዊ ደኅንነት ሲረጋገጥ የሚችለው ዜጎች ሁሉ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ሲያደርጉ ነው፡፡ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ከነዚህ ሁኔታዎች አንዱ በነፃ የመደራጀት መብት ነው፡፡ መደራጀትም የተበታተነ ኃይል ተሰባስቦ ጠንካራ አቅም እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

የሲቪክ ማሕበራትም የመደራጀት መብት ውጤቶች ናቸው፡፡ ግለሰቦችና ቡድኖች በራስ ተነሳሽነት ለተለያዩ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎች ሲቪክ ማሕበራትን ያቋቁሟቸዋል፡፡ እነሱም ከመንግስት ነፃ ሆነው ማሕበራዊ አገልግሎቶችን በመስጠት መንግሥትን ከማገዛቸውም ሌላ ለዴሞክራሲያዊው ሥርዓት መጎልበት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡ ለሕዝቡ በዴሞክራሲያዊ መንገድ በመንግሥት ፖሊሲ አፈጻጸም ሂደት ቁጥጥርና ተሳትፎ ማድረጊያ መድረኮች ሆነውም ያገለግላሉ፡፡ ጥሩ የሲቪክ ማሕበራት የመተጋገዝና የሥራ ፍቅር ባህልም እንዲያድግ ይረዳሉ፡፡ በዚህ መሠረት እናንተም አግባብ ባላቸው የሲቪክ ማህበራት ከአሁን ጀምሮ አባል በመሆን ንቁ ተሳትፎ በማድረግ ልትለማመዱና የሚጠበቅባችሁን የዜግነት ድርሻ ልትወጡ ይገባችኋል፡፡ በንቁ ተሳትፏችሁም የሥራ ባህላችሁን ማሳደግና የሥራ ፍቅርንም ለማዳበር መቻል ይጠበቅባችኋል፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

***ግሳዊ ጠቀሜታ፣*** ሰዎች ከአንድ ነገር በነፍስ ወከፍ የሚያገኙት ጥቅም::

***ማሕበራዊ ጠቀሜታ፣*** ከአንድ ነገር ሰዎች በጋራ ወይም የተወሰኑ የሕዝብ ክፍሎች በወል የሚያገኙት ጥቅም::

***ቅስቀሳ፣*** ሰዎች አንድን ዓላማ ወይም ተግባር እንዲረዱ፣ እንዲደግፉ፣ እንዲቃወሙ ወዘተ... ስማድረግ የሚካሄድ የማግባባት ወይም የማነሳሳት ተግባር::

***የሥራ ፍቅር፣*** ሥራ ስመኖር የሚያስፈልግ መሆኑን በመረዳት ሥራን የማክበር ስሜት::

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ::*

## I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆነ «ሀሰት» በማለት መልሱ::

1. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ሊያስገኝ የሚችለው ግላዊ ጠቀሜታን ብቻ ነው::
2. የምንኖረው በውድድር ዓለም ውስጥ ስለሆነ ማንኛውም ጠቃሚ ተግባር ሊከናወን የሚገባው በግል ብቻ ነው::
3. የሥራ ፍቅር የሚገለፀው ስለሥራ ጠቀሜታ በመናገር ብቻ ነው::
4. የሲቪክ ማህበራት ተደራጅተው ለሕዝብ ሰፊና ጠቃሚ ተግባር ለማከናወን እንዲችሉ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል::
5. ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሥራ ፍቅር እንዲፈጠር ይረዳል::

## II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በግል የማይከናወን፣ | ሀ. ቤተሰብ፣ ቀበሌ ፣ወረዳ፣ ክልልና አገር:: |
| 2. ከሲቪክ ማሕበራት ጠቀሜታዎች አንዱ፣ | ለ. የንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ውጤት:: |
| 3. ማሕበራዊ ጠቀሜታን የሚያገኙ አካላት፣ | ሐ. የሲቪክ ማሕበር:: |
| 4. ከመንግሥት ጣልቃ ገብነት ነፃ የሆነ፣ | መ. የአካባቢ ልማት:: |
| 5. ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ | ሠ. በመንግሥት አቅም ብቻ ሊሠሩ የማይችሉትን ሥራዎች ማገዝ። |
| | ረ. ባህላዊ ጫና:: |
| | ሰ. ለንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ የሚያመች ሁኔታ:: |

## III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

1. ከሲቪክ ማሕበራት ጠቀሜታዎች አንዱ፤
   ሀ. አባላቱን ለፖለቲካ ሥልጣን ማብቃቱ፣
   ለ. መንግሥት የአቅም ውስንነት ለሳለዉ ተክቶት መሥራቱ፣
   ሐ. የመንግሥትን ፖሊሲዎች ለማዳበር ሕዝብ የሚሳተፍበትን መድረክ መፍጠሩ፣
   መ. ለተገፉ ማሕበራዊ ክፍሎች የፖለቲካ ወገንተኛነት ይዞ መታገሉ::
2. ማናቸውም ጠቃሚ ተግባራት፤
   ሀ. በግል ሊከናወኑ ይገባል፣
   ለ. በጋራ ሊከናወኑ ይገባል፣
   ሐ. በግል ወይም በጋራ ሊከናወኑ ያስፈልጋል፣
   መ. መልሱ አልተሰጠም::
3. ስለሲቪክ ማሕበራት እውነት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. በግለሰብ ወይም በቡድን በራስ ፈቃድና ተነሳሽነት ሊመሠረት ይችላል፣
   ለ. ከመንግሥት በሚሰጠው አመራር መሠረት ይሠራል፣
   ሐ. ማሕበራዊ እንጂ ኢኮኖሚያዊ ዓላማ አይኖረውም፣
   መ. መልሱ አልተሰጠም::
4. ከአባላቱ ንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማሕበራዊ ጠቀሜታን የሚያገኙ፤
   ሀ. ሀገሪቱ፣
   ለ. የቀበሌው ሕብረተሰብ፣
   ሐ. የወረዳው ሕብረተሰብ፣
   መ. ሁሉም ትክክል ናቸው::

## IV የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ::

1. የሲቪክ ማሕበራት በነፃ ------------------ መብት ውጤቶች ናቸው::
2. አንድ ሕብረተሰብ በአካባቢው በጋራ አንድ የልማት ሥራ በታታሪነት አከናውና ከውጤቱ ከፍ ያለ አገልግሎት ቢያገኝ ይህ የ-------------------------ማሕበራዊ ጠቀሜታ አንድ መገለጫ ይሆናል::

## V የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡

1. ከሲቪክ ማሕበራት ጠቀሜታዎች ሁለቱን ጥቀሱ ::
2. ከንቁ ሕዝባዊ ተሳትፎ የሚገኙትን ግላዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታዎች ልዩነት ምሳሌ እየሰጣችሁ አስረዱ::

# ምዕራፍ አስራ አንድ

# እውቀትን መሻት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ተ ምረሽ ስታጠናቅቅ/ስታጠናቅቂ፧***

- የዕውቀትን ዋና ዋና ምንጮች ታውቂያለሽ/ ታውቃለህ::
- ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከትን በመለየት የዕውቀት ጠቀሜታን ትረዳለህ/ትረጃለሽ::
- የንባብ ልምድና የመረጃ አያያዝ ጥቅምን ታውቂያለሽ/ታውቃለህ::

## 11.1 ዋና ዋና የዕውቀት ምንጮች፧



ሥዕል 11.1 መጻሕፍት የዕውቀት ምንጮች ናቸው



ሥዕል 11.2 ትምህርት የዕውቀት ምንጭ ነው



ሥዕል 11.3 ሰዎችም የዕውቀት ምንጮች ናቸው

- በሥዕል 11.1 የምንመለከታቸው ሰዎች ለዕ ውቀት ምንጭ የሚሆኑ መረጃዎችን ከየት እያገኙ ይመስላችኋል?
- በሥዕል 11.2 እና 11.3 ላይ የምትመለከቷ ቸው የዕውቀት ማግኛ ዘዴዎች በምን ይመሳ ሰላሉ? ልዩነታቸውስ ምንድነው?

**ጥቅምት፧**

ወርሀ ጥቅምት በብዙ የሀገራችን አካባቢዎች በሁ ለት ነገሮች ትታወቃለች፣ በአበባና በእሸት:: አበባ የሠላም፣ የደስታና የምሥራች ምልክት ነው:: ከዚህ ባሻገር ሰዎች አበባን ለፍቅር፣ ለታማኝነት፣ ለምስጋና መግለጫና ለመሳሰሉት ይጠቀሙበታል:: አበባ በሐዘን ጊዜም ያገለግላል:: ምክንያቱም አበቦች ቶሎ የሚረግፉ በመሆናቸው ለሰው ዕድሜ አጭርነት በምሳሌነት ይቀርባሉ::

የጥቅምት ሌላው መለያ እሸት ነው:: ወተትና ቅቤ እንደልብ የሚገኝበትም ወር ነው:፡ ምን ይኼ ብቻ ፧ጥቅምት የማር እመቤትም ናት፧ ያውም የማር እሸት! “ማር መቁረጥ በጥቅምት”፣ “እህልን መቆ ጠብ በጥቅምት”፣ “ልጅን በጡት፣ እህልን በጥቅ ምት” የሚሉት የአበው አባባሎች በጥቅምት ሁሉም ነገር በብዛት መገኘቱን ብቻም ሳይሆን፣ የሚገኙትም ነገሮች ምርጥ ምርጥ መሆናቸውን ያሳያሉ::

አባባሎቹ የተገኘውን ነገር በጥንቃቄ መያዝ እንደሚያስፈልግም ይጠቁማሉ:: ለምሳሌ "ልጅን በጡት፣ እህልን በጥቅምት" የሚለውን እንው ሰድ:: ልጅ በሕጻንነቱ በሚገባ ካልያዙት ካልመገ ቡት ወይም ካልተንከባከቡት፣ ሲያድግ መልካም ዜጋ አይሆንም:: በጥቅምት ሰብሉ እንዳይጐዳ በት በመጠበቅና በመንከባከብ እንዲሁም በታህሣሥና በጥር ወራት ያገኘውን ምርት በሥርዓት ካልያዘው፣ በሰኔና በሐምሌ መራቡ አይቀርም:: ስለሆነም ምርቱን ከቡቃያነቱ ጀምሮ በጥንቃቄ መያዝ ያስፈልጋል ማለት ነው::

ጥቅምት የምትታወቀው በእነዚህ ነገሮች ብቻ አይደለም:: የወንዝ ውሃውም ጥርት ብሎ የሚገ ኘው በጥቅምት ነው:: ችግሩ የጥቅምት ውሃ ፈላጊው ትንሽ ነው:: "ውሃ የጥቅምት ነበርሽ ማን በጠጣሽ፤ ምክር የድሃ ነበርሽ ማን በሰማሽ" የሚባለው ለዚህ ነው::

*(ካሕሳይ ገብረ እግዚአብሔር፣ 1998፣112-115 ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ 1**

***ከዚህ በላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ስለጥቅምት ወር የጻፈው ሰው የጽሑፉን መረጃ ከየት ያገኘው ይመስላችኋል?
2. ደራሲው መረጃውን እንዴት ሲሰበስበው ቃስ ትላላችሁ?
3. ከዚህ ተነስታችሁ ዕውቀት ሲገኝ የሚችልባ ችውን የመረጃዎች ምንጮችን ዘርዝሩ::

ዕውቀት ከዕድሜያችን፣ ከልምዳችንና ከትምህርት ደረጃችን በምናገኘው መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሚያድግ የህሊና ሀብት ነው:: ዕውቀት ባለን መረጃ ልክ የሚመዘን ነው ማለት ይቻላል:: ስለዚህ በዕውቀት መዳበር ሂደት ውስጥ የመረጃ ጉዳይ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም::

ዕውቀት ከመጻህፍት፣ ከጋዜጦች፣ ከሬዲዮና ከቴሌቪዥን እንዲሁም ከሰዎችና ከአካባቢያችን የሚገኝ ነው፡፡ በመሆኑም አካባቢም አንዱ የዕውቀት ምንጭ ነው፡፡ ለምሳሌ ከፍ ሲል ያነ በብነውን የጥቅምት ወር ጽሑፍ ለማዘጋጀት ደራሲው አካባቢውን በሚገባ ተመልክቷል፣ የአባቶችንም አባባል አዳምጦ መዝግቧል:: ይህ ሁኔታ ዕውቀት በመገብየት ሂደት ውስጥ የምል ከታን፣ የማድመጥን፣ የንባብንና የመረጃን ቁርኝት ያመለክታል::

ዕውቀትን ከአካባቢያችን የምናገኘው ነገሮችን በቀጥታ በመመልከት፣ በማሽተት፣ በመቅመስ፣ በመዳሰስና በማድመጥ ነው:: ስለአካባቢያችን ወንዞች የውሃ መጠን መጨመር ወይም መቀነስ፣ ስለሰዎች ሠላማዊ እንቅስቃሴ፣ በአካባቢያችን ስላለው የልማት ሁኔታ ዕውቀት የምናገኘው በቀጥታ በአካል በቦታው ተገኝተን ነው::

በሳይንሳዊ መረጃ ላይ የተመሠረተ ዕውቀት ከምናገኝባቸው ምንጮች ዋናው ትምህርት ቤት ነው:: ይህ የሚሆነውም በልዩ ልዩ ሙያዎች የሠለጠኑ መምህራን በትምህርት ቤት ስለሚገኙ ነው:: እነሱም በታማኝ መረጃ ላይ ያተኮረ ዕው ቀት እያደራጁ ያቀርባሉ:: በእርግጥ ልዩ ልዩ ጽሑፎችን በማንበብም ብዙ ዕውቀት ልናገኝ እን ችላለን:: እንደ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ያሉትም ጥሩ የዕውቀት ምንጮች ናቸው:: በጉብኝትም ዕው ቀት የሚገበይባቸው መረጃዎች አሉ:: ለምሳሌ በሀገራችን ስለሚገኙት ስለጥያ ትክል ድንጋዮች፣ ስለጭስ ዓባይ ፏፏቴ፣ ስለባሌ ድሬ ሼህ ሁሴን የአምልኮ ቦታ፣ ስለሐረር ግንብ፣ የሰው ዘር መገኛ ስለሆነው ስለሐዳር፣ እንዲሁም ስለስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ማወቅ ስንሻ፣ የጉብኝት መረጃ ዋናው የዕውቀት ምንጭ ይሆናል::

ይሁንና ለዕውቀታችን መዳበር የሚያስፈልጉትን መረጃዎች ስንወስድ ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: ምክ ንያቱም አንዳንድ ጋዜጦች ወይም ሬዲዮ ጣቢ ያዎች እንዲሁም ግለሰቦች የተዛባ ወይም ሐሰ ተኛ መረጃ ካቀረቡልን የምናገኘው ዕውቀት የተዛባ ሊሆን ስለሚችል ነው፡፡ ስለዚህ መረጃ ውን ከመቀበላችን በፊት፣ ከሌሎች ምንጮች ጋር ማመሳከር እንዲሁም መምህራንንና አዋቂ ሰዎ ችን መጠየቅና ማረጋገጥ ይጠበቅብናል::

**መልመጃ ፪**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሥሩ።*


1. ከሚከተሉት ርእሶች መካከል የሚመቻችሁን በመምረጥ ወይም መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ርእስ በመውሰድ መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች ሰብስቡ። መረጃዎቹንም በተለያዩ መንገዶች አደራጁቸው፣
   ሀ. የት/ቤታችሁና የወላጆች ግንኙነት ምን እንደሚመስል፣
   ለ. የዕብድ ውሻ በሽታ መንስኤውና ሲደረግ የሚገባው ጥንቃቄ ምን እንደሆነ፣
   ሐ. በአካባቢያችሁ ያሉ ገበሬዎች፣ አርብቶ አደሮች ወይም ነጋዴዎች መሠረታዊ ችግሮች ምን እንደሆኑና እንዴትስ ሊያስወግዷቸው እንደሚጥሩ፣
   መ. በመማር ሂደት ውስጥ የወላጆች ድርሻ ምን እንደሆነ።
2. እነዚህን የሰበሰባችኋቸውን መረጃዎች በሚገባ አደራጅታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

## 11.2 ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት፤


- ኋላቀር አስተሳሰብና አመለካከት ስንል ምን ማለታችን ነው?
- በአካባቢያችሁ የምታስተውሏቸው ምን ዓይነት ኋላቀር አመለካከቶች አሉ?

**የመምህርት ገላኔ የቤት ሥራ፤**


መምህርት ገላኔ የሚያስተምሯቸውን የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉ ኋላቀር አመለካከትና አስተሳሰቦች መዝግበው እንዲያመጡና በክፍል ውስጥ እንዲወያዩባቸው አደረጉ። ተማሪዎቹም በማኅበረሰቡ ዘንድ ይስተዋላሉ ያሏቸውን ኋላቀር አመለካከቶችና አስተሳሰቦች በዝርዝር ይዘው መጡ። የተወሰኑት ተማሪዎች ይዘዋቸው የመጡት የሚከተሉትን ነበሩ።





ተማሪ ባልቻ




ተማሪ አያህሉሽም




ተማሪ መኪያ




ተማሪ ዘማርያም




ተማሪ ኦጁሉ

**መልመጃ ፫**

*የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።*

1. ከአምስቱ ተማሪዎች መካከል ኋላቀር አመለካከት ይዘው የመጡት የትኞቹ ናቸው? ይህን ለማለት ምክንያታችሁ ምንድ ነው?
2. እናንተስ እነዚህን ዓይነት ኋላቀር አስተሳሰቦች ባካባቢያችሁ አስተውላችኋል? እስቲ እየጠቀሳችሁ በክፍል ውስጥ ተወያዩባቸው።
3. የእነዚህ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች መነሻ ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል?
4. ኋላቀር አመለካከቶች ዕውቀት የመሻትና የማዳበርን ዝንባሌ እንዴት ይጎዳሉ?

ኋላቀር አመለካከት በሳይንስ ባልተደገፈ ጭፍን ግምት ላይ የተመሠረተ ጎጂ ልማድ ነው። በተለይ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች ስንጠቃ ለኋላቀር አስተሳሰቦች የመጋለጥ ዕድላችን ይሰፋል። ለምሳሌ በቴክኖሎጂ ታግዘን በቂ ምርት ማምረት ካልቻልን፣ ዝናብ ሲያንስ ወይም ሲበዛ ሰብላችን ይጠፋብናል። ያኔ እንራባለን።

ስንራብም አንድ በደል ሠርተን አምላክ የተቆጣን ሊመስለን ይችላል። ነገር ግን በዘመናዊ ትምህርት በሚገኙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ተጠቅመን ብናመርትና ራሳችንን ብንችል ከዚህ ዓይነት ጭፍን ግምት እንራቀቃለን። ሰዎች የጤና መቃወስ ችግሮችም ይገጥሟቸው ይሆናል። አንዳንድ ግለሰቦች ለሕመማቸው መነሻ

የሚሆን ምክንያት እንዳለ ያስባሉ:: ለምሳሌ ኤድስን ከፈጣሪ ቁጣ ጋር የሚያያይዙ ሰዎች አይጠፉም:: ይህ ታዲያ ስለበሽታዎች አመጣጥ ያልተጨበጠ አመለካከት መፍጠር ነው::

ኋላቀር አመለካከቶች ለባዕድ አምልኮ ሊዳርጉን ይችላሉ:: ባዕድ አምልኮም በሕይወት ላይ ምንም ተጽዕኖና ፋይዳ የማይኖራቸውን ነገሮች መለኮታዊ ኃይል እንዳላቸው በማመን የእነሱ ተገዥ መሆን ነው:: አንዳንድ ሰዎች የተለያዩ እንስሳት መንፈሳዊ ኃይል አላቸው ብለው በማመን ለእንስሳቱ ግብር ያስገቡላቸዋል:: ሌሎች ደግሞ ዝናብ ሲጠፋ ወይም ሌላ ዓይነት ችግር ሲገጥማቸው ይህን ያደረገው የወንዙ አምላክ ነው ወይም የእንስሳት ውቃቢ ነው ብለው በማሰብ ለሚያምኑበት ነገር መስዋዕት ያቀርባሉ::

በኋላቀር አመለካከትና አስተሳሰብ ሥር ያሉ ወገኖች ልማትን በሥራ ከማምጣት ይልቅ "ያለልኝን አላጣውም" በማለት ዕድላቸውን መጠባበቅ ይመርጣሉ:: መሰሎቻቸው ከችግር ተላቀው ሲመለከቱም "ዕድሉ ጥፎለት ነው" ይላሉ:: ኑሮ አልሳካ ካላቸውም ዕድላቸውን ወደ ማማረር የአስተሳሰብ ቀውስ ይገባሉ::

ለዚህ ነው "ለመከራ የጣፈው ቢነግድ አይተርፈው" የሚለውን አፍራሽ ምሳሌያዊ ንግግር የምንሰማው:: ዕድልን የተመለከተ ግጥምም አለ፤

"ወይ እኔን ግደለኝ ወይ ዕድሌን ባርከው
ሆዴ ተቀደደ ሲርበኝ የማከው::"

ይህን መሰል አዝማሚያ ደግሞ መሸነፍንና ተስፋ መቁረጥን ያስከትላል::

ሰዎች ተስፋ ሲቆርጡም በራሳቸው ከመተማመንና በትግል ከችግር ከመውጣት ይልቅ ራሳቸውን አደጋ ላይ ሊጥሉ ይችላሉ:: በጥቅሉ ሲታይ ኋላቀር አመለካከቶችና አስተሳሰቦች ጎጂነታቸው ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ጉዳታቸውንና ፋይዳቢስነታቸውን ለማጎበረሰቡ በተግባር በማሳየት በሂደት ልናስወግዳቸው ይገባል:: አስቀድመን ግን እኛ ራሳችን በትምህርታችን ጠንክረን አስተሳሰባችንን በሳይንሳዊ አመለካከት ላይ መመሥረት ይጠበቅብናል::

**መልመጃ 4**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡***

1. ኋላቀር አስተሳሰቦች በጤና ላይ ምን ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ?
2. በባዕድ አምልኮ መጠመድ የሚመጣው ከምንድነው? እሱስ ምን ጉዳት አለው?
3. በትምህርት መግፋት ከኋላቀር አስተሳሰቦች ለመላቀቅ እንዴት ይረዳል?

## 11.3 መረጃ፤

- እናንተ መረጃዎችን በሥርዓቱ አደራጅታችሁ ትይዛላችሁ? እስካሁን በሥርዓት የያዛችኋቸው ምን ምን መረጃዎች አሏችሁ?
- ያሏችሁን መረጃዎች በሚገባ አጠናቅራችሁ መያዛችሁ ጥቅሙ ምንድነው?

**አስተዋዩ ዘበርጋ፤**

ዘበርጋ በጥያ ትክል ድንጋዮች አካባቢ ካለች አንዲት ገጠር ት/ቤት የሚማር የ6ኛ ክፍል ተማሪ ነው:: ይህ ልጅ በተፈጥሮው ንቁ፣ በትምህርቱም ትጉሕ ነው:: ገና ማንበብና መጻፍ እንደቻለ፣ የእናትና የአባቱን፣ የወንድሞቹንና የእህቶቹን እንዲሁም የራሱን የልደት ቀንና የትውልድ ቦታ ወላጆቹን እየጠየቀ በማስታወሻው ላይ አሰፈረ:: ከዚያም ዕድሜው እየበሰለ ሲመጣ፣ የሌሎች ሥጋ ዘመዶቹን የሕይወት ታሪክ ጭምር በማጠያየቅ ባጭሩ መዘገበ:: በዚህም ሥራው እሱ የየትኛው የጉራጌ ቤተሰብ ተወላጅ እንደሆነ ለማወቅ ሞክሯል::

ከዚህም አልፎ የዚያን አካባቢ አምስት ቀበሌዎች መጠሪያ ስሞች ከአዛውንቶች እየጠየቀ መዘገበ:: ቀጥሎም ቀበሌዎቹ ለምን እነዚህን ስሞች ሊያገኙ እንደቻሉ አዛውንቶቹን እየጠየቀ በትልቅ ማስታወሻ ላይ ጻፈ:: አሁን በቅርብ ጊዜ ደግሞ የጥያን ትክል ድንጋዮች ታሪክ ከአካባቢው ተወላጆችና ከመምህራን እየጠየቀ መመዝገብ ጀምሯል:: ይህን የ6ኛ ክፍልን የሥነዜጋና ሥነምግባር ትምህርት ተምሮ ሲያገባድድ ደግሞ፣ ስለቤተሰቡ፣ በአካባቢው ስለሚስተዋሉ ጠቃሚ ተሞክሮዎች ከዚህ ሰፋ ያለ መረጃ እንደሚያሰባስብ ተናግሯል::

ዘበርጋ ይህን ያድርግ እንጂ አንዳንድ ጓደኞቹ ግን ልክ እንደሥራፈት ያዩታል:: "ዘበርጋ ትምህርቱን ከማጥናትና በትርፍ ጊዜው ቤተሰቡን ከማገዝ ይልቅ የረባ-ያልረባ ነገር ሲሞነጫጭር ይውላል" እያሉ ይሳለቁበታል::

መልመጃ 5

*ከላይ በቀረበው መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. ዘበርጋ ትክክል ነው ወይስ በርግጥም የሥራ ፈት ሥራ እየሠራ ነው?
2. ዘበርጋ ይህን የጀመረውን ተግባር የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ከመረጃ መሰብሰቡ ጎን ለጎን ምን ማድረግ ያለበት ይመስላችኋል?

መረጃ ስለቤተሰባችን፣ ስለአካባቢያችን፣ ስለራሳ ችን፣ ስለ ትምህርት ቤታችን፣ እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ ስለሀገራችን ጠቃሚ ሐሳቦች የምናገኝበት መንገድ ነው፡፡ ዘበርጋ ይህን በመረዳቱ ነው አቅሙ የፈቀደለትን ነገር ሁሉ እየተከታተለ የሚ መዘግበው፣ ስለዚህም ሊደነቅ ይገባዋል፡፡

መረጃ ጠቃሚ በመሆኑ በተከታታይ ሊሰበሰብና በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል በማንኛ ውም ወቅት የምናገኘውን መረጃ ሳናቃልል መመዝገብ አለብን ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ከሳምንት በፊት የነበረውና ዛሬ ያለው የአየር ሁኔታ ቢያንስ መጠነኛ ልዩነት ማሳየቱ አይቀርም፡፡ ስለሆነም ሳምንት መዝግበንዋል ብለን ዛሬ ማለፍ የለብንም፡፡

በዚሁ ዓይነት የንግድ ዕቃዎች ዋጋ፣ የጤናችን ሁኔታ፣ በሰዎች ላይ የሚስተዋሉ ባሕርያት፣ የእንስሳትና የዕፅዋት ዕድገት ወዘተ በየጊዜው ሊለዋወጡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ሳናቋርጥ እየተ ከታተልን መመዝገብ ይገባናል፡፡

መረጃ በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባል ስንል በአንድ በኩል በምሥጢር መጠበቅ አለበት ማለታችን ነው፡፡ ለምሳሌ የቤተሰቦቻችንንም ሆነ የራሳችንን ባሕርይ ወይም የጤንነት ሁኔታ ስንመዘግብ በምሥጢር ማስቀመጥ አለብን፡፡ በዚህ ዓይነት በምሥጢር ሊያዙ የሚገባቸው የግል፣ የቤተሰብ፣ የሕዝብ፣ የመስሪያ ቤት፣ የሀገርና ሌሎችም ጉዳ ዮች አሉ፡፡ ጥንቃቄ በሌላ በኩል መረጃዎች እንዳ ይጠፉ ወይም እንዳይባክኑ ለመጠበቅ ይጠቅ ማል፡፡


መረጃዎችን መመዝገብ ብቻ ሳይሆን የተመዘ ገቡትን በሥርዓት ማስቀመጥ ከጥፋት ያድና ቸዋል፡፡ መረጃዎች በሥርዓት ካልተቀመጡ ስንፈልጋቸው ላይገኙ ይችላሉ፣ ወይም ይመሰቃ ቀሉና ለመለየት ያስቸግረናል፡፡ ባልታወቀ ሁኔታ ሊሰረቁብንም ይችላሉ፡፡ ከተሰረቁብን ደግሞ ምሥጢራችን ከመውጣቱም በተጨማሪ እኛ የለፋንበትን ሌላው ይጠቀምበታል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ እንደ ዘበርጋ ያለ ንቁ ሰው መረጃ ከመሰ ብሰብ ጎን ለጎን፣ ሰነዶችን በጥንቃቄ ስለመያዝና በሥርዓት ስለማስቀመጥ ግንዛቤ ማግኘት አለበት፡፡

መልመጃ 6

*በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡*

1. መረጃ ጠቃሚ ነው የሚባለው ለምንድን ነው?
2. መረጃ በአግባቡ ካልተያዘ ምን ጉዳት ያስከትላል?

## 11.4 የማንበብ ልምድ፤



11.4 ንባብ በቤተመጻሕፍት



11.5 ንባብ በቤት ታዛ ሥር



11.6 ንባብ በዛፍ ሥር

- አዘውትራችሁ ታነባላችሁ? የምታነቡ ከሆነ በየቀኑ ለምን ያህል ጊዜ የማንበብ ልምድ አላችሁ? የማታነቡ ከሆነስ ለምን አታነቡም?
- ምን ዓይነት ጽሑፎችን ታነባላችሁ? ለምን እንዲህ ያሉ ጽሑፎችን ለማንበብ ትወዳላችሁ?
- አዘውትራችሁ የምታነቡት የት ነው? እንደዚያ ያለ ቦታ የምትመርጡትስ ለምንድነው?

### የማነው ትክክል?

ግደይ፣ ጠንክርና ዘምዘም የሚባሉት የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች ስለንባብ ልምዳቸው የተለያየ አቋም አላቸው:: ይህንንም አቋማቸውን እንደሚከተለው ገልጸውታል::

**ግደይ፣** እኔ ለንባብ በጣም ከፍ ያለ ፍላጎት አለኝ:: ብዙ ዓይነት ጽሑፎችን አነባለሁ:: ጽሑፎቹም ጋዜጦች፣ መጽሔቶች፣ መጻሕፍት ወይም ደብተሮቼ ሊሆኑ ይችላሉ:: የማነበውም በቂና ተመጣጣኝ ብርሃን ባለበት ቦታ ማለትም በዛፍ ሥር፣ በቤተመጻሕፍት ውስጥ፣ በቤት ታዛ ሥር፣ በቤት ውስጥ ነው::

**ዘምዘም፣** ግደይ ልክ አይደለህም:: ማንበብ የሚገባን ትንሽ ትንሽ ብቻ ነው፤ አለበለዚያ ዓይናችን ሊጠፋ ይችላል:: አባቴም ብዙ የሚያነብ ሰው ሥራፈት ነው ራሱንም ያሳምማል ብሎኛል:: ማንበብ ያለብንም ደብተራችንንና መማሪያ መጽሐፎችን ብቻ መሆን አለበት:: ሌላ ነገር ማንበብ ያለብን እንደነ ቲቸር በደንብ ስናድግ ነው:: ስናነብም በቤተ መጻሕፍትና በቤታችን የጥናት ክፍላችን ውስጥ ብቻ መሆን አለበት::

**ጠንክር፣** ግደይም ሆነ ዘምዘም ተሳስታችኋል:: የምናገኘውን ጽሑፍ ሁሉ ማንበብ የለብንም:: እነቲቸር የሚሰጡንን የቤት ሥራ ለመሥራት የሚያስፈልጉንን መጻሕፍት እናነባለን:: ልቦለዶችንም ማንበብ አይከፋም:: ጋዜጣ ከሆነ ግን የስፖርት አምዶችን ብቻ ማንበብ ይበቃል:: ሌሎች ጽሑፎችን ማንበብ ግን ጥቅም የለውም::

**መልመጃ ፯**

*ከላይ በቀረበው ውይይት መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ::*

1. ከሦስቱ ተማሪዎች ስለንባብ የተሻለ አቋም ያለው ማነው? ለምን ይመስላችኋል?
2. ከሦስቱ ተማሪዎች ክርክር ከተወያያችሁ በኋላ ስለማንበብ ልምድ ምን ተገነዘባችሁ?

ንባብ ዕውቀታችንን የምናዳብርበት መሣሪያ ነው:: ስንማርም መምህራን የሚነግሩንን ብቻ መቀበል ሳይሆን፣ እኛም ብዙ አንብበን ተጨማሪ ዕውቀት ማግኘት አለብን:: ስለሆነም ገና ከልጅነታችን ጀምረን ከንባብ ልምድ ጋር አብረን ማደግ ይገባናል:: ስለንባብ ልምድ ልብ የምንላቸው ጉዳዮችም አሉ:: በምናነብበት ጊዜ ተመጣጣኝ ብርሃን ያለው ቦታ መምረጥ አለብን:: ከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ ብርሃን ባለበት ቦታ ማንበብ ለዓይን ጠንቅ ነው:: አንዳንድ ሰዎች በፀሐይ ውስጥ ሆነው ወይም እጅግ ከፍ ባለ የኤሌክትሪክ ብርሃን ያነባሉ:: በደከመ ብርሃን የሚያነቡም ሰዎች ያጋጥሙናል:: እንዲህ የሚያደርጉ ልጆች ሲያጋጥሟችሁ ለዓይን ሕመም እንዳይጋለጡ ምከሯቸው::

ሌላው ልብ ማለት ያለብን የንባብ ምርጫ ጉዳይ ነው:: ማንበብ የሚገባን የምንማረውን ትምህርት ብቻ አይደለም:: ተጨማሪ መረጃ የሚሰጡ ጽሁፎችንም ማንበብ ይጠበቅብናል:: የጋዜጦችንና የመጽሔቶችንም የተለያዩ አምዶችን ቢያንስ አለፍ አለፍ እያልን ማንበብ አለብን:: ለንባብ ጊዜና ቦታ መወሰን አስፈላጊ ቢሆንም፣ እነዚህን ነገሮች አመካኝቶ ከንባብ መዘናጋት ግን አያስፈልግም::

የግድ በቤተመጻሕፍት ብቻ ካልሆነ አላነብም ማለት የለብንም፡፡ ተመጣጣኝ ብርሃን እስካለ ድረስ በዛፍ ሥር፣ በታክሲና በአውቶቡስ ላይ፣ በሳሎን ውስጥ፣ በመኝታ ቤታችንና በሌሎችም ሥፍራዎች ማንበብ ይቻላል፡፡

ደራሲ መንግሥቱ ለማን፣ አቶ ይድነቃቸው ተሰማን፣ ፐሮፌሰር አክሊሉ ለማን፣ አቶ ይልማ ዴሬሳን፣ ባለቅኔ ጸጋዬ ገብረ መድኅንን የመሳሰሉ የሀገራችን ታላላቅ ሰዎች ታላቅ ለመባል የበቁት ብዙ ከማንበብና ነገሮችን በጥልቀት ከመመርመር ነው፡፡ እናንተም የእነሱን አርአያ በመከተል የታወቃችሁ ምሁራን ሆናችሁ ሀገራችሁን ለማ ስጠራት ብዙ ማንበብ አለባችሁ፡፡

**መልመጃ ፰**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. ለማንበብ የተወሰነ ቦታ መምረጥ የግድ አስፈላጊ አይደለም የተባለው ለምንድነው?
2. አዘውትሮ ማንበብ ምን ጥቅም ያስገኛል?
3. በመማርና ብዙ በማንበብ ለሀገራቸው ውለታ የሠሩ ሦስት ሰዎችን በቃል መጠይቅ ወይም በንባብ መረጃ አሰባስቡ፡፡ ከዚያም እነዚህ ዜጎች ለሕዝባቸውና ለሀገራቸው የዋሉትን ውለታ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## 11.5 የትምህርት አጠናን ዘዴ፤

- ትምህርታችሁን ማጥናት ከመጀመራችሁ በፊት ምን ምን ዝግጅት ታደርጋላችሁ?
- ትምህርታችሁን በማጥናት ሂደት ምን ሥልት ትከተላላችሁ? ስትጨርሱስ?

**ከድርና ብርመጪት፤**

እኛ ትምህርት ቤት ከድርና ብርመጪት የሚባሉ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ፡፡ ከድር አንዳንዴ በክፍል ውስጥ እንቅልፉ ይመጣበታል፡፡ በትምህ ርቱም ደከም ያለ ውጤት አለው፡፡ ብርመጪት ግን ጎበዝ ተማሪ ናት፡፡ በክፍል ውስጥ መምህ ራን ሲያስተምሩ ያልገባትን ነገር ትጠይቃለች፣ ሌሎች ሲጠይቁም በመመለስ ትሳተፋለች፡፡

መምህርት ብርክቲ ይህን የሁለቱን ልጆች ልዩነት አስተውለዋል፡፡ አንድ ቀን መምህርቷ ሁለቱ ልጆች ትምህርታቸውን እንዴት እንደሚያጠኑ ለክፍሉ እንዲያስረዱ ጠየቋቸው፡፡

ከድር እንዲህ ሲል አስረዳ፡፡ በየቀኑ ማጥናት ይሰለቸኛል፡፡ የማጠናው ፈተና ሲደርስ ነው፡፡ የምፈተነው ትምህርት ነገ ነው ሲባል ደብተሬን አነሳና ከመኝታ ክፍሌ እገባለሁ፡፡ ከዚያም እስኪደ ክመኝ ማጥናት ነው፡፡: ሳጠናም የማይገባኝ ነገር ካለ ምንም ማድረግ አልችልም፣ እዘለዋለሁ፡፡

ብርመጪትም በተራዋ ቀጠለች፡፡ እኔ በአንድ ቀን ብዙ በማጥናት ራሴን ማስጨነቅ አልወድም፡፡ በየቀኑ የተማርኩትን ከሥር ከሥር አጠናለሁ፡፡ ካልገባኝም ከጓደኞቼ ጋር እነጋገርበታለሁ፡፡ እኔም ካልገባኝ አስተማሪዬን እጠይቃለሁ፡፡ ጥናት ከመጀመሬ በፊት የሚያስፈልጉኝን ነገሮች ማለ ትም እንደ መዝገበ ቃላት፣ ማስታወሻ ደብተር፣ ማገናዘቢያ መጻሕፍት አዘጋጃለሁ፡፡ የማነበውንም ነገር በማስታወሻ እይዛለሁ፡፡ እንደዚህ ካጠናሁ በደንብ ይገባኛል፡፡ ለዚህ ይመስለኛል ባለፈው ዓመት አንደኛ ወጥቼ የተሸለምኩት። ዘንድሮም በቴስቶች ጥሩ ውጤት እያገኘሁ ነው፣ አንደኛ እንደምወጣ አልጠራጠርም፡፡

**መልመጃ ፱**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. ከከድርና ከብርመጪት ጥሩ የጥናት ልምድ ያለው ማነው ትላላችሁ? ለምን?
2. ከተራ ቁጥር1 መልሳችሁ አንጻር ስታዩት ጥሩ ውጤት ለማምጣት እንዴት ማጥናት ያስፈልጋል?


የጥናት ንባብና ሌላው ንባብ መጠነኛ ልዩነት አላቸው፡፡ ጠቅላላ ዕውቀትና መረጃዎችን የምና ነበው ባገኘንበት ቦታ ሁሉ ሊሆን ይችላል፡፡ በእን ዲህ ዓይነት ንባብ ማስታወሻ መያዝና እየመላ ለሱ ማንበብ የግድ አይደለም፡፡

በጥናት ንባብ ግን የትምህርቱ ነጥቦች እስኪገቡን ድረስ እየመላለስን እናነባለን፡፡ ስናጠናም ብር መጪት የጠቀሰቻቸውን አስፈላጊ የጥናት መሣሪ ያዎች ማዘጋጀት አለብን፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጸጥታ ያለው ቦታ መምረጥና ምቹ መቀመጫ ዎች ላይ መቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

ስናነብም ነገሮችን በትኩረት እየመረመርን መሆን ይገባዋል፡፡ ያልገቡንንም ነጥቦች ለይተን በማውጣት ለጓደኞቻችን ወይም ለክፍል ውይ ይት ማቅረብ ያስፈልገናል፡፡ የምናነበውም ደብተ ሮቻችን ብቻ መሆን የለበትም። የተማርናቸውን ርእሶች የሚመለከቱ መጻሕፍትን በማፈላለግ ተጨማሪ ማብራሪያዎችን ማግኘት የጎበዝ ተ ማሪማሪ ተግባር ነው፡፡ አጥንተን ሲበቃንም ፍሬ

ነገሮችን ምን ያህል እንደተረዳን ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን በመሥራት ራሳችንን መመዘን ተገቢ ነው:: እሱም ግለምዘና ይባላል::

ጥናት የሚከተለው ዓይነት ሂደት አለው፤




**መልመጃ 10**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

1. የጥናት ንባብና ሌላው ንባብ ምን ልዩነት አላቸው?
2. በጥናት ወቅት ያልገቡን የትምህርቱ ነጥቦች ቢኖሩ ምን ማድረግ አለብን?
3. በምታጠኑበት ጊዜ በሚከተሉት ደረጃዎች ላይ ምን ማድረግ ይኖርባችኋል?
   ሀ. ቅድመ ዝግጅት በምታደርጉበት ወቅት፣
   ለ. በጥናት ውስጥ ባላችሁበት ወቅት፣
   ሐ. ጥናት ካጠናቀቃችሁ በኋላ::

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሥር ስለዕውቀት ምንጮች፣ ስለጎጂ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች ተወያይተናል፡፡ ዕውቀት እንደ ትምህርት ቤት፣ መጻሕፍት፣ ጋዜጦችና ከመሳሰሉት ልዩ ልዩ ምንጮች የሚገኝ ነው፡፡ ይህ እውቀትም ራሳችንን እንዲሁም አካባቢያችንን ለመለወጥ የሚያስችለን መሆኑን አስተውለናል፡፡

ስለጎጂ አመለካከቶችና አስተሳሰቦችን በተመለከተም ያነሳነው ነጥብ ጠቃሚ ቁም ነገሮችን አስጨብጦናል፡፡ ተጨባጭ ባልሆኑ ግምቶችና ልማዶች መመራት የኋላቀር አመለካከት ተገዥ እንደሚያደርገንም ተረድተናል። እሱም ራሳችንን ለመለወጥና አካባቢያችንን ለማልማት የምናደርገውን ጥረት እንደሚያቃውስ ጥርጥር የለውም፡፡ ለጤንነት ጉዳትም ሊዳርገን እንደሚችል ይገባናል፡፡ ስለጥናትም ያነሳናቸውን ፍሬ ነገሮች ባጭሩ እንዲህ ልናስቀምጣቸው እንችላለን፡፡

ጥናት ቅድመ ዝግጅት ያስፈልገዋል፡፡ በዚህ ደረጃም ለጥናት የሚያስፈልጉንን ነገሮች አሟልተን እናቀርባለን፡፡ ወደ ጥናቱ ስንገባ በአንድ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተቀምጠን ተግባራችንን እናከናውናለን፡፡ አጥንተን ስንጨርስ ደግሞ በልዩ ልዩ መልክ ራሳችንን እንመዝናለን፡፡

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

*ዕውቀት፣* ንድፈ ሐሳቦችን፣ ነገሮችንና ሁኔታዎችን በጥልቀት የመረዳት ችሎታ።
*መረጃ፣* ስለሰዎች፣ ስለአካባቢ፣ ስለነገሮች፣ ስለጉዳዮች ለመረዳት የሚሰበሰብ ጥሬ ሐሳብ።
*ኋላቀር አመለካከት፣* በሳይንስ ያልተደገፈ፣ በልማድ ብቻ የሚታመን ጎታች ግምትና እምነት።
*ባዕድ አምልኮ፣* ነገሮች በሕይወት ላይ መለኮታዊ ተጽዕኖ እንዳላቸው በመቀበል ማምለክ።
*ጥናት፣* ንድፈ ሐሳብን በጥልቀት ለመረዳት ጽሑፋዊ ወይም ሌሎች የመረጃ ምንጮችን እየፈተሹና እየመረመሩ ማጤን።
*ንባብ፣* የተለያዩ መረጃዎችን ከያዙ ጽሑፎች ጋር መነጋገር።
*ግስምዘና፣* ከጥናት በኋላ ጥያቄዎችን በመሥራት የተረዱትን ፍሬ ነገር መከለስ።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

*ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ፡፡*

*I የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ትክክል ካልሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ፡፡*

1. ዋናው የዕውቀት ምንጭ ት/ቤቶች ናቸው፡፡
2. ትምህርት ሲስፋፋ ኋላቀር አመለካከትም ሥር እየሰደደ ይሄዳል፡፡
3. የተሻለ ቤት ውስጥ ስመኖር የተሻለ ዕውቀት ያስፈልጋል፡፡
4. መረጃ ዕውቀትን ለማዳበር አንዱ አማራጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡

*II በ "ለ"ሥር የተዘረዘሩትን በ"ሀ" ሥር ከተዘረዘሩት ጋር አዛምዱ፡፡*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ኋላቀር አመለካከት ነው፣ | ሀ. ሴት ልጅን ማስተማር ጥቅሙ ትንሽ ነው፡፡ |
| 2. ዋናው የዕውቀት ምንጭ፣ | ለ. የጥናት ቁሳቁሶችን መምረጥ፡፡ |
| 3. ጥናት፣ | ሐ. ሰንደቃዓላማን ማክበር፡፡ |
| 4. ቅድመ ጥናት፣ | መ. ከሌሳው ንባብ በተለየ ሁኔታ ይካሄዳል፡፡ |
| 5. የመረጃ ምንጮች | ሠ. ትምህርት በትኩረት የሚነበብበት ሂደት፡፡ |
| | ረ. ትምህርት ቤት፡፡ |
| | ሰ. ሬዲዮ፣ አረጋውያን፣ ሞባይል፡፡ |

*III ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡*

1. ኋላቀር አስተሳሰቦች ሲቀየሩ የሚችሉት መቼ ነው?
   ሀ. ሕዝብ በትምህርት ሲታነጽ፣
   ለ. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሲያድጉ፣
   ሐ. በትምህርታችን ስንገፋ፣
   መ. ሁሉም፡፡
2. ስለጥናት ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. ማጥናት የሚቻለው በትምህርት ቤት ብቻ ነው፣
   ለ. በደንብ ማጥናት የሚገባን የፈተና ሰሞን ሲቃረብ ነው፣
   ሐ. ውጤታማ መሆን የሚቻለው ከሥር ከሥር ሲጠና ነው፣
   መ. ከጓደኞች ጋር ማጥናት ትኩረትን ይረብሻል፡፡
3. ከሚከተሉት መካከል መረጃ ሊሰጠን  የሚችለው የትኛው ነው?
   ሀ. ቴሌቪዥን፣
   ለ. ሬዲዮ፣
   ሐ. ጋዜጣ፣
   መ. ሁሉም፡፡
4. በጥናት ጊዜ ማስታወሻ መያዝ በዋናነት ለምን ይጠቅማል?
   ሀ. ያልገቡንን ጉዳዮች፣ ለውይይት ለማቅረብ፣
   ለ. የእጅ ጽሑፍን ለማሻሻል፣
   ሐ. ማስታወሻ መያዝ ብዙም ጥቅም የለውም፣
   መ. ሁሉም፡፡
5. ከሚከተሉት መካከል ኋላ ቀር አስተሳሰብ የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. አዘውትሮ ማንበብ አጉል ፍልስፍና ውስጥ ይጨምራል፣
   ለ. ሴቶች በማንኛውም ብቃታቸው ከወንዶች ዕኩል ናቸው፣
   ሐ. ሴትን ልጅ ማስተማር ሁሉንም ይጠቅማል፣
   መ. ሀ እና ለ ኋላቀር አስተሳሰብ ናቸው፡፡

*IV የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ፡፡*

1. ዕውቀት እየዳበረ እንዲሄድ ማድረግ ምን ጥቅሞች አሉት?
2. ጥናት ከሌሳው የአነባብ ሂደት የሚለየው በምንድነው?
3. ባዕድ አምልኮ ለኋላ ቀር አስተሳሰብ ሲዳርግ የሚችለው እንዴት ነው?
4. ኋላቀር አመለካከቶችን ለማስወገድ የሚቻለው እንዴት ነው?